በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የ2006/2007 ኦዲት ዓመት
የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት
አጠቃላይ ዘገባ

ጥራዝ 2

ግንቦት 2007
አዲስ አበባ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በ2006/2007 የኦዲት ዓመት የተከናወኑ ኦዲቶች ዓመታዊ ሪፖርት እና የመ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም

1. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት መንግስት የሀገርቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘትና በፌዴራል መንግስት መዋቅር ስር ባሉ መ/ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነት ግልፅነትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ በኢፌዴሪ ህገ ወመንግሥት አንቀጽ 55/1 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግስት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌደራል መንግስት ገንዘብና ንብረት በወጡት ሕጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት፣ የአካባቢ ጥበቃ፤ የቁጥጥር ኦዲቶች፤ ልዩ ኦዲቶች እና ሌሎች ኦዲቶች ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌደራል መንግስት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሒሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን ማከታተል፣

ናቸው፡፡

1.1 የመ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነቶች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራሉ መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፤
- ፌዴራል መንግሥት ከብር 1 ሚሊዮን /አንድ ሚሊዮን ብር/ በላይ የሚጠይቅ ሥራ የግል ሥራ ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግል ሥራ ተቋራጮች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑንና ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ለፌዴራል መንግሥቱ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፤
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፡፡ የፌዴራል መንግሥት የኦዲትና የሂሣብ አያያዝ ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፤

- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፡፡
- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስለመንግሥት በጀት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ የሚያቀርበውን ዓመታዊ የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ሃሣብ ይሰጣል፣ ስለሁኔታውም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዘገባ አስተያየቱን ይገልጻል፡፡

የሚሉት ናቸው፡፡

1.2 <u>የሪፖርቱ ዓላማ</u>

ሪፖርቱ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በአንቀጽ 13/1 እና 2 መሠረት በ2006/2007 የኦዲት ዓመት ባከናወናቸው ኦዲቶች የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች፣ ምክር ቤቱ ለ2006 በጀት ዓመት የፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘቱን ለማረጋገጥና በሪፖርቱ በቀረበው መረጃ መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት እንዲያስችለው፤ እንዲሁም መ/ቤታችን በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ለመወጣት ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ የ2006/2007 የኦዲት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ለማመልከት ነው፡፡

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች መሰረት ያደረጉት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶችን የ2006 በጀት ዓመት ሒሳብ፣ የአለም ባንክ እና ሌሎች ዕርዳታ ሰጪዎች የሚሰጡትን የመሰረታዊ ከለላ ድጋፍ ኦዲት ለማስደረግ መንግስት በገባው ውል መሠረት በብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት፣ የወረዳ ፋይናንስና የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን እንደገና ለማቋቀም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/1984 የተቋቀሙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በሌሎች የሙያው ፈቃድ በተሰጣቸው የተፈቀደላቸው የኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ተደርገው የተገኘውን ውጤትና በመ/ቤታችን የተከናወኑ ልዩ ኦዲት ሥራዎችን ነው፡፡

የኦዲት ሪፖርቱ የኦዲቱ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ጋር በሚደረግ የመውጫ ስብሰባ ላይ የተነሱ ሃሣቦችን ያካተተ፣ ለእያንዳንዱ

ኦዲት ተደራጊና ተቆጣጣሪ መ/ቤት የኦዲት ሥራው እንዳለቀ እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡ ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፤ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ስራም የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች፤ አጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸውን የመንግሥት ሂሣብ አያያዝ ስርዓት መሠረት በማድረግ እና በኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት እና ሰነዶች፤ እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በዚህ ሪፖርት መ/ቤታችን ባለው የሰው ኃይልና በተመደበለት በጀት በ2006/2007 የኦዲት ዓመት ያከናወናቸው ሥራዎች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የ2006/2007 የኦዲት ዓመት የመ/ቤቱ ዕቅድና አፈፃፀም፤ ዋና ዋና የስራ ክፍሎች ክንውን ሪፖርት፤ መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮች፤ የመፍትሄ ሃሣቦችና አጭር ማጠቃለያ ቀርቧል።

በሁለተኛው ክፍል የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ የኦዲት ሥራን በተመለከተ የቀረበው ሪፖርት የልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች እና የአካባቢና የክዋኔ ኦዲትን እንዲሁም መንግሥት ከዓለም ባንክ እና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ለመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ለክልል መንግሥታት የተሰጠውን ሂሣብ ተከታታይ ኦዲት ያጠቃልላል፡፡

ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በኮርፖሬሽኑና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶችን የሚመለከት ይሆናል፡፡

2. የ2006 በጀት ዓመት ፋይናንስ እንቅስቃሴ እና የ2006/2007 ኦዲት ሥራዎች ዕቅድና አፈጻጸም

2.1 ሥራ ላይ የዋለው በጀት

በ2006/2007 የኦዲት ዓመት የተፈጸሙ ሥራዎችን ለማከናወን የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለውን በጀት በተመለከተ በመ/ቤቱ አዲስ አሠራር መሠረት የመ/ቤቱ የኦዲት ሥራ ዓመት ከጥር 1/2006 - ታህሣስ 30/2007 ቢሆንም፤ የ2006 በጀት ዓመት ስራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2006 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

ተ.ቁ	የወጪ አርዕስት	የበጀት ኮድ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሠራበት በጀት
1.	ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች	6100	14,886,864.38.	14,800,087.32	86,777.06
2.	ለአላቂ እቃዎች	6200	6,650,706.21	5,790,086.42	860,619.79
3.	ለቋሚ ንብረቶችና ግንባታ	6300	300.00		300.00
4.	ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች መዋጮ	6400	432,897.78	429,913.45	2,984.33
	ድምር		**21,970,768.37**	**21,020,087.19**	**950,681.18**

በሰንጠረዥ እንደተመለከተው የበጀት አፈፃፀሙ 95.67% ስራ ላይ ውሏል፡፡

2.2 የመ/ቤቱ የሰው ኃይል ሁኔታ

ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 419 እና ለድጋፍ ሰጪ 264 በድምሩ 683/ ይህ ቁጥር አዲስ በተሻሻለው የመ/ቤቱ መዋቅር ወደ 825 ከፍ ተደርጓል/ሲሆን፣ በጥር ወር 2006 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 244 ኦዲተሮችና 160 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 404 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 58 ኦዲተሮችና 31 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 89 ሠራተኞች የተቀጠሩ፣ለድጋፍ ዘርፍ 1 ሠራተኛ በዝውውር የተመደ ሲሆን፣ 5 ኦዲተሮች በጡረታ የተገለሉ፣ 2 በሞት የተለየ፣ 57 ኦዲተሮች በፈቃዳቸው ለቀዋል። ከድጋፍ ሰጪ ክፍሎችም 25

በፍላጎታቸው ፣ 4 በጡረታ የተገለሉ 1 በሞት የተለየና 1 በዲሲፒሊን የተባረረ በድምሩ 97 ሠራተኞች በኦዲት ዓመቱ ለቀዋል፡፡

በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 173 ወንዶችና 88 ሴቶች በድምሩ 261፤ የድጋፍ ሰጪ 62 ወንዶችና 74 ሴቶች በድምሩ 136 ሠራተኞች በአጠቃላይ 397 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን ፣ 286 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ይህም ቁጥር በነበረው መዋቅር ከተፈቀደው ጋር ሲነጻጸር የኦዲት ዘርፍ 261/419(63.00%) እና የድጋፍ ዘርፍ 136/264(51.51%) በአጠቃላይ 397/683(58.12%) ስለሆነ ፣ 41.87% በሰው ኃይል ያልተሞላ ክፍት መደቦች መሆኑን ያሳያል።

2.3 <u>የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድና ክንውን</u>

መ/ቤቱ በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ በአራት ዳይሬክቶሬቶች እና የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከጥር 1/2006 እስከ ታህሣስ 30/2007፤ የ135 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች /በኦዲት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በእቅድ የተያዘው 137 የነበረ ቢሆንም እንደ መ/ቤት ይቆጠሩ የነበሩ 2 ኦዲት ተደራጊ ተቋማት በቅርንጫፍነት ደረጃ በመደልደላቸው የመ/ቤቶቹ ብዛት ወደ 135 ዝቅ ሲል የቅርንጫፎቹ ቁጥር ደግሞ ከ 27 ወደ 29 ከፍ ብሏል/ የመደበኛ ኦዲት ለማድረግ በእቅድ በተያዘው መሠረት የ133 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና የ26 ቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ አንድ መ/ቤት ሂሳቡን ዘግቶ ለኦዲት ባለማቅረቡና 1መ/ቤት ደግሞ በሰው ኃይል ምክንያት ኦዲት አልተደረገም።

ከዚህም በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በዕቅድ ያልተያዙ በፍ/ቤቶች ትህዛዝና በተለያዩ አካላት ጥያቄ መሰረት 6 ልዩ ኦዲቶች ተከናውነው ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካለት ቀርቧል፡፡

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማስከበር በፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተም ከተሰጠው የድጋፍ ሂሣብ ውስጥ የ2006/2007 ኦዲት ዓመት በ300 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ)፣

ሂሣቡን ለማስተዳደር የተዘረጋዊ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ብቃት ያለውና አጥጋቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ኦዲት ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፤ በኦዲት ዓመት የ300 መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ተከናውነው ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተልኳል፡፡ ይህም ክንውን ከበጀት ዓመቱ እቅድ ጋር ሲነጻፀር 100.00% ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን የ133 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች እና በ300 የወረዳና ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ በሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር የተሰጡት የኦዲት አስተያየት ከ2005/2006 ኦዲት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ ቁ.	መግለጫ /የኦዲት አስተያየት/	በፌዴራል መንግሥት ኦዲት የተደረጉ ሂሣቦች ብዛት		የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ተከታታይ ኦዲት		አጠቃላይ	
	በጀት ዓመት	2005	2006	2005	2006	2005	2006
1	አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀጥታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Clean Opinion)	59	39	1	1	60	40
2	ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion)	49	63	280	299	329	362
3	አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለጽ አስተያየት የተሰጠባቸው (Disclaimer of opinion)	7	11			7	12
4	የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው (Advers Opnion)	15	20			15	19
5	ሂሳባቸውን በወቅቱ ባለመዝጋታቸው አስተያየት ያልተሰጠባቸው	2	1			2	1
	ድምር	132	134	281	300	413	434

2.4 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ ፕሮጀክቶችና የእርዳታ ሂሣቦች ላይ የተከናወነው የፋይናንስ ኦዲት

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንና በውጭ እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ሂሣብ በሙሉ ኦዲት ለማድረግ የመ/ቤቱ አቅም ውሱን በመሆኑ ላለፉት ጊዜያት የነዚህ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ሂሣብ የኦዲት ሙያ ፈቃድ ከመ/ቤቱ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶችና በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እየተደረገ በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ላይ ኦዲት ተደራጊው ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ በማሳወቅ ክትትል ተደርጓል፡፡

በዚህ መሠረት በ2006 በጀት በዓመት በመንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የልማት ድርጅቶች 78፣ ፕሮጀክቶች እና የእርዳታ ሂሣቦች በግል ኦዲት ድርድቶች 174 ኦዲቶች በድምሩ 252 (ይህ ቁጥር በአንድ በጀት ዓመት የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረገው መ/ቤት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን ብቻ እንደ አንድ በመቁጠር የተወስደ ነው) የተለያዩ በጀት ዓመት ሂሣቦች የተከናወኑ ሲሆን፣ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑትን በኦ ዲቶች በተመለከተ በተለይም አቋም መውሰድ ያልተቻለበትና የጎላ ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተቀባይነት የሚይሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው የልማት ድርድቶችን ዋና ዋና ግኝቶች በዚሁ ጥራዝ በክፍል 3 ከገጽ 405 ጀምሮ ቀርቧል፡፡

2.5 የክዋኔ ኦዲትን በተመለከተ

በመንግሥት የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋለዣውንና እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መወጣተቸውን ለማረጋገጥ መ/ቤቱ የክዋኔ ኦዲት ያከናውናል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2006-2007 የኦዲት ዓመት (Audit Calendar) በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች ከጥር 2006 በፊት ተጀምረው የዝርዝር ኦዲት ስራቸው ወደዚህኛው የኦዲት ዓመት የዞሩ 6 ኦዲቶች/ ከዚህ ውስጥ 2 ተቋርጦ በሌሎች ሁለት የተተኩ/ እና ከጥር 2006 በኋላ ተጀምረው እስከ

ታህሣስ 30/2007 የሚጠናቀቁ 16፤ እንዲሁም ከነሐሴ 2006 በኋላ ተጀምረው የዳሰሣ እና ቅኝት ሥራቸውን በማጠናቀቅ ወደ ሚቀጥለው የኦዲት ዓመት የሚዛሩ 6 የክዋኔና የአከባቢ ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡

በዚሁ መሠረት የእቅድ ዘመኑ የክዋኔና አካባቢ ኦዲት ፕሮጀክቶች አፈጻፀም ሲታይ ካለፈው ዓመት የዞሩትን 6 ኦዲቶች ጨምሮ በዚህ የእቅድ ዘመን ወጪ መደረግ ከሚገባቸው የ22 ለማከናወን ከታቀደው ውስጥ 18 ኦዲቶች ሥራ ተጠናቅቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን፣ የ1 ኦዲት በሰው ኃይል እጥረት እና 1 ሌላ ኦዲት ደግሞ ከስልጣን ክልል ወሰን ውጭ መሆን ምክንያት እንዲቋረጡ ተደርጓል። 1 ኦዲት ከሚታላለፉት አስቀድሞ የተጠናቀቀ እና የ3 ኦዲቶች ሥራቸው ተጀምሮ በተለያየ የኦዲት ደረጃ ላይ ወደ ቀጣዩ ዓመት የተላለፉ ሲሆን፣ ሁለት ኦዲቶች ተጀምረው የሚተላለፉት አልተጀመሩም። ይህም ከእቅድ አንጻር ሲታይ ሪፖርታቸው ወጪ የተደረጉት 18 ኦዲቶች (90%) ሲሆን ፣ የኦዲት ስራቸው ተጀምረው የዞሩት 3 ኦዲቶች (60%) መ/ቤቶች በመሆኑ ከአጠቃላይ ከሰው ኃይል እጥረት አንጻር ሲታይ ዕቅዱ ክንውን አጥጋቢ መሆኑን ያሣያል፡፡

የኦዲት ስራቸው የተጠናቀቁት 18 የክዋኔና አካባቢ ኦዲቶች ሪፖርቶቹ ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን ፣ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች በዚሁ ጥራዝ ተራ ቁጥር 11 ስር በዝርዝር ቀርቧል/

2.6 <u>አጠቃላይ የመንግሥት ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት</u>

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተላከው የ2006 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀው የ2006 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2.6.1 **በመልሶ ማበደር መሰብሰብ የነበረበት ሂሳብ ብር 418,803,484.57 ፣**

ግኝት

የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፌደራል መንግስት ፋይናንስ የሚተዳደርበት ማንዋል መሰረት በመልሶ ማበደር ከተሰጠው ብድር ውስጥ በበጀት ዓመቱ ተመላሽ መደረግ የነበረበት ሂሳብ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለስኳር ፋብሪካዎች ከተሰጠው ብድር ውስጥ መሰብሰብ የነበረበት የወለድና ቅጣት ሂሳብ ብር 418,803,484.57 እስከ ሰኔ 30/2006 ዓ.ም ድረስ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል ፡፡ ሁኔታውን በተመለከተ ዋናው ገንዘብ እንዲተላለፍ ሲደረግ ወለድና ቅጣት ግን የክፍያ ጥያቄ በመ/ቤታችን ቀርቦ ክፍያ ባለመፈጸማቸው በስራ ክፍሉ አስተባባሪነት የሚመለከታቸውን የስራ ሀላፊዎች ክብር ሚኒስቴሩ የማይከፍሉበት ምክንያት እንዲያነጋግሩ በማድረግ በክብር ሚኒስቴሩ ትእዛዝ የሚጠበቅባቸውን ክፍያ እንዲፈጽሙ ትእዛዝ ቢተላላፍም እስከ ዛሬ ድረስ ምንም አይነት ክፍያ ባለመፈጸማቸው ነው፡፡ በቀጣይም ክፍያ እንዲፈጸም የውይይት መድረክ ተዘጋጅቷል በማለት ኦዲት አስደራጊዎች ገልጸዋል፡፡

ስጋት

የብድር ተመላሽ በወቅቱ አለመሰብሰቡ የበጀት እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከተለያዩ በመልሶ ማበደር ገንዘብ ከወሰዱ ድርጅቶች ተመላሽ መደረግ የሚገባውን የዋና ገንዘብ እና ወለድ ክፍያ በቂ የሆነ ክትትል በማድረግ ተበዳሪው ዕዳውን በወቅቱ እንዲከፍል ማድረግ ይገባል፡

2.6.2 **ለክልሎች የካፒታል፣ የውጭ አገር ብድርና እርዳታ የተፈቀደው በጀት ስራ ስለመዋሉ ማረጋገጥ ያልታቻለ ብር 586,258,548.00፣**

ግኝት

ለክልሎች ከተፈቀደላቸው የካፒታል የውጭ አገር ብድርና እርዳታ በጀት ብር 586,258,548.00 ስራ ላይ ስለመዋሉ የቀረበ ማስረጃ ባለመኖሩ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም። ሁኔታውን በተመለከተ የውጭ አገር የብድርና የእርዳታ በጀት መደበኛውን የሂሳብ ፍሰት ሳይከተል ቀጥታ ወደ ክልሎች እንዲደርስ የሚደረግና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል የማይተላለፍ መሆኑን በመግለጽ ማስረጃ ሊያቀርቡ የማይችሉ መሆኑን ኦዲት አስደራጊዎች ገልጸዋል፡፡

ስጋት

ወደ አገር ውስጥ የገባ የእርዳታ ሂሳብ ላይታወቅ ናለብክነት ሊዳረግ ይችላል።

የማሻሻያ ሀሳብ

በዕቅድ የተያዘው ስራ እንዲሳካ የቅርብ ክትትል በማድረግ አፈፃፀሙን መከታተል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

2.6.3 **ለ2006 በጀት ዓመት የመነሻ ሂሳብ ሚዛን /Opening balance/በተመለከተ**

ግኝት

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/ሀ መሰረት የበጀት

ዓመቱ ሂሳብ ሪፖርት ሲዘጋጅ የአጠቃላይና ተቀፅላ ሌጀሮች መነሻ ሚዛን ከ2005 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሚዛን በትክክል መተላለፉንና ሂሳቡም ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣

1. በተሰብሳቢ ሂሳብ ከ2005 በጀት ዓመት የዞረ ሂሳብ ተብሎ ለ2006 በጀት ዓመት መነሻ ምዝገባ በሂሳብ መደብ 4210 የተመለከተው ብር 32,653,472.28 ከመቼ ጀምሮ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንደተመዘገበና ሂሳቡም የምን እንደሆነ የተቀፅላ ሌጀር ተለይቶ ባለመመዝገቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

2. በተከፋይ ሂሳብ ከ2005 በጀት ዓመት የዞረ ሂሳብ ተብሎ ለ2006 በጀት ዓመት መነሻ ሂሳብ ምዝገባ በሂሳብ መደብ 5052 ብር 13,274,435.33 እንድሁም በሂሳብ መደብ 5054 ብር 8,251,376.10 በድምሩ ብር 21,525,811.43 የተወሰደው ከመቼ ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ እንደተመዘገበና ሂሳቡም የምን ሂሳብ እንደሆነ በተቀፅላ ሌጀር ተለይቶ ባለመመዝገቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሁኔታውም ኦዲት አሰደራጊዎች ሲገልፁ፣ የተጠቀሱት የሂሳብ መደቦች በቀጣይነት በማጣራት ተቀፅላ ሂሳብ ሌጀር እናዘጋጃለን በማለት መልስ ሰጥተዋል ።

<u>ስጋት</u>

በአቅራቢው ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም የተከፈተ ተቀፅላ ሌጀር አለመኖሩ ከማን እንደሚሰበሰብና ለማን እንደሚከፋል እንዳይታወቅ ከማድረጉም ባሻግር፣ ውስን የመንግስትን ሀብት ለብክነትና ለብልሹ አሰራር ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያዛባ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦች የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003ን መሰረት ያደረገ መሆን አለባቸው ፣ እንዲሁም የስራ ኃላፊዎች የሂሳብ ምዝገባዎቹ በመመሪያው መሰረት መከናወናቸውን መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡ የሂሳቦቹ ሁኔታም ተጣርቶ አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.6.4 **የእርዳታ (ቻናል ሶስት)ሂሳብ በተመለከተ**

ግኝት

የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሂሳብ አያያዝ ስርአት፣ በManual 3, FGE Accounting system volume 1.3 Project report A.185 ምእራፍ 3 ላይ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (ማእከላዊ ሂሳብ መምሪያ) በሁሉም የገንዘብ ፍሰት መንገዶች የሚመጡ እርዳታዎችን እና ልዩ የእርዳታ ገንዘቦችን በመዝገብ ይይዛል፣ እንዲሁም በሁሉም የሂሳብ ምንጮች የሂሳብ እንቅስቃሴ በማጠቃለልና ዓመታዊ ሂሳብ በመዝጋት በፌዴራል ዋና ኦዲተር ያስመረምራል በሚለው መሰረት ተግባሪያዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በቻናል 3 ስር የሚጠቃለለው ማለትም በለጋሾች በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ በእነሱ ቁጥጥር ስር ሆኖ በተጠቃሚው መ/ቤት ስም የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠለት ስራ ላይ የሚውለውን ገንዘብ ተከታትሎ በሂሳብ ውስጥ መጠቃለል ሲገባው ይህ ተግባሪያዊ ሳይሆን ተገኝቷል ፡፡

ስጋት

በሁሉም ፍሰት ዓይነቶች (በገንዘብ / በአይነት እርዳታ እና ብድር) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ገንዘብ ተከታትሎ ካልተመዘገበ በትክክለኛ የምዝገባ ሂደት ሀገሪቷ ውስጥ የሚፈሰውንም ሆነ የሚንቀሳቀሰውን ገንዘብ ለማወቅ ያስቸግራል።

በተጨማሪም ወደ ሀገር ውስጥ ስለፈሰሰው እርዳታ በለጋሾቹ በኩል ለተለያዩ ዓለም አቀፍም ይሁን ሀገር አቀፍ ባለድርሻ አካላት በሪፖርት የሚገለጸውን የገንዘብ መጠን ትክክለኝነት ለማወቅ ያስቸግራል።

የማሻሻያ ሃሳብ

የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ማንዋሉ ላይ በተገለጸው መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ የሚፈሰውን ገንዘብ ተከታትሎ መመዝገብና ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡

2.6.5 **በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሒሳብ መግለጫ የማያቀርቡ መኖራቸው**

ግኝት

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 59 መሰረት ሚኒስቴሩ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትና የማእከላዊ ግምጃ ቤትን ሂሳብ በማጠቃለል የፌደራል መንግስትን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህ አንጻር ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ አቅርበው የተስተካከለው ሂሳብ መግለጫም የሚጠቃለል መሆኑንና አመታዊው የገቢና ወጪ ሂሳብ ትክክለኛውን ሁኔታ የሚያሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለናሙና ያህል ከታዩት መ/ቤቶች የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፣በውኃ፣ የመስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት ፣ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን ፣የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ፣የአዳማ ዩኒቨርስቲ ፣የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ፣ የዲላ ዩኒቨርስቲ ፣የጎንደር ዩኒቨርስቲ ፣የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ፣መቀሌ ዩኒቨርስቲ ፣ የወሎ ዩኒቨርስቲ ፣መቱ ዩኒቨርስቲ ፣የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኦዲት ወቅት ተገኝተው ሪፖርት የተደረጉ የተለያዩ አላግባብ

የተመዘገቡ፣ በስህተትና በድጋሚ የተመዘገቡ የተሰብሳቢ የተከፋይ እና የገቢና ወጪ ሂሳብ በሂሳብ ያላካተቱ በመኖሩ፣ በየሪፖርታቸው በቀረበው ዝርዝር ላይ ማሴተካከያ እንዲያደርጉ ቢገለጽም፣ ሪፖርት አቅራቢ መስሪያ ቤቶች በተሠጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሂሳብ መግለጫው ሳይስተካከል ሪፖርት ያቀረቡና ያልተስተካከለውም ሂሳብ መግለጫ በተጠቃለለው የፌደራል መንግስት አመታዊ ሂሳብ ውስጥ የተካተተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

የሂሳብ አቅራቢ መ/ቤቶች በተገኙት የኦዲት ግኝቶች ምክንያት የመ/ቤቶቹን የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የተዛባ ስለሚያደርጉት የተጠቃለለውን የመንግስት የገቢና የወጪ ዝርዝር ሂሳብ ሪፖርት ከማዛባቱም ባለፈ ተዓማኒ እንዳይሆን ያደርገዋል፣

<u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u>

በሚመለከተው የመንግስት ፋይናንስ የስራ ክፍል የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል፡፡ለሂሳቡም የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ሊደረግ ይገባል። ለወደፊቱም ሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ኦዲት የተደረገው የሂሳብ ሪፖርት ላይ ተመስርተው ሂሳባቸውን አስተካክለው ማቅረባቸውን የሚረጋገጥበት ስርዓት በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

2.7 <u>የሌሎች ስራ ክፍሎች አፈፃፀም</u>

2.7.1. <u>የዋና ኦዲተር ልዩ ጽ/ቤት</u>

ወደ ዋና ኦዲተር ጽ/ቤት የሚመጡ እንግዶችን የማስተናገድና በዋና ኦዲተር የሚመሩ ስብሰባዎችን ለሚመለከታቸው የማሳወቅ እና የማስተባበር ስራዎች ተሰርቷል፣ ምላሽ ለሚያስፈግጋቸው ደብዳቤዎች በወቅቱ ምላሽ ተሰጥቷል፣ ከሐምሌ/2005 እስከ ሰኔ 30/2006 የደረሱን የ78 የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና በመንግሥትና አጋር ድርጅቶች የሚተገበሩ 174 ፕሮጀክቶች በድምሩ 252 ኦዲት ሪፖርቶችን ከሂሳብ ምርመራ አገልግሎትና ፈቃድ ከተሰጣቸው

ኦዲተሮች የደረሱን በየኦዲት አስተያየታቸው ተለይተው በመመዝገብ ADVERSE እና DISCLAIMER የሆኑትን የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የማስተካከያ መርሀ ግብር እንዲያዘጋጁ በማሳሰብ፣ የ16 ልማት ድርጅቶች ኦዲት ሪፖርት ኮፒው ለሕዝብ ይፋ ውይይት እንዲቀርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ተልኳል፣ ከሐምሌ 2006 እስከ ታህሳስ 30/ 2007 ዓ· ም ለመ/ቤታችን የደረሱን የ37 የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና በመንግሥትና አጋር ድርጅቶች የሚተገበሩ የ31 ፕሮጀክቶች ኦዲት ሪፖርቶች ታይተው በየኦዲት አስተያየታቸው ተተንትነው የተየዙ ሲሆን፣ የአራት ድርጅቶች የኦዲት አስተያየት ሊያሰጡ የማይቻልና አንድ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠበት በመሆኑ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው ደብዳቤ ተጽፏል፣

በ2006 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርታቸው ከደረሱን የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት የኦዲት አስተያየት ሊያሰጡ የማይቻልና አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው የሆኑት ድርጅቶችን ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ በማካተት ረቂቅ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጄክቶች የ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በ2006 ዓመታዊ የዋና ኦዲተር ሪፖርት በጥቅል በማካተት ቀርቧል፣ የ2006 ለፓርላማ የሚቀርበውን ዓመታዊ ሪፖርት በማጠናቀር በ3 ጥራዝ ተዘጋጅቶ አጭር መግለጫው ሚያዝያ 14/2006 ዓ· ም በክቡር ዋና ኦዲተር ለፓርላማ ቀርቧል፣

ከፓርላማ ጋር የሚደረጉትን ግንኙነት በማስተባበር፤ የኦዲት ስራችንን በሚመለከቱ የተለያዩ ሪፖርቶች እንዲደርሱ ተደርጓል፣ የAFROSAI-E ስብሰባ ዝግጅት ሥራዎችን ማሳተፍና ማስተባበር ስራዎች ዝግጅት ተደርጎ ስብሰባው ከሚያዝያ 27 እስከ ግንቦት 1/2006 ዓ.ም ተካሄዶ በስኬት ተጠናቋል፣ ከተጠየቁት ልዩ ኦዲቶች በልዩ ጽ/ቤቱ ኦዲት በማድረግ የ4 ልዩ ኦዲት ሪፖርት ወጪ ተደርጎ ለጠየቀው አካል የተላከ ሲሆን፣ 1 ልዩ ኦዲት በማከናወን ላይ ነው፣

2.7.2. የህግ ክፍል

መ/ቤቱ የሚከሰስበትንና የሚከስባቸውን ጉዳዩች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መከታተልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣ ከተለያዩ የመ/ቤት ሠራተኞች ከሥራ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ላይ የሕግ ምክር ሲጠይቁ ምክር መስጠት፣ ከመ/ቤቱ ከሁሉም የስራ ክፍሎች ለሚቀርቡ የቃልም ሆነ የጽሑፍ የሕግ አስተያየቶች ጥያቄዎች የሕግ አስተያየት መስጠት፣ መ/ቤቱ ሲወክል የሕግ አገልግሎቱ በተወከለበት መድረክ ሁሉ በመገኘት የተወከለበትን ጉዳይ መፈጸም፣ መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው ሥልጠና ላይ መሳተፍና ሲጠየቅም ሥልጠና መስጠት፣ መ/ቤቱን የሚመለከቱ ህጎች ደንቦችና መመርያዎች (የስነ ምግባርን ጭምር) ከወቅቱ ጋር እንዲሄዱ በየጊዜው በመፈተሽ መስተተካከል የሚገባቸውን በማጥናት ለመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ማቅረብ፣ በመ/ቤቱ በማንኛውም የስራ ክፍል የተፈጸሙ የህግ ጥሰቶች ሚያጋጥሙ ከሚመለከተው ሃላፊ ጋር በመነጋገር እንዲስተካከል ወይንም የማሰተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

2.7.3. የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት

የተቋሙን የ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2007 በጀት አመት የስራ ዕቅድ ማዘጋጀትና በስራ ላይ ማዋል፣ ወቅታዊ የክትትልና ግምገማ ስራዎች ማድረግ /ወርሃዊ የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ/ የስራ ዕቅዶችን ማስፈጸሚያ በጀት ማዘጋጀት እና ለየስራ ክፍሎች መደልደልና አጠቃቀሙን መከታተል፣ ተቋማዊ አቅምን ለመገንባት የተቀረፁ ፕሮጀክቶች አተገባበርን መከታተልና ማስተባበር፣ የዳይሬክቶሬቱን የመፈጸም አቅም በሰው ሃይልና በስልጠና ማጠናከር በሌሎች አግባብነት ባላቸው የኮሚቴ ስራዎች ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ዋናዋና የታቀዱ ስራዎች ነበሩ፡፡

በዚህም መሰረት የመ/ቤቱ የ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት አግባብ ላላቸው አካላት ሁሉ እንዲደርሳቸው መደረጉ፣ የተቋሙ የ2007 የስራ ዕቅድና በጀት ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅ በማድረግ በስራ ላይ እንዲውል መደረጉ፣ የ2007 በጀት ዓመት የመጀመርያና

ሁለተኛ ሩብ ዓመት የስራ አፈጻጸምና የበጀት አጠቃቀም ሪፖርቶች የማጠናቀር ስራ ተሰርቷል፤ ለ2008 በጀት ዓመት የበጀትና ስራ እቅድ ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማደራጀት ለሁሉም የስራ ክፍሎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ በዳይሬክቶሬቱ ውስጥ የሚገኙ ክፍት የስራ መደቦች በሰራተኛ እንዲሞላ መደረጉ፣ የእውቀትና ክህሎት ክፍተትን ለማጥበብ 3 የዳይሬክቶሬቱ ሰራተኞች በፕሮግራም በጀት ዝግጅት እና በኮምፒውተር የታገዘ የመረጃ አደረጃጀትና አጠቃቀም ዘዴ ላይ ስልጠና እንዲወስዱ መደረጉ እና ተቋማዊ አቅምን ለመገንባት እንዲያስችል ታስቦ በዝግጅት ምዕራፍ ላይ ባሉ ሁለት ፕሮጀክት ቀረጻ ላይ በመሳተፍ የመ/ቤቱ ፍላጎት በአግባቡ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

2.7.4. <u>የፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስ/ዳይሬክቶሬት</u>

የመ/ቤቱ አብይ ተግባር የሆነውን የኦዲቱን ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ማከናወን እንዲቻል ለኦዲት ስራ የሚያስፈልጉ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈፀም፣ ግዥዎች በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ማድረግ፣ የመ/ቤቱን ንብረቶች በአግባቡ መመዝገብና መቆጣጠር ፤ የሂሳብና የንብረት መቆጣጠርያ መዝገቦችንና ሰነዶችን በአግባቡ መያዝና መጠበቅ፤ ለኦዲት ሲፈለጉም አቅርቦ ማስመርመር የሂሣብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቆ መላክን በእቅዱ አካትቶ ወደስራየተገባ ሲሆን ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በመ/ቤቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋሉ ወጪዎችን ክፍያ መፈጸሙ፣ የግዢ እቅድ በማዘጋጀት በግዥ ዕቅዱ መሰረት የተገዙ እቃዎች ንብረት ክፍል ገቢ በማድረግ ለተገልጋዮች በወቅቱ እንዲደርሱ ተደርጓል፤ የመ/ቤቱን የፋይናንስ አፈጻጸም በተመለከተ የ2006 በጀት ዓመት አመታዊና የ2007 በጀት ዓመት የመጀመርያና ሁለተኛ ሩብ ዓመት ሪፖርቶች አግባብ ላለው አካል ሁሉ እንዲደርሱ ተደርጓል፤የሂሳብና ንብረት ሰነዶች፣ ሪፖርቶችና የሥራ መረጃዎች ተጠናቅረው ለማንኛውም ዓይነት ጠቀሜታ ሊውሉ በሚያስችል ሁኔታ በማደራጀት እና ወቅቱን ጠብቆ እንዲተላለፍ መደረጉ፣ ገቢና ወጪ

የሆኑ ሂሣቦች በተገቢው መንገድ በመመዝገብ እና ለሚመለከታቸው አካላት እንዲላኩ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

2.7.5. የትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክቶሬቱ የተቋሙን ራዕይ እና ተልዕኮ ሊያሣካ የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል በጥራትና በብዛት እንዲኖር የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ለመስጠት መነሻ የሚሆን የፍላጎት ደሰሳ ጥናት በማድረግ ተለይተው በታወቁ አካባቢዎች ላይ ስልጠና መስጠት ወይም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ የተሰጡ ስልጠናዎች ያስገኙትን ፋይዳ መገምገም፤ ቀደም ሲል በተጀመሩና በሂደት ላይ የሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ስራዎች ላይ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ የሚሉ ተግባራትን በእቅድ ይዞ ወደስራ የገባ ሲሆን ባለፉት 9 ወራት ውስጥ ሠራተኞች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ስልጠና እንዲያገኙና የሁለተኛ ዲግሪና የፕሮፌሽናል ስልጠና በመከታተል ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች አስፈላጊውን ክፍያ ወቅቱን ጠብቆ እንዲፈጸም የማመቻቸት ስራ ለመስራት ተሰርቷል፤ በማኔጅመንት ዲቨሎፕመንት፣ በኮሙኒኬሽን ማኔጅመንት፣ በኮሙኒኬሽን ቱልኪት፣ በቴክኒካል አፕዴትና ሪፍሬሽመንት፣ በፕሮፌሽናላይዜሽን ወርክሾፕ፣ በኢንቫይሮንመንት ወርክ ሾፕ፣ በ13ኛው የአፍሮሳይ/ኢ. ጠቅላላ ጉባኤ እና በኳሊቲ አሹራንስ ሪቪው ላይ በአጠቃላይ በ10 የስልጠና አይነቶች እና ስብሰባዎች ላይ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ሰራተኞች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም IFMIS ስልጠና ለ29 ኦዲት ባለሙያዎች፣አመታዊ የዕቅድ ዝግጅት የሚደረግበትን ቦታ የማመቻቸት ስራ ተከናውኗል፣በእቅድ ወቅት የሚሰጡ ስልጠናዎች /ቴክኒካል አፕ ዴት፤ የእቅድ ተርሚኖሎጅዎች/ተለይተዋል፡የቢ.ኤስሲ ስልጠና ለግማሽ ቀን ተሰጥቶአል፣ በመልካም አስተዳደር ዙሪያ ውይይት አንድ ቀን ከግማሽ ተደርጎአል፤

በተጨማሪ ከሱዳን እና ከሶማሊያ አገራት ዋና ኦዲት መ/ቤቶች ለመጡ የኦዲት ባለሙያዎች ለሶስት ሳምንታት የልምድ ልውውጥ መድረክ በማመቻቸት ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል፤ መ/ቤቱን ለቀው ለሄዱ ሰራተኞች ለኤ.ሲ.ሲ.ኤ እና የሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች በውል የገቡትን

ግዴታ የተወጡ ስለመሆኑ ማጣራት እየተደረገ ግዴታቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ያልተወጡትን በመለየት የተከፈለላቸውን ሂሳብ በማጣራት ገንዘብ እንዲመለስ መደረጉ፣ የዳይሬክቶሬቱ አፈጻጸም መመሪያ የሚሻሻልበት ስራ እየተሰራ በመሆኑ ለጊዜው የሚያገለግል የአሰልጣኞች መመልመያ መስፈርት ድራፍት መዘጋጀቱ እና የስልጠና ፍላጎት መለያ ጥናት እየተደረገ በየስራ ክፍሉ ያሉትን ክፍተቶች በመዳሰስ ስልጠናዎች እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

2.7.6. የኢንፎርሜሽን ሰርቪስ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ዳይሬክቶሬቱ መ/ቤቱ ወቅቱን የጠበቀ እና ውጤታማ የኦዲት ሪፖርት ማዘጋጀት እንዲችል የኦዲቱን ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መደገፍ የዳይሬክቶሬቱ ዋናው ዓላማ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ ከግብ ለማድረስ ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መገንባት፣ሁሉንም የሥራ ክፍሎች በመረጃ ቴክኖሎጂ መደገፍና የወረቀት አጠቃቀምን መቀነስ፣የወቅቱን ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በሥራው ውጤታማ የሆነ የሰው ሃይል እንዲኖር ማስቻል ዋና አላማው በማድረግ እንዲሁም ካለው የስራ ባህርይ ማለትም ከውጭም ሆነ ከውስጥ ካሉበት የደህንነት ስጋቶች አንጻር የመረጃ ሥርዓት ደህንነት ፖሊሲ በመቅረጽ በስራ ላይ ማዋልን የእቅዱ አካል አድርጎ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

በዚህም መሰረት ባለፉት 9 ወራት ውስጥ በሰርቨር ውስጥ የተከማቹ በርካታ መረጃዎች ለተጠቃሚው ምቹ በሆነ መንገድ ለማቅረብ የሚያስችል ዲዛይን ማዘጋጀት፣ መረጃዎች በሚፈለገው መልኩ መግባታቸው ማረጋገጥ፣ የመ/ቤቱ ኢሜይል ሲስተም ለተጠቃሚዎች የተሰጠውን የሚስጥር ቁልፍ ተጠቃሚዎች በራሳቸው እንዲቀይሩ የሚያስችል አሰገዳጅ ሰርዓት እንዲዘረጋ መደረጉ፣የሰው ሃብት መረጃዎች ለአሰራር በሚያመች ሁኔታ በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ ማስቻል፣ አዲስ አንቲ ቫይረስ መጫን እና የሃርድ ዌርና የሶፍት ዌር ጥገናዎችን ማከናወን የሚሉት ለመስራት አቅዶ ሁሉም የመ/ቤቱ IT equipment ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ፀረ-ቫይረስ ፕሮግራሞች በትክክል መስራታቸውን እና በተለይም የዳታ ማዕከሉ አካባቢ ደህንነት የተጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ ስራዎች መሰራቱ፣

መረጃዎቹ በሚፈለገው መልኩ መግባታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ከእያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት የሚላኩ መረጃዎች ዝርዝር እንዲዘጋጅ መደረጉ፣ በመረጃ ማእከሉ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች እንዳይጠፉ ባክአፕ ማድረጉ፣ የመረጃ አልግሎት እቃዎችን/ሶፍትዌሮችን በሚገባ ሊይዝ የሚያስችል ሲስተም የተዘጋጀ ሲሆን የኮንፊገሬሽን ስራ እየተከናወነ መሆኑ፣ለፋይናንስና ግዥ ዳይሬክቶሬት የውሎ አበል ስራን ሊደግፍ የሚችል ሲስተም መዘጋጀቱ፣ ለሰው ሃብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ሰራተኞች ሶፍትዌር የማስተዋወቅ ስራ በማከናወን እና ስልጠና በመስጠት በሶፍትዌሩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት በማድረግ የማሻሻያ ስራው ተከናውኖ ወደ ስራ እንዲገባ መደረጉ፣ለስልጠና ክፍል በተዘጋጀው ሲስተም ላይ ከተጠቃሚዎች በተሰጠ አስተያየት የማስተካከያ ስራ ተከናውኗል፣ ለቤተመጻፍት ሰራተኞች አዲስ በተዘረጋው የቤተመጻሕፍት ሲስተም ላይ ስልጠና መሰጠቱና በዚሁ መሰረትም የቤተመጻሕፍት ዝርዝር መረጃዎች ወደ ሲስተሙ መግባት ጀምሯል፡፡

2.7.7. <u>የሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት</u>

መ/ቤቱ በልዩ ልዩ ህጐች ደንቦች እና መመሪያዎች የተሰጡትን የሥራ ኃላፊነትና ግዴታ በሚገባ ለመወጣት የሚያስችለው ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማንኛውም ጊዜ እንዲኖረው ለማስቻል ክፍት መደቦችን በቅጥር፣ በደረጃ እድገትና በዝውውር ለመሙላት፣ እና የእያንዳንዱ ሠራተኛ የሥራ መዘርዝር በአግባቡ በማዘጋጀት የመ/ቤቱን ዓላማ ስኬታማ እንዲሆን እገዛ ለማድረግና ሌሎች አስተዳደራዊ ሥራዎች ለመሥራት አቅዶ በዘጠኝ ወራቱ ውስጥ የ75 ሠራተኞች ቅጥር መፈጸሙ፣ ለ59 ሠራተኞች የደረጃ ዕድገት መሰጠቱ፣ የመ/ቤቱ ሠራተኞች የሥራ አፈጻፀም ሪፖርት በወቅቱ ተሞልቶ እንዲቀርብ ክትትል መደረጉ፣ በመሠረታዊ የስራ አካባቢና ደህንነትና ጤንነት ዙሪያ ለሁሉም ሰራተኞች የሚደርስ በራሪ ወረቀቶች መሰራጨቱ፡ በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ ላይ በሶፍትን በሃርድ ኮፒ ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች መሰራጨቱ ፣በኢቦላ በሽታ ዙሪያ የተዘጋጀ በራሪ ወረቀት እና በቪዲዮ የተደገፈ ማብራሪያ /outlook/ ለሚጠቀሙ

የመ/ቤቱ ሠራተኞች መሰራጨቱ፣ የኦዲቱን ሥራ በሚገባ ለማከናወን የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን የግቢና የንብረት ጥበቃ፣ የውሀ፣ የመብራት፣ የስልክ፣የመልዕክት፣የግቢ ውበትና ጽዳት አገልግሎቶችን በመስጠት በርካታ ተግባራትን መከናወኑንና በሌላም በኩል የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን የሰርቪስ እና ጥገና አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኙ፣ ጥገናቸው በኢንሹራንስ መሸፈን ያለበት አግባብ ባለው አካል በኩል በማስፈፀም፣ የትራንስፖርት ስምሪት አገልግሎት ለተጠቃሚዎች በተቻለ ፍጥነት እንዲቀርብ በማድረግ፣ የተቋረጡ፣ የተበላሹ እና የተሰበሩ የአገልግሎት መስጫ አውታሮች በአፋጣኝ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

መ/ቤቱ እስከ መጋቢት መጨረሻ 405 ሠራተኞች የነበሩት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 261 ኦዲተሮች 141 የድጋፍ ዘርፍ ሰራተኞች እና 3 የበላይ ሃላፊዎች ናቸው፡፡ በጾታ ስብጥር ረገድ ደግሞ 235 ወንዶች እና 170 ሴቶች ናቸው፡፡

2.7.8. <u>የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት</u>

የመ/ቤቱ ሀብትና ንብረት ከምዝበራ፣ ከማጭበርበር፣ ከስርቆት፣ አላግባብ ከመጠቀምና ከብልሽት መጠበቁን፣ የሚዘጋጁት የፋይናንስ መግለጫዎች ትክክለኛና ተአማኒነት ያላቸው መሆኑን ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በኦዲት በማረጋገጥ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን በመፈተሽና በመገምገም፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፣በማጣራት የመ/ቤቱ አመራሮች፣ ሠራተኞችና ሌሎችም የሚጠይቁትን ሙያዊ የምክር አገልግሎት በመስጠትና በማገዝ የመ/ቤቱ ዓላማ፣ ተልዕኮና ግብ እንዲሳካ ጥረት ማድረግን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን አቅዶ ወደ ስራ የገባ ሲሆን በበጀት አመቱ መጨረሻ የሂሣብ መዝጊያ ወቅት በጥሬ ገንዘብ፣ በሠነድና በአላቂ የቢሮ ዕቃዎች ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተገኘዉ ሂሣብ ለመንግሥት በትክክል ፈሰስ መደረግ የሚገባዉን ሂሣብ አጣርቶ ሪፖርት ማቅረብ፣ መ/ቤቱ የተጠቀመባቸዉን የገቢ፣ የወጪና የንብረት ሠነዶች የመጨረሻ ገጾች ላይ ምልክት በማድረግና በመዝጋት፣ በሣጥን ዉስጥ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተገኘዉን ጥሬ ገንዘብና ሠነድን በዝርዝ

በመቁጠር፣ በመዝገብ ከወጪ ቀሪዉ ሆኖ የሚታየዉን ሂሣብ ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ በንብረት ክፍል ዉስጥ ከወጪ ቀሪ ሆነዉ የተገኙትን አላቂ የቢሮ ዕቃዎችን አንድ በአንድ በመቁጠርና የሂሣቡንም ስሌት ትክክለኛነት የማረጋገጥ ስራ ሰርቷል፡፡

2.7.9. የውጭና የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት

የውጭና የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ተልዕኮ፤ ራዕይና ዓላማዎችን ለማሳካት በሚደረገው ርብርብ ሁሉን አቀፍ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም የውስጥና የውጭ ኮሚኒኬሽን ተግባራትን በማከናወን የተቋሙን መልካም ገፅታ ለመገንባት፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን አግባብ ባለው ሜዲያ በማሰራጨት ከደንበኞቹና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ግንኙነት ለማጐልበት የሚያስችል የህዝብ ግንኙነት ሥራ በማከናወን በተቋሙ የተግባር እንቅስቃሴዎች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መግባባት መፍጠር የሚሉትን ለማከናወን አቅዶ የመ/ቤቱን አገልግሎት የሚፈልጉ ባለድርሻ አካላትና ተገልጋዩችን ድጋፍ ማድረግ፣ የኢዲቶሪያል መተዳደሪያ ማንዋል ረቂቅ ተዘጋጅቷል፤ የሚመለከታቸው አካላት ግብዓት ሰጥተው ዳብሯል፡፡ የተቋሙን የፎቶ ግራፍና ቪዲዮ ቀረጻና የመስተንግዶ ስራ ማከናወን፣ የፌዋኦ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ መረጃ ለህብረተሰቡ ማድረስና የመ/ቤቱን መልካም ገጽታ መገንባት፣ የፌዋኦ ኩነቶችና የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረኮች ደረጃውን ጠብቀው በጥራት እንዲዘጋጁ ማደረግ ከዚህ የሚገኝውን ልምድ ለቀጣይ ስራዎች እንደ ግብዓት መጠቀምና የተገኘውን ተሞክሮ ለሌሎች ማስተላለፍ የሚሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

2.7.10. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ስርዓተ ጾታ ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎች

በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የግማሽ ቀን የቡና ጠጡ ፕሮግራም በማዘጋጀት ገለጻ እና ውይይት ተካሂዷል፣ በራሪ ወረቀት ተዘጋጅተው በoutlook ለሚጠቀሙ ለሁሉም የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሰራጭቷል፡፡ የዓለም የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ ቀንን የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት

ተከብሯል፡፡ በዕለቱም በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት፣ የቅድመ ወሊድ ክትትል እና ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚሰሩ ሠራተኞች ለኤች.አይ.ቪ የሚጋለጡበት ምክንያቶች እና መደረግ ያለባቸው መፍትሄዎች ዙሪያ የተዘጋጁ በራሪ ወረቀቶች በፕሮግራሙ ላይ ለተገኙ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሰራጭቷል፡፡

የስርዓታ ፆታን በተመለከተ ኮሚቴው ከስልጠና ክፍል ጋር በመተባበር በሁለት ዙር Women and career Challenges በሚል ርዕስ 76 ተሳታፍዎች የተሳተፉበት የፓናል ውይይት ተደርጎል። የስርዓታ ፆታ እና፣ የኤችአይቪ/ኤድስ እና የስነ ምግባር ነክ ጉዳዮች የ2007 ዓመታዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

2.7.11. <u>ኦዲት ምርመርና ስርፀት ዳይሬክቶሬት</u>

ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ውስጥ፡-

1. የ 125 የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሥጋት ክለሣ ስራ ተከናውኗል
2. ቋሚ የኦዲት ስራ ወረቀቶች በማሰባሰብ የማደራጀት ስራ ተሰርቷል
3. የኦዲት ጥራት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ ሃላፊ ቀርቧል
4. የጥራት ቁጥጥር ማንዋል ተከልሶ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ ሃላፊ ቀርቧል

5. ለዳይሬክቶሬቶች እንዲሠራጩ በታዘዘው መሠረት 28 ሰነዶች መሠራጨቱ፣
6. ለመ/ቤቱ ያልደረሱ ለመ/ቤቱ ስራ አስፈላጊ የሆኑ 16 መመሪያዎች 10 አዋጆችና 7 ደንቦች ለሰራተኛ ተደራሽ እንዲሆኑ ስካን በማድረግ በሰርቨር ላይ እንዲቀመጡ ተደርጓል
7. በ4 መ/ቤቶች ላይ የድህረ (የ2005/06) የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ተከናውኖ በግኝቶቹ ላይ ከዳይሬክቶሬቶች አስተያየት ከተሰበሰበ በኋላ ለመ/ቤቱ ሃላፊ ቀርቧል

8. የ8 መ/ቤቶች የቅድመ ኦዲት ሪፖርት(የ2006/07) የጥራት ማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል

2.7.12. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠትን በተመለከተ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለግል ኦዲተሮች እና ለሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፣ የማደስና የመሠረዝ ሥልጣን፣ እንዲሁም በማናቸውም የፌዴል መ/ቤትና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር የመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊ የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 5/16 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለ6 ኦዲተሮችና ለ66 የተፈቀደላቸው የሂሣብ አዋቂዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፣ ለ510 የሂሣብ አዋቂዎችና ለ108 ኦዲተሮች የዓመታዊ የሰርተፍኬት ዕድሣት ሥራ ተሰርቷል። /ይህ ስራ ጥር/2007 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጁ መሰረት ለተቋቋመው የኦዲትንግና ሂሳብ ቦርድ ተላልፏል።/ በተጨማሪም የ3 መ/ቤቶች ለ7 የውስጥ ኦዲት ሰራተኞች ደረጃቸው ተገምግሞ እንዲሰጣቸው በተጠየቀው መሰረት ተሰጥቷቸዋል።

3. በእቅድ አፈጻጸም ረገድ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄያቸው

3.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- በብዙ መ/ቤቶች ለሰራተኞች እና የአመራር አካላት በመንግስት ፖሊሲና ስተራቴጂ ላይ ስልጠና ሲሰጥ ስለነበር ሰነዶችን በወቅቱ የሚያቀርብና ለጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ባለመገኘቱ የኦዲቱ ስራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዳይጓዝ ማድረጉ ወይም ማጓተቱ፣
- ኦዲት ተደራጊዎች በኦዲት ማሰታወሻ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ አጠናቅሮ አለማቅረብ እና ሪፖርት ከቀረበ በኋላ ማስረጃዎች አሉን በማለት አጠናቅሮ ለማቅረብ የሚደረገው መጯጯጥ ኦዲቱን በተያዘለት የጊዜ ገደብ አጠናቅቆ ለመውጣት አለማስቻሉ፤
- እያንዳንዱ የስራ ክፍል እና ፈጻሚዎች የጠራ እቅድ አቅርቦ አፈጻጸምን የመከታተል አቅም ውስንነት መኖሩ
- ከሃምሌ 2006 ጀምሮ የተደረገውን የደመወዝ ማሻሻያ ተከትሎ የሰራተኞች ደመወዝ መሻሻል የታየበት ቢሆንም ለሌሎች የሲቪል ሰርቪስ መ/ቤት

ሰራተኞች የተደረገውን ማስተካከየው የመ/ቤታችንን ሰራተኞች ባለማከተቱ ከፍተኛ ቅሬታ መፍጠሩ

- በመ/ቤቱ ውስጥ ባለው ከፍተኛ የሰው ኃይል ፍልሰት የተነሳ አብዛኛው ስራ አዲስ በተቀጠሩ እና በቂ ክህሎት እወቀትና ልምድ ባላካበቱ ሰራተኞች የሚከናወን በመሆኑ በኦዲቱ ጥራት እና ቅልጥፍና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ፤
- ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ከደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ማነስ ጋር በተገናኙ እና በልዩ ልዩ ምክንያቶች መ/ቤቱን በመልቀቃቸው የኦዲት እቅዱ አፈፃፀም ላይ ተፅእኖ ማስከተሉ፤
- የተወሰኑ የመ/ቤቱ ኦዲተሮች የልዩ ኦዲት ስራ በመስራት ላይ በመሆናቸው በመ/ቤቱ በእቅድ የተያዙ ኦዲቶች በተወሰነ ደረጃ መዘግየታቸው፣
- የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ለልዩ ልዩ ማብራሪያዎችና ጉዳዮች ሲፈለጉ በወቅቱ አለመገኘት፣ሂሳባቸውን በወቅቱ ዘግተው አለማቅረብ፣ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ በወቅቱ ምላሽ አለመስጠት እና ለኦዲተሮች ሥራ የሚያስፈልግ ቢሮ በወቅቱ ያለመስጠት፣

ዋና ዋና ችግሮች ናቸዉ፡፡

3.2 <u>የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች</u>

- ክፍት የስራ መደቦችን በተፈላጊው የሰው ኃይል ለመሙላት በየሩብ አመቱ የቅጥር እና እድገት በማውጣት ችግሩን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡
- የሎጂስቲክስ እና ሌሎች ግብአቶችን አቅርቦት በማቀላጠፍ ከአንድ ስራ ወደ ሌላ ለመሸጋገር የሚወስደውን ጊዜ በማሳጠር ስራዎች በታቀደው ጊዜ እንዲከናወኑ ጥረት እየተደረገ ነው
- የሰው ኃይሉ በቅጥርና በእድገት እስከሚሟላ በየደረጃው ያሉ ሰራተኞች እና የስራ መሪዎች ክፍተቱን በመሸፈን እንዲሰሩ እየተደረገ ነው
- የተወሰኑ ሰራተኛ ትርፍ ሰዓቱን ጭምር መስዋዕት በማድረግ በመስራት ላይ ይገኛል
- ከሰራተኛ መልቀቅ፤ ሂሳብን በወቅቱ አለመዝጋት፤ መረጃን በወቅቱ አለማቅረብ እና ቢሮ በወቅቱ ካለመስጠት ጋር በተገናኘ የተከሰቱ ችግሮችን

በዘላቂነትለመፍታት መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው፡

- የእወቀት እና ክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችሉ አጫጭር ተግባር ተኮር ስልጠናዎች ተሰጥተዋል
- በመ/ቤቱ በሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ሰራተኞች የትምህርት ደረጃቸውን እና የሙያ ብቃታቸውን ለማሻሻል በሚያስችሏቸው ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ በማድረግ የቆይታ ጊዜአቸውን ለማራዘም ጥረት እየተደረገ ነው፤

ይህም ሆኖ የደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ጉዳይ የምክር ቤቱን ትኩረት የሚሻና አፋጣኝ መፍትዔ ካልተሰጠው የመ/ቤቱን አፈጻጸም ሊጎዳ በሚችል መልኩ የባለሙያ ፍልሰት መ/ቤቱን እየተፈታተነው እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል።

የ2006 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

መ/ቤታችን በ2006/2007 የኦዲት ዓመት በ135 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና በ29 ቅ/ጽ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊ ኦዲት፣ ባቀደው መሰረት የ133 መ/ቤቶችና የ26 ቅ/ጽ/ቤቶች ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን በኦዲቱ የታዩ ጉልህ የአሠራር ስህተቶችና ግድፈቶች ከመፍትሄ ሃሣቦች ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ክፍል የሚነሱ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች አብዛኞቹ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችን ደጋግመን ያቀረብናቸው ቢሆንም፣ በርካታ ጉድለት የታየባቸው መሥሪያ ቤቶች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አካላት አጥጋቢ እርምጃ ወስደው ባለመገኘታቸው አሁንም ደግመን ለማቅረብ አስፈላጊና ግዴታ ሆኖ በመገኘቱና በጉዳዩ ላይ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ4 መ/ቤቶች ብር 79,241.55 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንደሚገኝ ተውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 6 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ7 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 490,647.11 በማነስ የሚታይ ሲሆን ፣ በአንድ መ/ቤት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን /ክሬዲት የሚታይ መሆኑ ታውቋል ፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-7 እና 8 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ20 መ/ቤቶችና ለተለያዩ መ/ቤቶች ተጠሪ የሆኑ በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ- 8/ሀ - ሰ ተመልክቷል፡፡/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ/የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጓል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፤
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፤
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፤የተለያዩ ቼኮችና ባንክ በሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና በሌጀር ላይ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያለማስፈቀድ እና ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ ወይም በግዥ ሠራተኞች እጅ እንዲያዝ መደረጉ፤
- በካዝና እንዲቀመጥ ከተፈቀደው የጥሬ ገንዘብ በላይ ከፍተኛ ገንዘብ በሳጥን የሚያስቀምጡ መ/ቤቶች መኖራቸው ፣
- የተለያዩ ቼኮችና ባንክ በሒሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና በሌጀር ላይ ያልመዘገቡ፤

- በ8 መ/ቤቶች ብር 14,920,449.76 ከክፍያ መመሪያ ውጪ በመመሪያው ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፤ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1. <u>በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝባቸው መ/ቤቶች</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ78 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,025,166,722.71 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	687,904,623.73
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		866,529,560.55
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		267,354,369.34
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		<u>203,378,169.09</u>
ጠ/ድምር	ብር	<u>2,025,166,722.71</u>

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 666,440,245.66፣ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 433,466,219.10፣ የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ማስተባበሪያ ብር 174,399,737.92 ፤የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 144,266,244.06፤ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 102,154,467.22፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 77,514,902.99 ፣አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 64,943,966.34፣ የግብርና ሚ/ር ብር 64,408,202.66፤ እና ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 39,294,784.18 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2. <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- ለተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር ያልተዘጋ በ3 መ/ቤቶች ብር 111,803,250.27 መገኘቱ ፣
- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ4 መ/ቤቶችና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 6,414,090.56 መሆኑ፣
- በ3 መ/ቤቶች እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤትና 4 ቅ/ጽ/ቤቶቹ ብር 11,819,456.35 ከማን እንደሚሰበሰብ መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በመሆኑ፣ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣

- በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ በ4 መ/ቤቶች ብር 70,399,565.48 መገኘቱ፣
- ያልተሰበሰበ የቅድሚያ ክፍያ በ2 መ/ቤቶች ብር 4,977,146.17 መገኘቱ፣
- በ1 መ/ቤት በሪፖርት በብልጫ የተያዘ ቅድሚያ ክፍያ (የሂሳብ መደብ 4253) ብር 1,361,719.89 መገኘቱ

  ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ፣ዝርዝራቸው በአባሪ-10 ሀ እስከ ሰ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ/ እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግለቸው፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ25 መ/ቤቶችና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ አስራ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 176,939,859.99 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-12 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	148,034,104.83
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		10,680,464.83
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		18,212,198.44
ድምር	ብር	**176,939,859.99**

በአዋጁ ደንብና መመሪያው በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 118,073,560.67 ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 17,332,974.61፣በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 9,960,926.18 ፣ በሞጆ ቅ/ፅ/ቤት ብር 7,633,367.06 እና በድሬዳዋ ቅ/ፅ/ቤት ብር 7,507,248.72 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Coustom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖሪት የመጫኛ ማራገፊና ኢንሹራንስ ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግበር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀነስው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፤ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ሕግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበው ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልገሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስሩ ባሉ ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች 12 መ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ፣ቅጣት እና ከውዝፍ የዱቤ ሽያጭ መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 1,039,493,043.58 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-11 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 354,731,428.16 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ከጅንአድና አዲስ ፋና ያልተሰበሰበ)፣ በባህር ዳር ቅ/ፅ/ቤት ብር 194,121,340.97፣ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 160,697,495.76 ፣ በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት ብር 44,990,059.02 እና በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 43,092,521.89 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በውዝፍ የሚታየው ገቢም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው፣ ህንፃዎች በውላቸው ላይ በተገለፀው የግዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ላደረሱት የጉዳት ካሳ እና ውዝፍ የቤት ኪራይ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ለበርካታ ዓመታት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ መሆኑ ተውቋል ፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ አራት ቅ/ጽ/ቤቶች፣ 1 ተጠሪ ጽ/ቤት እና በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 265,302,012.62 እና በሌሎች 8 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የገቢ ሂሳብ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ የትራንስፖርት ወጪ ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት እንዳለበት በተደነገገው ከጅቡቲ ወደብ እስከ ቅ/ጽ/ቤቱ ደረቅ ወደብ ድረስ ለተጓጓዙበት የተከፈለውን ሂሳብ የሚያሳይ የትራንስፖርት ደረሰኝ(Inland freight invoice) ከዲክላራሲዎኑ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑና ተፈላጊ መረጃዎች በገቢ ደረሰኙ ላይ የማይጠቀስ በመሆኑ፤ብዛት ያላቸው ከፋዮች ባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል በአንድ ቅጠል የገቢ ደረሰኝ የሚዘጋጅለት መሆኑና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነተ ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-13 ሀ እና ለ ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች</u>

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 72,072,130.37 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ

ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡/የዝርዝሩ በአባሪ-15 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	28,178,903.75
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		43,893,226.62
በድምር	**ብር**	**72,072,130.37**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ በሁለት መ/ቤቶች ስር የሚገኙ አራት ቅ/ጽ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለፀ ከዋናው መ/ቤት ለሚላክለቸው ገንዘብ የገቢ ደረሰኝ የማያዘጋጁ መሆኑ ታውቋል። በተጨማሪም አንድ መ/ቤት/ መቐለ ዩኒቨርሲቲ ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፍቃድ የገቢ ደረሰኝ በማሳተም ብር 12,879,067.34 ገቢ የሰበሰበ መሆኑ ተውቋል። /ዝርዝሩ በአባሪ-14 እና 14/1 እና 15 ተመልክቷል/

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፉ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስበቸውን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና የገቢን ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች

በመንግሥት ሥም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ለማዕከላዊ

ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ/ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ15 መ/ቤቶች ብር 41,374,483.14 ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ /ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈሰስ መሆን እንዳለበት፤ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ሰልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

በገቢዎችና ባላስልጣንና ቅጽ/ቤቶች

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት፣ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 35 መሠረት ለመንግሥት መ/ቤት በስህተት ገቢ የተደረገ ሂሣብ መኖሩ ሲረጋገጥ ገንዘቡ ለባለመብቱ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በ2006 በጀት ዓመት በናሙና ከታዩት ውስጥ -
  - በከምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 2,630,021.95
  - በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 1,504,337.85
  - በአዳማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ብር 582,757.62

- በመቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ብር 635,835.15

በድምሩ ብር 5,352,952.57 በስህተት ተሰብስቦ የነበረ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ ተመላሽ ቢደረግም፣ አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበና ለከፋዩ ተመላሽ የተደረገው ሂሳብ ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

- በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት የጉምሩክ ስነስርአት አፈፃፀምና ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቃለለ መመሪያ ቁጥር 86/2005 ንዑስ ክፍል አራት(19) መሰረት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ እቃ ላይ ተገቢውን ምርት ለውጪ ገበያ እያቀረቡ ለመሆኑና በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት፣

- የቀረጥ መጠኑ ብር 28,252,497.56 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 2,905,137.04 የሆነ ጥሬ እቃ በቫውቸር ስርአት ከቀረፅ ነፃ ገብቶ በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው የቀረጥ መጠን ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋው ብር 700,946.29 የሆነ ጥሬ እቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገቡ ቢሆንም

ያልተወራረደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም ከቀረጥ ነፃ በገባው ጥሬ እቃ ልክ ምርት ለውጪ ገበያ ማቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/2002 አንቀጽ 86 እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/2002 አንቀጽ 26 በአንድ የሂሳብ ግዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ግዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ እንዳለበት ደደነግጋል፡፡በዚህ መሰረት ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ማጣራት በናሙና ከታዩት ውስጥ፡-
  - በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል በታክስ ከፋየይነት ተመዝግበው ነገር ግን ከተመዘገቡበት ጊዜ አንስቶ ወደ ታክስ ማዕከሉ መጥተው የማያሳውቁ 329 ግብር ከፋዮች እንዲሁም በተደጋጋሚ ባዶ / Nil / የሚያሳውቁ 88 ግብር ከፋዮች መኖራቸው ፡፡
  - በኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግበዉ ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳዉቁና ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 6 ግብር ከፋዮች መኖራቸው ፡፡
  - በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ለገቢ ግብር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስና ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግበዉ ገቢያቸውን በወቅቱ የማያሳዉቁና ግብርም የማይከፍሉ እንዲሁም ገቢያቸውን ማሳወቅ ያቆሙ 27 ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው በመንግስት ተቋም ከተቀጠሩ ሰራተኞች የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት አሰሪው መስሪያ ቤት በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እየሰበሰበ ገቢ እያደረጉ ለመሆኑ የሚከታተልበት ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 43(ሀ) መሰረት ማንኛውም ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በማናቸውም ሁኔታ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲይዝ አይፈቀድለትም፡፡

ነገር ግን በመቀሌ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ከቢረ ኢንተርፕራይዝ ሀላ/የተ/የግል/ማህ አዋጁ በማይፈቅደው አኳኋን አንድ ግብር ከፋይ ሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጠው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በባህር ዳር የቅ/ፅ/ቤት በኩል የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች ያሳወቁት ወርሃዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሽያጭ መጠን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ የባህር ዳር ጨርቃ-ጨርቅ ፋብሪካ አ.ማ የሀምሌ እና የነሐሴ ብር 12,098,238.87 እንዲሁም የመስከረም፤ የጥቅምት፤ የህዳር እና የታህሳስ በባለስልጣኑ የታተመ ደረሰኝ የተሰበሰበ ሽያጭ ብር 603,950.43 በጠቅላላው የብር 12,702,189.30- summery report ባለመቅረቡ የሽያጩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ ሀ-ለ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ክፍል 7 ንዑስ አንቀጽ 26 ተራ ቁ. 1 ሀ እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ግብር ባለስልጣኑ ዘንድ በመቅረብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ወይም ባለስልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ማስታወቅ እና ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ለባለስልጣኑ ለወከለው ሰው ከገቢ ማስታወቂያው ጋር በአንድነት ታክሱን መክፈል አለበት በሚለው መሰረት የቅርጫፍ ጽ/ቤቱ የግብር ከፋዮች የ2006 በጀት ዓመት የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ማሳወቀቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-
  - በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 21 የሆኑ ድርጅቶች የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ ባለመገኘቱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አልተቻለም ፡፡
  - በጅማ ቅ/ፅ/ቤት በኩል የሊሙ ሊበን የመጋቢት ወር የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀና በፋይሉ ውስጥ ያልተገኘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
  - በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤት በኩል ቁጥራቸው 9 የሆኑ ድርጅቶች የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ በግብር ከፋዮች ፋይል ውስጥ ባለመገኘቱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት አልተቻለም፡፡

ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

- በ4 መ/ቤቶች ብር 21,509,145.55 /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/ ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ከተቋራጮች ያልተሰበሰበ የመቀጫ ሂሳብ/የጉዳት ካሳ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በ2 መ/ቤቶች ብር 16,727,198.50 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ /ያልተሰበሰበ/ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31/1 ተመልክቷል/
- የአለርት ማዕከል በ2005 በጀት ዓመት ከግል የህክምና አግልግሎት ከሰበሰበው ገቢ ውስጥ የማዕከሉን ድርሻ 15% ለሆስፒታሉ ገቢም፣ ፈሰስም ያላደረገ ሲሆን፣ በዚህ በጀት ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ የማዕከሉን ድርሻ ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤
- የማዕድን ፍቃድ አውጥተው ማዕድን በማምረት ላይ ከሚገኙ ግብር ከፋዮች ውስጥ የሮያሊቲ ክፍያ 40 ከመቶ የክልሎች ድርሻ ለአፋርና ለኦሮሚያ ክልሎች እንዲሁም ለድሬዳዋ መስተዳደር የሮያሊቲ ድርሻ ክፍያ ሲፈጸም ገንዘቡ ለመድረሱ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 44,614,430.61 ለክልሎቹ የተከፈለው ሂሳብ ለመድረሱ የሚያሳይ ማረጋገጫ (ደረሰኝ) ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ገንዘብ የማይሰበሰቡ መሆናቸው፣
- የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታሉ በበጀት ዓመቱ ከፈጸመው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 1,601,290.49 ላይ የሥራ ግብር ያልቀነሰ እንዲሁም ለሆስፒታሉ የጤና ባለሙያዎች ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተፈቀደው የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ከክፍያው ላይ የገቢ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤
- ሌሎች 4 መ/ቤቶች የተለያዩ የገቢ አያያዝና አመዘጋገብ ችግር የሚታይባቸው መ/ቤቶች መሆኑ/በ አባሪ-18 ተመልክቷል/

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፣ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንድሁም በገቢ አሰበሰሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ20 መ/ቤቶች ብር 4,304,357,755.21 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገባና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 21 ተመልክቷል/ ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	12,350,459.20
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		**155,026,185.24**
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		1,871,866.24
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		4,135,109,244.53
ድምር	ብር	4,304,357,755.21

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው ዋናኛው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚሊተሪ ደመወዝና አበል የተከፈለ ብር 3,830,887,814.87፣ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር 27,350,502.50 እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 273,845,378.34 ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 110,930,205.38፣ መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,443,824.20፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 11,599,720.78 እና ዋቻሞ ዩኒቨርስቲ ብር 10,440,712.55 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት መገለፁና የሌሎች መ/ቤቶችም ክፍያ የተፈጸመባቸው ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላክው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰዉ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በየመ/ቤቶቹ ተጠያቂነትን ከመስፈን አንጸር የማስረጃዎቹ ሚስጥራዊት በመንግስት ታምኖበት የትኞቹ እንደሆኑ በግልፅ ተለይቶ በሚስጢር እንዲያዙና ቀሪዎቹን የሂሳብ ማስረጃዎችን በአግባቡ በመያዝ ለኦዲት ሊያቀርቡ ይገባል።

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ29 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 368,002,429.66 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 20 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,930.20
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		35,979,753.81
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		95,445,380.45
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		236,579,225.60
ድምር		368,002,429.66

ሆኖ ተገኝቷል ።

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣የቀረቡት ደረሰኞች የገዥውን ማንነት እንዲሁም ቀኑንና ነዳጁ የተሞላላቸውን እጥበትና ግሪስ የተደረገለትን መኪና ሰሌዳ ቁጥሩን የማይገልጽ፣ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጐላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንገሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና የልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ47 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 53,360,272.59 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-22 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,049,682.39
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		49,673,916.01
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		2,298,031.22
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		293,642.97
ድምር	ብር	53,360,272.59

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ የጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 20,309,358.20፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ብር 7,183,248.07 ፤ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 6, 864,329.08 ፤ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,971,271.40 ፣ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 3,392,102.00 የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ብር 3,286,245.49 እና የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ ብር 3,168,957.57 ሲሆኑ፤ ከምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ፣ ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች አበል ፣ደመወዝና ማበረታቻ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት/ ከ1 እስከ 6 ወር/ የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ11 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 28,175,126.27 እና በ16 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 4,897,884.43 በጠቅላላው ብር 33,073,010.70 በብልጫ ተከፍሎ

ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 23 ተመልክቷል/ በተጨማሪም በ5 መ/ቤቶች ብር 37,792,667.88 በብልጫ የተመዘገበ ወጪና በ2 መ/ቤቶች ብር 282,783.78 በድጋሚ የተመዘገበ ወጪ ተገኝቷል።

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድግሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰአት፤ለተለየያ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተተመነው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግና በብልጫ መመዝገብ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆንና ምዝገባውም አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ62 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 956,702,992.92 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 24 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	10,938,646.93
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		184,600,282.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		755,655,097.77
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		<u>5,508,966.22</u>
ጠ/ድምር	ብር	<u>956,702,992.92</u>

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 743,797,845.69 ፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 95,008,585.46 ፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 25,144,748.02 ፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,641,407.32 እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,791,692.29 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ በ4 መ/ቤቶች የብር 9,120,451.76 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ካልሆኑ ድርጅቶች የአገልግሎት ግዥ፤የተፈጸሙ መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ-24/1 ተመልክቷል፡፡/

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸሙ እና የተለያዩ ግዥዎችን ከአንድ አቅራቢ ብቻ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጠ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች በብር 6,802,769.45 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-25 እና አባሪ-25/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	1,269.00
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		3,222,404.66
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		2,609,367.38
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		969,728.41
ድምር	ብር	6,802,769.45

ከዚህም ውስጥ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 2,416,905.52 ፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,474,812.23 የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ብር 605,745.67 እና በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ ብር 499,871.83 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች 76,052,521.48 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው እንደሆነ ተውቋል። ከዚህም ውስጥ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 32,128,296.51፣ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 41,189,738.68፣ እና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ብር 2,734,486.29 ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጠው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዘው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 241,408,732.29 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 10 /ረ ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	12,126,710.24
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		130,334,104.66
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		98,947,917.39
ድምር	ብር	241,408,732.29

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ብር 129,633,744.23፣ የኢንዱስትሪ ሚኒሰቴር ብር 93,820,097.01 ፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,541,896.06 ፤ እና አማኑኤል ሆስፒታል ብር 2,876,348.12 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡

4.8 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/አ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ28 መ/ቤቶችና በሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 32,567,045.57 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 29 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	743,403.47
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		13,100,252.06
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		18,261,471.08
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		461,918.96
ድምር	ብር	32,567,045.57

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 11,978,865.61 ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 8,912,538.86 ፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ብር 4,520,703.09 እና የፌደራል ስፖርት ኮሚሽን ብር 3,762,182.75 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ14 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 12,263,629.77 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2006 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -28 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	10,459,017.77
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		1,745,791.37
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		58,820.63
ድምር	ብር	12,263,629.77

ሲሆን ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 107,912,890.55 ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-27 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 <u>በመስክ ላይ ለነበሩ የግንባታ ዕቃዎች (Material on Site) ክፍያ የተፈጸመ ስለመሆኑ፤</u>

በፌዴራል ግዥ አፈጻጸም መመሪያ በሳይት ላይ ያሉ ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም በ6 መ/ቤቶች በሳይት ለሚገኙ ዕቃዎች ብር 76,063,137.72 ለተለያዩ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገንዘብ አላግባብ እንዲተካ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከዚሁ ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች

በ2 መ/ቤቶች ብር 16,727,198.50 በብድር ከተሰጡ የግንባታ ዕቃዎች ከክፍያቸው ተቀናሽ ያልተደረገ/ ያልተሰበሰበ ብድር ሂሳብ እና በውል በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ግንባታውን በማያጠናቅቁት ተቋራጮች ላይ የጉዳት የካሳ ጥያቄ በውሉ መሰረት በመቅረብ ቅጣት መሰበሰሰብ ሲገባቸው ይህንን እንደማያደርጉ ተውቋል።

ለግንባታ የቀረቡ ግብዓቶች ስራ ላይ ሳይውሉ ክፍያ መፈጸሙና ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጸምላቸው ቀደም ሲል የተሰጠቸው ብድር ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸሙ ከውል በላይ ክፍያ እንዲፈጸም፣ የተሰጠ ብድርም እንዳይሰበሰብ ክፍተት ይፈጥራል።

በመሆኑም ያልተሰበሰበው የግንባታ ግብዓቶች ብድር እንዲሰበሰብ የወሰዱትን ግንባታ በወቅቱ በመያጠናቅቁ ተቀራጮች ተገቢው የጉዳት ካሳ በውሉ መሰረት እንዲጠየቅና የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገበቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 12,037,955.78 እና በ4 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 16,145,008.22 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-30 እና 30/1 ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ይገኝበታል፡፡

አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

5. የተከፋይ ሂሣብ

5.1. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ45 መ/ቤቶችና በሶስት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 973,746,519.63 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-32/ ሀ ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	471,753,684.35
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		107,526,920.03
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		339,929,947.33
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		54,535,967.92
ድምር	ብር	973,746,519.63

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 460,160,937.67 ፣ ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 330,805,868.99 ፤ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ብር 43,306,907.03 ፤የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 71,434,198.75 እና ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,535,123.38 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ አስገዳጅ ሕጎች መሰረት ገቢ ሰብስበው የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ በ15

መ/ቤቶች ብር 41,374,483.14 መኖሩ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-16 ተመልክቷል/ የተከፋይ ሂሳቡ መድኃኒት ሽያጭ ፣ ከቅጣት፣ ከበጀት ተመላሽ የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ሂሳብ ይጨምራል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር የሰራዊት የደመወዝ ተከፋይ ብር 247,264,224.87 በተመለከተ የመከላከያ ሚ/ር ከተሰጠው ተልኮና ግዳጅ መነሻነት ደመወዛቸውን በወቅቱ ቀርበው ያልወሰዱ የሰራዊት አባላት ከተሰጣቸው ግዳጅ ሲመለሱ ያለእንግልት ደመወዛቸውን እንዲወሰዱ በማሰብ የመከላከያ ከፍተኛ ኃላፊዎች ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በመነጋገር ደመወዛቸውን በግዳጅና በተለያየ ምክንያት ያለወሰዱ የሰራዊት አባላትን ደመወዝ ማሰቀመጫ መደቡ D የሆነ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንዲከፈት ጠይቀው በቀን 09/10/1995 ዓ.ም. በቁጥር አሂመ1/7/47 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተጻፈ ደብዳቤ ተፈቅዶ መከፈቱን ገልጸዋል፡፡ይሁን እንጂ ገንዘቡን አላግባብ ለሌላ አካል በማበደር እየተጠቀመበት በመሆኑ ተገቢው ቁጥጥር ካልተደረገ ለግል ጥቅም ሊውል የሚችልበት ሁኔታ የሰፋ ነው፡፡

በሂሳብ መደብ 5021 በተከፋይ ሂሳብ የሚታየው ብር 1,831,070.50 በአየር ሀይል ጠቅላይ መምሪያ ለረጅም ጊዜ በምዝገባ የታየ ሂሳብና ተከፋይ ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ ማን እንደሆነ በግልጽ የማያሳይና ገንዘቡም በጠቅላይ መምሪያው የባንክ ሂሳብ ውስጥ የማይገኝ ሲሆን ትክክለኛ የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር (Chart of Accounts) ባለመረዳት የተፈጠረ የምዝገባ ስህተት መሆኑን በመገንዘብ አስፈላጊውን ማጣራት እያደረግና ወደፊት በማጣራት በሂደቱ የምናገኛቸውን የምናሳውቃቸሁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ይህ ሂሣብ በመንግሥት የሂሣብ አሠራር መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ ተደርጐ ጥያቄው ሲቀርብ የገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርን በመጠየቅ መከፈል ሲገባው ሂሣቡ በወጪ ተመዝግቦ ለዓመታት ሳይከፈል መቀመጡ ገንዘቡም ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደተቀመጠ ለማወቅ የማያስችል በመሆኑና ለብክነት እንዲጋለጥ የሚያደርግ መሆኑን በመጥቀስ ሂሣቡ ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ፣ ጥያቄው ሲቀርብ ክፍያ እንዲፈጸም አሳስበናል።

የሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2. <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 164,658,370.51 መኖሩ፣
- በተከፋይ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 42,641,122.73 መገኘቱ፣
- አላግባብ በዕዳ ወይም ተከፋይ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ በ3 መ/ቤቶች ብር 19,683,605.46 መገኘቱ፣
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ2 መ/ቤቶች ብር 2,534,141.80 መታየቱ፣
- የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በ3 መ/ቤቶች ብር 19,069,335.68 መኖሩና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ከተቀጽላ ሌጃር አዘጋጃጀትና አያያዝ ችግሮች እንደሚታባቸው ተረጋግጧል። /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ለ እስከ ረ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ37 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ በመደበኛ በጀት ብር 232,148,072.37 እና ከፒታል በጀት ብር 3,163,827.82 በድምሩ ብር 235,311,900.19 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	28,749,427.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		131,483,352.93
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		69,620,145.66
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		5,458,974.33
ጠ/ድምር	ብር	235,311,900.19

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 31,741,412.73 ፣ ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 22,712,013.47 ፣ ዲላ ዩንቨርሲቲ ብር 16,422,282.30 ፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 14,825,649.05 እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ብር 14,250,809.51 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶች ብር 38,473,539.74 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሳይፈቀድ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ላይ ወጪ አድርገው የተጠቀሙ ሲሆን፣ ሌሎችሶስት መ/ቤቶች ብር 129,293,924.35 የበጀት ዝውውር

ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ከተመደበለት አርዕስት ውጭ የተጠቀሙ መ/ቤቶች መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 <u>ያልተሰራበት በጀት</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ99 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 1,027,319,514.59 እና ካፒታል ብር 1,549,338,191.03 በድምሩ ብር 2,576,657,705.62 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	453,820,282.97
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		173,840,330.75
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		738,777,713.43
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		1,210,219,378.47
ድምር	ብር	2,576,657,705.62

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ትምህርት ሚ/ር ብር 588,887,158.78 ፣ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 396,086,596.34 ፣ አርባ ምንጭ ዩ.204,362,089.53፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስፖርት ኮሚሽን ብር 195,186,880.58 ፣ ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር

94,374,733.95፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር 97,582,653.71 እና በደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ ብር 88,024,688.01 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተጨማሪም ሁለት መ/ቤቶች ከተፈቀደላቸው ከውስጥ ገቢ በጀት ሥራ ላይ ያልዋለ ብር 24,693,679.88 ተገኝቷል።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል ፣ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ</u>

7.1 <u>የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች</u>

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	22 መ/ቤቶች
›ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	18 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	11 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ	30 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	31 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	43 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	12 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	11 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው	6 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ	6 መ/ቤቶች

ዋስትና በሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ ስለመሆኑ	6 መ/ቤቶች
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	2 መ/ቤቶች
ከዋናው ግምጃ ቤት በጥቅል ወጪ የሚደረጉ ንብረቶች/መድሓኒቶች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር የማያደርጉ መ/ቤቶች	6 መ/ቤቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-34 / ሀ እስከ ቸ ተመልክቷል፡፡/

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አገጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከመችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይተል።

ሌሎች የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው 5 መ/ቤቶች ዝርዝራቸው በአባሪ-30/ሸ የተመለከተ ሲሆን፣ ችግሮቹ በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዘበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም

በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 ተሽከርካሪ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ20 መ/ቤቶች	192 ተሽከርካሪዎች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ23 መ/ቤቶች	247 ተሽከርካሪዎች
የተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ያልተቋቋመባቸው መ/ቤቶች	በ4 መ/ቤቶች	
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ1 መ/ቤቶች	4 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/ በመሆኑም ም/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው እንዲሁም የተሽከርካሪ ማህደር እንዲቋቋም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8. ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በ32 መ/ቤቶች እና 7 ቅ/ጽ/ቤቶች/ ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየመ/ቤቶቹና በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9. ልዩ ልዩ

9.1 የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት፣

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በዋናው ግቢ ከተማሪዎች ምግብ ቤት የሚሰበሰበው ተረፈ ምግብ አያያዝና አወጋገድ በአካባቢ ጥበቃ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምግብ ማዘጋጃ ወጥ ቤት እጥብጣቢ እና የተማሪዎች ሽንት ቤት የሚወጣው ፍሳሽ ማስወገጃ በአግባቡ ስለማይሰራ በአባቢው መጥፎ ሽታ እያመጣ መሆኑ፣
- በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ እንደ የሽንኩርትና የድንች ልጣጭ ያለና ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ትርፍራፊ ምግብ በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ውስጥ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እየፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም የተማሪዎች ካፍቴሪያ የምግብ ማብሰያ አዳራሽ በአግባቡ የማይጸዳ መሆኑና ይህም በተማሪዎችና በሰራተኞች ላይ የጤና ችግር ሊያስከትል እንደሚችል፣

9.2 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራቦርድ

- የተሸጡ የመንግስት ድርጅቶች የተጠቃለለ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ የማይዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በባለፉት በጀት ዓመታት በተከታታይ ኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በ2006 በጀት ዓመትም እርምጃ ያልተወሰደ

በመሆኑ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የሚነሱትን የሰው ሃይልና ሌሎች ችግሮች ለሚመለከተው አካል በመጠየቅና በማስፈቀድ ሥራው በማከናወን ዓመታዊ ሪፖርት ሊያዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የኦዲት ሪፖርት በድጋሚ አሳስበላል።

- በንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ስር በተለያዩ መጋዘኖች ከ18 ድርጅቶች ከተወረሱ ንብረቶች ውስጥ በናሙና ከታዩት መጋዘኖች ውስጥ 617 ዓይነት እቃዎች የሚገኙ መሆኑና በአብዛኛው ጣቃዎች፤ የተሰፉ ቱታዎች፤ ጥቅል ክሮች ፤ ሹራቦች፤ ጥቅል እና ብትን ጥጦች፤ የተለያየ ስፔር ፓርቶች እንዲሁም በጣም የተከማቹ ኬሚካሎች፤ መስሪያ ማሽኖች እና የመሳሰሉት የሚገኙ እና ሳይሸጡ ወይም ሳይወገዱ ለብዙ ዓመታት የቆዩ በመሆናቸው ጨርቆቹ በአይጥ ከመበላታቸው በተጨማሪ ኬሚካሎች በጸሀይ ደርቀው እና ተበላሽተው የሚገኙ መሆኑ፤ በሰነድ አስተዳደር እና ሰራተኛ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከሚፈርሱ ድርጅቶች የተረከባቸው የሰራተኞችን የግል ማህደሮች፤ የሂሳብ ሰነዶች፤ የመዝገብ ቤት ፋይሎች፤ ደንቦች እና መመሪያዎች፤ ማንዋሎች እና የመሳሰሉት በ6 መጋዘኖች በመረከብ ለይቶ በመያዝ እና በማደራጀት ለተገልጋዮች ግልጋሎት እየሰጠ የሚገኝ ቢሆንም በኦዲት በታዩት 4 መጋዘኖች በተለይም በስላሴ መጋዘን የሚገኙት ሰነዶች መደርደሪያ ቢኖርም በቂ ባለመሆኑ እና ፋይሎች በመበታተናቸው በጎርፍ ሳቢያ፤እንዲሁም በንጽህና ጉድለት ምክንያት ተመልካች በማጣታቸው ብዙዎችም መደርደሪያቸው ተዛሞ ሊወድቅ በመድረሱ ከጥቅም ውጭ

እየሆኑ መሆኑ እና በሌሎችም መጋዘኖች ተመሳሳይ ችግር ያላቸው ከመሆኑም በላይ በመጋዘን እጦት በየጆንያ ውስጥ ታስረው የሚገኙ በመሆኑ ለችግሮቹ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

10. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ሂሳብ ኦዲት አስተያየትና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች

10.1 መግቢያ

ዳይሬክቶሬቱ በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS) እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ሶስተኛ ዙር (PBS III) እና የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች (በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2006/7 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃለው በሚከተለው ሁኔታ ቀርበዋል፡፡

10.2 <u>በ2006/7 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች</u>

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም;-

ጥሬ ገንዘብ

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የሚደረግ ቢሆንም ቆጠራዉ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ አልፎ አልፎ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣

ተሰብሳቢ ሂሳብ

- የቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረዳቸው እና አለመፈጸማቸዉ፣፣
- አልፎ አልፎ ለተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሣቦች ዋና እና ተቀጽላ ሌጀሮች አለመቋቋም እና የተቀጽላ ሌጀሮች ምዝገባ ወቅታዊ አለመደረግ፤

ወጪዎች

- የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የዉሎ አበል ፎርምና ተመኑ (rate) በአግባቡ አለመሞላት፡

የሂሳብ ሪፖርት

- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች አልፎ አልፎ በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣

ንብረት

- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣
- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ፤
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣ እና
- በአብዘኛዉ መ/ቤቶች የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያዎች አለመመዝገብ፡
- የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች በወቅቱ አለመወገድ፣

የክትትል ኦዲት

- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖር፣
- የግንዛቤ ማነስ፣እና

- ተገቢው ትኩረት አለመስጠት

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

10.3 በ2006/7 የኦዲት ዘመን በተከናወኑ ተከታታይ ኦዲቶች ላይ የተሰጡ የውስጥ ቁጥጥር ኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinions)

በ2006/7 የኦዲት ዘመን (ከጥር/2006 እስከ ታህሣሥ/2007) 300 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች የተከናወኑ ሲሆን፣ በተከታታይ ኦዲቱ ወቅት በውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ላይ የተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች (Audit Opinions) እንደሚከተለው ተጠቃሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የተሰጠው የኦዲት አሰትተያየት	የኦዲቱ ብዛት (በቁጥር)	በመቶኛ (%)
1	ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified)	1	0.33
2	ነቀፌታ ያለበት (Except for)	299	99.67
3	ተቀባይነት የሚያሳጣ (Adverse)	-	-
4	አቋም የማይወስድ (Disclaimer)	-	-
	ድምር	300	100

ማስገንዘቢያ፡-

- ለእያንዳንዱ መ/ቤት የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ከዚህ ጽሑፍ ቀጥሎ በተቀጽላ (Annex I) ተያይዟል፡፡

10.4 የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመሠረታዊ አገልግሎቶች 'PBS III' ፕሮጀክት የ2006 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ (PFS) የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመከተልና በስምምነቱ በተቀመጠው (TOR) መሠረት ኦዲት ተደርጎል፡፡

የኦዲት ስራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ደረጃ በተዘጋጀው የተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የተከናወነ ዓመታዊ ኦዲት ሲሆን፣ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት "ነቀፌታ የሌለበት" (Unqualified) ነው፡፡

11. ክዋኔ እና የአካባቢ ኦዲት ግኝቶችና ማሻሻያ ሀሳቦች

11.1 የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋትና አቅም ለመገንባት የሚሰጠውን ድጋፍ እና ክትትል በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ መረጃ እና የፕሮጀክት ፕሮፋይል ስለማዘጋጀቱ

1. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የሚገልጽ ዝርዝር ወቅታዊ መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የኢንዱስትሪዎችን ፕሮፋይል ሊያዘጋጅ፣ የዋና ዋና ግብዓቶች የዋጋ ተመን መግለጫ (factor cost sheet) ሊያደራጅና ሊያሰራጭ እንዲሁም ለዘርፉ ስለሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ለህብረተሰቡ ሊያስተዋውቅና የሰበሰባቸውን መረጃዎች ለባለሀብቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

2. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ኢንስቲትዩቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተላቸው 52 ኢንዱስትሪዎች ለሁሉም የካምፓኒ ፕሮፋይል ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤ በኢንስቲትዩቱ የተያዘው የኢንዱስትሪዎችን ዝርዝር መረጃው ያልተሟላ መሆኑ ማለትም (የድርጅቱን አላማ፣ የካፒታል መጠን፣ ወደ ሥራ የገባበት ዘመን፣

የተጠቀማቸው ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አይነት፣ ለአገር የፈጠረው ፋይዳ ማለትም በስራ እድል፣ በአመት የማምረት አቅም፣ የተጠቀመው ቴክኖሎጂ፣ የሚጠቀመው ግብአትና መጠን ወዘተ) መሆኑ፤ የዋና ዋና ግብዓቶች የዋጋ ተመን መግለጫ የተዘጋጀ ቢሆንም ማስረጃውን ለሚጠይቁ ብቻ የሚሰጥ እንጂ መረጃውን የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ በመጠቀም ለምሳሌ በመረጃ ድረገፅ (web-site) ያልተቀመጠ መሆኑ እና ኢንስቲትዩቱ ስለሚሰጣቸው ድጋፎች ለህብረተሰቡ በሚገባ ያላስተዋወቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ስለማድረጉንና የተሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው፤</u>

3. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡ ባለሀብቶች የመሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች (ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

4. ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ የትብብር ደብዳቤ በመፃፍ የሚረዳቸው ቢሆንም ድጋፉን ስለማግኘታቸው ክትትል የማያደርግ መሆኑን፣ እንዲሁም የባንክ ብድር አቅርቦት፣ የስልክ፣ የመብራት መቆራረጥ ችግሮች እስካሁን ያልተፈቱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት መጠይቅ የቀረበላቸው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶች የገለጹ መሆኑ፣

5. እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማለትም በየፕሮጀክት ሂደት (project phase) የሚያስገቡዋቸውን የተለያየ መጠን ያላቸው ለግብዓትነት የሚውሉ ቁሳቁሶችና ማሽነሪዎች ወዘተ ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን የማይከታተል መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን ድጋፍና ክትትል በተመለከተ</u>

6. ኢንስትትዩቱ ወደ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚገቡ ባለሃብቶች የፕሮጀክት ፕሮፋይል፣ የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ እንዲሁም በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በመሳሪያዎች ተከላ፣ በርክክብ ፍተሻ እና በማማከር ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

7. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ከ2004-2007 ዓ.ም በስትራቴጂክ እቅዱ ላይ የአዋጭነት ጥናት በማጥናት ለባለሃብቶች እንደሚያሰራጭ ቢገልፅም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በ2004 በጀት ዓመት በኢንስቲትዩቱ ከተለዩት 103 አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎች የተሟላ የፕሮጀክት ፕሮፋይል በማጠናቀቅ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው 20 አማራጭ የኢንቨስትመንት እድሎች የቅድመ አዋጭነት ጥናት ለማከናወን የታቀደ ቢሆንም ሥራውን በታቀደው መሰረት ሙሉ በሙሉ ለማከናወን ያልተቻለ መሆኑ፣ 10 ለሚደርሱ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ለመስጠት አቅዶ ለ5 ብቻ (50 በመቶ) ያከናወነ መሆኑ፣

- ኢንስቲትዩቱ በ2006 በጀት ዓመት 7 ለሚደርሱ ፕሮጀክቶች የዲዛይንና ግንባታ፣ የኮሚሽኒንግ፣ የማሽነሪ ተከላና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት ቢያቅድም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት እስከ 3ኛ ሩብ ዓመት 30 ለሚሆኑ የምርት ዓይነቶች የቅድመ አዋጭነት ጥናት (ፕሮጀክት ፕሮፋይል) ለመስራት አቅዶ 14 (የዕቅዱ 46 በመቶ) የቅድመ አዋጭነት ጥናቶች ብቻ ያዘጋጀ መሆኑ መታወቁ፣

<u>የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሃ ግብሮችን በተመለከተ፣</u>

8. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የኢንዱስትሪዎችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሃ ግብሮችን አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሊያስጸድቅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ ላይ የተሰማሩና ሊሰማሩ የሚፈልጉ ባለሃብቶች በሥራቸው ላይ በአንድም ሆነ በሌላ መልክ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን፣ ደንቦችን እና የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎችን በማጥናትና በመለየት ለሚመለከተው አካል የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ችግሮቹ የሚቀረፉበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡

9. ኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የግብይት ስትራቴጂ ለመንደፍ እና ተጓዳኝ ድጋፍ ለማድረግ ከ2004-2007 በስትራቴጅክ እቅድ ቢይዝም በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ያልገለፀ እና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

10. በኢንስቲትዩቱ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚያግዙ አዳዲስ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲወጡና የአሰራር ሥርዓቶች እንዲዘረጉ የቀረበ ጥናት ባይኖርም ለዘርፉ ችግር የፈጠሩ ነባር ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተለይተው እንዲሻሻሉ በግንቦት ወር 2006 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በጋራ ተጠንቶ መቅረቡ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

<u>ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ የሚያከናውናቸው ጥናቶችን በተመለከተ</u>

11. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪን መሰረት ለማስፋፋት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ማለትም ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀሙና የግብርናውን ዘርፍ የሚደግፉ ማሽነሪዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን፣ በውጭ ምንዛሪ የሚገዙትን በመተካት የገበያ ክፍተትን የሚሞሉ፣ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶችን በመለየት፣ በስትራቴጂክ እና አመታዊ እቅድ በመከፋፈል ጥናትና ምርምር ሊያከናውን ይገባል፡፡ የተጠኑትን ጥናቶችና ምርምሮች ውጤት ለባለሃብቱ በማስተዋወቅ ባለሀብቱ ኢንቨስት እንዲያደርግና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ በማግባባት የተጠናከረ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

12. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ኢንስቲትዩቱ የብረት ማዕድንን በአገራችን ለማውጣትና ለመጠቀም የሚያስችል ጥናት እያስጠና ሲሆን በኢንዱስትሪው ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮችና ክፍተቶችን ሊቀርፉና ሊሞሉ የሚችሉ ጥናቶችን ለማጥናትና ለማስጠናት በስትራቴጂክ እና በአመታዊ እቅዱ ለይቶ ያላሳየ መሆኑ፣ እንዲሁም የተጠኑ ጥናቶችን በዘርፉ

ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን በመለየት የማሳወቅ ስራዎችን በሚጠበቅበት መጠን ያላከናወነ መሆኑ፣

- የገበያ ክፍተትን በሚሞሉ እና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማፍለቅ በመንግስትና በልማታዊ ባለሀብቱ ቅንጅት ኢንቨስት እንዲደረግ ለመስራት በስትራቴጅክ እቅድ ቢይዝም የተሰራውን ስራ ያልተገለፀ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

<u>የገቢ ምርቶችን የሚተኩ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅም መገንባትን በተመለከተ፣</u>

13. ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት ድጋፍ (የቴክኒክ፣ የማቴሪያል፣ የገበያ ትስስር፣ ወዘተ) ሊያደርግ ይገባል፡፡

14. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ፡-

- የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመታት ለቆዳ፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለኮንስትራክሽን እና በ2005 በጀት ዓመት በቆዳ፣ ለስኳር፣ ለሲሚንቶ፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለኮንስትራክሽንና ለተሽከርካሪ ኢንዱስትሪዎች የመለዋወጫ አካላትን በራሱ ወርክሾፕ ለማምረትና በዘርፉ ለተሰማሩት ለማቅረብ በዕቅድ የያዘ ቢሆንም አለማከናወኑ፣

- በ2006 በጀት ዓመት በመንግስት ልዩ ትኩረት ለተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች (ለጨርቃ ጨርቅና

አልባሳት ኢንዱስትሪ፣ ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ ለብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች) ፈጣን እንቅስቃሴ ያላቸው 955 ዓይነት የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ኮምፖኔንቶች በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ የኢንጅነሪንግ ተቋማት እንዲመረቱ ለማድረግ እስከ 3ኛ ሩብ ዓመት እቅድ ቢይዝም 243 ዓይነት (የዕቅዱን 25 በመቶ) ብቻ መመረታቸውን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ ከመንግስት እና ከግል ተቋማት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ</u>

15. ኢንስቲትዩቱ ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ጋር አጋዥ ሥራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ፤ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም-ዓቀፍ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ እና የተጠናከረ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡

16. በኦዲቱ ወቅት በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይትና ከተከለሱ መረጃዎች

- በአገሪቱ ትልቁ የኢንዱስትሪ እድገት ሞተር ከሆነውና በዘርፉ ትልቅ ኃላፊነትን ከተረከበው ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የጠበቀ የስራ ግኑኝነት ወይም ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑን፣ በብረታ ብረት ዘርፍ አጋዥ ስራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ለመዘርጋት በአገር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር ኮሚቴ አዋቅሮ ችግሮችን ለመቅረፍ በ 2006

ዓ.ም እቅድ ቢይዝም ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊ አለማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በኢንስቲትዩቱ ለብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጡ የቴክኒክ ድጋፎችን በተመለከተ</u>

17. ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ የምርት ጥራትና ምርታማነትን ለማሳደግ የጥራት ደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ፍተሻና ማረጋገጫ ድጋፎችን እንዲሁም የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ በመሰረታዊ ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ዘርፉን ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችን ሊያዘጋጅና ሊሰጥ ይገባል፡፡

18. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ፡-

- በ2004 በጀት ዓመት ለ50 ምርቶች የጀረጃ ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ቢያቅድም ለአንድ ምርት ብቻ (አልሙኒየም ዚንክ ቅብ የቤት ክዳን ቆርቆሮ) ደረጃ ተዘጋጅቶና ፀድቆ ወደ ትግበራ የገባ መሆኑ እንዲሁም ለ10 ምርቶች የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ፍተሻ አገልግሎት ለመስጠት በዕቅድ ቢያዝም ስራው ያልተከናወነ መሆኑ፣

- በ2005 በጀት ዓመት የደረጃ ዝግጅት፣ የጥራት ፍተሻና የላቦራቶሪ አገልግሎት ለመስጠት የጥራት ደረጃ ሊወጣላቸው እና ሊከለስላቸው የሚገባቸውን የምርት ዓይነቶች በመለየት፣ ለደረጃዎች ኤጀንሲ የቀረበውን የጥራት ደረጃ መግለጫ ፕሮፖዛል በመከታተል ለማስፀደቅ 25 ለሚሆኑ ኢንዱስትሪዎች በእቅድ ቢይዝም 13 ፕሮፖዛል ብቻ ያከናወነ መሆኑ፣

- በ2006 በጀት ዓመት 38 ደረጃ የሚወጣላቸው /የሚሻሻሉ/ ምርቶችን ለመለየትና የምርት ጥራት ደረጃ ፕሮፓዛል ለማዘጋጀት እቅድ ቢይዝም እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት 28 ፕሮፖዛል ያዘጋጀ መሆኑ፣ እና የኢትዮጵያ ስቲል ፕሮፋይሊንግ እና ቢውልዲንግ የተባለ ድርጅት ለኤጋ ምርቶች የጥራት ፍተሻ እንዲደረግለት ጠይቆ ምላሽ ያላገኘ መሆኑን፣
- ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች ብቁ ሙያተኞች በሙያ ዓይነት፣ በደረጃና በመጠን በመለየት በተለዩት የሙያ ክፍተቶች ላይ በ2006 በጀት ዓመት እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት ለ390 ባለሙያዎች (35 በመቶ ለሴቶች) ስልጠና ለመስጠት ቢያቅድም ለ118 (30.26 በመቶ) ባለሙያዎች ብቻ ስልጠና የሰጠ ሲሆን ከነዚህ ስልጠናውን ከወሰዱት መካከል የሴቶች ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ አለመገለፁን፣
- በምርት ጥራት፣ በማሽኒንግ፣ በኳሊቲ ማኔጅመንት፣ በሚሊንግ፣ በኢ-አበላሽ {Non Distractive testing (NDT)} እና በግሪንዲንግ በ2004 ዓ.ም 20,579 ሰዓት ስልጠና ለመስጠት አቅዶ 64 ሰዓት ብቻ ሥልጠና መስጠቱን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ብረታ ብረት ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥ እና በውጭ አገር የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፣</u>

19. የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ጥናትና ትስስር ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም በኢንዱስትሪዎቹ የሚመረቱ

ምርቶች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥና ለውጭ ገበያ የተመረቱ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ለመሸጥ የሚያስችል የገበያ መረጃ፣ የገበያ ፍለጋ እና መደበኛ የገበያ ትስስር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

20. በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ፡-

- በ2004 በጀት ዓመት ለ20 ኢንዱስትሪዎች ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ትስስር ድጋፍ ለመስጠት ፋብሪካዎቹ የሚጠቀሟቸው ግብዓቶች፣ የሚያመርቷቸው ምርት ዓይነቶች እና የማምረት አቅማቸው መረጃ ከ25 ፋብሪካዎች የተሰበሰበ ቢሆንም ትስስር የመፍጠሩ ስራ ስለመከናወኑ የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ፣
- በ2006 በጀት ዓመት 20 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ፕሮፋይል በማዘጋጀት ለማስተሳሰር፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የግብዓትና የገበያ ትስስር ለመፍጠር፣ እንዲሁም በግብዓትና ምርት ሊተሳሰሩ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎችን ለማዋዋል በእቅድ ቢይዝም እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ የተከናወነ ስራ አለመኖሩን፣ ኤክስፖርት የሚያደርጉ የንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎች በዘጠኝ ወር ውስጥ 5873.6 ሺህ የአሜሪካን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 3884.72 ሺህ ዶላር የተገኘ ሲሆን አፈፃፀሙ የእቅዱን 66.12 በመቶ ብቻ መሆኑ፣
- ኢንስቲትዩቱ ምርቶችን የማስተዋወቅና የገበያ ጥናት ትስስር ለመፍጠር በአርማታ ብረት ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች አቅም መጎልበትን አስመልክቶ ለከተማና ኮንስትራክሽን ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤ የፃፈ መሆኑ፣

የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ከህንፃ አቅራቢ ድርጅት ጋር በመሆን በጋራ ግዥ የሚፈፅሙበትን በማመቻቸት 10 ሺ ቶን ብረት መግዛት መቻላቸውን እንዲሁም የጋራ ስምምነቶችን በማድረግ አለም አቀፍ ጨረታ ላይ መሳተፍ መጀመራቸውን እንዲሁም የተለያዩ ኤግዚብሽኖች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ መረጃዎችን መሳተፍ ይችላሉ ብለው ላመኑባቸው ድርጅቶች የሚያሳወቁ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም በናሙና የታዩ ድርጅቶች በገበያ እጦት ምክንያት ምርቶቻቸው በመጋዘኖቻቸው ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

21. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ኢንዱስትሪዎች (አስመን ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ ስቲሊ አር ኤም አይ ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ አለም ስቲል፣ አሚዩ ኢንጂነሪንግ፣ ኬጂ ኢንጂነሪንግ፣ የኢትዮጵያ ባሌስትራ ፋብሪካ አ.ማህበር፣ ብስራት ኃ.የተ.የግ.ማህበር፣ የኢትዮጵያ ስቲል ፕሮፋይሊንግና ቢልዲንግ) ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- በዘርፉ የተጠናከረ የገበያ ጥናት ባለመኖሩ በአሁኑ ወቅት የአርማታ ብረት ምርት ገበያውን የሸፈነ ቢሆንም በዚህ ዘርፍ መንግስት ተጨማሪ ኢንቨስትመንት እየሳበ እና አዳዲስ ኢንቨስተሮች እየገቡ በመሆኑ የገበያ ፍላጎትና አቅርቦት ያለመመጣጠን ሊመጣ እንደሚችል ስጋት እንዳላቸው፣ እንዲሁም መንግስት በተማከለ ደረጃ የብረት ግዥ ከፈፀመልን በኋላ የተለያዩ መጠን ያላቸውን ብረቶች አምርተን ለገበያ አቅርበን እያለ መንግስት ከኛ ከመግዛት ይልቅ ከውጭ አገር ምርት ስለሚገዛ የገበያ እጥረት መኖሩ፣ የምርት ትስስር አለመፈጠሩ እና የመሳሰሉትን ችግሮች ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት

ኢንስቲትዩት እና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ቢያሳውቁም የተሻሻለ ነገር እንደሌለ፣ እና

- 7ቱም ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃን ከውጭ አምጥቶ፣ በየብስ አጓጉዞ ፕሮሰስ አድርጎ እንደገና ለውጭ ገበያ ማቅረቡ ከፍተኛ ወጭ ስላለውና ከዋጋ አንፃር አዋጭ ባለመሆኑ (Lack of Competitiviness) ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ ማቅረብ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

22. እንዲሁም የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ኃላፊዎች ስለሁኔታው በሰጡት መልስ ብዛት ያላቸው መለዋወጫዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ምርቶች በገበያ ችግር ምክንያት በስቶክ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

23. በመሆኑም

- ✓ ኢንስቲትዩቱ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ዝርዝር መረጃ ማለትም-- (የኢንዱስትሪውን ስም፣ የባለቤትነት አይነት፣ የስራ አድራሻ፣ የድርጅቱን አላማ፣ የካፒታል መጠን፣ ወደ ሥራ የገባበት ዘመን፣ የተሰማራበት ዘርፍ፣ የተጠቀማቸው ኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች አይነት፣ ለአገር የፈጠረው ፋይዳ ማለትም በስራ እድል፣ በአመት የማምረት አቅም፣ የሚመረተው ምርት አይነት፣ የተጠቀመው ቴክኖሎጂ፣ የሚጠቀመው ግብአትና መጠን ወዘተ) ሊይዝ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ የዋና ዋና ግብዓቶችን የዋጋ ተመን መግለጫ (Factor cost) እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር መረጃውን ለሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ማግኘት የሚችልበትን ዘዴ በመጠቀም ለምሳሌ በመረጃ ድረገፅ (web-site) ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡

- ✓ ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የመሰረተ ልማት ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገርና ክትትል በማድረግ ድጋፉን ማግኘታቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና በድጋፉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማና በወቅቱ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማለትም በየፕሮጀክት ሂደት (project phase) የሚያስገቡዋቸውን የተለያየ መጠን ያላቸው በግብአትነት የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ ማሽነሪዎች ወዘተ ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ እና ሌሎች ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተላቸው 52 ኢንዱስትሪዎች እያንዳንዳቸው ፕሮጀክታቸውን የሚገልፅ የፕሮጀክት ፕሮፋይል በኢንስቲትዩቱ ሊኖራቸው (ሊዘጋጅላቸው) ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ በባለሃብቱ የተዘጋጀውን የአዋጭነት ጥናት ለማበልፀግና አስተያየት ለመስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶችን አውጥቶ በመጠቀም የተሰራውን ስራ በግልፅ ሊያሳይ ይገባል፡፡
- ✓ ኢንስቲትዩቱ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የፖሊሲና የህግ ድጋፍ፣ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸትና የግብይት ስትራቴጂ በመንደፍ ተጓዳኝ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ የሚያስፈልጉትን የጥሬ ዕቃዎችና የተለያዩ ግብዓቶች ለሚያስመጡ አምራቾች የውጭ ምንዛሬ ቅድሚያ እንዲያገኙ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ የብድር አሰጣጥ ስርዓቱ ለውጭ ባለሃብት እና ለአገር ውስጥ ባለሃብት ተመሳሳይ የሆነ መብት (ማለትም የውጭ ባለሃብት ያገለገለ ማሽነሪ ይዞ አገር ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ሲመጣ አሮጌው ማሽነሪ ዋጋ እንደብድር ማስያዣ ከመቆጠሩም በላይ ተጨማሪ ብድር የሚመቻችለት ሲሆን ለአገር ውስጥ ባለሃብትም ተመሳሳይ ማበረታቻ አያገኝም) እንዲያገኙ ተገቢውን ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡
  - ➢ መንግስት በሚያከናውናቸው የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ዘርፈ ብዙ ግብአቶችን ማለትም (የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችን፣ የጭነትና ገልባጭ ተሽከርካሪዎችን፣ የመስክ ተሽከርካሪዎችን፣ አርማታ ብረቶችን፣ ቆርቆሮዎችን፣ ቱቦላሬዎችን፣ ትራንስፎርመር፣ የኤሌክትሪክ ሞተሮችና ገመዶች ወዘተ) የሚገዛ ሲሆን የአገር ውስጥ አምራቾችም ምርት እንዲጠቀሙ ቅድሚያ የሚሰጥ ወይም ከጨረታው የተወሰነ ድርሻ መጠን ለአገር ውስጥ አምራቾች የሚሰጥ የአሰራር ሥርዓት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋጋር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
  - ➢ ያለቀለት ምርት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ እና ተመሳሳይ ምርት በአገር ውስጥ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ሲመረት ወይም ሲገጣጠም ለአገር ከሚሰጠው ፋይዳ (ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ወዘተ) አንፃር ከውጭ ከሚገባው ምርት ጋር በዋጋ ተወዳዳሪ

እንዲሆን የሚያደረግና የአገር ውስጥ ምርት ቅድሚያ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ሊሰራ ይገባል፡፡

- ለግብርና ግብዓቶች የተሰጠው የቀረጥ ማበረታቻ /መብት/ በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ በተሰማሩ አምራች ድርጅቶች ለሚመረቱ ትራክተሮች፣ ተቀፅላዎችና የውሃ ፓምፖች የሚካተቱበትን ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ በማጥናት ለሚመለከተው የመንግስት አካል የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- በዋራንቲ ጊዜ ለተበላሹ ወይም ቀድመው ተሟልተው ባልተላኩ ግብአቶች በምትክነት ለሚገቡ እቃዎች ጉምሩክ እንደግብአት በሁለተኛ መደብ ታሪፍ ሳይሆን እንደ መለዋወጫ እቃ ከፍተኛ ቀረጥ የሚያስከፍል ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ኤል ሲ ተከፍቶ ያልገባ ነው በማለት በቅጣት የዕቃውን ዋጋ ሶስት እጥፍ እንዲከፍል የሚያስገድድበት መመሪያ እንዲሻሻል ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- ከውጭ ተመርትው የሚገቡ የንዑስ ዘርፉ የምርት ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር በማድረግ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ በማድረግ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ቁጥጥር የሚደረግበትን ሁኔታ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊያመቻች ይገባል፡፡

- የኤሌክትሪክ ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመቅረብና በየጊዜው የሚታየው የኃይል መቆራረጥ የመለዋወጫ መቃጠልና የምርት መስተጓጎል ችግር እንዳይከሰት ጄኔሬተር የሚጠቀሙ መሆኑ ይህም ለተጨማሪ ወጭ የሚዳርጋቸው

በመሆኑ አምራቾች ከኮርፖሬሽኑ ጋር በገቡት ውለታ እና በከፈሉት መጠን የኃይል አቅርቦት የማያገኙ በመሆኑ ችግሮቹ እንዲቀረፉ ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የኤሌክትሪክ ብክነትን ለመቀነስ ተብሎ የኃይል መቆጣጠሪያ መሳሪያ (Power factor corrector) ለመግጠም የኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽኑ ከሁለት ዓመት በፊት ከፋብሪካዎች ክፍያ የሰበሰበ በመሆኑ መሳሪያው በአፋጣኝ የሚገጠምበትን ሁኔታ ኢኒስቲትዩቱ ክትትል ሊያደርግና የአምራቾቹ ችግር መቀረፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮችና ክፍተቶችን ሊቀርፉና ሊሞሉ የሚችሉ ጥናቶችን ለማጥናትና ለማስጠናት በስትራቴጂክ እቅዱ እና በአመታዊ እቅዱ ለይቶ ሊሰራ ይገባል፡፡ እንዲሁም የተጠኑ ጥናቶችን በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሃብቶችን በመለየትና የማሳወቅ ስራዎችን በአግባቡ ሊያከናውን ይገባል፡፡

- የገበያ ክፍተትን በሚሞሉ እና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማፍለቅ በመንግስትና በልማታዊ ባለሀብቱ ቅንጅት ኢንቨስት እንዲደረግ ለመስራት በስትራቴጅክ እቅድ በመያዝ ሊያከናውን ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ አቅም ግምት ውስጥ ያስገቡና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ፣ የገቢ ምርቶችን የሚተኩ፣ መሳሪያዎችና መለዋወጫዎችን በሀገር

ውስጥ የማምረት አቅምን ለመገንባት በዕቅድ ይዞ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ በመንግስት ልዩ ትኩረት ለተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች (ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ፣ ለቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣ ለብረታ ብረት እና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች) የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ኮምፖኔንቶች በዘርፉ ውስጥ በሚገኙ የኢንጅነሪንግ ተቋማት እንዲመረቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በአገራችን ትልቁ የኢንዱስትሪ እድገት ሞተር ከሆነውና ትልቅ ኃላፊነትን ከተረከበው ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር የጠበቀ የስራ ግኑኝነት በመፍጠር አንዱ ለሌላኛው አቅም ሊሆን የሚችልበትን አሰራር ሊፈጥር ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ተመሳሳይ ተግባር ከሚያከናውኑ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተመሳሳይ አላማ ካላቸው የመንግስትና የግል ተቋማት ጋር የጠበቀ ግንኙነት (በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥ፣ በገበያ ትስስር ወዘተ) ሊመሰርት ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ በብረታ ብረት ዘርፍ አጋዥ ስራዎችን ከሚሰሩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር እንዲሁም በአገር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትን በመዘርጋት የዘርፉን ችግሮች በተሻለ ለመቅረፍ እንዲያስችል የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡
- የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሀብቶች እና

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ምርት የማስተዋወቅና የገበያ ጥናትና ትስስር ድጋፍ ሊሰጥ እንዲሁም በኢንዱስትሪዎቹ የሚመረቱ ምርቶች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥና ለውጭ ገበያ የተመረቱ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ለመሸጥ የሚያስችል የገበያ መረጃ፣ የገበያ ፍለጋ እና መደበኛ የገበያ ትስስር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በማለት በሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

11.2 ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ብቃት ያለው ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

<u>የኦዲት ግኝቶች</u>

<u>ኃላፊነት የተሰጣቸው መ/ቤቶች ለህገወጥ የገንዘብ ዝወወውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን መለየታቸውን በተመለከተ</u>

24. ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉም መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ኃላፊነት እና ከገቢና ወጪ (import & export) ንግድ አንፃር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ሊለዩ ይገባል፡፡ የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከልም እነዚህ አካላት ግዴታቸውን አውቀው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

25. የኦዲት ቡድኑ በኦዲት ወቅት የህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመከላከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የፌደራል ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር

ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ለይተው ያላስቀመጡ መሆኑን ታውቋል፡፡

<u>ህገ-ወጥ የውጭ ምንዛሪ ግዥ እና ሽያጭ እንዳይፈጸም የሚደርገውን የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት በተመለከተ</u>

26. በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንጽ 10 ተ.ቁ 1 መሰረት የህገ-ወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ግዥ እና ሽያጭ እንዳይፈጸም ብሔራዊ ባንክ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የሚዘረጋው ሥርዓትም ግብይቱን ፈጽመው በተገኙ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ጥምረቶች ወዘተ..... ላይም ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ እና ለማዕከሉም ቢያንስ በየወሩ ሪፖርት ማድረግን ሊያካትት ይገባል፡፡

27. ማንኛውም ሰው ከባንኮች ወይም ፈቃድ ከተሰጣቸው መንዛሪዎች ጋር ካልሆነ ወይም ከብሄራዊ ባንክ የተለየ ፍቃድ ካላገኘ በስተቀር በውጭ ምንዛሪ ግብይት ለመሰማራት እንደማይፈቀድ በብሔራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንጽ 10 ተ.ቁ 1 ላይ የተደነገገ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች (በአዲስ አበባ ስታዲዮም አካባቢ፣ በብሔራዊ ባንክ ዋና መ/ቤት አካባቢ፣ በጋንዲ ሆስፒታል አካባቢ ወዘተ..) ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘቦች ምንዛሪ ንግድ በግልፅ እንደሚካሄድ በኦዲቱ ወቅት ከብሔራዊ ባንክ ከተገኘው መረጃ እና በሥፍራው በአካል በመገኘት በማየት /Physical Observation/ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት/ድርጅቶች ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያስችል የውስጥ ፖሊሲና ቁጥጥር ሥርዓት ያላቸው መሆኑን በተመለከተ

28. የፋይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተቋማት /ድርጅቶች/ የደንበኛቸውን ማንነት /customers identification and due diligence/ ጠንቅቀው ለማወቅ የሚረዳቸው አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ የሚዘረጉትም ሥርዓት ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያችል የውስጥ ፖሊሲና ቁጥጥር ሥርዓት ሊያካትት ይገባል፡፡ ተቋማቱም ይህንን ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደረጉ ለማስቻል ማዕከሉ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

29. ባንኮች የደንበኞቻቸውን ማንነት ለመለየት ከሚረዳቸው አንዱ እና ዋነኛው የደንበኞቻቸውን ማንነት ማወቅ /customer due diligence/ ቢሆንም ኦዲት ቡዲኑ በኦዲቱ ወቅት ካያቸው ሁለት የመንግስት ባንኮች እና አራት የግል ባንኮች በሀገር ዓቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ ባለመኖሩ አንዳንድ ደንበኞች የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ሲመጡ ከአንድ መታወቂያ በላይ የሚጠቀሙ ስለሆነ ደንበኞችን ማንነት ሙሉ ለሙሉ እንዳያውቁ እንቅፋት እንደሆነባቸውና ሥርዓቱን ለመዘርጋት ከመቸገራቸውም በተጨማሪ በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ላይ ለመሰማራት እና ሆን ብለው ለማሳሳት ወይም ለማጭበርበር ለሚፈልጉ ግለሰቦች መልካም አጋጣሚ ሊፈጥር እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

<u>የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን በተመለከተ</u>

30. የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብን (over or under invoicing of imported or exported goods) ለመከላከል ብሔራዊ ባንክ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

31. በኦዲት ወቅት በተሻሻለው የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 16 ተ.ቁ 3. ላይ የገቢ ወይም የወጪ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ ማቅረብ (over or under invoicing of imported or exported goods) በሚሳተፉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ ከሌሎች ቅጣቶች በተጨማሪ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ንብረት ሶስት እጥፍ እንዲከፍሉ የተቀመጠ ቢሆንም በብሄራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ እና የገቢ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ በሚያቀርቡት ላይ በአዋጁ መሰረት እርምጃ እየተወሰደ እንዳልሆነ እንዲሁም ለፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከል ሪፖርት እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

በህገ ወጥ ንግድ እና የሰዎች ዝውውር ሥራ አማካኝነት የህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሚጠረጠሩትን የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ለማዕከሉ ሪፖርት ማድረጋቸውን በተመለከተ

32. የንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር እና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ እና ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ሥራ እንዲሁም በውጭ አገር ሥራ በማስቀጠር አማካኝነት የሚገኝ የውጭ ምንዛሪን ሆነ ብር በሕገወጥ መልክ ያዘዋውራሉ ብለው የሚጠረጥሩትን ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት ለማዕከሉ በየወሩ ሪፖርት የሚያቀርቡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረጉ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት፡-

- በናሙና ከታዩት የንግድ ሚኒስቴር፣ የማዕድን ሚኒስቴር እና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር መከላከልን በተመለከተ ከፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ ንግድ ሚኒስቴር በህገ ወጥ ንግድ ስራ፣ ማዕድን ሚኒስቴር ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ስራ እና ሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች ወይም በኤጀንሲዎች በኩል የሚደረግ ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ዝውውር ሲያጋጥማቸው ለማዕከሉ ሪፖርት እንደማይደረግ፣

- ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ በተከለለ የንግድ ዘርፍ ውስጥ ተሰማርተው እየሰሩ የሚገኙ 84 የውጭ ባለሀብቶች እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፈቃድ ያልታቀፉ ወይም እንደዜጋ ተቆጥረው የዜግነት ፈቃድ አግኝተው ሥራ እንዲሰሩ ሳይፈቀድላቸው እንደሀገር ውስጥ ባለሀብት ተቆጥረው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ በኢትዮጵያ የቆዩና

በተለያየ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ 162 ድርጅቶች በድምሩ 246 የውጭ ሀገር ድርጅቶችና ግለሰቦች መኖራቸው በሀገር ውስጥ ያፈሩትን ገንዘብ በህገወጥ መንገድ ከሀገር ሊያሸሹ እንደሚችሉ ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ እና ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ መቻሉን ነገር ግን ጉዳዩ ለማዕከሉ ሪፖርት እንዳልተደረጉ፣

- በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱት የማዕድን ምርቶች በሚመረቱበት ወቅት ምን ያህል እንደተመረተ እና ምን ያህሉ ለገበያ እንደቀረበ የሚያሳይ ሪፖርት ለማዕድን ሚኒስቴር እንዲቀርብ የማይደረግ እና በማዕድን ሚኒስቴርም የተዘረጋ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩ፣ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የከበሩ ማዕድናት የጥራት ደረጃ መለኪያ ባለመኖሩ ደረጃ የሚወጣለት ናሙናውን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ስለሆነ፣ የናሙና ማዕድኑን ውጭ ሀገር ይዞ የሚሄደው ማዕድኑን ያወጣው ድርጅት ስለሆነ ደረጃውን አሳንሶ ሊያስራ እንደሚችል ስጋት መኖሩን፣
- በቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የከበሩ ማዕድናት ቁጥጥር ስራ ላይ የተሰማሩት ባለሙያዎች ስለማዕድናት በቂ ዕውቀት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ በቀላሉ መለየት የሚችል መሳሪያም የሌለ በመሆኑ እና በኮንትሮባንድ መልክ ወደ ውጭ ሀገር ሲወጡ ሀገሪቱ ከማዕድን ምርት ሽያጭ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ የሚደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዲስፋፋ የሚያደርግ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች ተሟልተው ዕቃዎች እንዲወጡና እንዲገቡ መደረጉን በተመለከተ፣

34. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ብሔራዊ ባንክ የደነገጋቸው ሁኔታዎችና ግዴታዎች መሟላታቸውን እያረጋገጠ ማናቸውም ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ወይም የውጭ ምንዛሬ ከኢትዮጵያ እንዲወጡም ሆነ እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ይዞ ሊወጣ የሚችለው የኢትዮጵያ የገንዘብ ኖት መጠን ብር 200 ብቻ እንደሆነ በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2008 አንቀጽ 16 ተ.ቁ 4. ቢሆንም ወደ ጅቡቲ ለሚሄዱ የከባድ መኪና ሹፌሮች ከብር 15,000 እስከ 30,000 ድረስ ይዘው እንደሚወጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የግል አሰሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ያገኙትን ገቢና በውጭ አገር ተቀጥረው የሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚያስችላቸው አሰራር መዘርጋቱን በተመለከተ፣

36. ወደ ውጭ አገር ሠራተኞችን የሚልኩ አገናኝ ኤጀንሲዎች በሚልኩበት አገር ያለው አገናኝ ኤጀንሲ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈላቸው ገንዘብ ግልጽነት ባለው መልክ ወደ አገር ውስጥ ባለ ባንክ መግባቱ የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በውጭ አገር የሚኖሩ እና በሀገር ውስጥ ያሉ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎች የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ኤምባሲም ሆነ በሌላ መንገድ ገንዘባቸውን የሚልኩበት ህጋዊ አሰራር ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡

37. በኦዲቱ ወቅት ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወደ ተለያዩ አረብ ሀገራት የሄዱ ዜጎች የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ

የሚያስችላቸው ተደራሽ የሆነ ህጋዊ የመላኪያ መንገድ እንዲኖራቸው የሚያስችል በአቅራቢያቸው በሚገኘው የኢትዮጵያ በኤምባሲም ሆነ ቆንጽላ ጽ/ቤት በኩል እንዲሁም በብሔራዊ ባንክ በኩል የተዘረጋ ስርዓት ባለመኖሩ ዜጎች ለዘመዶቻቸው በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እና በኤጀንሲዎች በኩል የሚልኩ መሆኑንና ይህም ለጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት መሆኑን ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>በብሔራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መካከል ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ለመከላከል የተዘረጋ ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ፣</u>

38. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና ከሀገር የሚወጡ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ ማንኛውም ግብይቶችን በሚመለከት ብሔራዊ ባንክ እና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በጋራ ለመስራት የሚያስችል የተቀናጀ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

39. በኦዲት ወቀት ብሔራዊ ባንክ ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች ፈቃድ ሲሰጥ (import and export permission) ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለመታገዙ በመ/ቤቶቹ መካከል የሚደረጉትን የመረጃ ልውውጦች ወይም መፃፃፎችን ይዘው የሚሄዱት እራሳቸው ባለጉዳዩች /አስመጪ እና ላኪ ነጋዴዎች/ እንደሆኑ፣ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ከሀገር መውጫ ድንበር አካባቢ በጋላፊ እና በቦሌ አለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የመንገደኞች ጓዝ ውስጥ ህገወጥ የገንዘብ እንቅስቃሴን ለመፈተሽ፣ ለመያዝ እና የተገኘውን የህገወጥ ገንዘብ መጠን ሪፖርት ለማድረግ የተዘረጋ ሥርዓት ባለመኖሩ በተመደቡት ሠራተኞች ታማኝነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሥርዓት በመሆኑ የቁጥጥር ስራው የላላ እንዲሆን ማድረጉን ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የድንበር አስተዳደርና

ኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክተር በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

40. በመሆኑም

- የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴር፣ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የፌደራል ስነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የተቋቋሙበት ዓላማና ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንጻር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሥራቸው ከገንዘብ ዝውውር ጋር የተያያዘ በመሆኑ በየዘርፋቸው ለህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን ሊለዩ፣ በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርጉ የሚያስችል አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የፋይናንስ መረጃ ደህንነት ማዕከልም በየጊዜው የሚከሰቱ የተለያዩ ለውጦችን በማካካት በእነዚህ ተቋማት ሊለዩና መከላከያ ሊበጅላቸው በሚገባቸው አካባቢዎች ላይ ድጋፍ ሊያድርግና አፈጻጸማቸውንም ሊከታተል ይገባል፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌሎች የአገሪቱ ከተሞች በተለያዩ ቦታዎች በግልፅ የሚካሄደውን ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘቦች ምንዛሪ ንግድ ለማስቆምና የምንዛሪ አገልግሎት በባንክና እንደባንክ የመመንዘር አገልግሎት እንዲሰጡ ፈቃድ በተሰጣቸው አካላት ብቻ እንዲከናወን ጉዳዩ በዋነኛነት የሚመለከታቸው የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና ሌሎች የመንግስት አካላት በተቀናጀ መልክ ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ፣ ህብረተሰቡም የህገወጥ ምንዛሪ አገልግሎት በአገሪቱ ኢኮኖሚም ሆነ ደህንነት ላይ የሚያመጣውን ሥጋት እንዲገነዘብ ለማድረግ የሚረዳ

የግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያደርጉበትን አሠራር ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

- የፋይናንስ ተቋማት የደንበኞቻቸውን ማንነት ለማወቅ /customer due diligence/ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ ማንነትን የሚገልጽ መታወቂያ /National ID/ መኖሩ ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው የዚህ ተግባራዊነት እንዲፋጠን የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግስት አካላት ጋር በመነጋገር ተግባራዊ እንዲደረግ የራሱን ግፊት ሊያደርግ ይገባል፡፡ የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ተብለው የተሰየሙ የንግድ የሙያ ሥራዎች /designated non-financial businesses and professions/ (የሪል ስቴት፣ የህግ ባለሙያዎች፣ አማካሪዎች፣ የኦዲት ድርጅቶች ወ.ዘ.ተ.) የካሽ እና ተጠርጣሪ የግብይት ሪፖርት ለማዕከሉ የሚያሳውቁበት አሰራር ለመዘርጋት በማዕከሉ በየካቲት 2006 ዓ.ም የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በብሄራዊ ባንክ እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የወጪ እና የገቢ ንግድ እቃዎችን ዋጋ ከተገዙበት ወይም ከተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ አስበልጦ ወይም አሳንሶ /under and over invoicing of import and export/ የቀረጥ ነጻ መብት ተጠቃሚ የሆኑትን ጨምሮ በሚያቀርቡት ላይ በተቀመጠው ህግ በሚያዘው መሰረት ተገቢ እርምጃ ሊወሰድ እና በእንደዚህ አይነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ሀብት ወይንም ገንዘብ እንዳገኙ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችን መረጃዎች በየጊዜው ለማዕከሉ የሚተላለፍበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በህገ ወጥ ንግድ ስራ፣ ህገ ወጥ የማዕድን ማውጣት ስራ እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች ወይም በኤጀንሲዎች በኩል የሚደረግ ህገወጥ የውጭ አገር ገንዘብ ዝውውር ልውውጥ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል የዘርፍ መ/ቤቶች የማስተካከያ እርምጃ ሊወስዱ እና በእንደዚህ አይነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ሀብት ወይንም ገንዘብ እንዳገኙ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችን ደግሞ ለማእከሉ ሪፖርት የሚያሳወቁበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ለኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ በተከለለ የንግድ ዘርፍ ውስጥ የውጭ ዜጎች ተሰማርተው እንዳይሰሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ በህገወጥ መንገድ ካፒታል ወደ ውጭ ሀገር እንዳያሸሹ ሊያደርግ የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ማዕድን ሚኒስቴር በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱት የማዕድን ምርቶች አምራቾች ምን ያህል እንዳመረቱ እና ምን ያህል ለገበያ እንዳቀረቡ በየወቅቱ ሪፖርት እንዲቀርብለት፣ እንዲሁም ውጭ ሀገር ተልከው ደረጃ ለሚወጣላቸው የማዕድን ምርቶች ደረጃቸውን በማሳነስ እንዳይቀርብ ትክክለኛ በአገሪቱ የሚመረቱ ማዕድናት ደረጃ የሚታወቅበት ሥርዓት ሊዘረጋና ሊተገበር እንዲሁም በእንደዚህ አይነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ሀብት ወይንም ገንዘብ እንዳገኙ የሚጠረጥሯቸውን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶችን ለማዕከሉ ሊያሳውቁ የሚያስችል የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በአገሪቱ የመውጫ በሮች ላይ የህገወጥ ዕቃዎች ዝውውር ቁጥጥር ላይ የተመደቡ ሠራተኞች የከበሩ ማዕድናት በህገወጥ መንገድ ከአገር እንዳይወጡ የተጠናከረ ቁጥጥር ማድረግ እንዲችሉ ለባለሙያዎች ስለማዕድናት ባህሪያት የግንዛቤ ስልጠና ሊሰጣቸውና የተጠናቀረ የፍተሻ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥምም ማዕከሉ ሪፖርት ሊደረግለት ይገባል፡፡
- በብሔራዊ ባንክ ከተፈቀድው የገንዘብ መጠን በላይ ወደ ጅቡቲ ለሚሄዱ የከባድ መኪና ሹፌሮች መመሪያው ተጠብቆ የሚሰራበት ሁኔታ እየተፈቀደ ያለው የገንዘብ መጠን ወይ መመሪያው በፍጥነት የሚስተካከልበት ሁኔታ እንዲመቻች የሚመለከታቸው አካላት በመቀናጀት መፍትሔ ሊሰጡት ይገባል፡፡
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣ ቆንስላ ጽ/ቤቶች እና ብሔራዊ ባንክ በጋራ ውጭ ሀገራት የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን የሰሩበትን ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት ለመላክ የሚያስችላቸው ተደራሽ የሆነ ህጋዊ የመላኪያ መንገድ እንዲኖራቸው የሚያስችል ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ብሔራዊ ባንክ ለገቢ እና ለወጪ ዕቃዎች ፈቃድ ሲሰጥ (import and export permission) የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወደ አገር ውስጥ የሚገባው ወይም የሚወጣው በተሰጠው ፈቃድ መጠን መሆኑን ሊያረጋግጥና ከዚህ ጋር የተያያዙ መረጃዎችንም ባንኩና ባለስልጣኑ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ የጋራ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በማለት በሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

11.3 የግብርና ኤክስቴንሽን በተለይ የሰብል ኤክስቴንሽን አፈፃፀምን በተመለከተ፣

የኦዲት ግኝቶች

<u>በተለያየ ስነ ምህዳር የኤክስቴንሽን አገልግሎት መሰጠቱን በተመለከተ፤</u>

41. በተለያየ ስነ ምህዳር ውስጥ ለሚገኙ አርሶ አደሮች የአካበቢውን ስነ ምህዳር መሰረት ያደረገ የግብርና አመራረት ዘይቤንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አካባቢ ተኮር የኤክስቴንሽን ስልት ተቀይሶ ሊተገበር ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ✓ በምሥራቅ ኦሮሚያ ምዕራብ ሐረርጌ ዞን የአርሶ አደሮች እና የባለሙያዎች ስልጠና የጊዜ ሰሌዳ ዕቅድ አዘገጃጀት የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር ተከትሎ የበልግ እና የመኸር እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ወቅትን ያገናዘበ አለመሆኑን በመግለጽ ዞኑ በተደጋጋሚ ለክልሉ ቢገለጽም መፍትሄ ያልተሰጠ መሆኑን፣

- ✓ በአማራ ብሔራዊ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በሞረትና ጅሩ ወረዳ አርሶ አደሩ የጥቁር አፈር ማንጣፈፍ ቴክኖሎጂን በራሱ ባህላዊ ዘዴ እየተጠቀመ እንዳለና የአፈር ማንጣፈፊያ (IBAR-BBM) ቴክኖሎጂ የወረዳውን የአፈር ባህርይና በአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መመለስ ባለመቻሉ በጥቅም ላይ እየዋለ አለመሆኑን፣

- ✓ በኦሮሚያ ክልል የምስራቅ ወለጋ ዞን በዲጋ ወረዳ ወረዳው ሦስት የአየር ክልል ያለውና የሚዘራበት ወቅትም የተለያየ በመሆኑ ዘር በሚፈልጉበት ጊዜ በወቅቱ ሊቀርብላቸው አለመቻሉን ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ለኢንዱስትሪ የሚሆን ምርት እንዲመረትና የኢንዱስትሪ ትስስር እንዲፈጠር ለማድረግ የሚሰጠውን ድጋፍ በተመለከተ፤

43. ለአካባቢው የአየርና የአፈር አይነት ተስማሚ የሆነ የኢንደስትሪ ግብዓት የሚሆን የሰብል ምርት አርሶ አደሩ እንዲያመርትና ከኢንደስትሪ ጋር ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሊሰጥና ስለአፈጻጸሙም በየወቅቱ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ በአዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን በተካሄደ ዳሰሳ ጥናት ላይ በሀገሪቱ ከፍተኛ ምርት ከሚገኝባቸው ሰብሎች አንዱ ስንዴ መሆኑና ይህንንም ጥሬ ዕቃ በመጠቀም በርካታ የዱቄት ፋብሪካዎች ቢመሰረቱም በተለይ ዱረም ስንዴ በበቂ መጠንና ጥራት በሀገር ውስጥ ባለመመረቱ ስንዴ ከውጪ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

45. በተጨማሪም በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ በሚያመርቷቸው ምርቶች ላይ በመመስረት የኤክስፖርትና የኢንደስትሪ ምርቶች ላይ ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግ ቢሆንም ሌሎች ለኢንደስትሪ ግብዓትነት የሚውሉና ለኤክስፖርት የሚሆኑ ምርቶችን አርሶ አደሩ እንዲያመርት በጥናት ላይ ተመስርቶ የተሰራ ስራ መኖሩን እንደማያውቁ፣

- ✓ ስንዴን በተመለከተ ለአርሶ አደሩ የተሻሻለ ዝርያ ሊቀርብለት ባለመቻሉ ለኢንዳስትሪ ግብዓት የሚሆን ስንዴ ማቅረብ እንዳልቻለ እና የማስተሳሰሩ ስራ በሀሳብ ደረጃ እንዳለ እና ተግባራዊነቱ ግን በሚፈለገው ደረጃ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

<u>የአርሶ አደሩን ዘመናዊ አሰራሮችንና የግብርና ምርቶች ተጠቅሞ የማምረት ፍላጎት ግንዛቤ ለማሳደግ ዕቅድ ታቅዶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

46. በግብርና ላይ ለተሰማራው ህብረተሰብ ክፍል የግብርና ምርቶችን የማምረት ፍላጎቱና ለምርታማነት ማነቆ የሆነውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት አቀባበል ችግር ለመፍታት የሚያስችል በእቅድ ላይ የተመሰረተ ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ✓ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን ኦሞናዳ ወረዳ በተደረገው ውይይት በወረዳው ካሉት 18 ቀበሌዎች ውስጥ 5000 ሄክታር ያላነሰ የኮትቻ አፈር እንዳለ ቢገለጽም የኮትቻ አፈር ልማትን በዘመናዊ መልክ ለማልማት የተያዘ ዕቅድ አለመኖሩን፣

- ✓ በምዕራብ ሸዋ ዞን በኤጀሬ ወረዳ በአርሶ አደር የማሰልጠኛ ማዕከል ለማካሄድ ከታሰበው ቴክኖሎጂ የማስተዋወቅ ስራ ባሻገር በአርሶ አደር ደረጃ በስፋት ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ አለመዘጋጀቱን፣ በወረዳው በሚገኙ ቀበሌዎች የኮትቻ አፈርን በዘመናዊ መልክ ለማልማት የተያዘ ዕቅድ አለመኖሩን፣ ሁሉንም ሰብሎች ሙሉ ለሙሉ በመስመር ለመዝራት የተያዘው ዕቅድ ዝቅተኛ መሆን በተለይ ማሽላን በመስመር ለመዝራት በዕቅድ አለመያዝ እንዲሁም የማዳበሪያ ዕቅድን በተመለከተ በተለይ ዩሪያ በምክረ ሀሳቡ ውጪ ዝቅ አድርጎ ማቀድ፣

- ✓ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን የኤጀሬ ወረዳ አሞቱ ቀበሌ የግብአት አስተቃቀድ አቅርቦትና ስርጭት በተሰጠው ስልጠናና ምክረ ሀሳብ መሰረት አለመፈጸሙን ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በአርሶ አደሩ በኩል ያለውን የግብዓት

አጠቃቀም ማነቆዎች ሊፈታ በሚያስችል መልኩ የክትትልና ድጋፍ ስራው በሚፈለገው ደረጃ አለመካሄዱን ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ችለናል፡፡

የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ያሉ የሜትሮሎጂ ጣቢያዎችን በተመለከተ፤

48. እያንዳንዱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠርያና መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ እንዲኖረውና ወቅታዊ የሆነ የአየር ሁኔታ ዘገባና ትንበያ መረጃ እንዲያቀርብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

49. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በደብብ ብ/ብ/ህ/ብ/ ክልሎች በሚገኙ 16 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ያሉ የስራ ኃላፊዎችና አርሶ አደሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ እንዲሁም በአካል በመገኘት ለማየት እንደተቻለው አስራ ሁለቱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያካተተ የሜትሮሎጂ ጣቢያ የሌላቸው መሆኑን፣ የአየር ሁኔታ ትንበያ በተሟላ መልኩ እንደማይሰጡ እና የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ ሲገልፁ፣ በቀሪዎቹ በአማራ ክልል በሚገኙ አራት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ሬንጌጅ ብቻ እንዳለና ይህንን መሰረት በማድረግ የተሟላ ባይሆንም የዝናብ ሁኔታ መረጃ ለመስጠት እንደሚሞክሩ ገልጸዋል፡፡

የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች በቋሚነት የሚታዩበት ኢግዚቢሽን ማዕከል እንዲደራጅ መደረጉን በተመለከተ፤

50. የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የግብርና ቴክኖሎጂ ሞዴል ሥራዎች ትምህርት ሊሰጡ በሚችሉበት ሁኔታ በማሰባሰብ በቋሚነት የሚታዩበት ኢግዚቢሽን ማዕከል (የተለያዩ የሰብል

ዝርያዎችን፣ የእርሻ መሳሪያዎችን፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን፣ የተለያዩ የአረም አይነቶችን፣ የሰብል በሽታዎችን፣ ሰብል አጥቂ ነፍሳትና ተባይ ናሙናዎችን፣ የግብርና ውጤቶችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን) እና ሰርቶ ማሳያ እንዲያደራጁ እና በመረጃ ማዕከልነትም ጭምር ማገልገል እንዲችሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች እገዛ ሊደረግ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በጋምቤላ ክልል፡-

- ✓ ሰርቶ ማሳያ ከ2.5 እስከ 3 ሄክታር መሆን ሲኖርበት በማጃንግ ዞን በጎደሬ ወረዳ የሚገኙ 12 የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የእያንዳንዳቸው የሰርቶ ማሳያ ስፋት 0.5 እስከ 2 ሄክታር የሚደርስ ሲሆን ከአንዱ በስተቀር ቀሪዎቹ አጥር የሌላቸው መሆኑን፣

- ✓ ያሉት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት በሙሉ በቁሳቁስ (ጠረጴዛ፣ ብላክ ቦርድ፣ ቾክ፣ የመሳሰሉት) ያልተሟሉና ሰርቶ ማሳያቸው በሰብል ልማትና ጥበቃ፣ በእንስሳት ሀብት ልማትና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ሥራ ለማከናወን የተከፋፈለ አለመሆንና የሰርቶ ማሳያ ቦታ የሌላቸው መሆኑን፣

52. በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መኖር ያለባቸውን ቋሚ ኢግዚቢሽኖችን በተመለከተ በ2005 ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣው የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት መመሪያ ላይ የተለያዩ የሰብል ዝርያዎችን፣ የእርሻ መሳሪያዎችን፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን፣ የተለያዩ የአረም አይነቶችን፣ የሰብል በሽታዎችን፣ ሰብል አጥቂ ነፍሳትና ተባይ ናሙናዎችን፣ የግብርና ውጤቶችንና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለኢግዚቢሽኑ በተዘጋጀ ቦታ እንዲያስተዋውቁ የሚል ቢሆንም በናሙና በታዩት ክልሎች ባሉ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ይህንን ማየት አልተቻለም፡፡

<u>በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ለአርሶ አደሩ በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እና ለልማት ሰራተኞች የብቃት ማረጋገጫ መሰጠቱን በተመለከተ፤</u>

53. በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በተዘጋጀው የስልጠና ካሪኩለም መሰረት እንዲሆን፣ በአንድ ክፍል ውስጥ ከ20-30 የሚሆኑ ሰልጣኞች ብቻ እንዲሰለጥኑ እንዲሁም የልማት ሰራተኞችን ብቃት በመፈተሽ ማረጋገጥ እንዲቻል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

54. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን በመንገሺ ወረዳ በ15ቱም ቀበሌዎች የሞጅላር (በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና) ሌሎችም ስልጠናዎች ያልተጀመሩ መሆኑን፣ በ2005 ዓ.ም በደቡብ ክልል የባለሙያዎችም ሆነ የልማት ሰራተኞች የሙያ ብቃት ምዘና እንዳልተካሄደ ከተከለሱ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

55. በጋምቤላ ክልል የግብርና ልማት አሰራር ሁኔታ ላይ በአራት የባለሙያዎች ቡድን ከተደረገው የዳሰሳ ጥናት ውስጥ የቡድን አንድ ሪፖርት ላይ በጋምቤላ ክልል በማጃንግ ዞን የጎደሬ ወረዳ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ባሉባቸው ቀበሌዎች የሞጅላር ስልጠና (በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና) ጅምር ላይ የነበረ ቢሆንም ሰልጣኞች እስከ መጨረሻ ትምህርቱን ተከታትለው አለመጨረስና የጨረሱትም ቢሆን ሰርትፊኬት አለማግኘታቸው እንደ ችግር ተጠቁሟል፡፡

56. በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የሚገኙ የስራ ኃላፊዎች እና አርሶ አደሮች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- ✓ ወቅታዊና አጫጭር ስልጠና የሚሰጥ እንደሆነና በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠናን ከንድፈ ሀሳብ ጀምሮ እስከ

ተግባር ድረስ ለመስጠት የሚያስችል ጅምሩ እንዳለ፣ ነገር ግን የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ከተቋቋሙበት አላማ አንዱ አርሶ አደርን ማሰልጠን ቢሆንም ይህንን አላማ ከግብ ማድረስ እንዳልተቻለ፣

- ✓ በናሙና ከታዩት የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኘው ከኮትቾ ሶፋኒ ቀበሌ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋም በስተቀር ሌሎቹ በበብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና እየሰጡ እንዳልሆነ፣ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ለባለሙያዎች ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት ቅድመ ዝግጅትና በመሳሪያ ልምምድ እንዲያደርጉ የማይደረግ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ተፈታኞች ፈተናውን የማያልፉበት ሁኔታ መኖሩ፣ ያለፉትም ቢሆኑ እየለቀቁ መሆኑን፣
- ✓ በናሙና በታዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ለሚገኙ ባለሙያዎች በ2006 ዓ.ም በክልሉ የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም ተግባራዊ ያልሆነበት ሁኔታ መኖሩን አስረድተዋል፡፡

<u>የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

57. ለአርሶ አደሩ በሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስራ ላይ የአርሶ አደሩን እርካታ ለመገምገምና ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት እርካታ ያልተገኘባቸውን በመለየት ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

58. ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው በሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ላይ የአርሶ አደሩን እርካታ

ለመገምገም የሚያስችል አሰራር ሥርዓት መዘርጋቱ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ሥርዓቱ ቢዘረጋም እርካታውን ለማወቅ የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት በወቅቱ አለመከናወኑ እንደክፍተት የሚታይ መሆኑን፣ የዳሰሳ ጥናት ባልተደረገበት ሁኔታ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች በመቶኛ 80 መድረሱ በዕቅድ አፈፃፀሙ ላይ የተጠቀሰ መሆኑን እና የደሰሳ ጥናቱ የኦዲት ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ እንዳልተጠና ለማወቅ ችለናል፡፡

<u>አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሩን በማደራጀት አተገባበሩን በማየት ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

59. የኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ለመስጠት እንዲያመች አርሶ እና ከፊል አርሶ አደሩን በልማት ቡድን፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ እንዲሁም የምርት እሴት በሚጨምሩ ቡድኖች ማደራጀትና አተገባበራቸውን በማየት እንዲሻሻሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

60. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ✓ በአማራ ክልል በአዊ ዞን በዳንግላ ወረዳ አባድራ አጋጋ እና ጉልት አብሽካን ቀበሌ እንዲሁም ደቡብ ጎንደር ዞን በደራ ወረዳ ሽሜ ማርያም እና ወንጨጥ ቀበሌ የክላስተር ቡድኑ በተገኘባቸው በሁሉም ቀበሌዎች 1ለ5ም ሆኑ የልማት ቡድኖች ተሰብስበው ቢወያዩም ከዚህ በፊት በዘልማድ ሲገናኙ ከሚያደርጉት ንግግር የተለየ አጀንዳ ይዘው ችግሮችን ነቅሰው በማውጣት መፍትሔ ከመስጠት ደረጃ ላይ የደረሰ ውይይት እንደማያካሂዱ፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ሞረትና ጅሩ ወረዳ በወይራ አንባ ቀበሌ አርሶ አደሩ በአደረጃጀቱ ወቅታዊ ስራዎች ላይ የመነጋገር ሁኔታ ቢኖርም ደረጃ እየተሰጣጡ መገማገም የሌለ መሆኑና አደረጃጀቱ ውጤታማ እንዳይሆን እንዳደረገ፣

- ✓ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በነጋ ጫላ ቀበሌ የመኸር ስራዎችን በሚገባ አደራጅቶ በመረጃ አለመያዝና የአንድ ለአምስት አደረጃጀት የግምገማ ውጤት በማህደር አለማዘጋጀት ከ2005/6 ምርት ዘመን የበልግ እና መኸር ምርት ወቅት የመስክ ክትትል እና ድጋፍ ሪፖርት ላይ መገለፁን፣

<u>በተሰበሰቡና በተቀመሩ ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይ የስልጠናና የምክር አገልግሎት ስለመስጠቱ፤</u>

61. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከምርምር የሚወጡ ፓኬጆች፣ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና አሰራሮች የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሰረት ባደረጉ የደሰሳ ጥናቶች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል፡፡ በተዘጋጁት ፓኬጆች ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይ የስልጠናና የምክር አገልግሎት እንዲሰጥና የመጣውን ውጤት በመገምገም ለቀጣይ እንደ ግብዓት መጠቀም እንዲቻል በየደረጃው ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2005 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በአማራ፣ ትግራይና ደቡብ ክልሎች ላይ በአፈፃፀም ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን አርሶ አደሮች በመለየት በተሻሻለ ፊልም ቀረፃ ማሰራጨትና በሚሻሻለው የኮትቻ አፈር ትምህርታዊ ፊልም እንዲካተት የማድረግና የማሰራጨት ስራ ያልተከናወነ መሆኑን፣

- ✓ በአማራ ክልል በግብርና ቢሮ የክረምት ስራዎቻችን የሚገኙበት ሁኔታ በሚል በሀምሌ 30/2006 ከተደረገ የመስክ ሪፖርት ላይ በአጠቃላይ ሲታይ በአማራ ክልል በመስመር የመዝራት ቴክኖሎጂ መሻሻል እየታየበት የመጣ ቢሆንም አንዳንድ ዞኖች ግን አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ የታየ

ሲሆን፣ ለአብነት ያህል ደቡብ ጎንደር 32%፣ ሰሜን ጎንደር 40%፣ ደቡብ ወሎ 46% መሆናቸውን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

<u>የሴቶችና የወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ላይ የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ፤</u>

63. በግብርና ኤክስቴንሽን በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎትና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያ እና በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠናዎች ላይ በእኩል ሁኔታ ሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተጠቃሚነታቸውንም ለማረጋገጥ እንዲያስችል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

64. ስለሁኔታው በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- ✓ ሴቶች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰሩ የሚፈለግ በመሆኑና የባህልንም ተፅዕኖ መቀነስ ባለመቻሉ ሴቶች ከወንዶች እኩል ኤክስቴንሽን ላይ የመሳተፍ ችግር እንዳለ፣ በዕቅድ ደረጃ ሴቶች 30 በመቶ ወጣቶች 10 በመቶ ተጠቃሚ ይሁኑ የሚል ቢሆንም ለሴቶች ስልጠና ተዘጋጅቶ ለመስጠት ሲሞከር ወደ ስልጠና የሚወጡበት ሁኔታ ባለመኖሩ ዕቅዱን ተፈፃሚ ለማድረግ እንዳልተቻለ፣

- ✓ ወጣቶችን በተመለከተ በተለይ በ2006 ዓ.ም ተደራጅተው በተለያየ የልማት ስራዎች እንዲሳተፉ የማድረግ ስራ እየተሰራ ቢሆንም የመሬት ፍላጎታቸውን ማሟላት ባይቻልም ወጣቶችን ተሳታፊ ለማድረግ መሬት በኮንትራት ተከራይተው እንዲሰሩ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ እንደሚገኝ፣

- ✓ በአጠቃላይ በመስክ ስራ ወቅት መረዳት እንደቻልነው ተሳትፎአዊ የግብርና ኤክስቴንሽን ስርዓት ላይ በተገለፀው

መልኩ ወጣቶችና ሴቶች ላይ የተሰራው ስራ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>ደረጃዎችን በማውጣት በደረጃው መሰረት የአርሶ አደር ማሰልጠኛዎቹ እንዲሟሉ ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

65. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ ደረጃ ሊያወጣና ተግባራዊነቱንም ሊከታተል ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአወጣው ደረጃ ተቋማቱን መሰረት ለማደራጀትና ማሰልጠኛዎቹ የተሟሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች ድጋፍና ተገቢውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

66. በመስክ ጉብኝት ወቅት በታዩ ክልሎች ያሉ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት

- ✓ የማሰልጠኛ ተቋማቱን ለማደራጀት የሚያስችል ደረጃ ወጥቶ በዕሁፍ እንዳልደረሳቸውና አልፎ አልፎ ከወረዳው በሚላክላቸው ቼክ ሊስት የሚጠቀሙ መሆኑን፣

- ✓ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ሊሰጥባቸው በሚገባቸው ሶስት ሙያዎች ማለትም ሰብል፣ ተፈጥሮ ሀብትና እንስሳት ጥበቃ የተሟላ የኤክስቴንሽን ባለሙያ ባለመኖሩ፣ በከፍተኛ ሁኔታ ባለሙያው ስራ የሚለቅበት ሁኔታ በመኖሩና ተከታታይነት ያለው ስልጠና ለአርሶ አደሩ አለመሰጠቱን፣

- ✓ አንድ ባለሙያ ለበርካታ አርሶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሰጥ በመደረጉ አርሶ አደሩ የተሟላ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረጉ፣

- ✓ ለአርሶ አደሩ የተሟላ ስልጠና ለመስጠት በማሰልጠኛ ተቋማቱ ሊኖሩ የሚገባቸው ካሜራ፣ ወንበሮች፣ የመብራትና የውሀ አገልግሎት፣ ኮምፒውተር፣ የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የተሟላ የእርሻ መሬትና የተግባር ማስተማሪያዎች ያልተሟሉ

መሆኑ፣ ለባለሙያዎች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ቁሳቁስ (መንቀሳቀሻ) ያልተሟሉባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ለመረዳት ችለናል፡፡

<u>አርሶ አደሩ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

67. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አርሶ አደሩ የምርት ጥራትና እሴትን የሚጨምሩ እንዲሁም ብክነትን በእጅጉ የሚቀንሱ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀም ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በግብርና ሚኒስቴር ደብዳቤ ቁጥር ሃ/to 0021/06 ቀን ጥር 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ሪፖርት ላይ፡-

- ✓ በአማራና ደቡብ ክልሎች ከድህረ-ምርት ክምችት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የምርት ብክነት (በተለይ በነቀዝ ምክንያት) መኖሩ እንደተስተዋለ፣
- ✓ በድህረ ምርት ክምችት ወቅት ከ20-30% የሚሆነው ምርት የጥራትና መጠን ብክነት እንደሚደርስበትና አብላጫው ብክነት ደግሞ የሚከሰተው በመጀመርያዎቹ ሶስት የክምችት ወራት ውስጥ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩ ተገልጿል፡፡

69. በኦዲቱ ወቅት ቀርበው ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ ከ2005/6 ምርት ዘመን የበልግ እና መኸር ምርት ወቅት የተደረገ የመስክ ክትትል እና ድጋፍ ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው በኤጀሬ ወረዳ ሰፊ ሽፋን ያለው ኮትቻ መሬት የሚገኝ ቢሆንም ቢቢኤምን ለአርሶ አደሩ በማስተዋወቅ ጥቅም

ላይ ሊውል የሚችል ቢሆንም በወረዳው መጋዘን ውስጥ በብዛት ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑን ለማየት መቻሉ፣

- ✓ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን በዲጋ ወረዳ ሌሊሳ ዲምቱ እና ቢቂላ ቀበሌ የአንዳንድ ሰብሎች ዘር እጥረት እንዳለና ጥያቄ ቢያቀርቡም ምላሽ ያላገኙ መሆኑ፣

70. በመስክ ጉብኝት ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት ያሉ የስራ ኃላፊዎች እንዲሁም አርሶ አደሮች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፡-

- ✓ ፍላጎትና አቅርቦት እንዳልተጣጣመ እንዲሁም የሚቀርቡት ግብዓቶች በተለይ ምርጥ ዘር ላይ (ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ቅምብቢት፣ ኢሉ፣ ኤጀሬ ወረዳዎች እና በአማራ ክልል ደቡብ አቸፈርና ፋርጣ ወረዳዎች) ጥራታቸውን የጠበቁ እንዳልሆኑና በአንዳንድ ወረዳዎች ላይ የጤፍ በመስመር መዝሪያ ቴክኖሎጂ ከእርሻ ጊዜ ዘግይቶ የመጣበት ሁኔታ መኖሩን፣

- ✓ ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች (መጋዘን፣ ማጨጃ፣ መውቂያ፣ የመሳሰሉት) ላይ የተጠናከረ ስራ ተሰርቷል ማለት እንደማይቻል፣ ለድህረ ምርት ባለሙያ የስራ ድርሻ ያልተቀመጠ እንደሆነ፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂዎች (በመስመር መዝሪያ፣ አፈር ማጠንፈፊያ (BBM) የመሳሰሉት) ሳይጠኑ እየመጡ አርሶ አደሩ ሳይጠቀምባቸው አለአግባብ በመጋዘን ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

<u>ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን አቅርቦት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

71. ሚኒስትር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና የሪፖርት ልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከክልሎች፣ ከዞኖች፣ ከወረዳዎች እና

ከአርሶ አደሩ ጋር የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም አምራቾች መረጃዎችን በወቅቱ የሚያገኙበት የመረጃና የኢንፎርሜሽን ስርዓት ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

72. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ላይ፡-

- ✓ በኮማንድ ፖስት አማካኝነት የሚሰበሰበው መረጃ በስልክ ጉትጎታ እንጂ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ተዘርግቶ በዘመናዊ አይ.ሲ.ቲ የተያዘ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ፣ የመረጃ ማሰባሰብያ ፎርማት /ቅፅ/ ስታንዳርዱን በጠበቀ መልኩ አለመዘጋጀቱ፣

- ✓ የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ በየጊዜው የሚዘጋጁና ተከልሰው የሚወጡ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ፓኬጆችና የማስተማሪያ ማንዋሎች ወዘተ በመ/ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ በየወቅቱ እንዲወጡ (እንዲጫኑ) ባለመደረጉ በኢንተርኔት መረጃ ማግኘት ለሚፈልጉ ባለድርሻዎች ተደራሽ ካለመሆኑም በላይ የተጠቃሚ ቁጥርን ለማወቅና አስተያየቶችን ለመቀበል አለመቻሉ ክፍተት መፍጠሩ የተገለጸ ሲሆን በ2005 እና በ2006 ዓ/ም ዕቅዶች ላይ በግልፅ ያልታየ መሆኑን፣

- ✓ ከክልሎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች በወቅቱ ያለመድረስ ችግር እንዳለባቸው ከግብርና ልማት ዘርፍ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ታህሳስ 22 ቀን 2005 ላይ መገለጹን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው መመስረታቸውንና በቅንጅት መስራታቸውን በተመለከተ፤</u>

73. በግብርና ልማት የተሰማሩ የተለያዩ አካላትን የሚያገናኙ የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው ሊቋቋሙ ይገባል፡፡

እነዚህን ካውንስሎች ለማጠናከር የሚያስችል አቅም እና ጠንካራ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የተቀናጀ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሊቀርብለት ይገባል፡፡

74. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- ✓ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከተፃፈ ማስታወሻ ለመረዳት እንደተቻለው በሱማሌ ክልል ከሚገኙ 9 ዞኖች፣ 68 ወረዳዎችና 713 ቀበሌዎች ውስጥ በሦስት ዞኖችና በጅጅጋ ወረዳ የልማት አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስሎች የተቋቋሙ ሲሆን፣ በሌሎች ዞኖችና ወረዳዎች ያልተቋቋሙ መሆኑ፣

- ✓ የደቡብ ክልል፣ የሲዳማና ጉራጌ ዞኖችና የኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎች ሰነድ ላይ፡-

  - በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ 14 ዞኖች ውስጥ 11 (78%)፣ ከ 136 ወረዳዎች 47 (35%) ካውንስሎች የተቋቋሙ ሲሆን፣ በ 3,759 ቀበሌዎች በሙሉ ያልተቋቋሙ መሆኑን፣

  - በደቡብ ክልል ከሚገኙ 18 ዞኖች ውስጥ 17 (94%)፣ ከ 265 ወረዳዎች 127 (48%) ካውንስሉን ያቋቋሙ ሲሆን፣ ከ 6,434 ቀበሌዎች ሁሉም ካውንስሉን እንዳላቋቋሙ፣

  - በኦሮሚያ ክልል ካውንስሉን 11 ዞኖች ቢቋቋሙም ጉባኤውን ያካሄዱት አራቱ ብቻ መሆናቸውን፣

  - በደቡብ ክልል ካውንስሉን ካቋቋሙት 17 ዞኖች ውስጥ አስራ አንዱ ጉባኤውን ያካሄዱ ሲሆን፣ 127 ወረዳዎች ጉባኤው የተካሄደው በ 34 ቱ መሆኑን፣

- ✓ በጋምቤላ ክልል በአራት የባለሙያዎች ቡድን ካደረገው የዳሰሳ ጥናት ውስጥ የቡድን አንድ ሪፖርት ላይ መገንዘብ

እንደተቻለው በጋምቤላ ክልል በዲማ እና መንገሺ ወረዳዎች የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል በወረዳ ደረጃ ተለይቶ ያልተቋቋመ ሲሆን ስለአደረጃጀቱና የአተገባበር መመሪያው የግንዛቤ እጥረት እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀት እንዲሁም በክልሎችና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል የልምድ ልውውጥ እንዲደረግ ያለውን ድጋፍ በተመለከተ፤</u>

75. ሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል የግብርና ቢሮዎች ዕቅድ በማቀድ ለክልል ባለሙያዎች የስልጠና መድረኮችን አውደ ጥናቶችን በማዘጋጀትና በተሻሉ ተሞክሮዎች ላይ በክልሎችና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል የልምድ ልውውጦችን በማካሄድ አቅማቸውን እንዲያጎልብቱ ሊደረግ ይገባል፡፡

76. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2004 እና 2005 በጀት ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ፡-

- ✓ ስራዎች በሚፈለጉበት ወቅት አለመከናወን፣ ይህም ወቅቱን ያልጠበቀ ስልጠና ለክልሎች በመስጠቱ ክልሎች በወቅቱ ሊጠቀሙበት እንዳልቻሉ መግለፃቸውን እንዲሁም በበልግ ወቅት በምሥራቅ ሸዋ ዞን እና በባሌ ዞን ከፍተኛ ሥራ እንዳለ እየታወቀ አብዛኛውን ጊዜ ስልጠና ለባለሙያውም ሆነ ለአርሶ አደሩ በዛን ወቅት ላይ መደረጉ በሥራዎች ላይ እንቅፋት መፍጠሩን፣

- ✓ የተሰጡ ድጋፎችና ክትትሎች ያስገኙትን ፋይዳ ግብረ-መልስ የመሰብሰብ ስራ ማነስ፣ የሚሰጡ ስልጠናዎች ተግባር ነክ ከማድረግ አንፃር (70/30) የሚለውን መርህ በትክክል አለመፈፀም እና የተግባር ስልጠናዎች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በሚያሳይ መልኩ በምስል/ በቪድዮ እንዲሁም በመስክ መርጃ መሳሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ አለመቻሉን፣

77. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በነጋ ጫላ ቀበሌ የግብርና ሚኒስቴር የክትትል ቡድኑ ባደረገው ውይይት ለምርጥ ተሞክሮ ለተመረጡ አርሶ አደሮች ተሞክሮ የመጣበትን ሂደት የሚያሳይ የየወቅቱ መረጃዎችን በአግባቡ አለመያዝ ችግር እንደታየ በ2005/6 ምርት ዘመን የበልግ እና መኸር ምርት ወቅት የመስክ ሪፖርት ላይ ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>በኤክስቴንሽን አፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት አውደ ጥናት መካሄዱን ግብረ መልስ መሰብሰቡንና ጥናት መደረጉን በተመለከተ፤</u>

78. በግብርና ኤክስቴንሽን አሰራርና በአፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ከክልል ባለሙያዎች ጋር በመሆን አውደ ጥናት በማካሄድ፣ ግብረ መልስ በመሰብሰብና በማጥናት ለችግሮቹ የመፍትሄ ሀሳብ መስጠትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

79. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመለየትና በመቀመር ለተጠቃሚዎች እንዲዳረስ ቢደረግም የቴክኖሎጂውን ውጤታማነት የሚያረጋግጥ ግብረ መልስ አለመሰብሰብ፣ በተሰራጩት ምርጥ ተሞክሮዎች የተጠቃሚ አርሶ አደሮች ብዛት የሚገልፅ መረጃ መሰብሰብ አለመቻል የታዩ ክፍተቶች እንደሆኑና የተሰጡ ድጋፎችና ክትትሎች ያስገኙትን ፋይዳ ግብረ መልስ የመሰብሰብ ሥራ ማነስ እንዳለ ከግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ላይ ለመረዳት የተቻለና በ2005 ዓ/ም በግልፅ ያልታቀደ ሲሆን በ2006 ዓ/ም ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡

80. በፌደራልና በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላት ወጥተው በምርት ላይ ያሉ የበቆሎ፣ የስንዴ፣ የጤፍ፣ የገብስ፣ የሰሊጥና የባቄላ ሰብል ዝርያዎችን አቋምና ውጤታማነት በመስክ ከግብርና ምርምር ማዕከላት እና ከምርጥ ዘር ድርጅቶች ጋር በመገምገም ለቴክኖሎጂ አፍላቂዎች እና አቅራቢዎች ግብረ መልስ ለመስጠት

ታቅዶ ይህ ተግባር ሰብሎቹ በመስክ ላይ ባሉበት ወቅት መከናወን የነበረበት ቢሆንም አለመከናወኑን የ2006 የግማሽ አመት አፈፃፀም ሪፖርትን በመከለስ ለመረዳት ችለናል፡፡

በመሆኑም

- ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት በተለያየ ስነ ምህዳር ውስጥ የሚገኙ አርሶ አደሮችን የአመራረት ዘይቤ መሰረት ያደረገና የአርሶ አደሩን ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡

- ከአካባቢው የአየርና የአፈር አይነት ተስማሚ የሆነ ምርት ለማምረት የሚያስችል የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመዘርጋት የኢንደስትሪ ምርቶች እንዲመረቱ እንዲሁም በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ላሉ የሀገር ውስጥ አግሮ ኢንደስትሪዎች የአርሶ አደሩን ምርት እንዲጠቀሙና ከውጭ የሚገቡ ምርቶች እንዲቀንሱና የውጭ ምንዛሪን ማዳን እንዲቻል ትስስሩ ሊፈጠር ይገባል፡፡

- የተሟላና ትክክለኛ የአየር ሁኔታ ዘገባ ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ይቻል ዘንድ በየክልሉ በሚገኙ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት መሰረታዊ የሆኑ የአየር ሁኔታ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ መሳሪያዎችን ያሟሉ የሜትሮሎጂ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙላቸው እንዲሁም መረጃውን ለአርሶ አደሩ እንዲሰጡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎች ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት የተሟሉ እና በውስጣቸው የሚገኙ ሰርቶ ማሳያዎችም መመሪያው በሚያዘው መሰረት የተደራጁ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚያስተዋውቁ የመረጃ ማዕከሎች በመሆን የአርሶ አደሩን የአመለካከት ችግር የሚቀርፉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህንን ዓላማ

ለማሳካትም ሚኒስትር መ/ቤቱ ከክልሎችና በየደረጃው ከሚገኙ የግብርና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራትና ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በተዘጋጀው የስልጠና ካሪኩለም መሰረት እንዲሆን እና ለልማት ሰራተኞች የሚሰጠው የሙያ ብቃት ምዘና ባልተቆራረጠና ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲሰጥ እንዲሁም ስልጠናውን ያጠናቀቁ አርሶ አደሮች ሰርትፍኬት እንዲያገኙ ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና በየደረጃው ከሚገኙ የግብርና ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ለአርሶ አደሩ የሚሰጠውን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማሻሻልና ውጤታማ ለማድረግ የአርሶ አደሩን የግብርና ምርቶች የማምረት ፍላጎትና ችግሮች በመለየት አጠቃላይ ጥናት ሊጠናና በተደረገው ጥናት መሰረትም እርካታ ያልተገኘባቸውን ለይቶ ማስተካከያ በማድረግ አገልግሎቱን ለመስጠት እንዲቻል ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- አርሶ አደሩን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ እንዲሁም የምርት እሴት በሚጨምሩ ቡድኖች በማደራጀትና በማሳተፍ ውጤታማ የሆነ የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሁም የአደረጃጀቱ ያስገኘውን ውጤት በየጊዜው በመገምገም እንዲሻሻል ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ከምርምር የሚወጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብና በመቀመር ለአርሶ አደሩ እንደ የፍላጎቱ እንዲቀርብና ተሞክሮው እንዲሰፋ እንዲሁም ፓኬጆች

ላይ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ተከታታይነት ያለውና ከተግባር ጋር የተቀናጀ ስልጠናና ምክር በመስጠት ውጤቱን በመገምገም ለቀጣይ ስራዎች እንደ ግብዓት እንዲያገለግል ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሴቶችና ወጣቶች በግብርና ኤክስቴንሽን በሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎትና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙሪያና በሞጁላር ስልጠናዎች (በብቃት አሀድ ላይ የተመሰረተ ስልጠና) ላይ በእኩል ሁኔታ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በተለይ ሴቶች ቤታቸው ውስጥ እንዲሰሩ የሚፈለግ በመሆኑና ያለባቸውን የባህልን ተፅዕኖ ለመቀነስ ለሴቶች በሚዘጋጀው ስልጠና ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአርሶ አደር የማሰልጠኛ ተቋማቱን ለማደራጀት የሚያስችል ደረጃ ወጥቶ ለሚመለከታቸው አካላት በፅሁፍ እንዲደርስ እና መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ ደረጃ አሟልተው ስልጠናውን እንዲያከናውኑ ሚኒስትር መ/ቤቱ ለክልሎች ድጋፍ ሊያደርግና ሊከታተል ይገባል፡፡

- አርሶ አደሩ በቅድመ ምርትና ድህረ ምርት ላይ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች የምርት ጥራትና እሴትን የሚጨምሩ እንዲሁም ብክነትን የሚቀንሱ የቅድመና የድህረ ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን አርሶ አደሩ በሰፊው መጠቀም እንዲችል የማስተዋወቅና የማቅረብ ሥራዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተጠናከረ ድጋፍ እና ክትትል ሊደረግ

እንዲሁም ውጤታማነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በአይባር ቢቢኤም ለማጠንፈፍ አስቸጋሪ የሆኑ አካባቢዎች ላይ የተሰራጩ ቢቢኤሞች ወደ ሌላ ተግባር ላይ ሊውሉ ወደሚችሉበት አካባቢ እንዲዛወሩ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የኤክስቴንሽን ክፍሉ ከክልሎች ጋር ቋሚና ወጥ የሆነ የመረጃና ሪፖርት ልውውጥ ስርዓት ሊኖረው፣ በየጊዜው የሚዘጋጁና ተከልሰው የሚወጡ ምርጥ ተሞክሮዎች፣ ፓኬጆችና የማስተማሪያ ማንዋሎች ወዘተ በመ/ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ በየወቅቱ እንዲወጡ (እንዲጫኑ) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

- የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻልና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ እንዲሁም በግብርናው ላይ ላሉት ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ማምጣት እንዲቻል የልማት አካላት ግንኙነት ካውንስሎች በየደረጃው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቋቋሙና በልማት አካላቱ መካከል ጠንካራ የስራ ግንኙነት እንዲፈጠር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የክልል ባለሙያዎችም ሆኑ ውጤታማ የሆኑ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት እርስ በእርስ የስልጠናና የልምድ ልውውጥ መድረክ እንዲኖራቸው ዕቅድ በማቀድና ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ለአርሶ አደሮች የሚሰጠው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤት ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በኤክስቴንሽን አሰራሩ ላይ ያሉ ችግሮችን ለመለየትና የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት እንዲቻል ከክልል ባለሙያዎች ጋር በመተባበር አውደ ጥናት በማዘጋጀትና ግብረ መልስ

በመሰብሰብ እንዲሁም ጥናት በማካሄድ ሚኒስቴር ቤቱ ከክልሎችና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለተግባራዊነቱና ለውጤታማነቱ በተሻለ ሁኔታ ሊሰሩ ይገባል፡፡

በማለት በሪፖርቱ የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

11.4 የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲቱዩትን በተመለከተ የኦዲት ግኝቶች

<u>የስትራቴጂክ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅዶች የሚዘጋጁ እና በዕቅዱ መሰረት መስራቱን በተመለከተ፣</u>

81. ማዕከሉ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በስትራቴጂክ ዕቅዱ የተመነዘረ ዓመታዊ ዕቅዶችን በማዘጋጀት በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን ሊተገብርና በስራ አፈፃፀሙ የታዩ ችግሮችን በመለየትና እርምጃ በመውሰድ ሊያስወግድ ወይም እንዲቀንስ ማድረግ አለበት፡፡

82. ይሁን እንጂ የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር በስሩ ያሉ መ/ቤቶችን በማካተት ባዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድን መሠረት በማድረግ ማዕከሉ የራሱን የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2003— 2007 በጀት ዓመት) ያላዘጋጀ መሆኑ፣ በማዕከሉ የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣ እንዲሁም በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ መረጃዎች በግልፅ/በቁጥር፣ በፐርሰንት/ በሚያሳይ መልኩ ያልተቀመጡ መሆኑ፣ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች የመቀበል አቅሙ እየጨመረ የሄደ ቢሆንም ከ2003-2006 በጀት ዓመት የተቀበለው የተማሪ ቁጥር እንደ ቅደም ተከተላቸው 146፣ 543፣ 945 እና 1,023 ሲሆን በአጠቃላይ 2,657 ተማሪዎች በመሆኑ በእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ(GTP) መጨረሻ ላይ በ2007 በጀት ዓመት የተማሪዎች

የመቀበል አቅም 11,070 ይደርሳል ተብሎ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን በፊት ከነበረው አፈፃፀም ጋር ሲታይ የተያዘው ዕቅድ የተጋነነ መሆኑን

<u>በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራትና ስልጠናው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጥ የሚያስፈልጉ ሞጅሎች ስለመኖራቸው</u>

83. በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ከማጠናከርና ብቁና የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማፍራት አኳያ በቤተ መጻህፍትም ሆነ ለተማሪዎች የሚደርሱ የተለያዩ የስልጠና ሞጅሎችን በመግዛትም ሆነ በማዕከሉ በማዘጋጀትና በማባዛት ስልጠናውን በተጠናከረ ሁኔታ ሊሰጥ ይገባል፡፡

84. ይሁን እንጂ በቤተመጽሐፍቱም የቅርብ ጊዜ (ወቅታዊ የሆኑ መጽሃፍት) የሌሉ መሆኑ፣ መጽሃፍትን ተማሪዎች ተውሰው ወስደው ስልጠናቸውን የሚያጠናክሩበትና የቤት ስራዎቻቸውን የሚሰሩበት ሁኔታ ያልተመቻቸ መሆኑ፣ በ2006 ዓ.ም ወደ 27 የሚሆኑ ሞጅሎች ታትመው/ተባዝተው/ በቤተመጽሐፍት የተቀመጡ ቢሆንም በተማሪዎች ወጪ ተደርገው አገልግሎት አለመዋላቸው፣ በቤተመጽሐፍቱ ውስጥ ለተማሪዎች ከመፃህፍት ያጡትን መረጃ እና ተጨማሪ ዕውቀት እንዲያገኙ ሊያስችላቸው የሚያስችል የኢንተርኔት አገልግሎት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ እና እንዲሁም ከዲፕርትመንት ኃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለተማሪዎች ስልጠና የሚሰጥበት እና የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት መሳሪያዎች የተሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ

85. ተማሪዎች ስልጠና በሚወስዱበት ጊዜም ሆነ የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ሊሟሉ ይገባል፡፡

86. በኦዲቱ ወቅት ተማሪዎች ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ክፍሎች ውስጥ የተግባር መለማመጃ ማሽኖች በአብዛኞቹ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ ለምሳሌ በምግብ ዝግጅት የተግባር ክፍል/ኪችን/ ውስጥ ካሉት የተግባር መለማመጃ ማሽኖች ውስጥ ሰባት (7) ማሽኖች (dry food storage area, perseble food storage area እና ሌሎች አምስቶች የመሳሰሉት) የተበላሹ እና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን፣ አብዛኞቹ ማሽኖች ተቋሙ ሲመሰረት /ከ40 ዓመታት በፊት/ ጀምሮ የነበሩ መሆናቸውና በወቅቱ የነበረው የተማሪዎች ቁጥር 70 እና 90 ሲሆን በ2005 ዓ.ም ከተቀበለው የተማሪ ብዛት 945 ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ በጣም ሰፊ መሆኑን የተማሪው ቁጥር ሲጨምር የማሽኖች ቁጥር ያልጨመረ መሆኑ፤ እንዲሁም አሁን ያሉት ማሽኖችም በከፊል ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ /ሲንኩ የሚያፈስ፣ ውሃ ማሞቂያው የማይሰራ፣ የጋዝ ምድጃው የሚያፈስ፣ ባኔማሪዬ /የምግብ ማቆያ/ ወርሚንግ ቴብል፣ የማቀዝቀዣ ክፍሉ.... / መኖራቸው በተጨማሪ ተማሪዎች የምግብ ማብሰል በኪችን የተግባር ልምምድ ካደረጉ በኋላ የሚታጠቡበት መታጠቢያ እና ልብስ መቀየሪያ ክፍል የሌላቸው መሆኑን እና የመስተንግዶ ስልጠና የሚያደርጉበት ክፍል ወንበሮች የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው መሆኑን ፣

87. እንዲሁም በዋናው ግቢ ለሚማሩ ተማሪዎች ተብሎ የተሰራ መጸዳጃ ክፍል የሌለ ሲሆን በገነት ሆቴል ለሚማሩ ተማሪዎች አራት መጸዳጃ ክፍሎች ቢኖሩም ንፅህና የሌላቸው መሆናቸውን፣

ማዕከሉ ሁለት መምህራንን በአየር መንገድ የቲኬቲንግ ስልጠና ቢወስዱም ስልጠናውን በተግባር ለማዋል የሚያስችል ሶፍትዌር ባለመኖሩ የተግባሩን ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚሰጥ ንድፈ ሃሳብ ብቻ አሰልጥነው እንዲወጡ ማድረጉ እና የማሰልጠኛ ኮምፒውተሮች የተገዙ ቢሆንም አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑን ፣

<u>ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎች የተከናወኑ መሆኑን በተመለከተ</u>

88. ማእከሉ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ዕድገትና ልማት ጠቃሚና ችግር ፈች የሆኑ የተለያዩ ጥናትና ምርምር ሊያከናውን እና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያስተላለፍ ይገባል፡፡

89. ይሁን እንጂ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ስትራቴጂክ ዕቅድ/ከ2003-2007/ እና ማዕከሉ በ2005 ዓ ዓመታዊ ዕቅድ ላይ አስር የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማጥናትና በማሳተም ለሚመለከተው አካል/ለባለድርሻ/ ማስተላለፍ በሚል በእቅድ የተያዘ ቢሆንም የጥናትና ምርምር ስራዎች ያልተከናወኑ መሆኑን፤ እንዲሁም በሸራተን አዲስ በ2004 እና በ2005 ዓ.ም ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ ከተውጣጡ ባለሙያዎች በሆቴሎችና በቱሪዝም ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ የተጠኑ ጥናቶች ቢቀርቡም ማዕከሉ የተገኙ ችግሮችን እና ጠቃሚ ተሞክሮችን በማዘጋጀትና በማሳተም ለባለድርሻ አካላት ያላሰራጨ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ለተማሪዎች በስልጠና ወቅት የክፍለ ጊዜ ብክነት እንዳይኖርና የስልጠና አሰጣጥ ሂደትን መቆጣጠሪያ ስርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣</u>

90. በማዕከሉ የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ የክፍለ ጊዜ ብክነት እንዳይኖር እና ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ ወደ ተለያዩ የሆቴልም ሆነ የቱሪስት አገልግሎት መስጫ ተቋም በሚሄዱበት

ወቅት ማዕከሉ የስልጠና ሂደቱንም ሆነ የተግባር ልምምዱን ክትትልም ሆነ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለው ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

91. ሆኖም ለተማሪዎች ስልጠና የሚሰጠው በዋና ማዕከሉ ግቢ በሚገኙ ሁለት (2) የቲዎሪ መስጫ ክፍሎች እና በገነት ሆቴል ግቢ በሚገኙ በጊዜያዊነት በቆርቆሮ በተሰሩ ስምንት(8) ክፍሎች እና የሆቴልም ሆነ የቱሪዝም ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት አራት(4) ክፍሎች ናቸው፡፡ በገነት ሆቴል በሚገኙ ስምንት/8/ ክፍሎች ከዋናው ግቢ የሚርቁ በመሆናቸው በእነዚህ ክፍሎች አስተማሪዎች በሚቀሩበት ጊዜ በግቢው መከታተያ እና መቆጣጠሪያ ስርዓት አለመዘርጋቱን እና ተማሪዎችም የክፍለ ጊዜ ብክነት እያጋጠማቸው ተገቢውን ስልጠና የማያገኙ መሆኑን፣ በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከሞሉ ተማሪዎች እና መጠይቅ ከቀረበላቸው የዲፓርትመንት ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. በማዕከሉ የንድፈ ሃሳብ ስልጠና ሰላሳ በመቶ (30%) የተግባር ልምምድ ሰባ በመቶ (70%) ድርሻ የሚይዝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ለማድረግ በተለያዩ ሆቴሎችና የቱሪዝም አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሚሄዱበት ጊዜ የተግባር ልምምዱ በሚፈለገው ደረጃ እየተከናወነ ስለመሆኑ የክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት በማዕከሉ ያልተዘረጋ መሆኑን፣ እንዲሁም በልምምዱ ወቅት ለሚያጋጥማቸውም ችግር ድጋፍ የማያገኙ መሆኑን እና የተግባር ልምምዱን በብቃት ሳያከናውኑ እንደሚጨርሱ በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከሞሉ ተማሪዎች እና መጠይቅ ከቀረበላቸው የዲፓርትመንት ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

በማዕከሉ ለተማሪዎች የሚሰጥ የኪስ ገንዘብ በወቅቱ የሚደርሳቸው ስለመሆኑ

93. በማዕከሉ በመደበኛ ክፍለ ጊዜ ለሚማሩ ተማሪዎች በመንግስት የሚሰጠው የኪስ ገንዘብ በወቅቱ ሊደርሳቸውና ለሌሎች የመንግስት ተቋማት ተጨማሪ የተደረገውን ብር 90 ለማዕከሉ ተማሪዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡

94. ሆኖም በማዕከሉ ለሚማሩ መደበኛ ተማሪዎች ለአንድ ተማሪ የሚሰጠው የኪስ ገንዘብ በወር ብር 330 ሲሆን መንግስት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ለሌሎች የትምህርት ተቋማት ተጨማሪ በማድረግ ወደ ብር 420 ያደገ ሲሆን ለተቋሙ ተማሪዎች ግን ይህንን መሠረት በማድረግ ያልተጨመረ መሆኑ፣ የሚሰጠው የኪስ ገንዘብም በወቅቱ የማይደርሳቸው መሆኑን ይህም በአብዛኛው በማዕከሉ የሚማሩ ተማሪዎች ከክልል የሚመጡና ማዕከሉ ማደሪያ ክፍል የማይሰጣቸው በመሆኑ ከቤት ኪራይ ጀምሮ ያለውን ወጪ የማይሸፍን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኑሮን ከባድ ያደረገውና ለመማር አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ይህንንም ለመሸፈን ቤት የሚቀንስበት በመፈለግ ራቅ ያለ አካባቢ ስንሄድ ማዕከሉ የሚገኘው መሃል ከተማ በመሆኑ ለትራንስፖርት እንግልት መዳረግ፣ ሴቶች እራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጥ ስራ መስራት፣ በትርፍ ሰዓት ስራ ለመስራት ሲታሰብ ከትምህርት ጋር በመጋጨት ትምህርቱን ትኩረት ሰጥቶ ለመማር አለመቻል ለመሳሰሉት ችግሮች ያጋለጣቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ለማዕከሉ አስተማሪዎች የስራ መዘርዝር የሚደርስ መሆኑን በተመለከተ

95. ማዕከሉ በስሩ ለሚገኙ ሠራተኞች የስራ መዘርዝር በማዘጋጀትና በመስጠት ስራቸውን በወቅቱ እንዲሰሩ ማድረግ ይገባዋል፡፡

96. በማዕከሉ በስሩ ለሚሰሩ ሰራተኞችም ሆነ ለተማሪዎች የሚሆን የስነ ምግባር መመሪያ ሊያዘጋጅና ሊተገብር ወይም የስራ

መዘርዝር(Job discribtion) በማዘጋጀት ለሰራተኞች ሊያደርስ ይገባል፡፡

97. ሆኖም ማዕከሉ በስሩ ለሚገኙ አስተዳደር ሰራተኞች የስራ መዘርዝር እያዘጋጀ የሚሰጥ ቢሆንም ለአስተማሪዎች ወይም ለአካዳሚክ ክፍሎች ተዘጋጅቶ ያልተሰጣቸውና ለተማሪዎችም አዲስ ሲገቡ የመግቢያ ገለፃ (orientation) ብቻ የሚደረግላቸው ቢሆንም በፅሁፍ የማይደርሳቸው መሆኑ

<u>በማዕከሉ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ሞዴል ሆቴል መኖሩን በተመለከተ</u>

98. ማዕከሉ ሞዴል ሆቴል በመገንባት ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ሊያደርጉበትና ሊቆጣጠረው ይገባል፡፡

99. ማዕከሉ ከነሐሴ 08/1989 ዓ.ም ጀምሮ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ አማካይነት በራስ ሆቴሎች አስተዳደር ድርጅት ስር የነበረው የገነት ሆቴል ድርጅትን ለሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛነት እንዲውል የተወሰነ ሲሆን በዚሁ መሠረት ማዕከሉ በገነት ሆቴል ታችኛው ግቢ ባለ ሶስት(3) ኮከብ ሞዴል ሆቴል ለመገንባትና ለመቆጣጠር የታሰበ ቢሆንም የሞዴል ሆቴል ግንባታ ስራ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

100. ይኸውም ማዕከሉ የገነት ሆቴል ድርጅትን ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ የተረከበና ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ ባክቴክ በተባለ አማካሪ መሐንዲስ ድርጅት የሞዴል ሆቴል ዲዛይን ለማዘጋጀት ከማዕከሉ ጋር ውል በመዋዋል ጥናት ተዘጋጅቶ የቀረበ እና እስከ 1993 ዓ.ም. በተጠናው የዲዛይን ጥናት መሰረት በወቅቱ በነበሩ አመራሮች የግንባታ ስራዎች ሳይሰሩ አራት ዓመት በማስቆጠሩ ከባክቴክ አማካሪ ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ እና የሞዴል

ሆቴል ስራው (ግንባታው) ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተጀመረ መሆኑ ፣

<u>በገነት ሆቴል የሚገኙ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያ ክፍሎች ለመለወጥ የሚደረግ የዕድሳት ስራን በተመለከተ፣</u>

101. ሰልጣኞች በተመቻቸ ሁኔታ ስልጠና እንዲያገኙ በገነት ሆቴል የሚገኙ የመኝታ ክፍሎች ወደ ማስተማሪያ፣ ሰርቶማሳያና ወደቢሮነት ለመቀየር የተጀመረው የግንባታ ሂደት በማፋጠን ተማሪዎች በተመቻቸ ሁኔታ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ በ1998 ዓ.ም ጊዲዮን ደመቀ የተባለ አማካሪ መሐንዲስ በገነት ሆቴል የሚገኙ 104 የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማሰልጠኛና የተግባር መለማመጃ ክፍሎች ለመቀየር የዲዛይን ሥራን ጨረታ በማሸነፍ የዲዛይን ጥናት በማካሄድ ዲዛይን ሰርቶ ያቀረበ ሲሆን በዲዛይኑ ላይ በክለሳ ወቅት አስፈላጊ የሆነ የብረት አይነት በአግባቡ አለመጠቀሱን በሬንቦ አርክቴክቸር ተቆጣጣሪ መሐንዲስ በመገለፁና በዚሁ መሠረት ጌዲዮን ደመቀ ተቋራጭ አሟልቶ ማቅረብ ባለመቻሉ ለዚህም ብር 86,250 የተከፈለው መሆኑን ዲዛይኑም ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ መሆኑን፣ ከማዕከሉ እና ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ከተፃፉ ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. በመቀጠልም በ2000 ዓ.ም. የግንባታ ስራውን ለመቆጣጠር በጨረታ ያሸነፈው ሬይንቦ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ካሸነፈበት ዋጋ ከ25 በመቶ ባልበለጠ ዋጋ ስትራክቸራል ዲዛይኑን ያለጨረታ እንዲሰራ መደረጉ፣ ሬይንቦም የዲዛይን ጥናቱን በማዘጋጀት ያቀረበ ሲሆን ትክክለኛነቱ ሳይገመገም(ሳይጣራ) ለዚሁ ሥራ ብር 237,950 የተከፈለው መሆኑን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. በተጨማሪም በ2001 ዓ.ም ሬንቦ አርክቴክቸር ለሁለተኛ ጊዜ ባዘጋጀው ዲዛይን መሰረት ሳሙኤል ሣህለማርያም ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት የግንባታ ሥራውን ለመስራት የጨረታ ኮሚቴ ውሳኔ ቃለ ጉባኤ በስተቀር ሌሎች ጨረታውን የሚመለከቱ ማስረጃዎቸው እና ውል የተዋዋለበት ሰነድ ለኦዲት መቅረብ አለመቻሉና እንዲሁም ተቋራጩ የዕድሳት ሥራውን ከጀመረ እና ብር 4,177,119 ከተከፈለው በኃላ ዲዛይኑ ችግር ያለበት መሆኑን በመግለጹ ከሰኔ 22/2003 ዓ.ም.ጀምሮ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ከተቋራጩ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከማዕከሉ ውሉ እንደተቋረጠ ከተጻፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

105. እንዲሁም በ2002 ዓ.ም ለዚሁ የግንባታ ዕድሳት ስራ ለዲዛይን ሥራው በውስን ጨረታ የተቀጠረው አማካሪ ኤምኤች ኢንጅነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ለሶስተኛ ጊዜ የዲዛይን ሥራውን እንዲያከናውን የተደረገ መሆኑን እና ለዚሁ የዲዛይን ሥራው የኮንትራት ውል ስምምነት ለኦዲት ቡዱኑ ማቅረብ አለመቻሉ፣ ለዚሁ የዲዛይን ስራ ብር 267,882 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን እና የተፈፀመው ክፍያ በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ አለመቻሉ በኦዲት ወቅት ከማዕከሉ ከተጻፉ ደብዳቤዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

106. በተጨማሪ በኤም ኤች ኢንጅነሪግ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ለሶስተኛ ጊዜ ባቀረበው ዲዛይን መሰረት ለግንባታ ሥራው የተጠየቀው ዋጋ ከብር 10,318,719 ወደ 23,503,293 በ127.8% ከፍ በማለቱ እና ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅ ሆኖ በመገኘቱ ከሳሙኤል ሣህለ ማርያም የስራ ተቋራጭ ጋር የነበረው ውል ሰኔ 22/2003 ዓ.ም. ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑን ከማዕከሉ ከተፃፈ ደብዳቤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

107. በአጠቃላይ የኦዲት ቡድኑ ተጀምሮ የተቋረጠውን የግንባታ ስራውን በመስክ በተመለከተበት ወቅት በሮችና መስኮቶች

የሌሉት፣ ኮርኒሶች የተነቃቀሉ፣ የመታጠቢያ ቤት ዕቃዎች በሜዳ ላይ የተጣሉ መሆናቸው፣ በግቢው ውስጥ እና በግንባታው ቦታ ሳርና የተለያዩ እፅዋት በቅለውበት መታየታቸው በአጠቃላይ ለዕድሳት ስራው ከተለያዩ ወጪዎች ጋር ከ4 ሚሊዮን ብር በላይ የወጣበት መሆኑን እና ውጤታማ አለመሆኑን በተደረገ የመስክ ምልከታና ከክፍያ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የማዕከሉ የትምህርት መስጫ ክፍሎችን በተመለከተ</u>

108. የማዕከሉ የቱሪዝም እና የሆቴል የትምህርት ዘርፍ ማሰልጠኛ ክፍሎች ከተማሪዎች ቁጥር አንጻር በቂ እና የተሟላ እንዲሁም ለመማር ማስተማር ሂደቱ አመቺ ሊሆን ይገባል፡፡

109. ይሁን እንጂ ተማሪዎች ስልጠና የሚወስዱበት በገነት ሆቴል በሚገኙ ለጊዜው በተሰሩ ስምንት (8) የማሰልጠኛ ክፍሎች ሲሆን ክፍሎችም ጠባብና ከቆርቆሮ የተሰሩ መሆኑ፣ የአየር ሁኔታው ሙቀት ሲሆን በጣም የሚሞቁ፣ አየሩ ቀዝቃዛ ሲሆንም በጣም የሚቀዘቅዙ በመሆናቸው፣ ስልጠናው ምቹ ባልሆነ ሁኔታ እየተካሄደ የሚገኝ በመሆኑ ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎች በሙቀት ስለሚጨናነቁ የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ትኩረት እንዳይሰጡ ያደረገ መሆኑን በናሙና ተመርጠው መጠይቅ ከተደረገላቸው ተማሪዎችና በመስክ ጉብኝት ወቅት በተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በገነት ሆቴል አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ 104 የመኝታ ክፍሎች በዕድሳት ወቅት የንብረት ርክክብን በተመለከተ</u>

110. በገነት ሆቴል አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ 104 የመኝታ ክፍሎች ወደ ማስተማሪያና ሰርቶ ማሳያነት ለመቀየር የዕድሳት ስራ በሚሰራበት ወቅት በተገቢው መንገድ ርክክብ ሊደረግባቸውና በህግ እና ደንብ ተከትለው አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ ይገባል፡፡

111. ይሁን እንጂ በፊት የነበሩት 104 የመኝታ ክፍሎች በፈረሱበት ወቅት የክፍሎቹ በሮች እና መስኮቶች እንዲሁም ሌሎች ያገለገሉ ዕቃዎችን የእድሳት ስራውን ሲሰራ ከነበረው የሥራ ተቋራጭ ሳሙኤል ሳህለማርያም ጋር ሆቴሉ ርክክብ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተደረገ የመስክ ጉብኝት እና ከገነት ሆቴል ስራ አስኪያጅ ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት እና ለመፍታት የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣</u>

112. ማዕከሉ በሚሰጠው የስልጠና አገልግሎት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመለየትና ለችግሮቹም መፍትሄ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ ከክልሎችም ሆነ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

113. ሆኖም ማዕከሉ በሆቴልና ቱሪዝም የሚታዩ ችግሮች ላይ ለመነጋገር በሸራተን አዲስ ከተለያዩ ዩኒቨርስቲ ከተውጣጡ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በተዘጋጀበት ወቅት የተነሱ ችግሮች እና ጠቃሚ ተሞክሮዎችን በመለየት በህትመት መልክ ያላዘጋጀ እና ለባለድርሻ አካላት ያላሰራጨ መሆኑ፣ ለአስጎብኚ እና ለሆቴል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተለያዩ ስልጠናዎች ከተሰጡ በኋላ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት የተሻሻለ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት የሚሰራበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን፣ ከ2004 ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የማዕከሉ የመረጃ አያያዝ የተጠናከረ መሆኑን በተመለከተ</u>

114. በማዕከሉ የሚሰለጥኑ ተማሪዎችን እና አስተማሪዎችን ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ፣ በገነት ሆቴል ለሚሰራው የዕድሳት ስራ ላይ

የተመረጡ የተሳተፉ አማካሪ መሀንዲሶችን እና ተቋራጮችን የሥራ ክንውን የሚገልጹ መረጃዎችን የመሳሰሉት በማዕከሉ በተደራጀ ሁኔታ እና ስርዓት ባለው መልኩ ሊያዙ ይገባል፡፡

115. ሆኖም በማዕከሉ አዲስ ተማሪዎች ምዝገባን በተመለከተ ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም (TVET) በየዓመቱ የሚላኩ የመግቢያ መስፈርት፣ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች ከ2003-2005 ዓ.ም የተመረጡበት የምልመላ መስፈርት(ውጤት)፣ በማዕከሉ የተዘጋጀ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ/ከ2003-2005/፣ የ2003 በጀት ዓመት እና የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድ፣ የባክቴክ አማካሪ መሃንዲስ ለአገልግሎቱ ክፍያ የተፈጸመበት መረጃ፣ የኤም. ኤች. አማካሪ መሃንዲስ ለዲዛይን ጥናት የተፈራረመው የውል ስምምነት ማስረጃ፣ የተቋራጭ ሳሙኤል ሳህለማርያም ለግንባታ ሥራው ከማዕከሉ ጋር የተፈራረመው የውል ማስረጃ እና የተሟላ ጨረታ መረጃዎች፣ የመሳሰሉት መረጃዎች በማዕከሉ ስርዓት ባለው መልኩ ያልተያዙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት መረጃ እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቅረቡ ምክንያት መሆኑን፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ማዕከሉ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በየበጀት ዓመቱ ያልተጋነነ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በዕቅዱ መሠረት ሊተገብር ይገባል፡፡
- በማዕከሉ አዲስ እየተዘጋጁና እየተባዙ በቤተ መጽሐፍ (ላይብረሪ) ባልተቀመጡ የሞጅል ዓይነቶች ላይም በተጠናከረ ሁኔታ ሊቀጥል እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለስልጠና የሚያገለግሉና በገበያ ላይ ብዙም የማይገኙ መጻህፍቶች ማዕከሉ በኮፒ በማባዛትና በላይብረሪ

በማስቀመጥ ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች በመጻህፍቱ ሊገለገሉ የሚችሉ አካላት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

- በማዕከሉ የሚሰጠው የስልጠና ሂደት 30% በንድፈ ሃሳብ እና 70% በተግባር በመሆኑና በአብዛኛውን ተማሪዎች ዕውቀት የሚሸምቱት በተግባር ልምምድ ወቅት በመሆኑ የተግባር ልምምድ በሚያደርጉበት ክፍል የሚገኙና የተበላሹ ዕቃዎች በማሰራትም ሆነ አዲስ በመግዛት የግብዓት ችግር ሊወገድና ሊሟሉ ይገባል፡፡
- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በመለየት ለዘርፉ መሻሻል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማጥናት እና በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ሊያደርስ ይገባል፡፡
- በስልጠና አሰጣጥ ላይ የሚከሰቱ የክፍለ ጊዜ ብክነትን ለመቆጣጠርም ሆነ ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ ወደ ተለያዩ ሆቴሎችና የቱሪስት መዳረሻ በሚሄዱበት ወቅት ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለማዕከሉ በመንግስት የሚሰጠው የተማሪዎች የኪስ ገንዘብ በወቅቱ ሊደርስና ለሌሎች የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተደረገው ጭማሪ /ብር90/ ማዕከሉ መንግስትን በማስፈቀድ ለማዕከሉ ተማሪዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ማዕከሉ ለተግባር መለማመጃ አገልግሎት የሚሆን ሞዴል ሆቴልን በመገንባት ሊቆጣጠርና ተማሪዎች የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- በገነት ሆቴል የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያነት ለመለወጥ የተጀመረው የዕድሳት ስራ በመቀጠልና በፍጥነት

እንዲጠናቀቅ በማድረግ ማዕከሉ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራና ተማሪዎችም ሆኑ አስተማሪዎች በተመቻቸ ሁኔታ የስልጠና አሰጣጥ ሂደት የሚካሄድበት ሁኔታ ሊያፋጥን ይገባል፡፡

- በገነት ሆቴል ሲያገለግሉ የነበሩ የመኝታ ክፍሎችን ወደ ማስተማሪያ ክፍልነት ለመቀየር የተጀመረው የዕድሳት ስራ ወቅት ከፈረሱ ክፍሎች የተወገዱ ንብረቶች (ዕቃዎች) ርክክብ ሊደረግባቸውና በተገቢው መንገድ ሊወገዱ ይገባል፡፡
- በማዕከሉ የሚደረጉ ማንኛውም ለግንባታና የዕድሳት ስራ ወጪ የሚደረጉ ሂሳቦችን/ገንዘብ/ ማዕከሉ ሊቆጣጠርና የሚወጣው ወጪ ጥቅም ማስገኘቱን መገምገምና መቆጣጠር አለበት፡፡
- ማዕከሉ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመለየት፣ ለመፍታት እንዲሁም የልምድ ተሞክሮ ለመለዋወጥ የሚያመችና ወጥ የሆነ የመወያያ መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
- በማዕከሉ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች ተመልምለው የመጡበትን ሁኔታ የሚገልጽ ማስረጃ በእያንዳንዱ ተማሪ ማህደር ሊኖር፣ የተለያዩ ከቴክኒክ እና ሙያ(TEVT) የሚላኩ መስፈርቶች፣ በግንባታ ስራ የሚሳተፉ አማካሪዎችና ተቋራጮች የሚመለከቱ የጨረታ ዶክመንቶች /መረጃዎች/ እንዲሁም የውል ስምምነቶች የመሳሰሉት መረጃዎች በማዕከሉ የስልጠና አሰጣጡን የሚያፋጥኑ መረጃዎች ሊኖሩ እና መረጃውን ሊኖሩና በተደራጀ እና ስርዓት ባለው መልኩ ሊቀመጡ እንደሚገባ፡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

11.5 የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፋፊና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚደረገው ሽግግር አፈጻጸም በተመለከተ የኦዲት ግኝቶች

<u>የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፋያና ማሻሻያ እና ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው የሽግግር ተስማሚ የቴክኖሎጂ መረጣና ዝግጅትን በተመለከተ</u>

116. የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው ሽግግር ተስማሚ የቴክኖሎጂ መረጣ ለማካሄድ የሚያስችል መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሚደረገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ፕሮጀክት ዝርዝር የግንባታ ዲዛይን ጥናት ሊከናውንና በጥናቱም መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

117. ለዲጂታል ሽግግሩ ከሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል በማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ Ultra High Frequency (UHF) ፍሪክዌንሲ ሬንጅ የተሰሩ Dual cast (አናሎግ እና ዲጂታል ሲግናሎችን እያፈራረቀ የማሰራጨት አቅም ያላቸው) (73) ሰባ ሦስት የቴሌቪዥን ትራንስሚተሮች ተከላቸው የተጠናቀቀ ቢሆንም፤ ኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) የማሻሻያ እና ማስፋፊያ ፕሮጀክቱን ከማከናወኑ በፊት ይጠቀምባቸው ከነበሩት ሠላሳ አንድ (31) ትራንስሚተሮች በVery High Frequency (VHF) ሬንጅ ከሚሰሩት ውስጥ አምስቱ (5) የማሻሻያ ስራ ተከነውኖባቸው (UHF) አገልጎሎት መስጠት እንዲችሉ የተደረጉ ተደርዋል፡፡

118. ነገር ግን በድሬዳዋ የቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ ጽ/ቤትና የማሰራጫ ትራንስሜሽን የተገነባበት ቦታ የሲሚንቶ ፋብሪካ

የጥሬ ዕቃ ማመረቻ ክልል ውስጥ መሆኑን፣ የጣቢያው መስታዎቶች ከመሰባበራቸውም ባሻገር የጽ/ቤቱ ግድግዳ በመሰነጣጠቅ ዝናብ እያስገባ በማሽኖች ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን፣ የደሴ የቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያ የተገነባበት ቦታ ለመድረስ የሚያስችል መንገድ አለመሰራቱ፤ የጮቄ ተራራ ማሰራጫ ጣቢያ የተገነባበት ቦታ ከደብረ ማርቆስ ከተማ በ50 ኪሎ ሜትር የሚርቅ መሆኑና የማብራት አገልግሎት የሌለው በመሆኑ ለጀኔሬተር የሚያስፈልገው ነዳጅ ለማጓጓዝ እና ብልሽት በሚከሰትበት ወቅት የጥገና ባለሞያዎች (ቴክኒሺያኖችን) ወደ ቦታው ሂደው ችግሩ በወቅቱ እንዲስተካካል ለማድረግ የሚያስችል የተመደበ የትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖሩ::

119. የዲጂታላይዜሽን ሽግግር ለማድረግ ኮርፖሬሽኑን (በቀድሞው ኢሬቴድ) 2003-2007 የስትራቴጂክ እቅድ የተያዘና በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በየካቲት 30 ቀን 2003 ዓ.ም. የተቋቋመው ብሔራዊ ስትሪንግ ኮሚቴ ድርሻ ኤሬቴድ እያጠና ለሚያቀርባቸው የፖሊሲና የአቅጣጫ ጉዳዮች እንዲወስን ለማድረግ ቢቋቋምም ሽግግሩ ተግባራዊ ያልሆነ መሆኑ፣

<u>የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ መኖሩን በተመለከተ</u>

120. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ለማስፋፊያ ፕሮጀክቱ የቴክኖሎጂ ተከላ፤ የዕቃ አቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታና የኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) የመንግስትና የድርጅቱን የፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያን መሰረት አድርጎ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

121. ኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኤሬቴድ) የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ለፕሮጀክቱ የቴክኖሎጂ ተከላ፤ የዕቃ አቅርቦት፤ የሲቪል ግንባታና

የኮሚሽኒግ ሥራ ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በኮርፖሬሽኑ ያልተዘጋጀ መሆኑን ታውቋል፡፡

<u>የፕሮጀክት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ</u>

122. አገር አቀፍ የራዲዮና የቴሌቭዥን የማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክት በተቀመጠለት ጊዜ በዕቅዱ መሰረት ተጠናቆ ሥራ ሊጀምር ይገባዋል፡፡

123. በ2001 ዓ.ም አገር አቀፍ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ለማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የመሣሪያ ግዥውና የህንፃ ግንባታው ተጠናቆ ማሠራጫ መሣሪያዎቹን በመትከል ሥርጭት ይጀምራል የሚል ለፕሮጀክቱ በፀደቀ የጥናት ፕሮፖዛል ላይ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም በማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክት ጥናት ፕሮፖዛል እና በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ትራንስሚተሮች ተከላ ሥራ እስከ 2004 ዓ.ም ተግባራዊ በማድረግ የሬዲዮን ከ75% ወደ 95% የቴሌቪዥን ከ55% ወደ 86% ሽፋን በላይ ማድረስ እና የዲጂታል ስርጭት በየካቲት 2005 ዓ.ም ይጀምራል የሚል ቢሆንም አፈጻጸሙ ግን በዕቅዱ ከተጠቀሰው የጽ/ቤት ግንባታው በሦስት ዓመት፤ የዲጂታል ስርጭት ሽግግሩ ደግሞ ሁለት ዓመት የዘገየ መሆኑ እና በኦዲቱ ወቅትም የአንድ (ደርባ) ማሰራጫ ጣቢያ የትራንስሚሽንና የታወር ግንባታ ያልተጀመረ መሆኑ::

124. የዲጂታል መቀበያ መሳሪያዎች በዋነኝነት ሴት-ቶፕ ቦክስ፣ ዲጂታል ቴሌቪዥን (DTV) እና UHF አንቴና ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን እና የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች ለዲጂታል ሥርጭት ወደ DVB- T2 (Digital video Broadcasting Terrestrial 2nd generation) የመቀየር ሥራ፤ የSet Top Box (የዲጂታል ቴሌቪዥን ትራንስሚሽንን ለማየት ከቴሌቪዥን ጋር የሚገጠመው ዲኮደር)፤ የትራንስሚተር

አፕግሬድ (Transmitter Up Grading) እና የሄድ ኢንድ (Head End) ሥራ በተመለከተ በ2005 ዓ.ም መጠናቀቅ ሲገባቸው ስራው ያልተጀመረ መሆኑ::

125. ለዲጂታላይዜሽን የሚያገለግለው UHF የቴሌቪዥን አንቴናዎች በሀገር ውስጥ ገበያ በብዛት አለመኖርና ስለአንቴናው አስፈላጊነት ለህብረተሰቡ አስፈላጊውን ግንዛቤ የመፍጠር ስራ አለመከናወኑ ፡፡

126. የሬድዮና የቴሌቪዥን ማስፋፋና ማሻሻያ ፕሮጀክቶቹ ስራ በጥናት ላይ የተመሰረተና በተመደበለት በጀትና በኮንትራት ውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ

127. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው ሽግግር የተዘጋጀው ፕሮጀክት ስራን ፕሮጀክቱን የሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ በኮንትራት ውሉ በተቀመጠለት የገንዘብ መጠን መሰረት ማከናወን እና ተፈጻሚ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

128. የተቀናጀ የክትትልና ቁጥጥር የአሰራርና አደረጃጀት ሥርዓት በመፍጠር የፅ/ቤት የግንባታውን ሥራ በሁለት ዙር በሦስት ዓመታት ለመጀመሪያው ዙር (1st phase) የካቲት 2001 - ሐምሌ 2003 ዓ.ም ሲሆን ለሁለተኛው ዙር (2nd phase) ከጥቅምት 2002 - ሰኔ 2004 ዓ.ም ጊዜ ውስጥ የፅ/ቤት የግንባታውን በማጠናቀቅ ወደ ቴክኖሎጂ ገጠማው ይገባል የሚል ቢሆንም፤ በተግባር ግን የፅ/ቤት ግንባታው ፕሮጀክት በኮንትራት ውሉ ከተቀመጠው ከሁለት ዓመት በላይ የወሰደ መሆኑ፡፡

129. ከአናሎግ ወደ ዲጂታል ለሚያደርገው የሽግግር ስራ በሁለቱም ዙር (1st phase እና 2nd phase) የትራንስሚሽን ቴክኖሎጂ ገጠማው፤ ዲጂታል ስትዲዮና ተጓዳኝ ስራዎች ብቻ እንጂ ሌሎች

ዋና ዋና ወጪዎች (የመርከብ፣ የአውሮፕላን፣ ከወደብ ወደ መሃል አገር ለመጓጓዝ የማጓጓዣ፣ ለጉምሩክ ቀረጥ፣ የአማካሪ ክፍያ...ወዘተ) ወጪዎችን ባለመካተታቸው በፕሮጀክቱ ጥናቱ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ብር 642,096,007 (ስድስት መቶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ዘጠና ስድት ሺህ ሠባት ብር) 58% ወጪ የተደረገ መሆኑ

130. የፅ/ቤት ግንባታውን ሥራ በሁለትም ዙር በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በማጠናቀቅ ወደ ቴክኖሎጂ ገጠማው እንደሚገባ እንዳለበት እየታወቀ ጥቅምት 2002 ዓ.ም የሁለተኛው ዙር (2nd phase) የፅ/ቤት ግንባታውን ውል በተፈረመ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ የቴክኖሎጂውን ግባዓት አቅርቦትና የገጠማው ከሚያከናውነው የchina Poly group corporation Technologies Inc. ከተባለው ድርጅት ጋር የካቲት 2003 ዓ.ም የሁለተኛው ዙር (2nd phase) ውል ስምምነት ቢገባም በውል ስምምነቱ መሰረት አለመጠናቀቁ፡፡

<u>ለፕሮጀክቶች የስራ ተቋራጮችንና አማካሪ ድርጅቶችን መረጣ በተመለከተ</u>

131. ለማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክትን የግንባታ እና የቁጥጥር ሥራ ላይ የሚሳተፉትን ተቋራጮች ሆነ አማካሪዎች የአገልግሎት ግዢው ሲከናወን በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡ የአገልግሎት ግዢውን ያሸነፈው ድርጅትም ከኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) ጋር የኮንትራት ውል ሊገባና ሥራውም በውሉ መሠረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

132. ኮርፖሬሽኑ የቴክኖሎጂ ገጠማውን ሥራ ለማከናወን ብር 686,426,736.42 የሚያወጣ ስራን ከአንድ አቅራቢ ቻይና ፖሊ ቴክኖሎጂስ (china poly technologies inc.) ከተባለ

ድርጅት ጋር በሁለት ደረጃ (ፌዝ) ተከፍሎ ዋጋውም በድርድር እንዲሰራ መደረጉ ታውቋል፡፡ ነገር ግን ይህ ድርጅት የቴክኒክ ብቃቱ የተሟላ መሆኑና የመንግስት ድርጅት ስለሆነ የሚል የጨረታ ኮሚቴው ያቀረበው ድፍን ያለ ምክንያት በስተቀር በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 694/2001 አንቀጽ 52.2 መሰረት ከሌሎች ተለይቶ ለምን እንደተመረጠና ድርድር የማድረጊያ አትኩሮተ-ነጥቦች ዝርዝር ማስረጃ አለመቅረቡ፡፡

<u>የፕሮጀክት ማስፋፊያውንና የሽግግር ፕሮጄክቱን አፈጻጸም ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ</u>

133. ድርጅቱ ለማስፋፊያ ፕሮጀክት ጨረታውን ካሸነፈ ድርጅት ጋር ውል ሊዋዋል ይገባል፡፡ በውሉ ላይም ሥራው ተጠናቆ የማስረከቢያ ጊዜ፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ ጊዜ የፍተሽ ስነ ስርዓት እና ዋስትናን በተመለከተ ኃላፊነትንና ግዴታን በግልጽ ያስቀመጠ ሊሆን ይገባል፡፡ በግንባታ ሳይቶች ላይ ለሚኖሩ የጥራት ቁጥጥር፤ የዲዛይን መጣጣምና ሱፐርቪዥን ስራው በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት መከናወኑን በአማካሪ መሀንዲስ ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ የፕሮጄክቱን እንቅስቃሴ በየደረጃው ለመከታተል የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

134. በፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ዙር ጣቢያዎች ግንባታን በተመለከተ ከ19 ውስጥ የ16ቱ ጣቢያዎች አጠቃላይ ስራ ተጠናቆ ሐምሌ 2003 ዓ.ም የመጨረሻ ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን የሶስት ጣቢያዎች (ደሴ፣ ፊቼና ንፋስ መውጫ) ግንባታዎች ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቃቸው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ርክክብ አለመፈጸሙና በሦስት ዓመት የዘገየ መሆኑ፡፡

135. በፕሮጀክቱ ሁለተኛው ዙር እንዲገነቡ ከታቀዱ 58 የጣቢያዎች ግንባታዎች ከጥቅምት 2002 ዓ.ም እስከ ሰኔ 2004 ዓ.ም ተጠናቆ ርክክብ እንደሚፈጸም በኮንትራ ውሉ ቢቀመጥም፡፡ ከዚህ ውስጥ የ31 ጣቢያዎች ግንባታዎች ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቃቸው የጣቢያዎች ርክክብ ሳይከናወን ስራ የጀመሩና በሁለት ዓመት የዘገዩ መሆኑ፣

136. ተጠናቀው ርክክብ ከተፈጸመባቸው በ 8ኑ ማሰራጫ ጣቢያዎች መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት መስጠት ሳይችሉ የተበላሹ Generator፣ control unit፣ AC፤ AVR እና Exciter ሲሆኑ በተጨማሪም በ7ት ማሰራጫ ጣቢያዎች ላይ ደግሞ UPS የሚባለው መሳሪያዎች ተነቅለው ወደ ዋናው መ/ቤት መወሰዳቸው፣

137. ሁለተኛው ዙር የጽ/ቤት ህንፃ ግንባታ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ግምገማ የተከናወነው ቁፋሮ፤ ኮንክሪት ሙሌት እንዲሁም የግንባታ ግባዓቶችን በተመለከተ በድርጅቱ ማህንዲሶች ቁጥጥሩ የተከናወነ ሲሆን፤ የታወር ግንባታውን በተመለከተ ደግሞ የማቴሪያል አቅርቦትንም ሆነ ግንባታውን መሳሪያውን ለማቅረብና ለመትከል ባሸነፈው በራሱ በቻይናው ኮንትራክተር አማካኝነት እንዳተከናወነ፣ 32 ፕሮጀክቶች ደግሞ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ሙሉ ኃለፊነቱን ወስዶ እንዲሰራቸው የተደረገ መሆኑ፣

<u>የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ማዳረስንና አማራጭ ቻናሎችን መጀመር ተመለከተ</u>

138. የማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የፕሮግራም ስርጭት የአየር ሰዓት ውስንነትን ችግር ሊፈታ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቴሌቭዥን አማራጭ ቻናሎች ተከፍተው ሥራ ሊጀምሩ ይገባል፡፡

139. በማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ታሳቢ ተደርጐ በሁሉም ክልሎች የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች እንዲገነቡ፣ በድርጅቱ የሚታዩ ጉልህ የሆኑ ችግሮችን በተለይም የስርጭት አድማስ ውስንነት፣ የፕሮግራም ስርጭት ጥራት ጉድለትን ለመቅረፍ የሚል በኮርፖሬሽኑ (የቀድሞው ኢሬቴድ) ለፕሮጀክቱ በፀደቀ የጥናት ፕሮፖዛልና በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ተይዟል፡፡

140. በማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የ24 ሰዓት የሥርጭት ሽፋን ታሳቢ ተደርጐ በሁሉም ክልሎች የቴሌቪዥን ማሠራጫ ጣቢያዎች እንዲገነቡና ችግሩን እንዲቀረፍ የሚል ቢሆንም በ11 ማሰራጫ ጣቢያዎች (ጂንካ፣ ሀርገሌ፣ ፊቅ፣ ማጂ፣ ዲቾቶ፣ ጮቄ ተራራ፣ አዲረመፅ፣ ዋርደር፣ ቀብሪደሃር፣ አዳባ ዲንሾ፣ ጉባ እና ጐዴ የማሠራጫ ጣቢያዎች) በየሳምንቱ ከሰኞ እስከ አርብ ለ5፡00 ሰዓት እንዲሁም ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ለ10፡00 ሰዓት ብቻ ስርጭት እያከናወኑ መሆናቸው፡፡

141. በሀገርአቀፍ ደረጃ የተመረጠው DVB-T2 ስታንዳርድ 22 ፕሮግራም የማስተናገድ አቅሙ እና በሀገራችን አሁን ያሉትን የብሮድካስተሮች ብዛት ከግምት ውስጥ ሲገባ አንድ ሀገራዊ የጋራ ሄድ-ኢንድ (Head End) መጠቀም በ2005 ዓ.ም የዲጂታል ስርጭትን በማስጀመርና አሁን ያለውን የቴሌቪዥን ቻናል ብዛት ከስምንት (8) በላይ በማድረስ ለድርጅቱ፣ ለግል ተቋማትና ለክልል መንግስታት በቂ የአየር ሰዓት መመደብና አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ቋንቋዎች ማሣደግ የሚያስችል መሰረተ ልማት መገንባት የሚል ቢሆንም የቴሌቭዥን አማራጭ ቻናሎች አሁንም ድረስ ማሳደግ ያልተቻለ መሆኑ፡፡

ዘመናዊ አርካይቭ ስርዓትና ዳታቤዝ አደረጃጀትን በተመለከተ

142. በማስፋፊያ እና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ ዘመናዊ የኔትዎርክ አርካይቭና ኤዲቲንግ ስርዓት ሊዘረጋ፤ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ኦንላይን የሚተላለፉና የተላለፉ ዳታዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚያስቀምጥ ዳታ ቤዝ ሊገነባና የኮርፖሬሽን የፕሮዳክሽን ስራዎች ደህንነታቸው በመጠበቅ እንዲከማቹና በክምችት ክፍል የሚገኙ ግብዓቶች በቀላሉ የገቢ ምንጭና የፕሮዳክሽን ግብዓት ሊሆኑ በሚችሉበት ሁኔታ ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

143. ዘመናዊ የኔትዎርክ አርካይቭና ኤዲቲንግ ስርዓት በመዘርጋት የፕሮዳክሽን ስራዎች ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ በፍጥነትና በጥራት እንዲከናወኑ ማድረግ በክምችት ክፍላችን የሚገኙ ግባዓቶች በቀላሉ የገቢ ምንጭና የፕሮዳክሽን ግብዓት እንዲሆኑ ማስቻል የሚል በስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ የታቀደ ቢሆንም፤

144. የአርካይቭ ስርዓት ዲጂታላይዝ ማድረግ ስራ ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በጀት ዓመት በየዓመቱ ይተገበራል ተብሎ በዕቅድ ቢያዝም የትግበራው ስራ ግን እስከ ሰኔ 2006 ዓ.ም ያልተጀመረ መሆኑ፡፡

145. በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን የሚተላለፉና የተላለፉ ዳታዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚያስቀምጥ የመረጃ ቋት /Database/ በማዕከል ደረጃ ያልተዘጋጀና ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓት አለመኖሩን፤

146. በኮርፖሬሽኑ አርካይቭ ውስጥ ያሉ የማቴሪያሎች ወጪና ገቢ በሚደረጉበት ወቅት የሚደረገው ቁጥጥር የዘመኑ ቴክኖሎጂ የማይጠቀሙ በመሆኑ፣ ቁጥጥር ስራው ላይ በቂ የሰው ኃይል አለመመደቡ፣ የአርካይቭ ማቴሪያሎች እጅግ ብዛት ያላቸው ቢሆንም ተገቢ የሆነ የቁጥጥር ስልት አለመቀየሱ፣ እንዲሁም ድርጅቱ ከፍተኛ የድምፅና ምስል ክምችት ያለውና ሌሎች

ድርጅቶች የሌላቸው የፕሮዳክሽን ግብዓት ክምችት ያለው በመሆኑ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፡፡

<u>የምስል፤ የድምፅ ጥራትን በተመለከተ</u>

147. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የማስፋፊያና ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የፕሮግራም የምስልና የድምፅ ስርጭት ጥራትን በጠበቀ መልኩ ሊተገበር ይገባል፡፡ በኮርፖሬሽኑ የተዘጋጀው የምስልና የድምፅ ጥራት መቆጣጠሪያ መመሪያ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

148. የፕሮግራም ስርጭቱ በፕሮጀክት ጥናቱ እንደተቀመጠው የጥራት ደረጃ ላይ መድረስ ያልተቻለ መሆኑን፣ የቴሌቪዥንና የሬድዮ የስርጭት ድምፅ ጥራት ወጥነት የሌለው እና ድምፁም በትክክል አለመመጠን፣ አለመቆጣጠር ሲንክሮናይዜሽን አለመስራትና የድምፅ መቆራረጥ መኖሩ፡፡

ታውቋል፡፡

149. በመሆኑም

- ኮርፖሬሽኑ የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋትም ሆነ ለማሻሻል የገነባቸውም ሆነ የሚገነባቸው የመሰረተ ልማት አውታሮችና ሌሎች ግንባታዎች የሚሰሩበትን አካበቢዎች የተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና ቶሎ ቶሎ ሳይበላሹ አገልግሎት መስጠታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ሊያሰራቸውና ሊጠብቃቸው ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ በቀድሞው ኢሬቴድ የተዘጋጀውን እና የበላይ አመራር ለመስጠት የዲጂታላይዜሽን ትገበራ ስተሪንግ ኮሚቴ የተቋቋመለትን ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚደረገውን ሽግግር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ወደ ትግበራ የሚያስገባ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በመከለስ ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት የሚያቅዳቸውን ፕሮጀክቶቹን የቴክኖሎጂ ተከላ፣ የዕቃ አቅርቦት፣ የሲቪል ግንባታና የኮሚሽኒግ ሥራ የመሳሰሉትን ለመከታተልና ለማቆጣጠር የሚያስችል የፕሮጀክት ስራ አመራር መመሪያ (Project management manual) ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸውን ፕሮጀክቶች ሲቀርጽ ከፕሮጄክቱ ጋር የተያያዙ ሥራዎችና ወጪዎችን አስቀድሞበማጥናት፣ በመለየትና የሚከናወኑበትን የጊዜ ሠሌዳ ሊያቅድ እና አጠቃላይ የፕሮጄክቱ ወጪ ግምትን በማስቀመጥ ሥራዎቹ በተቀመጠላቸው ጊዜ በዕቅዱ መሰረት ተጠናቆ ሥራ የሚጀምሩበትን ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቱን ለማከናወን ኃላፊነት የወሰዱና የሚወስዱ የስራ ተቋራጮች በኮንትራት ውሉ በተቀመጠው የገንዘብ መጠን እና በታቀደው የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ማከናወናቸውን እየተከታተለ ግዴታቸውን በማይወጡት ላይ አስፈላጊውን የሕግ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ማናቸውንም በስሩ ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች የስራ ተቋራጭ አመራረጥ ላይ በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና ደንብን በመከተል ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ሊያከናውን፣ በድርድርም ሆነ ከአንድ አቅራቢ ግዥ ሲያከናውን ይህን ያደረገበትን ዝርዝር መስፈርት በግልጽ በማስቀመጥ ማከናወን ይኖርበታል፡፡
- በግንባታ ሳይቶች ላይ ለሚኖሩ የጥራት ቁጥጥር፣ የዲዛይን መጣጣምና ሱፐርቪዥን ስራው በተቀመጠለት መስፈርት

መሰረት መከናወኑን ሥራውን ለመስራት ኃላፊነት ከወሰደው የሥራ ተቋራጭ ገለልተኛ በሆነ አማካሪ (መሀንዲስ) ሊከናወን ይገባል፡፡

- ለሬድዮና ለቴሌቪዥን ማስፋፊና ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ተብለው ተገጥመው የነበሩ የተበላሹት በፍጥነት ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉይገባል፡፡ ከጣቢያዎቹ በተሌየ ምክንያት ተነቅለው የተወሰዱ መሳሪያዎቹም በፍጥነት ወደማሰራጫ ጣቢያዎቹ ሊመለሱና መጀመሪያ ለታለመላቸው እንዲውሉ ሊያደረግ ይገባል፡፡
- የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴ በየደረጃው ለመከታተል የሚያስችል ወጥ የሆነ የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡
- ኮርፖሬሽኑ የታቀደው ከአናሎግ ወደ ዲጂታል የሚደረገው ሽግግር እንዲፋጠን በማስደረግ ተጨማሪ አማራጭ ቻናሎች ሥራ እንዲጀምሩና የአየር ሰዓት እጥረት በመቅረፍ የአድማጩና የተመልካቹ ፍላጎትና ዕርካታን ሊያሳድግ የሚገባና የምስልና የድምፅ ስርጭት ጥራትን በጠበቀ መልኩ ሥርጭቶቹን የሚያከናውንበትን አሠራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- በፕሮጀክቱ ዘመናዊ የኔትዎርክ አርካይቭና ኤዲቲንግ ስርዓት በመዘርጋት የፕሮዳክሽን ስራዎች ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ መከማቸት፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ኦንላይን የሚተላለፉና የተላለፉ ዳታዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚያስቀምጥ ዳታ ቤዝ በማደራጀት በቀላሉ የፕሮዳክሽን ግብዓት፣ ለተጠቃሚዎች የሚደርስበት ስርዓት ሊዘረጋና ለኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ ሊሆኑ ይገባል፡፡

በማለት በላክነው የኦዲት ሪፖርታችን ላይ አሳስበናል፡፡

11.6 የሶስተኛ ወገን መድን ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ የኦዲት ግኝቶች

<u>ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለሚሰበስበውና ለተጎጂዎች ለሚከፍለው የካሣ ክፍያ የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ፣</u>

150. የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በሚከፍሉት ተመን ላይ ተጨማሪ አስር በመቶ (10%) ተሰልቶ እንዲከፍሉ በማድረግ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሊሰበስቡ ይገባል፡፡ ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለኤጀንሲው ለሚያስገቡት የመድን ፈንድ ሂሳብ አያያዝን ለማስተዳደር የሚረዳ የሂሳብ መዝገብ ሊዘጋጅና የፈንዱም ሂሳብ በየዓመቱ ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪ ኤጀንሲው የ3ኛ ወገን ባልገቡና ገጭተው ባመለጡ ተሽከርካሪዎች ለሚደርስ የአካልና የሞት አደጋ ጉዳት የሚከፍለውን የካሣ ክፍያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ገጭተው ያመለጡ ተሽከርካሪዎችን ፈልጎ በመያዝ ገንዘቡን ማስመለስ አለበት፡፡

151. ነገር ግን ኤጀንሲው ስራ ከጀመረበት ከ2004-2006 ዓ.ም ድረስ ለተሰበሰበው የመድን ፈንድ ገንዘብ የሂሳብ መዝገብ ያልተዘጋጀለትና ፈንዱ መሰብሰብ ከተጀመረ ጀምሮም ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በተጨማሪ ኤጀንሲው የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ባልተገባባቸውና ገጭተው በሚያመልጡ ተሽከርካሪዎች ለደረሰ የአካልና የሞት አደጋ ጉዳት የካሣ ክፍያ መክፈል ከጀመረበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የከፈለውን የካሣ ክፍያ ገጭተው የሚሰወሩ አሽከርካሪዎች በፖሊስ ክትትል በቁጥጥር ስር አለመዋላቸው እና ለተጐጂዎች የተከፈለው የካሣ ክፍያ /ብር 1,186,594/ በሙሉ አደጋ ካደረሱት አካላት ያልተመለሰ መሆኑን፣

የ3ኛ ወገን የሚገቡ ተሽከርካሪዎች የሚከፍሉት የአረቦን ተመንን በተመለከተ፣

152. ኢንሹራንስ ኩባንያዎች የ3ኛ ወገን ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ለሚገቡት ተሽከርካሪ ለሚከፍሉት ክፍያ መጠን የሚገልፅ ግልፅ መመሪያ በኤጀንሲው ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም መመሪያ ለሚመለከታቸው አካላት ሊደርስና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ለሚገቡት የመድን ውል መክፈል ያለባቸውን ተመን የሚገልፅ የአረቦን ተመን መመሪያ በ2003 ዓ.ም በኤጀንሲው ቢዘጋጅም ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች (በባጃጅ) ተመን ላይ ለባለሶስት እግር ተመን ሳይሆን ለታክሲ በተቀመጠው ታሪፍ መሰረት የሚያስከፍሉ ኢንሹራንስ ኩባንያዎች መኖራቸውን፣

የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ በተመለከተ፣

153. የተሽከርካሪ አደጋ የደረሰበት ማንኛውም ህብረተሰብ በማንኛውም የጤና ተቋማት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማግኘት አለበት፡፡ ለዚህም የሚያስፈፅም መመሪያ ኤጀንሲው ሊያዘጋጅና ለሁሉም ለባለድርሻ አካላት የጤና ተቋማትን ጨምሮ ሊደርሳቸውና ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

154. ይሁን እንጂ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ በ2003 ዓ.ም በኤጀንሲው የተዘጋጀና የታተመ መሆኑና መመሪያው ለሚመለከታቸው የጤና ቢሮዎች መሰራጨቱ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በ2006 ዓ.ም በድጋሚ መመሪያው የታተመና የጤና ቢሮዎች መመሪያውን ለመንግስት የጤና ተቋማት ያስተላለፉ ቢሆንም ለግል የጤና ተቋማት ያላስተላለፉና በመመሪያው መሰረት የጤና ተቋማት ስራ ያልጀመሩ መሆናቸው ፣

የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ የሚውል የባንክ አካውንትን በተመለከተ፣

155. የተሽከርካሪ አደጋ ደርሶበት ወደ ማንኛውም ጤና ተቋም ለመጣ አካል እስከ ብር 2,000 ድረስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ይህንንም ለማስፈጸም በኤጀንሲው እና በባለድርሻ አካላት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

156. ይሁን እንጂ ማንኛውም ህብረተሰብ የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰበት ጊዜ በማንኛውም የጤና ተቋማት በመታከም የጤና ተቋሙም የህክምና ወጪ ክፍያውን ምቹ ለማድረግ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስም የባንክ አካውንት መከፈቱ እና በተከፈተው አካውንት ከ17ቱ ኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና ከኤጀንሲው የመዋጮ ድርሻ መሰረት ገንዘብ ወደ አካውንቱ ገቢ የተደረገና፣ ሁሉም የጤና ቢሮዎች የራሳቸው አካውንት እንዲከፍቱ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ደብዳቤ የተላከላቸው መሆኑ፣

157. በተሽከርካሪ ጉዳት ለደረሰባቸው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት በጤና ተቋማት ከተሰጠ በኋላ የጤና ተቋማቱ ከየክልላቸው ጤና ቢሮ እንዲጠይቁ ለማድረግ ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ የጤና ቢሮዎች የየራሳቸውን አካውንት ለመክፈት በሂደት ላይ መሆናቸውን ከአዲስ አበባ፣ ከኦሮሚያና ከደቡብ ክልል ጤና ቢሮዎች ለማወቅ የተቻለ መሆኑንና በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ስራ ያልጀመሩ መሆናቸው፣

ከ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቅጾችን በተመለከተ፣

158. ኤጀንሲው ከ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ጋር ተዛማጅ የሆኑና ሥራን ለማቀላጠፍ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቅጾች ወጥ በሆነ

መልኩ ሊዘጋጁ ለባለድርሻ አካላት ሊሰራጩ፣ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረግና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

159. በተሽከርካሪ አደጋ ወቅት ፖሊሶች የደረሰውን አደጋ ዝርዝር ሁኔታ ሞልተው ወደ ጤና ተቋማት የሚልኩበት ቅጽ ኤጀንሲው በበቂ ሁኔታ በማሳተም ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን አንድ ጊዜ 200 ፖድ መድረሱና ኮሚሽኑም ለአስሩም ክፍለ ከተማዎች ያሰራጨ መሆኑን ነገር ግን ከሚከሰተው የመኪና አደጋ አንፃር ሲታይ የቅጹ መጠን በጣም አናሳ መሆኑን እና እጥረት ያለ መሆኑን፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ቅጹ የደረሳቸው ቢሆንም ከሚደርሰው አደጋ አንፃር ሲታይ የደረሱት ቅጾች አነስተኛ በመሆናቸው እጥረት መኖሩ ፣

160. በተጨማሪ የጤና ተቋማት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ለሰጡት አገልግሎት የወጣውን ወጪ ከሚመለከተው አካል ለመጠየቅና ለማስመለስ የሚያገለግል ቅጽ በኤጀንሲው ታትሞ መዘጋጀቱ ታውቋል፡፡ የተዘጋጀውን ቅጽ የደቡብ ክልል ጤና ቢሮ በስራቸው ላሉ የመንግስት የጤና ተቋም የሰጡ፣ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በስሩ ላሉ የመንግስት የጤና ተቋማት ያስተላለፈ ቢሆንም ለሌሎች በፌዴራል ስር ላሉ የመንግስት የጤና ተቋማትም ሆነ በአዲስ አበባ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ ለግል የጤና ተቋማት ያልተሰራጨ መሆኑ፣

<u>የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ ስለመሆኑ፣</u>

161. ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለህብረተሰቡ በሚዲያ፣ በመጽሔት፣ በብሮሸር እና በዌብሳይት በመሳሰሉት ዘዴዎች በመጠቀም የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

162. ኤጀንሲው የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስን እና የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት በተመለከተ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራን እየሰራ የሚገኝ ቢሆንም ግንዛቤው በበቂ ሁኔታ ባለመድረሱ በሀገሪቱ አሉ ከሚባሉ 450,000 ተሽከርካሪዎች ውስጥ የመድን ሽፋን የገቡት 360,960 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 89,040 (20%) የመድን ሽፋን ያልገቡ መሆናቸው፣

163. በመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የካሳ ክፍያ ሥራ አፈፃፀም ላይ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

164. በኤጀንሲው የካሣ ክፍያን በተመለከተ ቅሬታ በሚቀርብበት ወቅት ቅሬታውን ተመልክቶ ያቀረበውን አካል ለማስተናገድ የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑ፣

<u>የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የቁጥጥርና ክትትል ስራ የተሰራ መሆኑን በተመለከተ፣</u>

165. ኤጀንሲው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በሀገሪቱ ያሉ ተሽከርካሪዎች ሁሉ የ3ኛ ወገን መድን ሽፋን እንዲገቡ፣ የመድን ሽፋን ሳይኖራቸው በመንገድ ላይ እንዳያሽከረክሩ በቅንጅት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

166. የ3ኛ ወገን የውል ሽፋን ሳይገቡ በመንገድ የሚያሽከረክሩ ተሽከርካሪዎች ላይ ኤጀንሲው ከፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመቀናጀት ቁጥጥር በ2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ለሶስት ቀን እና በ2006 ዓ.ም አዲስ አበባ፣ ባህርዳር፣ ድሬዳዋ፣ መቀሌ፣ ሀዋሳ እና አዳማ ላይ ከትራፊክ ፖሊስ ጋር በመሆን በተደረገው ቁጥጥር የ3ኛ ወገን የውል ሽፋን የሌላቸው 631 አሽከርካሪዎች የተከሰሱ መሆናቸው ከ2005 እና ከ2006 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ታውቃል፡፡ ሆኖም ክትትልና ቁጥጥሩ በአብዛኛው በዓመቱ ውስጥ የሚደረገው ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ባሉ ወሮች አካባቢ

መሆኑ እና ተከታታይነት የሌለው መሆኑ፣ የ3ኛ ወገን ባልገቡና ገጭተው ባመለጡ ተሽከርካሪዎች የተከፈለ የካሣ ጉዳት ተሽከርካሪዎች ያልተያዙና ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣ በሀገሪቱ አሉ ከሚባሉ 450,000 ተሽከርካሪዎች ውስጥ 89,040 (20%) የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ ያልገቡ መሆኑን ፣

167. እንዲሁም ኤጀንሲው በኦሮሚያ ክልል ቅ/ጽ/ቤት የ3ኛ ወገን መድን ሳይኖራቸው በመንገድ የሚያሽከረክሩ ተሽከርካሪዎችን በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ቁጥጥር እየተደረገ ሲሆን በቢሮው በኩል አዲስ እንደመሆኑ አጥጋቢ ስራ ተሰርቷል ማለት እንደማይቻልና በአዋሳ ያለው የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤትም በደቡብ ክልል የቁጥጥር ስራ የተሰራው በአዋሳ ከተማ ከፖሊስ ጋር በመሆን በ2006 ዓ.ም 3 ጊዜ የቁጥጥር ስራ የተሰራ ቢሆንም ክልል አቀፍ ስራ ያልተሰራ መሆኑን ፣

ታውቋል፡፡

168. በመሆኑም

- ኢንሹራንስ ኩባንያዎች የ3ኛ ወገን ከገቡ ተሽከርካሪዎች የሰበሰቡትን ገቢ በትክክል ለኤጀንሲው ማስገባታቸውን እና ከፈንዱ ወጪ የተደረገውን ክፍያ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲያስችል ለመድን ፈንዱ የሂሳብ ምዝገብ በማከናወን የሂሳብ መግለጫ ሊዘጋጅለትና በየዓመቱም ኦዲት ሊያስደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሚከፍለውን የካሣ ክፍያ ጉዳት አድርሰው የተሰወሩ ተሽከርካሪዎችን ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ሊያስመልስ ይገባል፡፡

- የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ሊከፍሉት የሚገባና ግልፅነት ያለው መመሪያ ለማውጣት የተጠናው ጥናት ከባለድርሻ አካላት በማድረስ የ3ኛ ወገን የሚገቡ

ተሽከርካሪዎች ትክክለኛና ወጥ የሆነ አረቦን ተመን ሊከፍሉ ይገባል፡፡

- በ3ኛ ወገን ላይ ለሚደርስ የተሽከርካሪ አደጋ ተጐጂዎች በማንኛውም የጤና ተቋማት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ለማግኘት እንዲያስችላቸው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ በሀገሪቱ ላሉ የመንግስትም ሆነ የግል የጤና ተቋማት በሚመለከተው አካላት በኩል ሊደርስ እና በመመሪያው መሰረት አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡
- ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ እንዲያገለግል በጤና ጥበቃ የተከፈተው አካውንት ውስጥ የገባው ገንዘብ በአዲስ አበባም ሆነ በክልል አካውንት ለከፈቱ የጤና ቢሮዎች በከፈቱት አካውንት ሊተላለፍና ሂሳብ ያልከፈቱ የጤና ቢሮዎችም እንዲከፍቱ በማድረግና ገንዘቡን በማስተላለፍ ስራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመስራትና ስራን ለማፋጠን የሚያመቹ ቅጾችን ማዘጋጀትና ዘመናዊ የመረጃ ስርዓቶችን በመዘርጋት ለባለድርሻና እና ለፈጻሚ አካላት እንዲደርሳቸው ማድረግና ተፈፃሚነታቸውን ግብረ መልስ የሚያገኝበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በተለያዩ ዘዴዎች እየሰጠ የሚገኝ ቢሆንም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበርና ለሁሉም ለማዳረስ በተጠናከረ ሁኔታና በተከታታይ መስጠት አለበት፡፡ በተጨማሪ የተዘረጋው ድረ ገፅ መመሪያዎችና ብሮሸሮችን የሚያወርድ እንዲሆን መሰራት አለበት፡፡
- በኤጀንሲው ለሚደረገው የካሣ ክፍያ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አግባብነትና ውስብስብነት በመገምገም ለዋና ዳይሬክተሩና

ለቦርዱ ለማቅረብ የሚረዳ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመስራት በተፈራረመው ስምምነት መሰረት ስራ ሊጀምርና የ3ኛ ወገን ሳይገቡ በመንገድ የሚያሽከረክሩ ተሽከርካሪዎችን ቁጥጥር ሂደት ሊጠናከር ይገባል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

11.7 በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የኦዲት ግኝቶች

<u>የወጪ ንግድ ዘርፍ ዕቅድ ዝግጅት በተመለከተ</u>

169. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በየኢንዱስትሪ ዘርፎቹ የወጪ ንግድ ገቢ በስትራተጂክ ዕቅዱ መጨረሻ ያስቀመጣቸውን ግቦች ማሳካት ይገባል፡፡ የስትራስቴክ ዕቅዱንም በሚያዘጋጅበት ወቅትም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ሊያሳትፍ በቅንጅት የሚሰሩበትን ሁኔታ ሁሉ ሊያመቻች ይገባል፡፡

170. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክስፖርት ዕቅድ የሚያዘጋጅ ቢሆንም ዕቅዱን ሲያዘጋጅ ከባለሃብቶቹ እና መንግሥታዊ የሆኑ ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን (የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን፣የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ንግድ ሚኒስቴር፣የግብርና ሚኒስቴር እና ሌሎች ተቋማት) ጋር፣ በበቂ ሁኔታ በመመካከር እና በመቀናጀት ስለማዘጋጀቱ መረጃው ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡ ዕቅዱንም ሲያዘጋጅ በተጨማሪም በዘርፉ ከተሠማሩ ባለሃብቶች ጋር የኤክስፖርት

እቅድ ዝግጅት ወቅት በቅንጅት ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረት እና ለአለም ገበያ መሸጥ ድረስ ያለውን የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ ተግባራዊ ስለመደረጉ መረጃው ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አልቀረበም፡፡

<u>የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና አፈጻጸምን በተመለከተ</u>

171. የተዘጋጀው የኤክስፖርት ዕቅድ በታሰበው መሰረት እየተከናወነ መሆኑ አፈጻጸመ ላይ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ በአፈጻጸም ላይ የታዩ ችግሮችና ክፍተቶችም ካሉ በአፋጣኝ መፍትሔ በመፈለግ ዕቅዱ እንዲሳካ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዘርፍ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2003-2007 ዓ.ም) መሠረት ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም. ባለው አራት የዕቅድ አመታት የዕቅድ አፈጻጸም ሲታይ

- ከቆዳና የቆዳ ውጤቶች የሚገኘው 1,255.4 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በእቅድ የተቀመጠ ሲሆን ክንውን 473.05 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (38%)፣ ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ በእቅድ የተያዘው 1,450 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ክንውኑ 356.21 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (24.63%)፣ ከአግሮ ፕሮሰሲንግ ምርቶችን በእቅድ የተያዘው 573 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ክንውን 202 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (35.24%) መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድና የዓመታዊ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የእቅድ አፈጻጸም መረጃ ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ</u>

172. የኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸም መረጃዎች በትክክል ሊመዘገቡና ትክክለኛ መረጃ እየተላለፈ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ መረጃዎቹም ተጠናቅረው ሊያዙና

ለሚመለከታቸቸው አካላት በሚፈለግበት ወቅት ሊቀርብ ይገባል፡፡

173. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2005 ዓ.ም የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት የወጪ ንግድ አፈጻጸም 98,988,000 እና በ2006 ዓ.ም 111,350,000 አሜሪካን ዶላር ተብሎ የተያዘ ሲሆን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በ2005 ዓ.ም በቀረበው ሪፖርት ላይ ግን 97,521,115 እና በ2006 ዓ.ም 111,074,645 አሜሪካ ዶላር በመሆኑ (በ2005 የአሜሪካን ዶላር 1,466,885 እና በ2006 የአሜሪካን ዶላር 275,355 ልዩነት መኖሩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተያዘው በመብለጥ የሚያሳይ መሆኑ) እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት መሠረት የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ በ2005 ዓ.ም 123,440,000 አሜሪካ ዶላር እና በ2006 ዓ.ም 132,950,000 አሜሪካ ዶላር ሲሆን በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል የቀረበ ግን በ2005 ዓ.ም 121,073,599 እና በ2006 ዓ.ም 130,267,531 አሜሪካን ዶላር መሆኑን፣ (በ2005 የአሜሪካን ዶላር 2,366,401 እና በ2006 የአሜሪካን ዶላር 2,682,469 ልዩነት መኖሩን) በኦዲት ወቅት ከተከለሰው የሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከ2005-2006 ዓ.ም እና ከጉምሩክ የሚቀረብ የአሲኩዳ ሲስተም ከ2005-2006 ዓ.ም መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

174. በናሙና ተመርጠው በኦዲት ከታዩት ፋብሪካዎች መካከል በአሸራፍ ቄራ ኃ.የተ.የግል.ማህበር ወደ ውጪ የሸጠው የሥጋ ምርት በ2004 ዓ.ም አጠቃለይ ከውጪ ንግድ የተገኘ 187,507.79 አሜሪካ ዶላር ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የቀረበው ግን 370,000 የአሜሪካን ዶላር በመሆኑ ልዩነት ያለው መሆኑ፣ በኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር የ2006 በጀት ዓመት የኤክስፖርት ሽያጭ አፈጻጸም ሪፖርት መሠረት

ዕቅድ 11,283,000፤ክንውን 7,262,000 የአሜሪካ ዶላር ሲሆን፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግን ያቀረበው የኤክስፖርት ሽያጭ አፈጻጸም ሪፖርት መሠረት ዕቅድ 15,081,000፤ክንውን 7,440,000 የአሜሪካ ዶላር መሆኑን ከተከለሱ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና ከፋብሪካዎቹ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የወጪ ምርት አፈጻጸም የክትትል እና ግምገማ አሰራርን በተመለከተ</u>

175. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የግምገማ አሰራር የዘርፉን እቅድ አፈጻጸም በሚመለከት ወሰኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር ሊያደርግ ይገባል፡፡ በሚደረጉትም ስብሰባዎችና ውይይቶች የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን ለኢንስቲትዩቶችና ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርትና ግብረ መልስ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የግምገማ አሰራር የዘርፉን እቅድ አፈጻጸም በሚመለከት ወሰኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች፤ ውይይቶችና ከውይይቶቹ የሚገኙ መረጃዎችን በመተንተን ለኢንስቲትዩቶችና ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርት /ግብረ መልስ የማይልክና ክትትል የማይደረግ መሆኑን በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ ፋብሪካዎች ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፤

<u>መረጃዎች መሰብሳብ፣ ማዳራጀት፣ መተንተን እና ማስራጨትን በተመለከተ</u>

176. የኢንዱስትሪ ሚኒስትር በማዕከል የተደራጁ መረጃዎችን የመረጃ ኔት ዎርክ በመዘርጋት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ተጠቃሚዎች በተለያዩና በተሻሻሉ የስርጭት ዘዴዎች ተደራሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በማእከል የሚደራጁት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ዋና

ዋና መረጃዎች በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማጠናከር፣ የማደራጀትና የመተንተን ስራዎችን መስራት ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ወቅታዊ፣ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና ለሚመለከታቸው የዘርፉ ተጠቀሚዎች በተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በአንድ ማዕከል የመረጃ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የፋብሪካ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

177. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪው የማምረት አቅምን ለማሳደግ የሚያግዝ የመረጃ ሥራ አመራር ሥርዓትን ለማሻሻል ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም አግባብ የሆኑ መረጃዎችን (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የደረጃ፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳርያዎች እና የመሳሰሉት) በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና የማጠናቀር ለማከናወን በዕቅድ ቢይዝም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በማዕከል የሚደራጁት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎች (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች፤የግብይት እና የመሳሰሉት) መረጃዎች በየጊዜው የማሰባሰብ፣ የማጠናከር፣ የማደራጀትና የመተንተን ሥራ በዕቅዱ መሰረት እየተሰራ የማይደርሳቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ድርጅቶች /ፋብሪካዎች/ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በኢንዱስትሪ ምርቶች የወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የመሠረተ ልማት አውታሮች መሟላቱን በተመለከተ

178. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት በሚያከናውኗቸው ድጋፎችና አገልግሎቶች ሂደት ከክልሎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ ይህን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ ለኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ-ልማት አውታሮች እንዲስፋፉ ለማድረግ ዕቅድ ይዞ ነበር፡፡

179. ነገር ግን በኦዲቱ ወቅት

- ባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ. በፊት ከነበረው የፋብሪካ የኃይል ፍላጎት 4 ሜጋዋት ሲሆን አዲስ ማሽን ሲተከል አጠቃለይ 10.5 ሜጋዋት በማስፈለጉ ለኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን በተደጋጋሚ በግቢያቸው ውስጥ ካለው ንዑስ ጣቢያ ኃይል እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም ከሌላ ንዑስ ጣቢያ ወደ 6 ኪ.ሜ. ላይ የሚገኝ በ6 ሚሊዮን ብር ከፍለው እንዲያስገቡ በመደረጉ ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉን ከፋብሪካው ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፤
- በደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ የዳሽን ሲሚንቶ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ተጨማሪ 300 ቶን በቀን የሚያመርት ፋብሪካ ግንቦት 2002 ዓ.ም. የተጠናቀቀ ሲሆን እስከ እስከ ጥቅምት/2007 ዓ.ም ድረስ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ባለማግኘቱ ምክንያት ምርት እያመረተ እንዳልሆነ ከፋብሪካው ሥራ አስፈጻሚ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ

ለማወቅ ተችሏል፤

- በባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ.፤በደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ፤ በቴክኖ ሞባይል መጋጣጠሚያ ፋብሪካ፤በኒው ዊንግ ቆዳ ፋብሪካ፣ በቤዛ ኢንዱስትሪ እና በአይካ አዲስ ቴክስታይል ፋብሪካ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥና መዋዥቅ ምክንያት ማሽኖቻቸውን እንዲበላሹ እና ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸው እንዲሁም በምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ መሆኑን

በመስክ ጉብኝት ወቅት ከፋብሪካው ኃላፊዎች ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>በኢንደስትሪ ዘርፍ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራትን በተመለከተ</u>

180. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የሰው ኃይልን በማብቃት ለኢንደስትሪው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል የሚሟላበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ፋብሪካዎች በጨርቃ ጨርቅ እና ቴክስታይል ዘርፍ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ከኢንዱስትሪው ገሃድ አለም አሰራር ጋር የማይተዋወቁ መሆኑ፣ ይህም ማኑፋክቸሪንጉ በሚፈልገው ዲሲፕሊን ተማሪው ታንጾ የማይወጣ መሆኑ፤ የፋብሪካውን ሥርዓት እና ቴክኖሎጅ ጋር ተላምደው እንዲመረቁ የሚያስችል ሥርዓት አለመኖሩን ከኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅና አልበሳት፤ባህርዳር ጨርቃጨርቅና አልበሳትና አይካ ቴክስታይል ኃላፊዎች ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ለኢንዱስትሪዎች የሚሰጥ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ አሰራርን በተመለከተ

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሰጠው የተለያዩ የማበረታቻ ድጋፍ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪ ምርቶች የኤክስፖርት ገቢን ለማሳደግ የኤክስፖርት ማበረታቻዎች በተፈቀዱበት አግባብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለመከታተልና ለማረጋገጥ በዕቅድ ላይ ተይዟል፡፡ በኤክስፖርት ምርት ማምረት ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች ከውጭ ምርት ንግድ የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሪ እና ጥሬ ዕቃ ከውጭ ለማስገባት የሚጠቀሙት የውጭ ምንዛሪ (ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ልከው የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሬ እና ለዚሁ ምርትን ለማምረት ከውጭ አገር ለሚያስገቡት የጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙት የውጭ ምንዛሬ) ልዩነት/ብልጫ ሊያሳይ የሚችል እና በውጤቱ መሠረት አናሳ አፈጻጸም የሚያሳዩ ፋብሪካዎች ላይ ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት አሠራር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ በተጨማሪም በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ዓ.ም. መሠረት የተደነገጉት ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች፤የተመላሽ ቀረጥ ስርዓት፤ የቫውቸር ሥርዓት፤ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት፤የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት፤የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት እና የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ሲሆን እንዲሁም ማንኛውም ለወጪ ንግድ ምርት ማምረት አገልግሎት የሚውል ጥሬ ዕቃ (ግብዓት) ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር እንዲገባ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚዘረጋት የአሰራር ሥርዓት ቢኖርም ነገር ግን የተዘረጋው ሥርዓት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ባለመደረጉ፡-

- ለምሳሌ ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ልከው የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሬ እና ለዚሁ ምርትን ለማምረት ከውጭ አገር ለሚያስገቡት የጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙት የውጭ ምንዛሬ ልዩነት/ብልጫ የሚያሳዩ ፋብሪካዎች መኖራቸው፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት የጥቅምት እና የሕዳር ወር የወጪ ንግድ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ጥሬ ዕቃን ወደ አገር ለማስገበት በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በዲፖዝት እና ቫት መልክ የሚያዙ ገንዘቦች ሰነዶ ተሟልተው ሲቀርቡ በቶሎ የማይለቀቅ ወደ ውጭ ለተላኩ ምርቶች (በተመላሽ ቀረጥ ስርዓት መሰረት) የቀረጥ ተመላሽ ቅድመ ሁኔታዎቹን መሟላታቸው እየተረጋገጠ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በወቅቱ የማይከፈል መሆኑን፣
- ከሀገር ውጪ ለሚገቡ የጥሬ እቃዎች በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል የሚሰጠው የፋሲሊቴሽን አገልግሎት አንዳንዴ ስለሚዘገይ ምክንያት የታዛዘውን ስራ ደንበኞቻቸው ጋር በገቡት ውል መሰረት ምርቱ ተልኮ በጊዜው ባለማድረሱ በውሉ መሠረት መቀጫ በውጭ ምንዛሬ የሚከፍሉበት ሁኔታ መኖሩን፣
- የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ላይ ከተደነገጉት ሥርዓቶች ውጭ ከቀረጥ ነጻ ሁሉም ግብዓቶችንና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አገር እያስገባ እና ምርቱን ሙሉ በሙሉ ለሀገር ውስጥ ገበያ እያከፋፈለ ያሉ በውጭ ባለሀብት የተያዙ ፋብሪካዎች መኖራቸው፣

- ከተሰማሩበት አላማ ውጭ (ሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች አምርተው ወደ ውጪ መላክ ሲገባቸው) በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ እንዲሰማሩ በተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ምርቶቻቸውን እያከፋፈሉ ያሉ የውጭ ባለሀብቶች መኖራቸው

ከተከለሱ ዶክሜንቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>በወጪ ምርት ለተሰማሩ ፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ጥራትን በተመለከተ</u>

183. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኤክስፖርት ስራ ጋር በተያያዘ በጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ግብይት ስርዓት ላይ ለአምራች ላኪዎች የተለያዩ ከግብአት አቅርቦት ጋር በተያያዘ አቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት ይገባል፡፡

184. በኢንዳስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ 2004-2007 ዓ.ም ላይ በምርትና ግብዓት ቅብብሎሽ ሰንሰለት ላይ የሚያጋጥሙ የአሰራር ችግሮችን በጥናትና ምርምር በመፍታት፣በጥቃቅን፣ አነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተሳለጠ የግብዓትና ምርት ትስስር እንዲሁም የከፊል-ኮንትራታዊ ቁርኝት እንዲኖር ሙያዊ ድጋፍ መስጠት ነው የሚል ተቀመጧል፡፡

185. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቆዳ የኤክስፖርት ዘርፍ የሚፈለገውን ውጤት ለማስመዝገብና በአለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል የቆዳ ጥራት የሚሻሻልበትና ምርታማነቱ የሚጨምርበት ስልት ለመንደፍ እና ትኩረት እንዲሰጥ ከግብርና ሚኒስቴርና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ቢኖርም ውጤታማ አለመሆኑ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች

ኢንስቲትዩት ሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችላል፡፡

<u>ለፋብሪካዎች የግብዓት አቅርቦት ትስስርን በተመለከተ</u>

186. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ አገር ውስጥ ገቢ ምርቶችን የሚተኩ የአገር ውስጥ ምርቶች ለገበያ ተደራሽ እንዲሆኑ የግብይት ስትራቴጂ መንደፍና ስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጂያዊ ውጤት ተኮር (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት ገቢ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የውጭ ምንዛሪ ለማዳን እና የኢንዱስትሪውን መሠረት ለማስፋት ከፍተኛ ድርሻ ስላላቸው የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲስፋፉ ዕቅድ ተይዟል፡፡

187. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡት ፋብሪካዎች ማካከል በአይካ አዲስ ጨርቃጨርቅ፤ባህርዳር ጨርቃጨርቅ አ.ማ እና ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ የጥጥ አቅርቦት እጥረት በተዳጋጋሚ የሚከሰትና ያለውም ጥጥ ጥራት ጉድለት ያለውና የአለም ገበያ ያገናዘበ ባለመሆኑ ፋብሪካዎቹ በውጭ ምንዛሪ እያስገቡ መሆኑን በፋብሪካዎቹ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፤

<u>ለወጪ ምርት ለማሳደግ የጥናትና ምርምር ሥርፀት ሥራዎችን በተመለከተ</u>

188. ሚ/ር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎችን ማካሄድ ይገባል፡፡

189. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 181/2002 ዓ.ም መሠረት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠው ተግባር የቆዳና የቆዳ ውጤቶች

ኢንዱስትሪዎች ዘርፍን ለማሳደግ የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር የምርት ልማትንና የሰው ሃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር ይሰራል፤ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል እንዲሁም በዘርፉ የሀገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከር እንደሚያግዝ ይደነግጋል፡፡

190. በዚህም መሠረት የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 180/2002 ዓ.ም መሠረት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠ ሥልጣንና ተግባር መካከል፤ ለዘርፉ ድጋፍ የሚያደርጉ የምርምር ተቋማትን፤ዩኒቨርሲቲዎችን፤ የጥጥና የጨርቃጨርቅ አምራች ማህበራትን እና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማቀናጀት በዘርፉ ችግሮች ላይ ምርምሮች ማካሄድና የምርምር ውጤቶቹ ሲጸድቁ ተግባራዊ እንዲያደርግ ተቋቁሟል፡፡

191. ይሁን እንጂ በሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ኢንስቲትዩቱም የወጪ ንግድ ምርት ላይ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ላይ ዘርፉን የሚመለከት እና ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ለማከናወን ከሚመለከተቸው አካላት ጋር በመተባበር በሁሉም ዘርፎች የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ተከናውነው ተግባራዊ ስለመደረጋቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች መስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለማቅረባቸው፣

በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

192. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ጉዳዩን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤የክትትል ሥርዓት ከተዘረጋ ዓመታት አልፈዋል. ይህ ከላይ ጀምሮ በብሄራዊ ኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ፣በሚኒስቴሩ የበላይ አመራር፣ ኢንስቲትዩቶች፣ የልማት ቡድኖችና ግለሰብ፣ ባለሙያዎች ይከናወናል ቢሉም የተከናወኑ ጥናቶች ተጠይቀው አላቀረቡም፡፡

ለወጪ ንግድ ማምረት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግን በተመለከተ

193. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በግብይት ዙሪያ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት የአምራች ድርጅቶችን የኤክስፖርት ገበያ የመድረስ አቅማቸውን ለመገንባት ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎቹን ለመደገፍ የተቋቋሙትን ኢንስቲቲዩቶች ከሌሎች ዓለም ዓቀፍ ዕውቅናና ብቃት ካላቸው ተቋማት ጋር በማቆራኘት አቅማቸውን በዘላቂነት የሚገነባበት ስርዓት መዘርጋት ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት የኢንዱስትሪ ዘርፉን ለመደገፍ የፈፃሚውን ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ የሚያስችሉ የትምህርት፣ የሥልጠና እና የልምድ ልውውጥ በማካሄድ፣ በራስ የመተማመንና ችግር የመፍታት ብቃትን ማጎልበት ዕቅድን አካቷል፡፡

194. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ፋብሪካዎች የኢንዱስትሪዎቹ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሥልጠናዎችን (በቴክኒክ፣ በሥራ አመራርና በግብይት ዙሪያ) ክፍቶች በሚታይባቸው ሙያዎች ዳሳሰ ጥናት በማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በዘርፉ በተቋቋሙ ኢንሰቲትዩቶቹ በኩል በቂ ሥልጣና የማይሰጥ መሆኑን በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

195. ለሌሎች ፋብሪካዎች የሚሰጥም ስልጠናም ቢሆንም በኤክስፖርት ምርት መጠን፣ጥራት እና የኤክስፖርት እቅድ አፋጻጸም ላይ ያስገኘው ጠቀሜታ/ ፋይዳ የማይገመገም መሆኑን ከተደረገው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎችን ለመደገፍ የተቋቋሙት የኢንስቲትዩቶችን አቅም ለማጎልበት ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በሀገር ውስጥ እና በውጭ

ሀገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር ለኢንዱስትሪዎች የቴክኒክ ድጋፍ በጋርመንት እና በግብይት የሥራ መስኮች ብቻ በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ የተሰጠ ሲሆን በሌሎቹ መስኮችና ኢንዱስትሪዎች ያልተሰጠ መሆኑን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት 2006 ዓ.ምና የ2007 በጀት አመት የጥቅምትና የሕዳር ወር እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>ለወጪ ምርቶች የገበያ መረጃ እና ድጋፍን በተመለከተ</u>

196. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ምርቶችን በአለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ ወደ ተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች መግባት የሚያስችል የግብይት ስትራቴጂ መንደፍና ስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

197. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ስትራቴጅያዊ ውጤት ተኮር እቅድ (2004-2007 ዓ.ም) መሠረት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት ለኢንዱስትሪ ምርቶች የገበያ አድማስ ማስፋት፣ ኢንቨስትመንትን መሳብና ፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማረጋገጥ ዕቅድ ተይዟል፡፡

198. ይሁን እንጂ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አዳዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማፈላለግና በስፋት የኢንደስትሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የጋራ መግባቢያ በማዘጋጀት እና የገበያ ማስፋፋት ስትራቴጅ በመቅረጽ በውጭ አገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በኩል ተግባራዊ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ፋብሪካዎች ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

199. በመሆኑም

- የኤክስፖርት ዕቅድ ሲያዘጋጅ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢንስቲትዩቶች፣ ከባለሃብቶቹ እና መንግሥታዊ የሆኑ ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን ጋር በመመካከር እና በመቀናጀትና በጥናት ላይ የተመሠረተ ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት እና ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለበት፣

- በዘርፉ ከተሠማሩ ባለሃብቶች ጋር በቅንጅት ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጀምሮ እስከ ምርት ማምረት እና ለአለም ገበያ መሸጥ ድረስ ያለውን የአሰራር ክፍተቶችን በየዘርፎቹ በመለየት ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫ አስቀድሞ በማስቀመጥና ለመካለከልና ችግሮቹ በሚከሰቱበት ወቅትም አፋጣኝ ምላሽ/እርምጃ መውሰድ አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርብ የፋብሪካዎች የወጪ ምርቶች እቅድ አፈጻጸም ከፋብሪካዎቹ እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር የሚታየውን ልዩነት በማስታረቅ ትክክለኛ ከውጭ ምንዛሪ አገራቱ የገባቸው ገቢ እንዲታወቅ ሁሉም መረጃቸው አንድ አይነት የሚሆንበት አሰራር ዘርግቶ ለሚመለከተው አካል አንድ አይነት ሪፖርት መቅረብ አለበት፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእክስፖርት ዕቅድን የሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላትን በዝርዝርና በጋራ በማዘጋጀት እና እቅድ አፈጻጸሙንም በመገምገም በጋራ ለፋብሪካዎች የግምገማ ሪፖርት /ግብረ መልስ በመላክ ክትትል ማደረግ አለበት፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ (ኤክስፖርት ዘርፍ) በተመለከተ መረጃዎችን በአንድ ማዕከል በማደራጃት የመረጃ አገልግሎት

ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግና ወቅታዊ፣ ትክክለኛና የተሟላና የተደራጀ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው የዘርፉ ተጠቀሚዎች በተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀምና ለዘርፍ ተጠቀሚዎችን በማስተዋወቅ አግባብ የሆኑ መረጃዎችን (ምርጥ ተሞክሮዎች፣ የምርምርና ስርፀት ውጤቶች፣ አዳዲስ የለውጥ መሳሪያዎች፤የግብይት እና የመሳሰሉት)፤ በማእከል በማደራጀት ወቅታዊ፣ አለም አቀፍ እና የተሟሉ ወሳኝ የሆኑ መረጃዎችን በየጊዜው በማሰባሰብ፣ በማጠናከርና በመተንተን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ፋብሪካዎች የሚያገኙበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ፤ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዘርፎቹ የመሠረተ ልማት አገልግሎትን በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና የመሳሰሉትን አቅርቦት የሚያገኙበትን፣ ኃይል እንዳይቋረጥ እና በተፈለገው መንገድ እንዲቀርብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የሃይል አቅርቦት ዕጥረት ለመፍታት ለፋብሪካዎቹ በቂ ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከሚመለከተቻው አካላት ጋር በመተባበርና በየጊዜው በመወያየት፤ የኢንዱስትሪ መለማመጃ ሥራዎችን (workshop) በማስፋፋት ለኢንደስትሪዎች የሚያስፈልግ ብቁ የሰው ኃይል የሚያፈራበት አሰራር ሥርዓት በመፍጠር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወጡ ተመራቂዎች

ከሥራው ሁኔታና የኢንዱስትሪው ባህሪ ጋር እንዲተዋወቁ መደረግ አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ የተሰመሩት ባለኃብቶች ለማበረታታት ጥሬ ዕቃን ወደ አገር በሚያስገቡበት ወቅት የቀረጥ ማበረታቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር በመመከካር ለተጠቃሚዎች የቀረጥ ተመላሽ ገንዘብ በወቅቱ እንዲመለስላቸው በማድረግ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ማስኬጃ (Working Capital) እጥረት እንዳያጋጥማቸው ማድረግ አለበት፤

- የውጭ ዜግነት ያላቸው ባለሃብቶች ከተሰማሩበት አላማ ውጭ (ሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶች አምርተው ወደ ውጪ መላክ ሲገባቸው) በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ እንዲሰማሩ በተመረጡ የንግድ ስራዎች ላይ የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ምርቶቻቸውን እንዳይከፋፈሉ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ መወሳድ አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ 768/2004 ዓ.ም በተከተለ መልኩ ለውጭ ባለሀብት ከቀረጥ ነጻ ሁሉም ግብዓቶችንና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ አገር እንዲያስገቡና ምርቱን ኤክስፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ የሀገሪቱን ህግ በማስከበር ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዲኖርና ሀገር በቀል አምራች ድርጅቶች በማበረታታት ሀገሪቷ ከቀረጥና ታክስ ገቢ እንዲታገኝ ማድረግ አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፋብሪካዎች የሚሰጠው የማበረታቻ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑና በአፈጻጸሙ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመዘርጋት ለዘርፍ የሚሰጥ ማበረታቻ ድጋፍ ያስገኘው ውጤትን ማረጋገጥ አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ መፍትሄ ለመስጠት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ዝርዝር ጥናት በማካሄድ ከበለድርሻ አካለት ጋር ስምምነት ሊኖርና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንዑስ ዘርፎችን ለመደገፍ የተቋቋሙት ኢንስቲትዩቶች አቅም ለማጎልበት ተመሳሳይ አላማና እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ዕውቅናና ብቃት ካላቸው ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር በሁሉም የሥራ መስኮች በሚፈለገው መጠን ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነትን በጥራትና በመጠን ለውጥ ማምጠት አለበት፤

- ሚ/ር መ/ቤቱ ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠርና የጋራ ስምምነትን በማዘጋጀት ለዘርፉ ችግር ፈቺ የሆኑ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎችን በሁሉም ዘርፎች ላይ ማከናወን አለበት፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየንዑስ ዘርፉ በተቋቋሙ ኢንሰቲትዩቶች በኩል የኢንዱስትሪዎችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ሥልጠናዎችን (በቴክኒክ፤ በሥራ አመራር፤በግብይት ዙሪያና በሌሎችም) ዳሳሰ ጥናት በማካሄድ ክፍቶችን በመለየት ሥልጣና መስጠት አለበት፤የሚሰጥ ስልጠናም የሚያመጣው ፋይዳ መገምገም አለበት፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ንግድ ላይ ለተሠማሩ የፋብሪካዎቹን የዕውቀትና የቴክኖሎጅ ሽግግር በማድረግ የግብይት አቅም እንዲያጎለብቱ እና የኤክስፖርት ምርት ለማሳደግ አምራቾቹ እርስ በራሰቸው እንዲማማሩ የልምድ ልውውጥ መድረክ ማዘጋጀት አለበት፤

- ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አዳዲስ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማፋላለግና በስፋት የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊያዘጋጅ እና የገበያ ማስፋፋት ስትራቴጅ በመቅረጽ በውጭ አገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ እምባሲዎች በኩል ተግባራዊ ማድረግ አለበት፤

በማለት የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

11.8 በከተማ ልማት፣ ቤቶች እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ምንጭ፣ዝግጅትና እና አፈጻጸምን በተመለከተ

የኦዲት ግኝቶች

<u>ክልላዊ የከተማ ዕቅድ/ፕላን መዘጋጀቱን በተመለከተ</u>

200. በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን ብሔራዊ የከተማ ልማት ዕቅድ መሰረት ያደረገ ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድ/ ፕላን (Regional urban development Plan) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ እርሱንም መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ከተማ የከተማ ልማት ፕላንና (Local Development Plan) የአካባቢ ልማት ፕላን ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

201. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኦሮሚያና በሐረሪ ክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ መስተዳድሮች ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድ ፕላን አለመዘጋጀቱ ታውቋል፡፡ የአካባቢ ልማት ፕላንን ለማዘጋጀት ክልላዊ የከተማልማት ዕቅድ ፕላን ያልተዘጋጀ በመሆኑ፤ የሀረሪ ከተማ የአካባቢ ልማት ፕላን ከዚህ በፊት የተዘጋጁ የሌሎች ከተሞች ማስተር ፕላንን በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን፤ የጅማ ከተማም እንደዚሁ በሌሎች ከተሞች ተሞክሮ ላይ በመመርኮዝ የአካባቢ ልማት ፕላንን አዘጋጅተዋል፡፡ የድሬደዋ ከተማ በ5 ዓመት እንደገና መሰራት ሲገባው ባልተሰራ የተቀናጀ የልማት ፕላን(Inetegrated

devolopmenet plan) ፕላንን በመጠቀም የአካባቢ ልማት ፕላን እንዳዘጋጁ ታውቋል፡፡

<u>በከተማ ፕላን ዝግጅት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎን በተመለከተ</u>

202. የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የሕዝብ ተሳትፎ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ የህብረተሰቡ ፍላጎት መሟላቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

203. የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የመሰረተ ልማት አቅራቢዎችና የሕዝብ ተሳትፎን በማካተት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር በማድረግ የህብረተሰቡ ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የከተሞች ፕላን ከመጽደቁ በፊት የከተማው ህዝብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበት ሊደረግ ይገባል፡፡

204. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ከተሞች ከህዝብ ተወካዮች ጋር ውይይት የሚደረግ ሲሆን፤የመሰረተ ልማት አቅራቢ ከሆኑት ጋር በቅርበት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ፣ በፕላን ዝግጅት ወቅት የመሰረተ ልማት ተቋማት ፍላጎትና ስታንዳርድን በማምጣት ለማካተት ጥረት ቢደረግም የተዘረጋ የአሰራር ስርአት ባለመኖሩ የተነሳ ተቀናጅቶ በጋራ ባለመንቀሳቀስ በሚፈጠር ክፍተት ምክንያት መንገዶች መበላሸታቸውን፣ የውሃ ማፍሰሻ ቱቦዎች የቁሻሻ መጣያ እየሆኑ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለጅማ ለድሬደዋና ለሀረሪ፤ለኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

205. ከዚህ በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ክልሎች ውስጥ በሀረሪ ክልልና በድሬደዋ ከተማ የጸደቀው የከተማ ፕላን ለትግበራ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲመሩበት (እንዲመክሩበት) ማስገንዘቢያ የማይሰጥ በመሆኑ፡ በዚህም

ምክንያት ባለድርሻ አካላት የመሰረተ ልማት አቅራቢ የሆኑት ባለድርሻ አካላት የመንገዶች ባለስልጣን፣ ውሃና ፍሳሽ፣ ፅዳትና ውበት፣ አካባቢ ልማት፣ መብራት ኃይል፣ ቴሌኮሙንኬሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተቀናጀና የተናበበ ዕቅድ እንዳያቅዱ እንቅፋት እንደሆነ ለድሬደዋ ከተማ ኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡

<u>ከተማን ለማደስ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል እቅድ ስለመዘጋጀቱ፤</u>

206. የከተሞች ፕላን ሲዘጋጅ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የአረንጓዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በፕላኑ መሰረት ሊተገበሩ ይገባል፡፡ የከተሞች መልሶ ማልማት ዕቅድም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

207. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው በጅማ ፤በድሬደዋ፤ በሀረሪ እና በአዲስ አበባ ከተሞች ከተማን የማደስ ተግባር፤ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚታዩትን የፈራረሱ፤ ያረጁ፤ የተተዉ መዋቅሮች በከፊል ወይም በሙሉ በማስወገድ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የሚያስችል እቅድ እንዲዘጋጅ አልተደረገም፡፡

208. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው ከተሞች የጅማና የድሬዳዋ ከተሞች የአካባቢ ልማት ፕላን ሲዘጋጅ የአረንገዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታ እንዲካተት ቢደረግም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡ በአንዳንድ ቦታ ለአረንጓዴ ቦታ በተከለለ መሬት ላይ ከ60-70 የሚሆን አባወራ የሰፈረበትና በተጨማሪም የስፖርት ማዘውተሪያም ሆኖ እንደሚያገለግል ለኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

209. ስለጉዳዩ የከተሞቹ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው የጅማ ከተማ በፕላኑ ላይ ቢካተተም ቀደም ሲል በስፍራው የሰፈሩ ሰዎችን ለማንሳት የካሳ ክፍያ መክፈል ስላልተቻለ ወደ ተግባር አልመገባቱን ገልጸዋል፡፡ በድሬደዋ ከተማ ፕላኑ ላይ እንዲካተት ቢደረግም ተግባራዊ አለመደረጉን፣ በአፈጻጸም ደረጃ መልሶ የማልማት ስራ በተወሰነ ደረጃ የተጀመረ ቢሆንም ይህንንም በካቢኔ በማፀደቅ እንጂ ለምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ተደርጎ ተግባራዊ አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡

<u>የአካባቢ ልማት ፕላን በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ</u>

210. የከተሞች የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በየከተሞቹ ምክር ቤቶች ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ እና ለሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለውጥ የተደረገባቸው ቦታዎች በአካባቢ የልማት ፕላን (Local Development Plan) ላይ እንዲሰፍሩና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

211. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በድሬደዋ ከተማ ምክር ቤቱ የተቋቋመው በ2000 ዓ.ም ሲሆን የድሬደዋ የተቀናጀ ልማት ፕላን (Integrated Development Plan) የተሰራው – በ1997 ዓ.ም. የነበረ ቢሆንም እስካሁን ያልተከለሰና ለከተማው ምክር ቤት ቀርቦ አለመጽደቁ፣ የአካባቢ ልማት ፕላን (Local Development Plan) በከተማው ካቢኔ ቢጸድቅም ለከተማው ምክርቤት ቅርቦ አለመጽደቁ ታውቋል፡፡ በከተማው እየተሰራ ያለው የድሬደዋ ሪፈራል ሆስፒታል በአካባቢ ልማት ፕላን ላይ ያልሰፈረና በካቢኔም ሆነ በምክር ቤት እንዲጸድቅ ያልተደረገ ነው፡፡ በሀረሪ ክልል በየጊዜው የአካባቢ ልማት ፕላን ለውጦች

ተደርገው ለካቢኔ ቀርበው ሳይጸድቁ ወደ ትግበራ የተገባ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

212. ስለጉዳዩ የከተሞቹ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ ሲመልሱ በድሬዳዋ የአካባቢ ልማት ፕላን (Local Development Plan) በከተማው ካቢኔ ቢጸድቅም በመጀመሪያ መጽደቅ የነበረበት መዋቅራዊ ፕላኑ (Structural Plan) ለምክር ቤት ቀርቦ ስላልፀደቀ የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲጸድቅ ለምክር ቤቱ አለመቅረቡን ገልጸዋል፡፡ በሀረሪ የተደረጉ ለውጦችን በማሰባሰብ ለካቢኔ አቅርቦ ለማፅደቅ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

<u>የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ</u>

213. ፕላንን በሚመለከት ለሚደረግ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ ሲዘጋጅም የሚመለከታቸው አካላትን ሊያሳትፍና አስተያየት እንዲሰጡበት ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው የፕላን ዝግጅትን በሚመለከት መመሪያ፣ስታንዳርድና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት ቀደም ብሎ ያለውን ክፍተት ለማወቅ እንዲቻል የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ጥናቱን መነሻ በማድረግ ማንዋሉም ሆነ ደረጃዎችን እና ፕሮግራሞች እንዳልተዘጋጁ ታውቋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው ለክልል ከተሞችና ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ ለሆኑ ከተሞች የከተማ ፕላንን በሚመለከት የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍን የሚመለከት የአሰራር ማንዋል እንዲዘጋጅ አልተደረገም፡፡

214. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የድሬደዋ ከተማ መስተዳድርና የሀረሪ ክልል ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በአገር አቀፍ ደረጃ

የፕላን አዘገጃጀትና አፈጻጸም ማንዋል በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ አስተያየት እንዲሰጡበት ተልኮላቸው አስተያየታቸውን ሰጥተው የተመለሰ ቢሆንም፣ እስካሁን በሚመለከተው አካል ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉን ገልጸዋል፡፡ ለአዲስ አበባ ከተማ ፕላን ኢንስቲተዩት የቢሮ ኃላፊም ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስታንዳርዶችን ማንዋሎችን በማዘጋጀት ስልጠና ለመስጠት ጥረት እያደረገ ቢሆንም ነገር ግን የአዲስ አበባ ከተማ ውስብስብና ዓለም አቀፍ ከተማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዓለም አቀፍ ተሞክሮና ድጋፍ የሚገኝበት ሁኔታ አልተመቻቸም ብለዋል፡፡

<u>የጥናት ሰነዶች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ</u>

215. ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም ጥናቶች ሊጠኑ ይገባል፡፡ የተዘጋጁ የጥናት ሰነዶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ ጥናቶቹም በትክክል ሥራ ላይ የዋሉ ለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

216. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸምን በተመለከተ የተለያዩ የጥናት ሰነዶች በሚኒስትር መ/ቤቱ የተዘጋጁ ቢሆንም የጥናት ሰነዶቹ በናሙና በታዩት ለሀረሪ ክልልና ለድሬደዋ ከተማ የደረሱ ሲሆን ለአዲስ አበባና ለጅማ ከተማ እንዳልደረሳቸው ገልጸዋል፡፡ የጥናት ሰነዶቹ በደረሳቸው በድሬደዋ ከተማ መስተዳድርና በሀረሪ ክልል በትክክል ሥራ ላይ እንዲውሉ አልተደረገም፡፡ ይህንንም በሚመለከት በሚኒሰቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን ለኃላፊዎች ከቀረበው መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ በሰጡት አስተያየት ሰነዶቹ ሥራ ላይ

ስለመዋላቸው በተመረጡት የናሙና ከተሞች በፌዴራል ደረጃ እና በክልል ደረጃ ክትትል በማድረግ በአካልና በጽሁፍ ግብረመልስ ተሰጥቷል ቢሉም እስካሁን በኦዲቱ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረገው በፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ላይ ብቻ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ እንዳለ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

<u>ማንኛውም የጸደቀ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ</u>

217. የከተማ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በፕላኑ ላይ ከተመለከተው ውጭ ለሚፈጸም ጥሰት በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የልማት አፈቃቀድ ደንቦችን አጠቃላይ ተፈጻሚነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ክትትልና ግምገማ ሊደረግ ይገባል፡፡ የከተማ ፕላን በጊዜው የሚመጣውን ተለዋዋጭ የከተማ ዕድገት ባህሪ ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

218. ፕላን በሚዘጋጅበትና በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር በናሙና የታዩት የድሬዳዋ፣ የሐረር፣ የመቀሌ፣ የአዳማ፣ የደሴ፣ እና የጅማ ከተሞች ፕላን ዝግጅትና ትግባራ ላይ ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰራ ሲሆን፤ በባህር ዳር፣ በሀዋሳ እና በአዲስ አበባ ከተሞች ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ስለመደረጉ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ አልቀረበም፡፡

219. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ክልሎች ውስጥ በሀረሪና በጅማ ለኃላፊዎች በቀረበው መጠይቅና በመስክ ጉብኝት ወቅት እንደታየው እንዳንድ የከተማ ቦታዎች ለመኖሪያ ሥፍራ ታቅዶ የነበረው ወደ ንግድ ሥፍራ እንደተቀየረ፡ መንገዶች፤ የአረንጓዴ

ቦታዎችና ሌሎችም በትክክል በፕላኑ ላይ በተቀመጠላቸው ቦታ እንዳልተሰሩና ለሌላ አገልግሎት መዋላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

220. በተጨማሪም በናሙና በታዩት በጅማ ፤በድሬደዋና በሀረር ከተሞች በአካባቢ ልማት ፕላን ላይ ሰፍሮ ከሚገኘው ውጭ በግለሰቦችም ሆነ በተለያዩ ሴክተሮች የፕላን ጥሰት መፈጸሙን ለመመልከት ተችሏል፡፡ጥሰቱ ከተፈጸመባቸው ውስጥ፡-

<u>በድሬዳዋ ከተማ</u>፤

- የድሬደዋ ሪፈራል ሆስፒታል ግማሽ ለደን በተከለለና ግማሽ መዝናኛ በነበረ ቦታ የተሰራ መሆኑ፡፡

<u>በሀረር ከተማ፤</u>

- በደከር ሰፊ ወረዳ የደን ቦታ የነበረ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ የምግብ ዝግጅት ወርክ ሾፕ (ባለ ሁለት ፎቅ) ግንባታ፣
- በደከር ሰፊ ወረዳ የደን ቦታ የነበረ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ተጨማሪ የምግብ ዝግጅት ወርክ ሾፕ(ባለ ሁለት ፎቅ) ግንባታ፣
- በሐማሬሳ (ሀኪም) የደን ቦታ የነበረ ቁጥር አንድ እና ሁለት የልብስ ስፌት ወርክ ሾፕ(ባለ አራት ፎቅ)፣
- በሐማሬሳ (ሀኪም) የደን ቦታ የነበረ ተጨማሪ የልብስ ስፌት ወርክ ሾፕ ግንባታ (ባለ አራት ፎቅ)፣
- በሀማሬሳ ለመኖሪያ የነበረ ቦታ የልብስ ስፌት ወርክ ሾፕ ግንባታ (ባለ አራት ፎቅ)፣
- ቀበሌ 13 መምህራን ማሰልጠኛ ፊት ለፊት ለመኖሪያ የነበረ የውሀ ልማት ቢሮ ግንባታ፣

- ቀይ መስቀል ፊት ለፊት ለመኖሪያ የነበረ የመገናኛ ብዙሀን ቢሮ ግንባታ (ባለ 4 ፎቅ)

<u>በጅማ ከተማ፤</u>

- በመርካቶ አካባቢ የሚገኝው በተለምዶ ዶሮ ተራ የሚባለው ሰፈር በአዲሱ የከተማ ፕላን መሰረት ለመኪና ማቆሚያ ተብሎ የታቀደ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የንግድ ሱቆች የተሰሩበት መሆኑ፤
- በእስቴዲየም በስተጃርባ በአዊቱ ወንዝ ዳር፤ በበቾ ቦሬ ቀበሌ ዶሎሎ ወንዝ ላይ ከድልድዩ በላይኛውና በታችኛው ቦታዎች ላይ በጥቃቅንና አነስተኛ በተደራጁና በግለሰቦች የመኪና ማጠቢያ (ላቪያጆ) ተይዞ እየሰሩበት ሲሆን በፕላኑ መሰረት ግን ለበፈር ዞን ተብሎ የታቀደ መሆኑ፡፡
- ለበፈር ዞን የታቀደው በመርካቶ አካባቢ አርማታ በሚባለው ቦታ አዊቱ ወንዝ በበቾ ድልድይ ዳር በግራና ቀኝ በኩል ለንግድ እና ለመኖሪያ የሚያገለግሉ ቤቶች ወንዙን ተከትለው በቅርበት የተሰሩና አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው ነገር ግን ከዚህ በፊት በቦታው ላይ የወንዝ ሙላት ባስከተለው አደጋ ብዙዎቹ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱ

221. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩት የድሬዳዋ፣ የሐረር፣ እና የጅማ ከተሞች የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው ፕላን ዝግጅትና ትግባራ ላይ ለተከሰተው ጥሰት ምክንያት ምላሽ አልሰጡም፡፡ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ላይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር መሰረት በታዩት ከፍተቶች ላይ እያንዳንዱ ከተማ እርምጃ ስለመወሰዱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃ አልቀረበም፡፡

የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም የክትትልና የግምገማ ማንዋልና መስፈርትን በተመለከተ

222. በአገሪቱ ውስጥ ላሉ ከተሞች የሚዘጋጁ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት ስለመሆኑ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመገምገሚያ መስፈርትና ማንዋል ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በመስፈርቱም መሰረት በየከተሞቹ የሚሰሩት ፕላኖች ሊገመገሙ ይገባል፡፡

223. ይሁን እንጂ ከሚኒስትር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ከተሞች በተለያዩ አካላት የተሰሩትን የከተማ ፕላኖች አፈጻጸም አስመልክቶ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ የሚያስችል የተዘጋጀ መስፈርትም ሆነ ማንዋል አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ክትትልና የግምገማ ሪፖርት ግበረ-መልስና የተወሰደ እርምጃን በተመለከተ

224. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በመላው አገሪቱ የሚዘጋጁት የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሠረት ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ለዚህም በክልሎችና ቻርተር ባለው ከተማ የክትትልና የግምገማ ሥራ በማከናወን ድጋፍ ሊያደርግና እና ግበረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተሠጠው ግብረ መልስ መሰረትም የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ መሰዱንም ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

225. በኦዲቱ ወቅት ግምገማ የተከናወነ መሆኑን ነገር ግን በግምገማ ወቅት በርካታ ግኝቶች የተገኙ ቢሆንም እነዚህ ግኝቶች ላይ የእርምት ርምጃ ያልተወሰደ ሲሆን ስህተቶቹ በነበሩበት ሁኔታ ቀጥለው መገኘታቸውን እና ተመሳሳይ የሆኑ ስህተቶች እንደገና እየተደገሙ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት በስፍራው በመገኘት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የጅማ፣ የድሬደዋና፣የሀረር ከተሞች ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ግምገማ የሚከናወን ቢሆንም የግምገማው ግብረመልስ ሪፖርት እንደማይደርሳቸው ገልጸዋል፡፡

<u>ከከተማ ፕላን ምንጭ፤ ዝግጅት እና አፈጻጸም ጋር የተያያዙ መረጃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

226. ከከተማ ፕላን ጋር የተያያዙ በየጊዜው የሚመጣውን ተለዋዋጭ የከተማ ዕድገት ባህሪ ያገናዘበ የጥናት ሰነድና ማስረጃዎች ተደራጅተው መያዝ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱና የሚመለከታቸው የክልል አካላት ለከተማ ፕላን ምንጭና ዝግጅት የሚያገለግሉ መረጃዎች ሊያሰባሰቡ፣ ሊያደራጁና በማጠናቀር ሊያዙ ይገባል፡፡ የጥናቱ ማስረጃዎች በየከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲቀመጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

227. የተሰበሰቡትም መረጃዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ለሚመለከታቸው አካላት የሚደርስበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ስለከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ባለድርሻ አካላት (በተለይም የመሠረተ ልማት አቅራቢዎች) መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና ከተሞች የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊፈራረሙና ተግባራዊ ሊደርጉት ይገባል፡፡

228. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው የጅማ፣ የድሬዳዋና የሀረር ከተሞች የከተማ ፕላን የማመንጨት ሂደት ቃለ ጉባዔ፣ የመሬት አጠቃቀም ጥናት፤የመሰረተ ልማት እቅድ፣ የክትትልና ግብረ መልስ ሪፖርቶች፣ የረቂቅ ፕላኖች ውይይት ቃለ ጉባዔ እና ሌሎችም ማስረጃዎችን ከተለያዩ ቢሮዎቹ እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

229. በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የከተማ ልማት ቢሮዎች ማስረጃዎቹንም በኃላፊነት በማሰባሰብ ለሌሎች አካላት እንዲደርሱ አለማድረጋቸው ታውቋል፡ የመረጃዎች የልውውጥ

ሥርዓትም ያልተዘረጋና የከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባባር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ካላቸው ባለድርሻ አካላት (የመሠረተ ልማት አቅራቢዎችን ጨምሮ) ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ያልተፈራረሙ መሆኑ ታውቋል፡፡

230. በመሆኑም

- ክልሎች ክልላዊ የከተማ ልማት ዕቅድና ለእያንዳንዱ ከተማ የአካበቢ ልማት ዕቅድ (Local Development Plan) ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡
- ፕላኑም በሚዘጋጅበት ጊዜም አገር አቀፍ የልማት ስትራቴጂና ዕቅድ ላይ ሊመሰረትና የሚመለከታቸውን የፌዴራል እና የክልል አካላትን ሊያሳትፍ ይገባል፡፡
- ብሔራዊ፣ ክልላዊና የከተሞች ፕላን በሚመነጭበትና በሚዘጋጅበት ወቅት የመሰረተ ልማት አቅራቢዎችና የሕዝብ አስተያየት ሊካተትና ፕላኑ ተዘጋጅቶ ከመጽደቁ በፊት የከተሞቹ ነዋሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት ሊደረግ ይገባል፡፡ ፕላን ትገበራው ላይ ድርሻ ያላቸው አካላት ኃላፊነታቸውና ግዴታቸውን ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ተግልጸላቸው ተግባራዊ የሚያደርጉበት መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- የከተሞች ፕላን ሲዘጋጅ ምቹ የመኖሪያና የሥራ አካባቢ ለመፍጠር የአረንጓዴ አካባቢ ስፍራ እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በፕላኑ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የከተሞች የአካባቢ ልማት የመጨረሻ ረቂቅ ፕላኖች በየከተሞቹ ምክር ቤቶች /በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ እና ለሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌዴራል አካላት በወቅቱ እንዲደርሱ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በፕላን ትግበራ ወቅት ለውጥ የተደረገባቸው ቦታዎች በአካባቢ የልማት ፕላን (Local Development Plan) ክለሳ በሚደረግበት ወቅት በፕላኑ ላይ እንዲሰፍሩና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቁ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው ፕላንን በሚመለከት ለሚደረግ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የአሰራር ማንዋል በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ለከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም የሚጠኑ ጥናቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት እንዲደርሳቸው ሊደረግ፣ ከተሞቹም ጥናቶቹን ተግባራዊ ሊያደርጉት እና ጥናቶቹም በትክክል ሥራ ላይ የዋሉ ለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በአገሪቱ ውስጥ ላሉ ከተሞች የሚዘጋጁ የከተማ ፕላን ዝግጅትና አፈፃፀም በከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 መሰረት ስለመሆኑ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመገምገሚያ መስፈርትና ማንዋል ሊዘጋጅና በመስፈርቱም መሰረት በየከተሞቹ የሚሰሩት ፕላኖች ሊገመገሙ ይገባል፡፡
- የከተማ ፕላን ትግበራ ወቅት በፕላኑ መሠረት ተግባራዊ ሊደረግና በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡
- የከተማ ፕላን በሚተገበርበት ወቅት የፕላን ጥሰት እንዳይኖር ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በፕላኑ ላይ ከተመለከተው ውጭ ለሚፈጸም ጥሰት በወቅቱ እርምጃ ሊወሰድ የሚስችል ግልጽነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍን የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

ሚኒስቴር /ቤቱም ክልሎቹን ለማገዝ የሚያደርገውን የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ሊጠናከር ይገባል፡፡

- በፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረገው የክትትልና ግምገማ ተጠናቅሮ ሊቀጥልና ግበረ መልስ ለከተሞቹ ሊደርሳቸውና በግብረ መልሱ መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል በሚመለከታቸው አካላት ለከተማ ፕላን ምንጭና ዝግጅት የሚያገለግሉ መረጃዎች ሊሰባሰቡ፣ ሊደራጁና ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡የጥናቱ ማስረጃዎች በከተማው ማዘጋጃ ቤት እንዲቀመጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የከተማ ፕላን የሚመለከቱ መረጃዎች የተለያዩ አካላት እንዲጠቀሙበት፣ ለልምድ ልውውጥ ለጥናትና ለምርምር ጭምር እንዲያግዙ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ስለከተማ ፕላን ዝግጅት እና አተገባበር ባለድርሻ አካላት (በተለይም የመሠረተ ልማት አቅራቢዎች) ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ክልሎችና ከተሞች የጋራ መግባቢያ ሰነድ ሊፈራረሙና ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡በማለት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

11.9 በባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም አገልግሎት ብቃት ማረጋገጥን በተመለከተ

የኦዲት ግኝቶች

<u>የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የሚመለከት ፖሊሲ አፈጻጸምን በተመለከተ</u>

231. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎቶች አሰጣጥ የሚመለከት ፖሊሲ ከሚመለከታቸው ባለድርሻና አስፈጻሚ አካላት ጋር

በመመካከር ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ የወጣውን ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችና መስፈርቶች ሊያወጣ ይገባል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲው፣ የወጡት ደንብና መመሪያዎችና መስፈርቶች ለሚመለከታቸው አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ሊያሰራጭና ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

232. ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ፖሊሲ አዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም የወጣውን ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎችን በማዘጋጅት ለክልሎችና ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ያሰራጨ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የአዲስ አበባ መስተዳድር ባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች በክልልም ሆነ በዞን እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ያሉ ቢሮዎች ላይ የመመሪያዎች አፈፃፀም ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ</u>

233. ሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፤ ሞቴሎች፤ ሎጆች፤ሬስቶራንቶች፤ አስጎብኚ ድርጅቶች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶችን ሊያወጣ ይገባል፡፡ በወጣውም መስፈርት መሰረት ተቋማቱን በመመዘን ለተቋማቱ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ትክክለኛውን ደረጃ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ደረጃ የተሰጣቸው ተቋማት በተሰጣቸው ደረጃ መሥራታቸውን ሊከታተል፣ ሊቆጣጠርና የተቋማቱን ደረጃም ተገልጋዩ ህብረተሰብ እንዲያውቀው ሊደረግ ይገባል፡፡

234. ይሁን እንጂ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣ የባህል ምግብ ቤቶች) በኮከብ ደረጃ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ ቢሆንም የሆቴሎች የደረጃ ምደባ ስራ ተጠናቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ነገር ግን በተለያየ የኮከብ ደረጃ ራሳቸውን መድበው ራሳቸውን እያስተዋወቁ ያሉ ሆቴሎች ላይም ስለአገልግሎት አሰጣጣቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የቱሪዝም ቢሮዎች የተጠናከረ የክትትል እና የቁጥጥር ስራ የማይከናወን መሆኑና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉድለት በሚታይባቸው ሆቴሎች ላይ እርምጃ የማይወሰዱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

235. በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ 2003 ዓ.ም ከተዘጋጀው መስፈርት ናሙና በመውሰድ በሀዋሳ፣ በባህርዳር፣ በቢሾፍቱ፣እና በአዲስ አበባ ከተሞች በናሙና ከታዩት ባለሦስት ኮከብ እና ከዛ በላይ ናቸው ከሚባሉት 32 ሆቴሎች መካከል፤ መስፈርቱ የሚጠይቀውን፡- የሆቴሉ ውበትና እይታ ለእንግዶች አመቺ ያልሆኑ 9፣ በቂ የመኪና ማቆሚያ (parking) የሌላቸው 14፣ የእንግዳ ማረፊያ (loby) ክፍል፣ የኢንተርኔት እና የፅህፈት አገልግሎት የሚሰጥበት ቢዝነስ ሴንተር የሌላቸው 15፣ የእንግዳ ንብረት ማስቀመጫ ካዝና በየክፍሉ የሌላቸው 16፣ ሲፈለግ የሚቀርብ የህፃናት አልጋ (baby coach) የሌላቸው 16፣ ሲፈለግ የሚቀርብ ተጨማሪ አልጋ (extra bed) የሌላቸው 4፣ ሱት(suite) ክፍሎቻቸውን በተመለከተ ማሟላት የሚገባቸውን ቁሳቁሶች በየክፍሉ ሻይ፤ ቡና ማፍያና ቢላ ማንኪያ ሹካ ያላሟሉ 4፣ ምግብ ቤቱን በተመለከተ 2 ምግብ ቤት (restaurant) የሌላቸው 5፣ ሁለገብ አዳራሽ (function hall) የሌላቸው 2፣ የምግብ ዝግጅት ክፍልን (kitchen) በተመለከተ በጣም ከፍተኛ በሆኑ መሳሪያዎች የተደራጀ የእቃ ማጠቢያ ክፍል የሌላቸው 3፣

የልብስ ንፅህና መስጫ ክፍል (laundary) በተመለከተ እራሱን የቻለ ዘመናዊ የማጠቢያ፣የማድረቂያ እና የሙተኮሻ መሳሪያ የሌላቸው 3፣ የእቃ ግምጃ ቤት (store) በተመለከተ ቢያንስ 2 የእቃ ግምጃ ቤት የሌላቸው 2፣ ሀይጅን ንፅህና (hygiene and sanitation) በተመለከተ 2፣ ደህንነት ጥበቃ (safety and security) በተመለከተ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ ደውል የሌላቸው 11፣ ህንፃው ከ2 ፎቅ በላይ ከሆነ የአደጋ ጊዜ መውጫ የሌላቸው 12፣ በኮምፒውተር የታገዘ የሻንጣ መፈተሻ ማሽን የሌላቸው 15፣ ዘመናዊ የደህንነት ካሜራ (security surveillance camera) የሌላቸው 11፣ ዊልቸር (wheelchair) የሌላቸው 23፣ የሆቴሉ እንግዶች በድርጅቱ አገልግሎት ሲጠቀሙ በሚደርስባቸው አደጋ ለሚከሰት ጉዳትና እሳት አደጋ ኢንሹራንስ የሌላቸው 32፣ ሰራተኞች ማንነታቸውን የሚገልፅ የደረት ላይ መታወቂያ (ባጅ) የሌላቸው 6 ያላሟሉ ሆቴሎች ተገኝተዋል፡፡

236. ስለጉዳዩ በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ኃላፊዎች ተጠይቀው የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች) በኮከብ ደረጃ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት የተዘጋጁ ቢሆንም የሆቴሎች የደረጃ ምደባ ስራ ተጠናቆ ተግባራዊ ባለመደረጉ ምክንያት በፌደራል ደረጃ ሆነ በክልል የሚገኙ ትላልቅ ሆቴሎች ላይ የቁጥጥር ስራ ለማከናወን አስቸጋሪ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) በተመለከተ

237. ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ሊወጣላቸው እና ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም የባሕል ምግብ ቤቶች የአገሪቱን ባህልና ልማድ በበጎ ጎኑ የሚያንጸባርቁ መሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

238. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልልች የባሕል ምግብ ቤቶችና ሬስቶራንቶች ምን መስፈርት ሟሟላት እንደሚገባቸው መስፈርት እንዳልወጣላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በባሕርዳር ከተማ የቡሉናይል ሆቴል ከፊት ለፊቱ ያሉ ምግብ ቤቶች ፈቃዱን በምግብ ቤት ካወጡ በኋላ ማታ ማታ የባሕል ጭፈራ ቤቶች በመሆናቸው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ሀገር ቱሪስቶች በሆቴሉ ካረፉ በኋላ ሌሊት ከጭፈራ ቤቱ በሚወጣው ድምፅ ሰላማቸውን የሚያጡበት ሁኔታ መኖሩን ይህንን ጉዳይ ለክልሉም ሆነ ለከተማው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በተደጋጋሚ ቢያሳውቁም ምንም አይነት ምላሽ እንዳላገኙ ባለሀብቱ ገልፀዋል፡፡

239. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ምላሽ ሲሰጡ ለቱሪስት አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ የባሕል ምግብ ቤቶች (ሬስቶራንቶች) ደረጃ ያልወጣላቸው መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት ቤቱ ለባህል ምግብ ቤት ምቹ መሆኑን እንዲሁም በቤቱ ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች የአካባቢውን ባህል የሚወክሉ የሀገሪቱንም እሴቶች የጠበቁ

መሆናቸውን የሚረጋገጥ ቢሆንም አንዳንድ የባሕል ምግብ ቤቶች ፈቃዱን ያወጡት በባሕል ምግብ ቤት ሆኖ እያለ ማታ ማታ ፈቃድ ሳይጠይቁ የባህል ምሽት ቤቶች የሚያደርጉ መኖራቸውን እንዲሁም አብዛኞቹ ቤቱን በመከራየት የሚሰሩ በመሆኑ ለዚህ ስራ ተብሎ የተዘጋጀ ቦታ ባለመሆኑና የድምፅ መከላከያ (Sound Proof) የሌላቸው በመሆኑ ከነዚህ ቤቶች የሚወጣው ድምፅ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ሰላምን እየነሳ እንደሚገኝና ድርጊቱ የሚከናወነው በምሽት በመሆኑ ለቢሮዎቹ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ማድረጉን፣ በተጨማሪም የአገሪቱን ባህልና ልማድ ጠብቀው እየሰሩና በአገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችን እያስተዋቁወቁ መሆኑን ለማረጋገጥና በዚህ አግባብ የማይሰሩትን የባህል ምሽት ቤቶችን ለመከታተልና አጥፊዎችንም ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

<u>የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አካባቢዎች ጽዳትን በተመለከተ</u>

240. የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት መስህብ ስፍራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ከሚመለከታቸው የክልልና የከተማ አካላት ጋር በመተባበር አካበቢው የሚጠበቅበት መመሪያ ወጥቶ ተግባራዊ የሚደረግበትን ሁኔታ ሊያመቻቹ ይገባል፡፡

241. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ክልሎች መካከል በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ በአሞራ ገደል አካባቢ የፅዳት ጉድለቶች መኖራቸውና እንዲሁም የልመና ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ፣ በሀዋሳ ሌክ ቪው ሆቴል ፊት ለፊት ለበርካታ ዓመታት ምንም አገልግሎት የማይሰጥ በቆርቆሮ የተሰራ መጋዘን መኖሩ ሀይቁ ፊት ለፊት እንዳይታይ ማድረጉ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህርዳር ብሉ ናይል ሪዞርት በመግቢያው በር ላይ የፍሳሽ

ማስወገጃ ቦይ ባለመኖሩ የተኛው ጎርፍ የሪዞርቱን ውበትና ዕይታ ከመቀነሱ ባሻገር ለእንግዶች መተላለፍያ መንገድ አስቸጋሪ መሆኑን በመስክ ኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

<u>በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች ግንባታን በተመለከተ</u>

242. በኮከብ ደረጃ የሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የሚገነቡበት ስፍራ በከተማው ማስተር ፕላን ውስጥ ሊካተት ይገባዋል፡፡ በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ንድፍ ስራ ከመጽደቁ በፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል የቱሪስት ቢሮዎች በኩል ለሆቴል አገልግሎት አመቺ መሆኑን የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

243. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በኮከብ ደረጃ የሚገኙ ትላልቅ ሆቴሎች የሚገነቡበት ቦታ በከተማው ማስተር ፕላን ውስጥ ተካተው አልተያዙም፣ የግንባታው ቦታም ለሆቴል አገልግሎት አመቺ መሆኑን የሚረጋገጥበት የአሰራር ስርአት በቢሮው እንደሌለ ገልጸው፣ ነገር ግን ግንባታው ከተጀመረ በኋላ መስፈርቱን ተከትሎ እንዲሰራ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል እናደርጋልን ሲሉ ገልፀዋል፡፡

244. ለባህርዳር ከተማ አስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ስፖርት መምሪያ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ቀደም ብለው የተገነቡ ሆቴሎችን በተመለከተ ምንም አይነት የምዘና አስተያየት መስጠት ባንችልም የማስፋፊያ ስራ በሚሰሩበት ወቅት አንዳንድ ድጋፍና ክትትል የምናደርግበት ሁኔታ አለ፡፡ የህንፃው ንድፈ ሀሳብ በአግባቡ ለመገምገም ተቋሙ በሙያተኛ ደረጃ የእውቀት ጉድለት (ክፍተት) ያለበት ሲሆን ከኢንቨስትመንት ተቋምን ከከተማ ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር

በመጀመሪያ ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችለው የጋራ መግባቢያ ሰነድ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም አልፎ አልፎ ከቢሮው እውቅና ውጪ የሚገነቡ ሆቴሎች እንዳሉና የምናውቃቸው ግንባታ ጀምረው ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት ጥያቄ ሲያቀርቡ ብቻ እንደሆነ ጨምረው ገልጸዋል፡፡ ለሆቴል ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ ሲሰሩ ቢገኙ እንኳን እርምጃ የሚወስዱበት የአሰራር ስርአት እንደሌለ አስታውቀዋል፡፡

245. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማትና አጠቃቀም የሥራ ሂደት አስተባባሪ ተጠይቀው ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡበት ሥርዓትም ሆነ በዚህ ሙያ የተመደበ ባለሙያም መ/ቤታችን የለውም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ሴክተራችን ስለግንባታዉም ሆነ ስለፈቃዱ የሚያውቅበት የአሰራር ሥርዓት የለውም ሲሉ ገልፀዋል፡፡

246. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው በክልል ደረጃ ለሆቴል ተለይቶ የተዘጋጁ ቦታዎች በግልፅ ተለይቶ ስለመቀመጣቸው ቢሮው የሚያውቀው ነገር እንደሌለ፣ በክልሉ ትልልቅ ሆቴሎች በሚገነቡበት ወቅት አስቀድሞ ለቢሮው የማሳወቅ ክፍተት ያለ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከቢሮው ጋር የጋራ ስምምነት እንዲገቡ ከተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት ለመስራት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

247. ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ለተባለው አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ በከፍተኛ ደረጃ ክፍተት

እንደሚታይ፣ ይህንን ስራ የሚከታተለው አካል ተለይቶ ስላልተቀመጠ አንዳንድ ባለሃብቶች ቦታው ለሆቴል አገልግሎት አመቺ ለመሆኑ በባለሙያ መጠናታቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ሳይኖር ገንዘብ ስላላችው ብቻ ፎቅ በዘፈቀደ እንደሚገነቡ ገልጸዋል፡፡ ይህንን ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ በመመሪያ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ከቢሮው እውቅና ውጪ የሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች ግንባታውን ከጨረሱ በኋላ ከቀረጥ ነፃ የተለያዩ ዕቃዎችን ለማስገባት እንዲፈቀድላቸው ከኢንቨስትመንት ቢሮ ወረቀት ይዘው ሲመጡ ነው ሆቴል እየሰሩ መሆኑን የምናውቀው እንጂ ስለ ህንፃ ይዘት ምን እንደሆነ የኛ ቢሮ የሚያየው ምንም ነገር ባለመኖሩ በዚህ በኩል ትልቅ ክፍተት ይታይበታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

<u>በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡትን የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በተመለከተ</u>

248. በሆቴል ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሃብቶች በህግ የተቀመጠው የመገልገያ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ የማስገባት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ባለሀብቶች የማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ሲጠይቁት የተጠየቀው ዕቃ ከሆቴል ስራ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ዝርዝሩን በማየትና በማረጋገጥ ሊፈቅድላቸው ይገባል፡፡ ወደ አገር ውስጥ በማበረታቻው ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ የሆቴል የቁሳቁስ እቃዎች፣ፊኒሽንግ ማቴሪያል እንዲሁም ተሽከርካሪዎች ሲገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ በዓይነት እና በብዛት መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡

249. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግስት እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በተላከ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች፣ ሎጆች እና አሰጎብኚ ድርጅቶች ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈቀዱ የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች የሚፈልጉት ዕቃ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ደብዳቤ ከመጻፍ ውጪ የተጠየቀው ዕቃ ከስራው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ የተጠየቀው ዕቃ ብዛትና በዓይነት የማያዩና ዕቃዎቹና መሣሪያዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡም ተዘርዝረው የሚያዝበት የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

250. ስለጉዳዩ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኃላፊዎች ተጠይቀው ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት ተለይተው የሚመዘገቡበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ የሚፈቀዱና የማይፈቀዱ እቃዎችን ዝርዝር ለማዘጋጀት ከፌዴራል፣ ከአዲስ አበባ፣ ከኦሮሚያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ ዕቀዎችን ምዝገባን ለማከናወን ደንብ እየተዘጋጀ ሲሆን ደንብ ሲፀድቅ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የእቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት ተመዝግቦ የሚያዝበት አሰራር ይዘረጋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማበረታቻ የሚሆን ከቀረጥ ነፃ ወደአገር ውስጥ የሚገቡ የዕቃዎችን ዝርዝር በዓይነት እና በብዛት መዝግቦ ለመያዝ ትልቁ ክፍተት ማፅደቅ እና መቆጣጠር ላይ ነው የግንባታ እቃዎች ዝርዝር (Bill of quantity) የሚያዘጋጁት ባለሀብቱና ኮንትራክተሩ በመሆኑ ታማኒነቱ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ሆቴል ሲገነባ ክትትልና ቁጥጥሩ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከሚሰጠው የቀረጥ ነፃ መብት አንፃር ትልቅ የሀገር

ሀብት እየባከነ ግለሰቦች ያለአግባብ የሚከብሩበት ሁኔታን ያመቻቻል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

<u>በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች፣-ሎጆች እና አስጎብኝ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት ንብረቶች መረጃ አያያዝና ልውውጥን በተመለከተ፣</u>

251. የቱሪዝም አገልግሎት ለመስጠት አዲስ ኢንቨስት የሚያደርጉም ሆነ ነባር ድርጅታቸውን የማስፋፋያ ሥራ ለመስራት በመንግስት የተፈቀደውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የተለያዩ የግንባታና የሆቴል መገልገያ ዕቃዎችን እንዲያስገቡ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡ በማበረታቻው ተጠቅመው የገቡት ንብረቶች ዝርዝር መረጃ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተመዝግቦ ሊያዝና የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች መረጃው እንዲደርሳቸው የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

252. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከቀረጥ ነጻ ማበረታቻ መሰረት በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች እና ሎጆች፣ አስጎብኝ ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የጠየቁትን፣ በማበረታቻው ተጠቅመው ያስገቡትን የግንባታ፣ የቁሳቁስ እቃዎች፣ ፊኒሽንግ ማቴሪያል እና የተሽከርካሪዎች መረጃዎችን በተደራጀ ሁኔታ መዝግቦ የማይዝ መሆኑን፣ ከቀረጥ ነፃ ስለገቡት ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት ባለሀብቱም ሆነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማያሳውቁ መሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃው እንዲደርሰው የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት የሌለው በመሆኑ መረጃው እንደማይያዝ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችላል፡፡

የቱሪዝም አገልግሎትን ለማበረታታት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶች ለተባለላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን የሚደረገውን ክትትል በተመለከተ

253. ከቀረጥ ነጻ የገቡ ንብረቶችም ለተባለላቸው ዓላማ ብቻ መዋላቸውን ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ማበረታቻውንም ከተባለለት ዓላማ ውጭ ተጠቅመው የተገኙ ባለሃብቶች ላይም በህጉ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

254. ይሁን እንጂ በአዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በናሙና በታዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በኮከብ ደረጃ ለሚቋቋሙ ሆቴሎች እና ሎጆች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች እና ለነባር ድርጅቶች ማስፋፋያ በማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የተፈቀዱና ከቀረጥ ነጻ የገቡ የመገልገያ ቋሚ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች በዓይነት ተዘርዝረው የሚያዙበት የአሰራር ሥርዓት ባለመኖሩና መረጃው ስለሌላቸው እቃዎቹም ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ክትትል እንደማያደርጉ ታውቋል፡፡

የቱሪስት አገልግሎት የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝ፤ አደረጃጀት እና አጠቃቀምን በተመለከተ

255. ለቱሪስቶች የተሰጡ አገልግሎቶች በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዝርዝር መረጃ ሊይዙ ይገባል፡፡ እነዚህ መረጃዎችም ለሚመለከተው የክልል ቱሪዝም በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተጠናቅሮ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃዎች በክልልና በሚኒስቴር

መ/ቤቱ በኩል የሚለዋወጡበት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ቴክኖሎጂ ሊደገፍ ይገባል፡፡

256. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን መረጃዎች በተጠናቀረ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

257. በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና የድሬዳዋ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቱሪስቶቹን የሚመለከቱ መረጃዎች ሰብስቦና አደራጅቶ እንዲይዙ ለማድረግና ለእነርሱም እንዲያሳውቋቸው ለማድረግ የተጀመሩ ጅምር ሥራዎች መኖራቸውን ነገር ግን የመረጃ ፍሰቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የቱሪስት አገልግሎት በሚሰጡ የዘርፍ ተቋማትና የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋርያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ</u>

258. ባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና በክልል ያሉ ቱሪዝም ቢሮዎች፣በየደረጃው ያሉ ለቱሪስት አገልግሎት የሚውሉ የኢንቨስትመንት፣ የግንባታ፣ የንግድ ፈቃድ ወዘተ በሚሰጡ አካላት መካከል የደረጃ፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና የብቃት ማረጋገጥን ተግባር በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማከናወን በመካከላቸው የጠበቀ የስራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

259. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለደረጃ ሆቴሎች የድጋፍ አሰጣጥ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተናቦ

የመስራት ችግር ያለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

260. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና እንዲሁም በአዲስ አበባ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሥራ ክፍሎች መካከል የስራ ግንኙነት እና ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ነገር ግን በተጠናከረ መልኩ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልሎች ጋር ያለው ግንኙነትም የተጠናከረ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ከአንዳንድ መ/ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ የመስራት ችግር አለ (የንግድ ፍቃድ የሚሰጡ አካላት ንግድና እንዲስትሪ ቢሮ ተባባሪ አይደሉም፡፡ ለአንዳንድ ድርጅቶች ከቢሮው እውቅና ውጪ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት ሳያደርጉ ፍቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ መኖሩን አክለው ገልፀዋል፡፡

<u>የቱሪዝም አገልግሎት መስጪያ ተቋማት የፈጠሩትን የሥራ ዕድል በተመለከተ</u>

261. በሀገሪቱ ውስጥ በቱሪዝም አገልግሎት የተሰማሩ ተቋማት በከተሞችም ውስጥ ሆነ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ሲቋቋሙ የሚቀጥሯቸው ሰራተኞች ቢያንስ 70 ከመቶው የአካባቢው ህብረተሰብ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ ይገባል፡፡ የሚቀጠሩ ሠራተኞች የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ለማረጋገጥ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በምክክር ሊሰሩ ይገባል፡፡

262. ይሁን እንጂ በሀገሪቱ በከተሞችም ሆነ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች ከዘርፉ ከሚገኘው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ በተሰማሩ ባለሀብቶች/ድርጅቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ እና በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ባለመኖሩ እንዲሁም የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት የሰለጠነ የሰው ኃይል በየአካበቢው ለማፍራት የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ የአካባቢ ሕብረተሰቦች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እያደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

263. ስለጉዳዩ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተጠይቀው በሀገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ የሚቋቋሙ የቱሪዝም አገልግሎት መስጪያ ተቋማቶች የሚቀጥሯቸው ሰራተኞች ቢያንስ 70 ከመቶው የአካባቢው ህብረተሰብ ያማከለ ለማድረግ ቢፈለግም የሚቀጠሩ ሠራተኞች የቱሪዝም እንዱስትሪው የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያሟሉ ለማድረግ በአገሪቱ በዚህ ሴክተር ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማግኘት እጅግ ከባድ ሆኗል፡፡ ነገር ግን በተቻለ አቅም የአካባቢው ህብረተሰብ የሥራ ዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባላቸው ደረጃ ላይ የሙያ ክህሎታቸውን ለማሳደግ በሥልጠና እንዲታገዙ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

264. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የሆቴሎችና የሪዞርቶች ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በከተሞችም ሆነ የቱሪስት መዳረሻ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች የሆቴል እንዱስትሪው

የሚጠይቀውን የሙያ ክህሎት ያላቸው የሰለጠነ የሰው ኃይል የማያገኙ መሆኑና በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ለመቅጠር ከፍተኛ የሆነ ውድድር መኖሩን ገልፀዋል ፡፡

265. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ላይ በሰጡት መልስ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቁጥራቸው እንዲጨምር ወቅታዊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በአልፎ አልፎ የሚሰጥ ቢሆንም በበጀት እጥረት ምክንያት የሚቋረጥበት ሁኔታ መኖሩ፣ የማሰልጠኛ ተቋማት የጥራት ደረጃና የመቀበል አቅም ውስን መሆኑ እንዲሁም በገበያ ላይ በዘርፉ የሰለጠነ የባለሙያ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ በመኖሩ ችግሮቹን ለመቅረፍ ከሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋማት ቴክኒክና ሙያ (TVET) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የጋራ ስምምነት ለመፈራረም የተለያዩ ስራዎች ለመስራት በጅምር ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

<u>በኮከብ ደረጃ ላሉ ሆቴሎች የሚሰጥ በውጪ ምንዛሪ የመገበያየት ፈቃድን በተመለከተ</u>

266. የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ የሆኑ በኮከብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች ደንበኞቻቸውን በውጭ ምንዛሪ ከማተናገዳቸው በፊት ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም ፈቃዱን እንዲያገኙ ለባለሀብቶቹ ተገቢውን ድጋፍ ሊደርግ ይገባል፡፡ ፈቃድ የወሰዱ ባለሀብቶችም ፈቃዳቸውን በየአመቱ ሊያድሱ ይገባል፡፡

267. በኦዲቱ ወቅት ከብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ እንግዶቻቸውን ለማተናገድ ፈቃድ ለማውጣት ባለሀብቶች የሚኒስቴር መ/ቤቱን የትብብር ደብዳቤ እንዲጻፍላቸው ሲጠይቁ እንደሚሰጣቸው ታውቋል፡፡ በዚህ መሰረት ብሔራዊ ባንክ አስከ ግንቦት 2 ቀን 2006 ዓ.ም (እ.ኤ.አ እስከ 10/05/2014) ድረስ

ደንበኞቻቸውን በማስተናገድ በውጪ ምንዛሪ ገንዘብ የመሰብሰብ ፈቃድ ከሰጣቸው 175 ድርጅቶች ውስጥ 108 ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች፣ሎጆች፣ ሪዞርቶች እና አስጎብኚ ድርጅቶች ሲሆኑ በ 2006 ዓ.ም 10 ያላሳደሱ 27 ፈቃድ ካወጡ ዓመት ያልሆናቸው ናቸው፡፡

268. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ተጠይቀው በኮከብ ደረጃ ያሉ ሆቴሎች የውጪ ሀገር ዜጎችን ለማስተናገድ በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ እንዲያገኙ ባለሀብቶቹ የትብብር ደብዳቤ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይፃፍልን ብለው በሚያመለክቱት መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚጽፉ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ዙሪያ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚችል አካል ባለመኖሩ በአብዛኛው ፈቃድ ሳያወጡ በሕገወጥ መንገድ የውጪ ምንዛሪ የሚሰበስቡ ሆቴሎችም መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

269. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለብሔራዊ ባንክ ላይሰንሲንግ ኢንስፔክሽን ዋና ክፍል ኃላፊ ተጠይቀው ለቱሪስቶች አገልግሎት የሚሰጡት ተቋማት በውጭ ምንዛሪ የግብይት ፈቃድ የምንሰጠው ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኮከብ ደረጃ ናቸው ብሎ በላከልን ማረጋገጫ መሰረት እንጂ ባንኩ የኮከብ ደረጃ ይኑራቸው አይኑራቸው የማረጋገጥ ሥራ እንደማይሰራ ገልጸዋል፡፡ ፈቃድ ጠያቂዎች ባንኩ ያወጣውን መስፈርት አሟልተው መገኘታቸውን ቦታው ድረስ በመሄድ በራሱ ባለሙያ ከተረጋገጠ በኋላ ከአፈፃፀም መመሪያ ጋር ፈቃዱ ይሰጣቸዋል፡፡ ድርጅቶችም ባገኙት ፈቃድና ባንኩ ባወጣው መመሪያ መሰረት የውጪ ምንዛሪ በመቀበል ስራቸውን ያከናውናሉ በማለት ምላሽ

ሰጥተዋል፡፡ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኙ በሕገወጥ መንገድ የሚሰሩትን ድርጅቶችን ለመቆጣጠር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የያዘ ኮሚቴ ተቋቁሞ አንዳንድ ስራዎች የተጀመሩ ቢሆንም የተጠናከረ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

270. በመሆኑም

- የቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በሚመለከት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሰራር ማንዋሎች በሁሉም አስፈጻሚ አካላት ሥራ ላይ ተግባራዊ መደረጉም በሚኒስቴር መ/ቤቱና በክልል ቱሪዝም ቢሮዎች ክትትል ሊያደርጉና በአፈጻጸም ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮችም አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆቴሎች፣ ሞቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች፣) የአዘጋጀውን የኮከብ ደረጃ ምደባ ሥራ በአፋጣኝ በመጀመር ደረጃ በመስጠት ተገልጋዩ ህብረተሰብም ለሚከፍለው ዋጋ ትክክለኛ አገልግሎት እንዲያገኝ ሊደረግና በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚታይ ጉድለቶችን ለመከላከል በአዲስ አበባም ሆነ በክልል ባሉ ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ስራ የሚሠራበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በውጭ ባለሙያዎች የደረጃ አሰጣጥ ሲከናወን የክህሎትና የሙያ ሽግግር እንዲኖር የሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የሚመለከታቸው የክልል ባለሙያዎች አብረው የሚሳተፉበት ሁኔታ የሚመቻችበት መንገድ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ለቱሪስቶች አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋሙ የባህል ምግብ ቤቶች የባህል ምሽት ቤቶች የሚሰጡትን አገልግሎት ምን መስፈርት ማሟላት እንደሚገባቸው የሚያሳውቅ ግልጽ

መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግና ተፈጻሚነቱም ላይ በሚመለከታቸው አካላት ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበትን የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የቱሪስት አገልግሎት የሚሰጡ የቱሪስት ተቋማት ሥፍራዎችና አካባቢያቸው ጽዳታቸው በአግባቡ የተጠበቀና ለተገልጋዮቹ ጥሩ መስህብ እንዲሆኑ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የክልልና የከተማ መስተዳደሮች ጋር በቅንጅት ክትትል እየተደረገ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆነ በክልል የሚመለከታቸው አካላት በኮከብ ደረጃ ለሚገነቡ ትላልቅ ሆቴሎች የህንጻው ግንባታ ስራ ከመከናወኑ በፊት የህንጻው ንድፍ ስራ ባለሀብቱ ሊሰራው ካሰበው ሆቴል ደረጃና ለሚጠበቅበት አገልግሎት አመቺ ስለመሆኑ የሚያረጋግጡበት ሥርዓት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ቱሪዝም ቢሮዎች የሚያረጋግጡበት ወይም አስተያየት የሚሰጡበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሆቴሎቹ የሚሰሩበት ስፍራ ለሆቴል ተብሎ በየከተሞቹ ማስተር ፕላን ተለይቶ በተቀመጠ ሥፍራ ሊሆንና አስፈላጊው መሰረት ልማት በቅድሚያ ሊሟላላቸው ትገባል፡፡
- በሆቴል ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት የትብብር ደብዳቤ ሲጠይቁ ለማገባት የፈለጉትን የዕቃ ዝርዝር ከሚገነቡት ሆቴል ጋር ያለው ተያያዥነት በአይነትና በብዛት አስፈላጊነቱ እያየና እያረጋገጠ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ እንዲፈቀድላቸው የትብብር ደብዳቤ ሊጽፍ ይገባል፡፡ ለክትትል ያመችም ዘንድ መረጃውን አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

- የቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት መሳሪያዎች፣ የመገልገያ ዕቃዎችና የግንባታ ዕቃዎች ብዛትና መጠን በትክክል እንዲታወቅ በሚመለከታቸው አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ የገቡት ዕቃዎችም ለተባለላቸው ዓላማ መዋላቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ከክልል የቱሪዝም ቢሮዎ ጋር በመቀናጀት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለቱሪዝም ፖሊሲ ማሻሻያ እንዲረዳና አገሪቱ ከዘርፉ ያገኘቸውን ጥቅም በግልጽ ለመረዳት እንዲቻል ለቱሪስት የተሰጡ አገልግሎት እና ሌሎች ቱሪዝም ነክ መረጃዎች በአገልግሎት ሰጪዎቹም ሆነ ዘርፉ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተጠናቅሮ በመያዝ ወቅቱን የጠበቀና ቀልጣፋ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት እና ከሌሎች የግንባታ፣ የፈቃድ እና የመሠረተ ልማት አቅራቢ ተቋማትና አስፈፃሚ መ/ቤቶች መካከል በተጠናከረ መልኩ ተቀናጅቶ የሚሰሩበት የተጠናቀረ የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በቱሪዝም አገልግሎት ዘርፍ በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲታገዝ ባለሀብቶች/ድርጅቶች እና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ ማሰልጠኛ ተቋማትን ጨምሮ ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ለማፍራት በመካከላቸው ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና የምክክር መድረክ ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚኒስቴር

መ/ቤቱና የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች ለተፈጻሚነቱ ሁኔታዎቹን ሊያመቻቹ ይገባል፡፡

- በውጪ ምንዛሪ የመሰብሰብ ፈቃድ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ያገኙት በአግባቡ መስራታቸውን፣ ፈቃዳቸውን በየወቅቱ ማሳደሳቸው እና ከባንኩ ፈቃድ ሳይወስዱ በውጭ ምንዛሪ እንዳይገበያዩ ለማድረግ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመቀናጀት የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በማለት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

11.10 የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል እና እንስሳት ምርምር ሥርዓት አፈጻጸም

የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች፡-

271. ለኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት ለሚውሉ እና ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ተልከው የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ የሚችሉ እንዲሁም የምግብ ጠቀሜታቸው ከፍተኛ የሆኑ የግብርና ምርቶችን ጥራታቸውን ለማሻሻል የሚያስችል አስፈላጊውን ምርምር ሊካሄድ ይገባል፡፡

    - በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረ ዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በ6ቱ (ቁሉምሳ፣ ወረር፣ ሆለታ፣ አምቦ፣ ባኮና አሶሳ) ከአከባቢያቸው ስነ ምህዳር ጋር የሚጣጣሙ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ሊውሉ የሚችሉ እና የግብርና የወጪ ምርትን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚያግዙ የግብርና ምርቶች በምርምሮች ማዕከላቱ በእቅድ ተይዘውና ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው በሚፈለገው ደረጃ የማይከናወኑ መሆኑ፣

- የቅባት እህሎች ጥራት ማሻሻያ ሙከራ አፈፃፀም በመልካሳ፣ በሆለታ፣ በወረር፣ በቁልምሳና በቦኮ እና በአምቦ ማዕከላት የተካሄዱት ምርምሮች አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች አተገባበር ላይ የአቅም ውስንነት ያለበት መሆኑ፣
- የቢራ ገብስን በጥራት ለማምረት የማያስችሉ ችግሮችና ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸው እነሱም ገብሱ በሚበቅልበት ወቅት አብሮ የሚበቅል የሲናር ችግር መኖር፣ ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተዘሩት ዘሮች ከሌላ ዝርያ ጋር የተቀላቀሉ በመሆናቸው አርሶ አደሮች ያመረቱት የቢራ ገብስ ጥራቱን ያልጠበቀ እንዲሆን በማድረጉ አርሶ አደሮች ካመረቱት ምርት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ያደረጋቸው መሆኑ፣
- በባቄላ፣ በአኩሪ አተር እና አተርን ጥራት ባለው መልኩ ለማምረት የሚያስችሉ ለዋግ፣ የትል እና የአረም መድሃኒት ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥናቶች እና የምርምር ውጤቶች በምርምር ማዕከላቱ ተከናውነው ነገር ግን ለተግባራዊነት ወደ አርሶ አደሩ ያልደረሱ መሆኑ፣
- በግብርና ምርምር ማዕከላቱ በተወሰነ ደረጃ በሚካሄዱ የቫይታሚንና የፕሮቲን ከፍተኛ ይዘት ያላቸውን የበቆሎና የስንዴ ዝርያዎች ውጤትን በግንዛቤ ማነስ ችግር ያልተጠቀሙበት መሆኑ ፣

272. በፌዴራል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ በግብርና ሚ/ር ግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የምርምር ድግግሞሽ (Duplication Of Effort) እንዳይኖር ሊደረግ ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣ ደብረ ዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳ፣ አምቦ፣ ባኮ፣ ወረር እና አሶሳ) በፌዴራል ግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ትስስርና ተግባቢነት የሌለ መሆኑ፣
- በማዕከላቱ የሚከናወኑ የምርምር ውጤቶችን በግብርና ኤክስቴንሽን እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየጊዜው በተከታታይነት የማያሳውቁ መሆኑን፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በፌዴራልና ክልል ምርምር ማዕከላት በመሰረታዊ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ፣ የማንጎ አመራረትና ድህረ ምርት አያያዝ ዘዴ፣ የወተት ከብት እርባታ ዘዴ፣ የበግና ፍየል ዕርባታ ሥልጠና፣ የሰሊጥ የተሻሻሉ አሰራሮች፣ በዶሮ እርባታ ላይ የተሰሩ ሥራዎች፤ዘመናዊ የበግና የፍየል ማድለብ ሥራ ሥልጠና እና የማንዋል ዝግጅት፤የእንስሳት መኖ እና አመጋገብ ዘዴ፤ቆዳና ሌጦን በአግባቡ የማምረት እና የመያዝ እንዲሁም ወደ ገበያ ማቅረብ ዘዴ የሥልጠና ማንዋል ዝግጅት፤የተሻሻሉ የንብ እርባታ ዘዴ፤ በስንዴ ዝርያ የማላመድ፣ በበቆሎና በተባይ መከላከል ዙሪያ በተደጋጋሚ/ በተመሳሳይ ወቅት እና ጊዜ ያለቅንጅት/ የተሰሩ/እየተሰሩ ያሉ የምርምር ተግባራት መኖራቸው፣

273. በኢንስቲትዩቱ በሚገኙ በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ያላቸውን ግብዓት እና የሰው ሃይል (scarce resource) በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራር ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በማዕከላቱ ሥር የሚገኙ ተመሳሳይ የምርምር ዘርፍ ላብራቶሪዎች የሚሠሩትን ሥራ አቀናጅተው የማይተገብሩ እና በአንዱ ዘርፍ ያለውን ላብራቶሪ ያለውን ዕቃ/ኬሚካል ሌላኛው ዘርፍ የማያውቀው መሆኑ፣
- በሁሉም ማዕከላት በሰብልና በእንሰሳት ዘርፎች በሚካሄዱ ምርምሮች አንዱ ምርምር ለሌላው የምርምር አይነት ግብአት እንዲሆን የሚያስችል ማለትም የኮምፖስት ሥራ፣ የከብት መኖን ከሌሎች ሰብሎች ጋር በማፈራረቅ፣ ለእንስሳት መኖ በማዋል ውጤታማ ሥራዎች የማይሰሩ መሆኑ፣ በቡድን ሊከናወኑ የሚችሉ የምርምር ስራዎችን በቡድን የማይሰሩ በመሆኑ አንድ ሰራተኛ ሥራ በሚለቅበት ወቅት ሌላው ሰራተኛ የተጀመሩ ተግባራትን ማስቀጠል ያልተቻለ መሆኑ፣

274. በአርብቶ አደርና እርጥበት አጠር አከባቢዎች በእንስሳት ሃብት ልማት፣ በእንስሳት መኖ በማምረትና በማሻሻል ዙሪያ የምርምር ውጤቶች/ቴክኖሎጂዎች/ ሊዘጋጁና ለተጠቃሚው ሊሰራጩ ይገባቸዋል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች (ወረር፣ ጅጅጋ እና አሶሳ) የእንስሳት ሃብት ልማት፣ የእንስሳት መኖና ምግብ የማምረትና የማሻሻል ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑ፣
- በእነዚህ አካባቢዎች የእንስሳት ዘርፍ ላብራቶሪ እንዲኖር አለመደረጉ፣ የእንስሳት ቴክኖሎጂ ሥርጭቱ ደካማ መሆኑ፣ የተሻሻሉ የወተት ከብት ዝርያዎች አቅርቦት አለመኖሩን፣

- የሲንክሮናይዜሽን (የኮርማና የጊደር ፍላጎት የማጣጣም ሥራ) ውጤታማ በማድረግ ተጠቃሚው ጋር እንዲደርስ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በቤንሻንጉል ክልል የእንስሳት እርባታ ስብጥር ወደ 47 በመቶ የሚወክሉት ፍየሎች መሆናቸውን መረጃዎች የሚያመለክቱ ቢሆንም በፍየሎች እና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ምርምር ያልተደረገ መሆኑ እና በንብ በሽታ እና በዶሮ እርባታ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ያልተደረገ መሆኑ፣

275. በሰብል እና በእንስሳት ዘርፎች የተገኙ የግብርና ውጤቶችን ግብይት ትስስርን ለመፍጠር እና አከባቢውን በይበልጥ ለማልማትና ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ተከናውኖ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱ ማዕከላት በሰብል እና በእንስሳት ዙሪያ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠርና ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በመልካሳ እና ቁሉምሳ የገበያ ትስስር ጥናቱ ባለመከናወኑ ድንች፣ ሽንኩርት እና ቲማቲም በአከባቢው በስፋት የሚመረት ቢሆንም የገበያ ችግር ያለባቸው መሆኑና በሆለታ በሰብል ዘርፍ ኑግ እና ተልባ ላይ አርሶ አደሩ ገበያ ላይ አቅርቦ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑ፣
- በእንስሳት ዘርፍ ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኤጀሬ፣ ደንዲ፣ ወልመራ፣ ጀልዱ፣ ጥቁር እንጪኒ፣ አቡሽጊ እና ቀቤና አከባቢ የመኖን ዘር እጥረት ለመቀነስ የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም የተመረቱ ዘሮችን አርሶ አደሮች በመሸጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚያስችላቸው ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑ፣

- በወረር በሰብል ዘርፍ ሰሊጥ፣ ስንዴና በቆሎ እንዲሁም በእንስሳት ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የእንስሳት ተዋጽኦን አርብቶ አደሩ/ከፊል አርብቶ አደሩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አለመቻላቸውን እንዲሁም በአሶሳ እና ባኮ አከባቢ አኩሪ አተር ለገበያ ቀርቦ ውጤታማ መሆን ያለመቻሉ፣

276. የህብረተሰቡን የግብርና ዕውቀት አድማስን ለማስፋፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶች ወደ አምራቹ መድረስ፣ መሰራጨትና አመቺ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች በልዩ ልዩ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች የማስተዋወቅ ተግባር መከናወን ይኖርበታል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት በግብርና ምርምር የተዘጋጁ የተለያዩ ማንዋሎች እንዲሁም ፓኬጆች በአከባቢው ቋንቋ ተተርጉመው ለባለድርሻ አካላት እና ለአርሶ አደሮች እንዲሰራጭ ያልተደረገ መሆኑ፣

- የተለያዩ ፓኬጆች እና የአሰራር ማንዋሎች በእንግሊዘኛ እና በአማርኛ ብቻ የተዘጋጁ ሲሆን በሌላ ቋንቋ (በሶማሊኛ፣ በአፋርኛ፣ በኦሮሚኛ...) ተተርጉመው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያልተደረገ መሆኑ፣

277. የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት...) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና መመሪያ እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል ጥናትና ምርምር ተከናውኖ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ህብረተሰቡ ለጉዳት እንዳይዳረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች የሚኖራቸውን ተጽኖ ለመቀነስ የአጠቃቀም ደንብና ሥርዓት እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያስችል ምርምር መካሄድ እንዳለበት ሃገራዊ

የግብርና ምርምር ፖሊሲና እስትራቴጂ የሚገልጽ ቢሆንም ያልተተገበረ መሆኑ፣

- በናሙና ተመርጠው በታዩ የምርምር ማዕከላት (ሆለታ፣አምቦ፣ ባኮ፣ አሶሳ፣ ደብረዘይት፣ መልካሳ፣ ቁሉምሳና ወረር) ማዕከላት የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት...) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ጥናት ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በተጠቀሱት ማዕከላት ከፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠቃቀም ጋር የተያያዘ የግንዛቤ ችግሮችን ለመቅረፍ የተሰሩ ስራዎች ባለመኖራቸው የአከባቢው ህብረተሰብ ኬሚካል የመጣባቸውን እቃዎችና በርሜሎች ለተለያዩ አገልግሎቶች (ለጋዝ፣ ለዘይት፣ ለውሃ...) የሚጠቀሙበት መሆኑ፣

278. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ምርምሮችን ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚከናወኑ ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እና ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተሰጡ ሥልጠናዎች በሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ውስጥ አፈጻጸማቸው ከዕቅድ ጋር ተነጻጸሮ የማይቀርብ መሆኑ፣ ሥልጠናዎች የሚለኩበት ወጥ የሆነ የመከታተያ ሥርዓት አለመኖሩ እና ግብረመልስ የማይሰጡ መሆኑ፣
- በቁሉምሳ በ2006 ዓ.ም በእንስሳት ምርምር የሥራ ሂደት የታቀደው ሥልጠና ለሌላ ጊዜ የተላለፈ መሆኑን፣ በአሶሳ በኩይሳ አርሶ አደሮች ለስልጠና ተመዝግበው በወቅቱ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ እና በወረር በበግ፣ በፍየል፣ በስንዴ፣ በሰሊጥ፣ በመኖ ዘሮች እንዲሁም በማዳቀል ሥራ

ዙሪያ ሥልጠና የተሰጣቸው ቢሆንም ግብረመልስ ያልተሰጠ መሆኑን፣

279. በኢንስቲትዩቱ የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ማዕከላት ሲመረጡ ግልጽ የሆነ መስፈርት (Criteria) ሊያወጡ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ እንዲሁም ለአርሶ አደሩ፣ለአርብቶ አደሩ እና በከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ የልቀት ማዕከል ሊኖር ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ ማዕከላት የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ ማዕከል (Implementing Center) ሆነው የተመረጡበትን መስፈርት የሚያሳይ ሰነድ ማግኘት አለመቻሉን እና የልቀት ማዕከላቱ ስነ ምህዳርን፣ የህብረተሰቡን አመራረት ሁኔታ፣ የማዕከላቱን ማስፈጸም አቅም ወ.ዘ.ተ መሰረት አድርገው ያልተመረጡ መሆኑ፣
- የማንጎ ምርት በስፋት በአሶሳ ያለ መሆኑን ማስረጃዎች የሚያመለክቱ ቢሆንም ማስተባበሪያው መልካሳ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም ከእንስሳት ጋር በተያያዘ ለአርብቶ አደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢ የልቀት ማዕከል የሌለ መሆኑ፣

280. የፌዴራል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች በአጭር ጊዜ ወደ ትግበራ ሊሸጋገሩ የሚችሉ፣ የሚፈለገውን ውጤት የሚሰጡና በአነስተኛ ወጪ ምርትን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርበታል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩ ስምንቱም ማዕከላት የምርምር ስራዎች ተግባራዊ እና ተግባራዊ ያልሆኑ እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውጤት ሊሰጡ የሚችሉና የማይችሉ ተብለው ተለይተው

በዕቅድ እንዲያዙ የማይደረጉ እና አፈጻጸማቸውም በዚሁ መልክ የማይቀርቡ መሆኑ፣

- በእንስሳት ዘርፍ የሚያዙ ዕቅዶች አብዘኛዎቹ በረጅም ጊዜ ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸው እና በእንስሳት ዘርፍ በነባር ዝርያዎች ላይ የሚደረገው ምርምር ሥራ ውስን መሆኑ፣
- እያንዳንዱ ቴክኖሎጂዎች ከቀረበ/ከተሰራጨ በኋላ ቴክኖሎጂዎቹን ወጪያቸውን መቀነስ እና በስፋት የማዳረስ ተግባር በማዕከላቱ አለመከናወኑን፣
- የመሬትን ለምነት ሊጠብቁ እና የፀረ- አረም ወጪን መቀነስ የሚችሉ (ኮምፖስት፣ ቬርሚ ኮምፖስት፣ አረምን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን በማፍለቅ...) ቴክኖሎጂዎችን በስፋት በማሰራጨት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አለመደረጉ፣

281. በግብርና ምርምር ማዕከላቱ የሚካሄደው የግብርና ምርምሮች የሚቀርቡ ቴክኖሎጂዎች ከአርሶ አደሮች ተጨባጭ ችግሮች የሚነሱ እና ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት መስፈርት ወጥቶላቸው የችግሮቹን አንገብጋቢነትና ተቋሟዊ የማስፈፀም አቅምን ያገናዘቡ እና የባለድርሻ አካላትን ስምምነት ያገኙ ሆነው የተመረጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

- ለግብርና ምርምር የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግሮች የማይነሱ እና የባለድርሻ አካላትን ስምምነት እንዲያገኙ የማይደረግ መሆኑ፣
- በቁሉምሳ በእንስሳት እርባታ/ዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ፣ በተፈጥሮ ግጦሽ ማሻሻያ ዘዴ፣ በእንስሳት መኖ ችግሮች ላይ፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፣ በእንስሳት ጤና፣ በበቆሎ ዘር ዙሪያ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የጥቁር አፈር ምርታማነት መቀነስን፣ የጉራጌ ዞን የአፈር ኮምጣጣነትን (Soil Acidity)፣ በስምንት ወረዳዎች ላይ ውርጭ የተከሰተ መሆኑን እና በስልጤ ዞን የአፈር

ለምነት እና የማዳበሪያ አጠቃቀም ችግርን፤በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የስንዴ ዝርያዎች በዋግ በሽታ መመታት፣ ሙሎ ወረዳ አከባቢ ንቦችን ሚለቅሙ ወፎች መኖራቸና የጤፍ በመስመር መዝራት ሥራ አድካሚነትን፣ በዞኑ የሚገኙ የልማት አካላት ግንኙነት ደካማ መሆኑ፤ በአምቦ የእንስሳት በሽታ፣ የበርበሬ ቫይራል በሽታ እና የማንጎ በሽታ (White scale mango)፤ በወረር በእንስሳት እርባታ/ዝርያ ማሻሻያ ዙሪያ፣ በተፈጥሮ ግጦሽ ማሻሻያ ዘዴ፣ በእንስሳት መኖ ችግሮች ላይ፣ በእንስሳት ተዋጽኦ፣ በእንስሳት ጤና፣ በበቆሎ ዘር ዙሪያ ችግሮች መኖራቸው የተገለጹ ቢሆኑም እነኚህን ችግሮች ከመፍታት አንጻር የተሰራው ሥራ በጣም አነስተኛ መሆኑ፣

- በመልካሳ አከባቢ አርሶ አደሮች የእርሻ መሳሪያ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ በተደጋጋሚ ቢገልፁም (የቢቢኤም ብዜት፣ የጤፍ መውቂያ፣ የመኖ መከርተፊያና የፓፓያ ማውረጃ፣ የበቆሎ መፈልፈያ፣ የጤፍ መውቂያ መሳሪያ) የእርሻ መሣሪያዎች በማምረት ችግሮቹ እንዲፈቱ ያልተደረገ መሆኑ፣

282. በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች አገልግሎት የሚውል (ከአቅም፣ ፍላጎታቸው እና እድገታቸው) ጋር ሊጣጣም የሚችል ቴክኖሎጂ ሊቀርብ ይገባል፡፡

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች የቀረቡ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ እና በግብርና ሥራ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ተብሎ ተለይቶ የተሰራጨ ቴክኖሎጂ አለመኖሩ፣

283. የግብርና ምርምር ማዕከላት የተሻሻሉ የግብርና ግብዓቶች የአገሪቱን ህግና ደንብ ተከትሎ ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም ቴክኖሎጂ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ ከተካሄደ በኋላ በምርምር ማዕከል ደረጃ የማላመድና የምርታማነት ብቃት ፍተሻ ሊከናወን ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት በስምንቱም ማዕከላት ወደአገር ውስጥ የገባው ቴክኖሎጂ በኳራንቲን ቆይቶ የጤና ክትትል የተደረገለት እና ከበሽታ ነጻ መሆኑን የሚያመለክት ሪፖርት በማስረጃነት ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፣
- በማዕከላቱ ኳራንቲን በማቆየት ፍተሻ የማድረጉ ሥራ የላላ/ውስንነት ያለበት መሆኑ በዚህም ምክንያት በመልካሳ አከባቢ በአገራችን ያልተለመዱ ተባዮችና በሽታዎች ገብተው ጉዳት ያስከተሉበት ሁኔታ መኖሩ፣
- በወረር ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚመጡ ዝርያዎችና ቴክኖሎጂዎች የሀገሪቱን ህግና ደንብ ተከትለው ባለመግባታቸው የጥጥ ዝርያዎች፣ የቲማቲም ቦርቧሪ በሽታዎች መከሰታቸው እና በተጠቃሚዎች ላይ ጉዳትና ኪሳራ ያስከተሉ መሆኑ፣

284. በፌዴራል የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች፣ ግንባታዎች እና የምርምር ተግባራት የሚጀመርበት እና የሚጠናቀቅበት ጊዜና ወጭ በአግባቡ ሊታቀድ፣ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት በወቅቱ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም አስፈላጊው ድጋፍ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- በታዩት ስምንቱም ማዕከሎች እንዲከናወኑ የተደረጉ የምርምር ተግባራት በጥልቀት የሚፈጁት የገንዘብ መጠን ተተምኖ ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ አለመቅረቡን ፣ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት አጠቃላይ የፈጁት

ወጪ እና ጊዜ ከዕቅዱ ጋር ተነጻጽሮ በማስረጃ አለመቅረቡን እና ክትትል ያልተደረገ መሆኑ፣

- በወረር እና በአሶሳ ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸውና ከሶስት አመት በፊት ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የነበረባቸው በማዕከሉ የሚገኙ ህንጻዎች አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲሁም አገልግሎት መስጠት ሳይጀምሩ ለመፍረስ፣ ለመሰነጣጠቅ... እየተዳረጉ መሆኑ፣
- በወረር የግብርና ምርምር ማዕከል የሚገኝ የፓንፕ ሳይት ግንባታ በጥናት ላይ ተመስርቶ የተገነባ ባለመሆኑ ከ2003-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ 2,000,000 ብር (ሁለት ሚሊዮን ብር) ወጪ ተደርጎበት በ2006 ዓ.ም ግንባታው እንዲቋረጥ የተደረገ መሆኑ፣
- ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በናሙና ተመርጠው በአዲቱ በታዩት የምርምር ማዕከላት ውስጥ በአራቱ ማዕከላት (በሆለታ፣ መልካሳ፣ ወረርና ቁሉምሳ) ብቻ 63 የምርምር ተግባራት እንዲቋረጡ መደረጉ፣
- በአምቦ እየተካሄዱ የነበሩ ሶስት የግብርና ተግባራት (Activities) እንዲዘገዩ መደረጉን፣ በአሶሳ በማዕከሉ በሰብል እና እንስሳት ዘርፎች የሚቀርቡ የምርምር ውጤቶች አቅርቦት መዘግየት የሚታይባቸው መሆኑ፣

285. ኢንስቲትዩቱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ ወይም የሚካሄዱ የምርምር ውጤቶች፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማሩ ወይም የሚሰማሩ አካላት በሰራ ላይ እንዲያውሏቸው እነዚህ ተቋማትን መዝግቦ በመያዝ የምርምር ውጤቶቹን ለሚፈልጉ አካላት ሊሰጥ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱን የግብርና ምርምር ማዕከላት በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ/ የሚካሄዱ ምርምሮች ፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራ/ የሚሰማራ ማንኛውም አካል ተመዝግበው በኢንስቲትዩቱ በማዕከላዊነት ተይዘው መረጃዎቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ፣
- እንዲሁም ከ2004 -2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ 17ቱም ማዕከላት ያወጡትን የምርምር ውጤቶች ማስረጃ በማዕከላዊነት በኢንስቲትዩቱ እና በየማዕከላቱ ተጠናቅሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፣

286. ኢንስቲትዩቱ የግብርና ምርምር ማዕከላትን የዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀማቸውን የሚገመግምበት እና ግብረ መልስ የሚሰጥበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኢንስቲትዩት ስር የሚገኙ የምርምር ማዕከላትም በዕቅድ የሚይዛቸውን ስራዎች ውጤታማነት ለማረጋገጥ በአፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችና በወቅቱ ለይቶ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ኢንስቲትዩቱ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩ ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት የዕቅድ አፈጻጸም ሂደት በታቀደው መሰረት መሆኑንና የሚጠበቀውንም ውጤት ከያዘው ግብ አንጻር ክትትልና ግምገማ የሚከናወን ያለመሆኑ፣
- በግብርና ምርምር ማዕከላቱ ለአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ለሙከራ የሚሰራጨው ዘር ከመዝራት እስከ አጭዶ ሰብስቦ ማስገባት ደረስ ያለው ሂደት የክትትልና ቁጥጥር ሥራ አነስተኛ መሆኑ፣

- በማዕከላቱ ለአከባቢው ለግለሰብ የሚሸጠው ዘር ግለሰቡ ያለው መሬት ሳይጣራ የሚሸጥላቸው በመሆኑ ግለሰቦች መልሰው ለአርሶ አደሩ በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩ፣
- በማዕከላቱ አከባቢ ድንገት የሚከሰቱ ሁኔታዎችን (Emerging issues) /የመኖ እጥረት፣ የተባይና በሽታ ክስተት.../ ተከታትሎ የአርሶ አደር፣ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩን ችግር ለመፍታት የሚደረግ ጥረት ያለመኖሩ፣
- በወረር በ2006 ዓ.ም የጥጥ ላብራቶሪ ሥራ የቆመ መሆኑ እንዲሁም ኢንስቲትዩ የተከሰተውን ችግር በመለየት ተከታትሎ የማስቀጠል ስራ አለመሰራቱ፣
- በ2004 ዓ.ም በማዕከሉ የተባዙ የመኖ ዝርያዎች (ሮደስ፣ ፓኒከም፣ሲንክረስ/በፍል፣ ዝሆን ሳር፣ አልፋ አልፋ፣ ላብላብ፣ ለም አተር፣ ሰስባኒያና ሉኪኒያ) 20.2 ኩንታል ዘር የተባዛ መሆኑ፣ በ2005 ዓ.ም 15 ኩንታል ታቅዶ 8.3 ኩንታል የተባዛ መሆኑ፣ በ2004 ዓ.ም የዝሆን ሳር 50,000 (አምሳ ሺ) ቁርጥራጭ የተባዛ መሆኑ፣ እንዲሁም በ2005 ዓ.ም የስንዴ (ደንደአ፣ ሽሪማ፣ ህዳሴ-5595 ፣አጎልቾ-5520፣ ዲገሉ፣ ቀቀባ እና ጋአምቦ) 278.45 ኩንታል የተባዛ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ለአርብቶ አደሩ እና ለከፊል አርብቶ አደሩ እንዲሰራጭ እና ጥቅም ላይ እንዲውል አለመደረጉ፣
- በመልካሳ ማዕከል በ2004 ዓ.ም ዕቅዱ ከአፈጻጸሙ ጋር ሲነጻጸር የባዮቴክኖሎጂ ሰብል ጥበቃ አፈጻጸም 75.82%፣ እርሻ ኢኮኖሚክስና ምርምር ሥርጭት 57.13%፤ በ2005 ዓ.ም የባዮቴክኖሎጂና ሰብል ጥበቃ 75.54%፣ እንጨት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች 51.85%፤ በ2006 ዓ.ም ባዮ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም 37.02% እና የሰብል ጥበቃ 70%

ሲሆን አፈጻጸማቸው ከዕቅድ በታች መሆኑና ክትትል ተደርጎ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፣

- በመልካሳ በ2006 ዓ.ም የቦቆሎና ቦሎቄ ዘሮች ተዋውቀው ሳያልቁን ወደ ምርት እንዲለወጡ ሳይደረግ የBreeder Seed በነቀዝ ተበልቶ ከማዕከሉ የጠፋ መሆኑ፣
- በመልካሳ የምርምር ማዕከል የሚገኙ በተለያዩ የሥራ ሂደት ስር የሚገኙ ኬዝ ቲሞች የበጀት ዕቅድ የሚሰራውን ስራ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ፣

287. በኢንስቲትዩቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት በሩብ፣ በስድስት ወር እና በአመት ለኢንስቲትዩቱ የዕቅድና የዕቅድ ክንውን እንዲሁም ፋይናንሽያል አፈጻጸም ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

- በኢንስቲትዩቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ተመድቦላቸው የግብርና ምርምር የሚያከናውኑ አካላት በሩብ፣ በስድስት ወር እና በአመት ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ የዕቅድና የዕቅድ ክንውን እንዲሁም ፋይናንሽያል አፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፣
- በኢንስቲትዩቱ በጀት ተመድቦላቸው የምርምር ተግባራትን ሲያከናውኑ የቆዩ ከ41 እስከ 44 ለሚደርሱ ለክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ለ16 የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ተቋማት ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደውን በጀት በየጊዜው እንዲወራረድ ሳያደርግ እያስተላለፈ መቆየቱ እንዲሁም የዕቅድ ክንውንና የፋይናንሻል አፈጻጸም ሪፖርት ተከታትሎ እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ሥርዓት ባለመኖሩ ከ1999 በጀት አመት እስከ ሚያዚያ 7ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ጠቅላላ ድምር ብር 108,722,241.00 (አንድ መቶ ስምንት ሚሊዬን ሰባት

መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ አንድ) ተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

288. ኢንስቲትዩቱ በግብርና ምርምር ማዕከላት የሚፈለገውን የሰው ሃይል ስብጥር በማጥናትና መዋቅር ሊዘጋጅ እንዲሁም በመዋቅሩ መሰረት የምርምር ማዕከላቱ የሚያካሂዱትን ምርምር መሰረት ባደረገ መልኩ በሰው ሃይል እንዲሟሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት 8ቱም የምርምር ማዕከላት በየማዕከላቱ የሚፈለገው የተመራማሪ ብዛት እና የትምህርት ደረጃ (የቢኤስሲ/ቢኤ/ቢኢዲ፣ ኤም ቪ ኤስሲ/ኤምኤስ ሲ/ኤም ኤ፣ዲቪ ኤም እና ፒ ኤች ዲ) ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠንቶ የሚፈለገው የሰው ሃይል ስብጥር መዋቅር ያልተሰራ መሆኑ በዚህም ምክንያት የፒኤችዲ ያላቸው ተመራማሪዎች በአንድ ማዕከል ላይ በብዛት ተመድበው እየሰሩ የሚገኙ መሆኑ፣

289. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ለምርምር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ግዥ የተመራማሪዎችን ፍላጎትና መስፈርት (specification) መሰረት በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ የሌሎች ባለሙያዎችን አስተያየት በማገናዘብ በተመራማሪዎቹ የተጠየቁት ግዥዎች በወቅቱ ሊከናወኑ ይገባል፡፡

- በኢንስቲትዩቱ የተከናወኑ ግዥዎች በወቅቱና ማዕከላት በጠየቁት መስፈርት እንዲሁም በባለሙያ አስተያየት መሰረት የሚከናወኑ አለመሆኑ፣
- ከ2004- 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች በማዕከላቱ ግዥ እንዲፈፀም ቢጠየቁም በወቅቱ ተገዝተው እንዲቀርቡ አለመደረጋቸውን፣
- ከማዕከላቱ ፍላጎት ውጪ በኢንስቲትዩቱ ተገዝተው የተላኩና በማዕከላቱ መጋዘን ውስጥ ለረጅም ዓመታት የቆዩ

መሳሪያዎች (ቶነሮች፣ ኬሚካሎች፣ አካፋና ዶማዎች፣ የእርሻ መሳሪያዎች ወ.ዘ.ተ) መኖራቸው፣

- የሜካናይዜሽን የሥራ ሂደት ከተቀመጠው እስፔስፊኬሽን ውጭ ማለትም ፋላት አይረን ጠይቆ ሺት ሜታል የተገዛለት መሆኑ እና ከደረጃ በታች የሆኑ በቀላሉ የሚታጠፉ/የሚበላሹ/ እስኩዌር ፓይፖች እንዲሁም በቲሹ ካልቸር ከደረጃ በታች የሆኑ እና የማይገጥሙ ዲስፖዝብል ጃሮች የላብራቶሪ ዕቃዎች ተገዝተው የቀረቡ መሆኑ፣
- በአሶሳ ማዕከል ግዥዎች ከግዥ ሰራተኛ ውጭ በተለያዩ ባለሞያዎች የሚፈፀሙ መሆኑ፣ ለምርምር ሥራ በብር 92,000 የተገዛ 10,000 ሜትር ገመድ የተጠየቀው መስፈርት መሰረት ባለመገዛቱ ያለ አገልግሎት መቀመጡ፣
- በአምቦ ማዕከል ተመሳሳይ ፕሪንተር ሳይኖር ከኢንስቲትዩቱ የተላኩ ቶነሮች መኖራቸው፣ ሽንብራ በማይመረትበት አከባቢ (በቁሉምሳ) የሽንብራ መዝሪያ መሳሪያ ተቀምጦ መገኘቱ እንዲሁም በመልካሳ ማዕከል 1.5 ሚሊዮን ብር ሊያወጣ የሚችል የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች (አምፑሎች፣ ጋስኬቶች፣ ፍሬንቻዎች...) ከተፈለገው በላይ ተገዝቶ ለብዙ አመታት በጆንያ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

290. ኢንስቲትዩቱ በዋናው መ/ቤት እና በሁሉም የግብርና ምርምር ማዕከላት ስራ ላይ ሊውል የሚችል የንብረት አያያዝ እና አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም ለምርምር ማዕከላቱ የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች፣ ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸውና የማይሰሩት ንብረቶች በአግባቡ ሊወገዱ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት በስምንቱም የምርምር ማዕከላት የንብረት አያያዝ ሥርዓት እና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- በማዕከላቱ በተለያዩ ማከማቻዎች (እርሻ መሳሪያዎች ፣ኬሚካሎች፣ የተለያዩ ዘሮች፣ ጋራዦች) ንብረት እንዲይዙ የሚደረጉ ባለሙያዎች ስለ ንብረት አያያዙ ዕውቀት የሌላቸው መሆኑ፣
- በማዕከላቱ ሥር የሚገኙ ንብረቶች (የእርሻ መሳሪያዎች፣ የእርሻ ግብዕቶች፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች፣ ኬሚካሎች፣ ተሸከርካሪዎች እና ዘረ መሎች/germ plasm) በአግባቡ ተይዘው ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጋቸው፣ ተጠግነው አገልግሎት ላይ የማይውሉ ንብረቶች በአግባቡ እንዲወገዱ አለመደረጋቸው፣ የላብራቶሪ ንብረቶች በትክክል ስለመስራታቸው መለካት(calibrate) አለመደረጋቸው፣
- ከተገዙ 10 ዓመት ያለፋቸው መሳሪየዎች በአሶሳ ሁለት አፈር መፍጪያ (Soil Grinder)፣ የሴንተር ፉጋል መሳሪያ፣ የመስመር መዝሪያ (Row Planter)፣የመስመር ማውጫ (row maker)፣ የመሬት ማስተካከያ (land leveler)፣የውሃ መስመር (Irrigation pipe) እና መፈልፈያ፤ በባኮ ኦቨኖች፣ ግሮውዝ ቻምበር እና ስድስት የላብራቶሪ ሼልፎች፣ አገልግሎት ሳይሰጡ በየማዕከሉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በአምቦ ያለ ክፍሉ ለብዙ አመት የተቀመጠ እና አገልግሎት ያልሰጠ እስፔክትሮ ሜትር መሳሪያ እና ከ2004 ዓ.ም በፊት ተገዝቶ የመጡ ሁለት ጂ ፒ ሲ ካሜራዎች እና ሶስት ቶነሮች፣ አገልግሎት ሳይሰጡ በየማዕከሉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በቁሉምሳ በማዕከሉ የማይፈለጉ ለረጅም ጊዜ የቆዩ የሽንብራ መዝሪያ መሳሪያ፣ አራት ትናንሽ መውቂያ መሳሪያዎች፣

ብዛት ያላቸው ጎግሎች እና ብዛታቸው 10 የሆኑ St. steel Word Furnace long በማዕከሉ የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን እና ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየ Growth Chamber መሳሪያ መኖሩ፣

- በመልካሳ በማዕከሉ ስር የሚገኝ ሁለት የሐር መፍተያ ማሽን ለአምስት ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጡ ከሚወገዱ ንብረቶች ጋር ተቀላቅሎ በክምችት መጋዘን ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- እንዲሁም መወገድ የነበረባቸው ንብረቶች በ4ቱ ማዕከላት (አሶሳ፣ ሆለታ፣ ቁሉምሳ እና ወረር) የሚገኙ 22 ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ አለመደረጋቸው፣
- በመልካሳ 1.5 ሚሊዮን ብር ሊያወጣ የሚችል የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች (አምፑሎች፣ ጋስኬቶች፣ ፍሬንቻዎች...) በጅንያ ተቀምጠው ለሌላ አደጋ እየተጋለጡ ያሉበት ሁኔታ መኖሩን ፣
- በስምንቱም ማዕከላት ብዛት ያላቸው ኬሚካሎች ተከማችተው እንዲሁም የተበላሹ እና ያልተበላሹ ሳይለዩ በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ በሚችል መልኩ የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩ፣

291. ኢንስቲትዩቱ በስሩ የሚገኙ ማዕከላት ላይ ኦዲት በማከናወን የውስጥ ቁጥጥሩ እንዲጠናከር ሊያደርግ እና በኦዲቱ ወቅት በተለዩ የአሰራር ግድፈቶች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 ማዕከላት በሁለት ማዕከላት (አሶሳ እና ባኮ) ከ2004-2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለማዕከሉ የመደበ ቢሆንም የተመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም ማዕከሉ

ለተቋቋመበት አላማ ብቻ ማዋሉን የሚያመለክት የፋናንስ አፈጻጸም እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፣

292. የግብርና ምርምር ማዕከላት ከዘር እና ተረፈ ምርት ሽያጭ ገቢ ሲሰበስቡ ገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ሊያደርጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡

- በኢንስቲትዩቱ በህዳር 1999 ዓ.ም (እ/ም/እመ 79/1998) የወጣ የሽያጭ መመሪያ ቢኖርም በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም የግብርና ምርምር ማዕከላት ከተረፈ ምርት የሚያገኙትን ገቢ አሰባሰብን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ያላደረጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ያልዘረጉ መሆኑ፣ እንዲሁም በማዕከላቱ የተባዙ ዘሮች በወቅቱ ባለመሰራጨታቸው (ለሽያጭ ባለመቅረባቸው) ለነቀዝ የተጋለጡ መሆኑ፣
- በዘር ብዜት የተገኘ ዘር ሽያጭ በወቅቱ ባለመከናወኑ በመልካሳ በ2006 ዓ.ም የተባዙ 721.03 ኩንታል የበቆሎ፣ ቦለቄ እና ጤፍ ዘሮች ለነቀዝ እየተጋለጡ መሆኑ፣ በ2004/2005 ዓ.ም የምርት ዘመን 180 ኩንታል የሆነ በቆሎ ዘር ለነቀዝ የተጋለጠ መሆኑ እንዲሁም የማሽላ ዘሮች በብዛት በነቀዝ በመጠቃታቸው ዘሩን ለማቆየት አስቸጋሪ ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑ፣
- በቁሉምሳ 45.25 ኩንታል የሆነ የባቄላ ዘር ለነቀዝ የተጋለጠ መሆኑን፣
- በሆለታ 20 ኩንታል ባቄላ እና አተር በነቀዝ ተበልቶ ከጥቅም ውጪ መሆኑ፣

- በናሙና ተመርጠው በታዩት ስምንቱም ማዕከላት የዘር ብዜት ማከማቻ መጋዘን ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሃሳቦች፡-

- የሀገራችን 85% አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ እንደ መሆኑ መጠን የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ከፍ እንዲል በማድረግ አርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለመጨመር እንዲሁም የግብርናው ዘርፍ ወደ ኢንዱስትሪው የሚሸጋገርበትን ሁኔታ የበለጠ ለማገዝ ለወደፊቱ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት ሊውሉ የሚችሉ የግብርና ምርቶች ላይ ምርምር መካሄድ አለበት፡፡

- የግብርና ምርምር ውጤቶች እንዲስፋፉ ለማድረግ እና በአርሶ አደሩ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የምርምር ተግባራትን ለማከነወን እንዲቻል በፌዴራልግብርና ምርምር፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ጠንካራ የሥራ ትስስርና ተግባቢነት ሊኖር ይገባል፡፡

- በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ የምርምር ተግባራት ውጤታማ እንዲሆኑ እንዲሁም ተግባራቱን ሳይቋረጡ ለማስቀጠል እንዲቻል ተመራማሪዎች ተግባራትን በቡድን ሊፈጽሙ እና በተለያዩ የምርምር የሥራ ዘርፎች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡

- አገሪቷ ከፍተኛ የእንስሳት ኃብት ያላት በመሆኑ ይህን ያላትን የእንስሳት ኃብት ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ እና አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ በአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች የእንስሳት ሃብት ልማት፣ የእንስሳት መኖና ምግብ የማምረትና የማሻሻል ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት አለበት፡፡

- የግብርና ቴክኖሎጂዎችን አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በማምረት ጥራትና ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ ሽጠው ለመጠቀምና በዚህ ሂደት ገበያቸው በቀጣይነት እንዲያድግ ለማስቻል በሰብል እና በእንስሳት ዙሪያ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር እንዲሁም የህዝቡን ባህል ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶች ተከናውነው ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡
- አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች የምርምር ውጤቶችን መርጠው እንዲጠቀሙ እና ለማስፋፋት እንዲችሉ በኢንስቲትዩቱ የተዘጋጁ የተለያዩ ማንዋሎች እንዲሁም ፓኬጆች በአከባቢው ቋንቋ ተተርጉመው ለባለድርሻ አካላት እና ለአርሶ አደሮች ሊሰራጩ ይገባል፡፡
- የተባይ መከላከያ ኬሚካሎች በአከባቢ (በሰው፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት) ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ጥናት ተጠንቶ ተግባራዊ ሊደረግ እንዲሁም ለተጠቃሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡
- በአገራችን የሚከናወኑ የግብርና ምርቶች በአብዘኛው በዝናብ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ በወቅቱ አምርቶ ተጠቃሚ ለመሆን እንዲችል ከግብርና ምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በወቅቱና በዕቅዳቸው መሰረት ሊከናወኑ እና የተጠቃሚውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የተሰጠው ሥልጠና በተግባር ስለመዋሉ ሊገመገም ይገባል፡፡
- በአገራችን ሁሉንም በግብርናው ዘርፍ ተሰማርቶ የሚገኘውን የህብረተሰብ አካል ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል ማዕከላት የልቀት (Center of Excellency) እና የትግበራ (Implementing Center) ሆነው ሲመረጡ በጥናት ወይም በመስፈርት ላይ ተመረኩዘው ሊመረጡ ይገባል፡፡

- ጥራታቸውን የጠበቁ ቴክኖሎጂዎች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ለአርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮቹ ለማሰራጨት እንዲቻል በግብርና መስኮች የሚካሄዱ ምርምሮች ተግባራዊ ምርምር፣ በአጭር ጊዜ ውጤት የሚሰጡና በአነስተኛ ወጪ ምርትን የሚያሳድጉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- የግብርና ምርምር ውጤቶችን አርሶ/አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ በስፋት እንዲሳተፍባቸው እና ውጤታማ ሊሆንባቸው የሚችልባቸውን የምርምር ውጤቶች በፍላጎቱ መሰረት መርጦ ለመጠቀም እንዲችል የሚካሄደው የግብርና ምርምርና የሚቀርበው ቴክኖሎጂ ከአርሶ አደሩ ተጨባጭ ችግር የሚነሱ እና ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት መስፈርት ወጥቶላቸው መመረጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- በግብርና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ከአቅማቸው ጋር የሚመጣጠን ቴክኖሎጂ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ወደ አገራችን የሚገቡ የግብርና ቴክኖሎጂዎች የተለያዩ በሽታዎችና ጸረ-ሰብል ነፍሳትን ይዘው እንዳይገቡ በቅድሚያ ኳራንቲን በማቆየት የጤና ክትትል ከተደረገ በኋላ ቴክኖሎጂው ከበሽታ ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
- ለኢንስቲትዩቱ የተመደበው ገንዘብ ለብክነት እንዳይዳረግ እንዲሁም ግንባታዎቹ በወቅቱ ተጠናቀው መስጠት የለባቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚከናወኑ ግንባታዎች፣ የምርምር ፕሮጀክቶች እና ተግባራት ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲጠናቀቁ ሊደረጉ፤ በማዕከላቱ እንዲከናወኑ የሚደረጉ ተግባራት በጥልቀት የሚፈጁት የገንዘብ መጠን ተተምኖ ከአፈጻጸሙ ጋር ተነጻጽሮ ሊቀርቡ፤ እንዲሁም እያንዳንዱ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት አጠቃላይ የፈጁት ወጪ እና ጊዜ፣ መፍጀት ከነበረባቸው ጋር ተነጻጽሮ መቅረብ አለበት፡፡

- የምርምር ውጤቶች ለሁሉም በግብርና ሥራ ለተሰማሩ ተጠቃሚዎች ለማስፋፋት እንዲሁም የድግግሞሽ ሥራን ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱ/ የሚካሄዱ ምርምሮች፣ በአገር ውስጥ የሚገኙ የብዜት ተቋማት እና በምርምር ሥራ ላይ የተሰማራ/ የሚሰማራ ማንኛውም አካል ተመዝግበው በኢንስቲትዩቱ በማዕከላዊነት ተይዘው መረጃዎቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የግብርና ምርምር ውጤቶችን ወጥና ተከታታይ በሆነ መልኩ ለማስፋፋት እና ማዕከላቱን ውጤታማ ለማድረግ የምርምር ተግባራት የዕቅድ አፈጻጸሙ ሂደት በታቀደው መሰረት መሆኑንና የሚጠበቀውንም ውጤት በመጨረሻ ከማስመዝገብ አንጻር ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር እንዲሁም የሀብት ብክነት እንዳይኖር ለማስቻል የክልል ግብርና ምርምር ማዕከላትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም 17ቱም የፌዴራል ግብርና ምርምር ማዕከላት ለኢንስቲትዩቱ የፋይናንሽያል እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በሁሉም ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር ተግባራት ወጥ እና ተመጣጣኝ የሆነ ውጤት ማስገኘት እንዲችሉ በየማዕከላቱ የሚፈለገው የተመራማሪ ብዛት እና የትምህርት ደረጃ ተጠንቶ ሊታወቅ እና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የግዥ ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም ተገዝተው የቀረቡ ንብረቶች ለሌላ ብክነት ሳይጋለጡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለመድረግ እንዲቻል በኢንስቲትዩቱ የሚናወኑ ግዥዎች በወቅቱና በተጠየቀው መስፈርት እንዲሁም በባለሙያ አስተያየት መሰረት መሆን አለበት፡፡

- የንብረት አያያዝ ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በኢንስቲትዩቱ የተገዙ ንብረቶች/ መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረጉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸውና የማይሰሩት ሊወገዱ ይገባል፡፡
- የተመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም ማዕከሉ ለተቋቋመበት አላማ ብቻ ማዋሉን ለማረጋገጥ በውስጥ ቁጥጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ክትትል ሊያደርጉ/ኦዲት ሊያከናውኑና በአሰራር ወቅት በተለዩ ግድፈቶች ላይ አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡
- የግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓት እንዲኖር እንዲሁም ከውስጥ የሚሰበሰብውን ገቢ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሽያጭ መመሪያን ተግባራዊ ሊያደርጉና ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግተው ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

11.11 በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የሚከናወነው የጭነት አስተላላፊነት /የክሊሪንግና የፎርዋርዲንግ/ እንዲሁም የደረቅ ወደብ አገልግሎት አሰጣጥ

በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የሚከናወነው የጭነት አስተላላፊነት /የክሊሪንግና የፎርዋርዲንግ/ እንዲሁም የደረቅ ወደብ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ

በጭነት ማስተላለፍ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች ስትራቴጂክ ዕቅድ የተዘጋጀና በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት በየበጀት ዓመቱ በመመንዘር ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ

293. በጭነት ማስተላለፍ ዘርፍ ለሚሰጡ አገልግሎቶች ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት በየበጀት ዓመቱ ሊመነዘርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከ2004 ዓ.ም. በፊት ሦስቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች (የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ አክሲዮን ማህበር፣ የባሕርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት እና የደረቅ ወደብ አገልግሎት

ድርጅት) በተናጠል የራሳቸውን የአምስት ዓመታት (2003 - 2007) ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅተው በመተግበር ላይ እንደነበሩ፣ ሆኖም ግን በሀገራችን የተመዘገበውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ የገቢና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴው በመጠን እና በዓይነት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመምጣቱ ይህንን ዕድገት ሊሸከምና ሊደግፍ የሚያስችል የትራንስፖርትና የሎጅስቲክስ ዘርፍ ማቋቋም በማስፈለጉ ቀደም ሲል በተናጠል ይሰሩ የነበሩትን ሶስቱን የመንግስት የልማት ድርጅቶች አንድ ላይ በማዋሀድና በማቀናጀት በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 ህዳር 11 ቀን 2004 ዓ.ም "የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት" በመባል እንዲቋቋም እንደተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በአዲሱ አወቃቀር ድርጅቱ (ኢባትሎአድ) የተሰጠውን ዓላማ መሠረት በማድረግ ሀገሪቱ በዘርፉ ያለችበትን ነባራዊም ሆነ አለማቀፋዊ ሁኔታዎች በመዳሰስ እና አገራዊ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ግብዓቶች ታሳቢ በማድረግ እንዲሁም በድርጅቱ ስር ያሉትን ዘርፎች ያቀናጀና ያጣጣመ፣ ከውህደቱ በኃላ ባሉት በቀሪዎቹ ስትራቴጂክ ዓመታት /2004 - 2007/ ምን መስራት እንዳለበት እና ከየት ተነስቶ የት መድረስ እንደሚገባው አመላካች የሆነ ተቋማዊ /Corporate/ ስትራቴጂክ ዕቅድ በወቅቱ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረጉንና በየበጀት ዓመቱ በመመንዘር ተግባራዊ በማድረግ አፈፃፀሙን በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ከተዘጋጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ አንፃር የሚገመግም መሆኑን በተመለከተ በአዲቱ ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ በ2004 እና በ2005 የበጀት ዓመታት አዲሱ ድርጅት አንድ ወጥ የሆነ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እንዳልነበረው፣ በመሆኑም ከ2004 እስከ ህዳር 2006 ባሉት በጀት ዓመታት በጭነት ማስተላለፍ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቋም ደረጃ በተዘጋጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ

መሰረት በየበጀት ዓመቱ በመመንዘር ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉን፣

- ✓ ከጥር 2004 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነ የ2004 በጀት ዓመት የሁለተኛ መንፈቀ-ዓመት እንዲሁም የ2005 እና የ2006 በጀት ዓመታት ወጥ የኮርፖሬት ዓመታዊ ዕቅድ በድርጅቱ (ኢባትሎአድ) የተዘጋጀ ሲሆን፣ ዘርፉም በዚህ መሰረት የበጀት ዓመታቱን ዕቅድ በመተግበር አፈፃፀሙን ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ እና ካለፈው በጀት ዓመት ክንውን አንፃር የሚገመግም ቢሆንም፣ ሀገሪቱ በዘርፉ ያለችበትን ነባራዊም ሆነ አለማቀፋዊ ሁኔታዎች በመዳሰስ እና አገራዊ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተቀመጠውን ግብ ከማሳካት አንፃር በዕቅድ ዓመታቱ ምን ያህል ማከናወን እንዳለበት እና የት መድረስ እንደሚገባው አመላካች ከሆነ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አስተሳሰብ አንፃር እንዲገመገም ይደረግ እንዳልነበረ፣ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>በዕቅድ ለተቀመጠው የገቢና ወጪ ዕቃዎች አይነትና መጠን የዕቃ አስተላላፊነት አገልግሎት መስጠትን በተመለከተ</u>

294. በዕቅድ ለተቀመጠው የገቢና ወጪ ዕቃዎች አይነትና መጠን በሀገር ውስጥ እንዲሁም በጅቡቲ ወደብ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የክሊሪንግና ፎርዋርዲንግ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ የተጠናከረ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚሰጥ አገልግሎት ሽፋንና አድማስን በማሳደግ ከየካቲት 1/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ የኮንቴይነር ጭነቶች በሙሉ እና ከ3 ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲገቡ የተላለፈ መመሪያ መኖሩን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ይህ መመሪያ ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ ያሉት የበጀት ዓመታት ዕቅድ ይህን መመሪያ ከማስፈፀም አንፃር የሚታቀድ መሆኑን በተመለከተ መረጃዎች በተከለሱበት ወቅት ከዚህ በታች በተገለፁት መሰረት፡-

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ወደ አገር የሚገባውን ኮንቴይነሮችና ጥቅል ደረቅ ዕቃ እስከ ሰኔ 2004 ዓ.ም. መጨረሻ ሙሉ በሙሉ ማስተናገድ የሚያስችል አቅም መገንባት፣
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት ከሀገሪቱ ኮንቴይነራይዝድ ጭነቶች በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚስተናገደውን የአገልግሎት ሽፋን በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 50% ማድረስ፣ እና
- ✓ በ2006 በጀት ዓመት ደግሞ በድርጅቱ አማካኝነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚጓጓዘውን ኮንቴይነራይዝድ ጭነቶች በ2005 በጀት ዓመት ካለበት 57 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማድረስ የሚሉት ብቻ ናቸው፡፡

295. በመሆኑም የ2004 ሁለተኛ መንፈቅ አመት፣ የ2005 በጀት ዓመት እንዲሁም የ2006 በጀት ዓመት ዕቅዶች ሁሉም የኮንቴይነር ጭነቶች እና ከ3 ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ ከየካቲት 1/2004 ጀምሮ በመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲገቡ የተላለፈውን መመሪያ ከማስፈፀም አንፃር እንዳልተዘጋጁ/እንዳልታቀዱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም. ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት ያለው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት አፈፃፀም በድርጅቱ ከተያዘው ዓመታዊ ዕቅድ እንዲሁም ሁሉም የኮንቴይነር ጭነቶች እና ከ3 ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ ከየካቲት 1/2004 ጀምሮ በመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲገቡ ከተላለፈው መመሪያ አኳያ ሲገመገም የሚከተለው ተገኝቷል፡-

- ✓ በ2004 ዓ.ም. በበጀት ዓመቱ ለ11,000 ኮንቴይነር/በTEU/ እና ለ450 ተሽከርካሪዎች/በቁጥር/ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ

የነበረ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ 27,084 ኮንቴይነር/በTEU/ (የዕቅዱን 246%) እና ተሽከርካሪ (RORO[1]) በቁጥር 4,422 (የዕቅዱን 982%) መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በድርጅቱ በባህር ከተጓጓዘው 128,476 ኮንቴይነር አንፃር የዕቅዱን 21% እና 18,962 ተሽከርካሪ/ በቁጥር/ አንፃር የዕቅዱን 23% ብቻ እንደሆነ፣

- ✓ በ2005 በበጀት ዓመት ለ93,668 ኮንቴይነር/በTEU/ እና ለ7,223 ተሽከርካሪዎች/በቁጥር/ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ አፈፃፀሙ 67,389 ኮንቴይነር/በTEU/ (የዕቅዱን 72%)፣ እና 3,931 ተሽከርካሪ (RORO) በቁጥር (የዕቅዱን 54%) መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በድርጅቱ በባህር ከተጓጓዘው 117,238 ኮንቴይነር/በTEU/ አንፃር የዕቅዱን 57% እና 19,848 ተሽከርካሪ /በቁጥር/ አንፃር የዕቅዱን 20% ብቻ እንደሆነ፣ እንዲሁም
- ✓ በ2006 በጀት ዓመት ለ77,914 TEU ኮንቴይነርና ለ4,450 ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ የነበረና አፈፃፀሙ 88,525 ኮንቴይነር/በTEU/ (የዕቅዱን 114%) እና 4,100 ተሽከርካሪ (RORO) በቁጥር (የዕቅዱን 92%) መሆኑን፣ ይሁን እንጂ በድርጅቱ በባህር ከተጓጓዘው 130,638 ኮንቴይነር/በTEU/ አንፃር የዕቅዱን 68% እና 20,839 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ አንፃር የዕቅዱን 20% ብቻ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ✓ በተጨማሪም የ2005 በጀት ዓመት ዕቅድን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዘውን ኮንቴይነራይዝድ ጭነት አገልግሎት ሽፋን ወደ 76.5% ለማድረስ ታቅዶ እንደነበረና ይህም የሽፋን ዕቅድ በእጅጉ የተጋነነ እንደሆነ የመጀመሪያው ስድስት ወር አፈፃፀም ከተገመገመ በኃላ እቅዱ እንደገና እንዲከለስ ፕሮፖዛል ቀርቦ እቅዱ ቀድሞ ከተያዘው በ50 በመቶ ተስተካክሎ እንዲዘጋጅ የተደረገ መሆኑን በዚህም መሰረት

[1] RORO = Roll On Roll Out (ተሽከርካሪ)

አስቀድሞ ከተያዘው 93,668 ኮንቴይነር/በTEU/ ወደ 58,619 ኮንቴይነር/በTEU/ ዝቅ እንዲል በመደረጉ አፈፃፀሙን 115% እንዲሆን ማድረጉን፣

- ✓ እንዲሁም በመልቲሞዳል በባህር ተጓጉዘው ወደ ባህር ወደብ ከደረሱ ጭነቶች በ2005 በጀት ዓመት በመልቲሞዳል በባህር ላይ ከተጓጓዘው 82,000 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ውስጥ 14,611 ኮንቴይነር/በTEU/ ማለትም 17.8% እንዲሁም በ2006 በጀት ዓመት ደግሞ 21,978 ኮንቴይነሮች/በTEU/ እና በመልቲሞዳል በባህር ላይ ከተጓጓዘው 17,220 ተሽከርካሪ ውስጥ በቁጥር 13,120 ተሽከርካሪ (76.2%) የሆነ ጭነት ከመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት በአሜንድመንት /ማሻሻያ በማድረግ/ ወደ ዩኒሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት እንዲዛወር ተደርጎ በደንበኛው ከጅቡቲ እንዲጓጓዝ የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>በጭነት አስተላላፊነት አገልግሎት ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የጊዜ ተመን /ስታንደርድ/ መሰረት የሚከናወኑ መሆኑን በተመለከተ</u>

296. የዕቃ አስተላላፊነት አገልግሎትን፣ አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ በተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ የጊዜ ተመን (ስታንደርድ) መሰረት በማከናወን ዕቃዎች በወቅቱ ለጭነት ዝግጁ እንዲሆኑ እና ወደ ሀገር ውስጥ እንዲጓጓዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት በድርጅቱ ተጓጉዘው ባህር ወደብ የደረሱ ጭነቶችን የሚፈለገውን የወደብና የጉምሩክ ፎርማሊቲ በወቅቱ በማሟላት ጭነቱን ለመንገድ ትራንስፖርት ዝግጁ በማድረግና በመጫን በተቀመጠው የእፎይታ ጊዜ/8 ቀን/ ውስጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲጓጓዙ ለማድረግ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 18 ቀን 2006 ስለ መልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት በኢትዮጵያና በጅቡቲ መንግሥታት መካከል ስምምነት የተፈረመ

መሆኑንና፣ ከዚህ በተጨማሪ ይህን ውል መሰረት ያደረገ ለሁለቱም አገሮች ጠቃሚ የሆነ፣ የዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀና የመልቲ ሞዳል ሥርዓት ዓላማን በሚገባ እውን ለማድረግ የሚያስችል የወደብና የጉምሩክ ክሊራንስ አሰራር ስርአት ስምምነት እ.አ.አ. በኖቬምበር 9 ቀን 2008 እንዲፈረምና ተፈፃሚ እንዲሆን የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በስምምነቱ መሰረትም የጅቡቲ ትራንዚተሮች ማህበር/ Asociation of transporters of Djibouti/ በባህር ወደብ ያለውን ወደብና የጉምሩክ ክሊራንስ ስራ የሚያከናውን ሲሆን፣ ድርጅቱ /ኢባትሎአድ/ ደግሞ በጅቡቲ ትራንዚተሮች ማህበር/ATD/ የወደብና የጉምሩክ ክሊራንስ ፎርማሊቲ ተጠናቆ የቀረቡለትን ጭነቶች በወደቡ በተቀመጠው የእፎይታ ጊዜ ውስጥ ወደ ሀገር ውስጥ የማጓጓዝ ስራ እንደሚያከናውን የተገለፀ ሲሆን፣ በዚህ መሰረት ከ2004 እስከ 2006 ባሉት የበጀት ዓመታት የነበረውን ክንውን በተመለከተ፡-

- በ2004 በጀት ዓመት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚመጡ የገቢ ዕቃዎች (በቀጥታ ከመርከብ ወደ መኪና የሚራገፉትን ዕቃዎች /Direct Delivery Cargo/ ሳይጨምር) ከተራገፉበት ሰዓት ጀምሮ ባሉት 48 ሰዓታት ውስጥ ከጅቡቲ ወደብ እንዲነሱ ለማድረግ በድርጅቱ ግብ ተይዞ የነበረ ቢሆንም፣ አፈፃፀሙ በበጀት ዓመቱ የወደብና የጉምሩክ ክሊራንስ አሰራር ስርአት ላለው የእቃ መጠን ምቹ ባለመሆኑ፣ በአንድ ወጥ የመርከብ ባለቤት (Carrier) የሰነድ ክሊራንስ ስራ ማለቅ ሲገባው መጠኑ ከፍ ያለ ሥራ ትንሽ አቅም ባለው የጅቡቲ የትራንዚተሮች ማህበር እንዲከናወን በመደረጉ የሥራውን ሒደት የተንዛዛና ጎታች እንዲሆን ማድረጉንና፣ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በዩኒሞዳል የትራንስፖርት ስርዓት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ኮንቴነሮች አማካይ የቆይታ ጊዜ 45 ቀናት የነበረ ሲሆን፣ በመልቲሞዳል የትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዙ ጭነቶች ደግሞ የ23 ቀናት

አማካይ ቆይታ ጊዜ እንደነበራቸውና በዚህም ምክንያት በበጀት ዓመቱ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚመጡ የገቢ ዕቃዎች(በቀጥታ ከመርከብ ወደ መኪና የሚራገፉትን ዕቃዎች /Direct Delivery Cargo/ ሳይጨምር) ከተራገፉበት ሰዓት ጀምሮ ባሉት 48 ሰዓታት ውስጥ ከጅቡቲ ወደብ እንዲነሱ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ማሳካት እንዳልተቻለ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

297. ይሁን እንጂ በ2005 በጀት ዓመት በጅቡቲ ወደብ ያለውን የክሊራንስ ስራ የሚፋጠንበትን አሰራር ለመዘርጋትና ለመተግበር ከኤ.ቲ.ዲ ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር ለመቅረፍ እና የATDን ክሊራንስ ስራ ለማፋጠን እ.አ.አ. ጃንዋሪ 27 ቀን 2009 አዲስ ተጨማሪ ስምምነት (SLA[2]) ተፈርሞ ሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን፣ በስምምነቱ አንቀፅ 3.3 መሰረት ኤ.ቲ.ዲ. እና ድርጅቱ የሚጠበቅባቸውን በተመለከተ የተቀመጠ ግዴታና ስታንደርድ ጊዜ ያለ ሲሆን፣ በዚህ መሠረት ካልተከናወነ በተለይ በATD በኩል በሚፈጠር ተደጋጋሚ የመድረሻ ቦታ ስህተት፣ ዕቃን በወቅቱ አለመጫን ችግር... ወዘተ በተመለከተ ATD[3] ስለ ጭነቱ ሪፖርት በወቅቱ ባለመላኩ ምክንያት ተያይዞ የሚመጣ የመጋዘን ኪራይ(የስቶሬጅ) እንዲሁም የዲመሬጅ ወጪዎችን እንዲከፍል እንደሚያደርግ እና በድርጅቱ (ኢባትሎአድ) በኩል ደግሞ መርከብ ከመግባቱ 48 ሰዓት በፊት ሰነድ ለATD ካልደረሰ በዚህ ምክንያት ለሚመጡ ተያያዥ ወጪዎች ድርጅቱ ተጠያቂ እንደሚሆን ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ሥራ ላይ እንዲውል በተደረገው አዲስ ተጨማሪ ስምምነት (SLA) በተቀመጡት በእያንዳንዱ ተግባራት መሰረት ድርጅቱ (ኢባትሎአድ) እና

[2] SLA = Service level agreement
[3] ATD = Asociation of transporters of Djibouti

ATD የሚፈፅሙ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ሲሞከር፡ የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡-

- ✓ በድርጅቱ (ኢባትሎአድ) በኩል የሚጠበቀውን ግዴታ በተመለከተ ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት በድርጅቱ/በፅድነት አስተላለፈነት ዘርፍ/ በኩል ምን ያህል ኦፕሬሽኖች እንደተከፈቱ፣ በየበጀት ዓመታቱ ከተከፈቱት እያንዳንዱ ኦፕሬሽኖች ምን ያህሉ መርከብ ከመድረሱ ከ48 ሰዓት በፊት ሰነድ ለATD እንዲደርስ እንደተደረገ እና ምን ያህሉ ከስታንደርድ ቀኑ በላይ እንደወሰዱ/ የቆዩበትን ቀን፣ ምክንያቱን እና የተወሰደውን እርምጃ ጨምሮ/ እንዲሁም በስምምነቱ ላይ በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት ድርጅቱ ግዴታውን ባለመወጣቱ ያስከተለው ችግር እና ከዚህ ጋር ተያይዞ በድርጅቱ የወጡ የስቶሬጅ፣ የዲመሬጅ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን በየበጀት ዓመታቱ ተተንትኖ እና ተጠናቅሮ የተያዘ መረጃ እንደሌለ፣

- ✓ በATD በኩል የሚጠበቀውን ግዴታ በተመለከተ ደግሞ ከላይ በተጠቀሱት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት ለተከፈቱ ኦፕሬሽኖች በATD ከተከናወኑት የወደብና የጉምሩክ ክሊራንስ ስራዎች ምን ያህሉ በስታንደርድ ጊዜው እንደተከናወኑና ምን ያህሉ እንደዘገዩ፣ ከተከፈቱት አጠቃላይ ኦፕሬሽኖች ውስጥ ምን ያህል ስህተቶች እንደተከሰቱ (ከኮንቴይነር ማሸጊያ/ኮንቴይነር ሲል/ ስህተት፣ የአስተሻሸግ ችግር፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ በማኒፌስት እና በሌሎች በሺፒንግ ሰነዶች)፣ በማን እንደተከሰቱ፣ ያስከተሉትን ተፅዕኖ እና የተወሰደውን እርምጃ በሚያሳይ እና ለውሳኔ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ የተተነተነ እና የተጠናቀረ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

- ✓ በመሆኑም ሁለቱም ወገኖች በኩል የተፈረመው ስምምነት በሚፈለገው መጠን ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ እና በስምምነቱ ላይ በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ባለመወጣታቸው ምክንያት ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት በሁለቱም ወገን የወጡ አላስፈላጊ ወጪዎች (የስቶሬጅ፣ የዲመሬጅ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች) ያሉበትን ሁኔታ በተሟላ ደረጃ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

298. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የድርጅቱ ዓመታዊ ዕቅድና አፈፃፀም ሪፖርት በተከለሰበት ወቅት፡-

- በ2005 በጀት ዓመት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚመጡ የገቢ ዕቃዎች (በቀጥታ ከመርከብ ወደ መኪና የሚራገፉትን ዕቃዎች /Direct Delivery Cargo/ ሳይጨምር) ከተራገፉበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አራት ቀናት ውስጥ ከጅቡቲ ወደብ እንዲነሱ ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ አፈፃፀሙ የመልቲሞዳል ኮንቴይነሮች አማካይ የጅቡቲ ቆይታ ጊዜ መስከረም 2005 ዓ.ም. ከነበረበት 63 ቀን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ወደ 5 ቀን ዝቅ ማድረግ መቻሉን፣ ባንፃሩ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ በዩኒሞዳል የትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዙት ኮንቴይነሮች አማካይ የጅቡቲ ቆይታ ጊዜ 36 ቀናት የወሰደ መሆኑን፣
- በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ ከቆይታ ጊዜ በላይ ለዘገዩ ጭነቶች ATD የስቶሬጅና ዴመሬጅ ወጭውን እንዲሸፍን በመደረጉ ከጥር 2005 ዓ.ም. በኋላ ድርጅቱ ከዚህ ወጭ በአብዛኛው የተላቀቀ መሆኑን፣
- ነገር ግን ድርጅቱ ዕቃዎችን በወቅቱ ባለማጓጓዙ ቅጣት እንዲከፍል መደረጉን በበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም

ሪፖርት ላይ የተገለፀ ቢሆንም መረጃው ተጠይቆ በተሟላ መልኩ ሊቀርብ ባለመቻሉ በኦዲቱ ወሰን (ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት) ያለውን አጠቃላይ የአፈፃፀም ደረጃ በተሟላ መልኩ ለመገምገም አልተቻለም፡፡

299. ይሁን እንጂ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓቱ በትክክል ስራ ላይ ውሎ ክትትሉ ከተጠናከረ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 2013 ጀምሮ እስከ ጃንዋሪ 15 2015 ድረስ በATD ለዘገዩ እያንዳንዱ ኦፕሬሽኖች ድርጅቱ ከATD 250,900.84 የአሜሪካን ዶላር የስቶሬጅ ሒሳብ የሰበሰበ መሆኑን እና በተጨማሪም የትራንስፖርት ማህበራት የተመደበላቸውን ኮንቴይነር በወቅቱ ባለማንሳታቸው ምክንያት እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 2014 እስከ ጃንዋሪ 15 2015 ድረስ በድምሩ 195,576 የአሜሪካን ዶላር የስቶሬጅ ሒሳብ እንዲከፍሉ እንደተደረገ፣

- ኦፕሬሽኖችን ቀድሞ ከመላክ አንጻር በአሁኑ ጊዜ ከ85 በመቶ እስከ 90 በመቶ የሚሆኑት ኦፕሬሽኖች መርከብ ጅቡቲ ከመድረሱ በፊት ለATD የሚላኩ መሆኑን፣ ከቅርብ ወደቦች (ምሳሌ ጅዳ፣ ጀበል ዓሊ፣...ወዘተ) ግን ይህን ጊዜ መጠበቅ የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩና በTIN እና በማኒፌስት መዘግየት ላይ ያሉት ችግሮች ሙሉ በሙሉ ባለመቀረፋቸው ከ10 በመቶ እስከ 20 በመቶ የሚደርሱት ኦፕሬሽኖች መርከብ ጅቡቲ ከደረሰ በኋላ የሚላኩ መሆናቸውን፣ እና

- ሌሎች ሦስተኛ ወገኖች (ወኪሎች እና ባለመርከቦች) በራሳቸው ምክንያት የዘገየ ኦፕሬሽን ሲኖር በየኦፕሬሽኑ ማብቂያ ላይ የተከሰተው ወጭ ተሰልቶ እንዲከፍሉ የሚደረግ ሲሆን፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ሶስተኛ ወገን ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ የከፈለውን ሒሳብ ሰነዶች መካከል መርጦ ለማውጣት

የኦዲቱ የቆይታ ጊዜ የሚበቃ ባለመሆኑ ያልቀረበ መሆኑን የድርጅቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

<u>የየብስ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ</u>

300. የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎች በፍጥነት ለማጓጓዝ የሚያስችል አስተማማኝ የጭነት ተሽከርካሪ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፡፡ የመልቲ-ሞዳል ኮንቴይነር የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ምልልስ ስታንደርድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ጭነት ለማጓጓዝ ከድርጅቱ ጋር ውል የገቡ ማሕበራትና ድርጅቶች እንዲሁም የድርጅቱን ተሽከርካሪዎች ጨምሮ በቀን የሚያስፈልገው አማካይ የጭነት ተሽከርካሪዎች መጠን ሊሰላና ተሽከርካሪዎቹም ለጭነት እንዲቀርቡ/እንዲሰማሩ በማድረግ አፈፃፀማቸው ሊገመገምና አስፈላጊው እርምጃም ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሀገሪቱን ወጪና ገቢ ንግድ ፍሰቱን የሚደግፍ አስተማማኝ የትራንስፖርት አቅርቦትን ለማረጋገጥ የድርጅቱን ከባድ ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ጭነት ለማጓጓዝ ከድርጅቱ ጋር ውል የገቡ ማህበራትና ድርጅቶች ያስመዘገቧቸውን ተሽከርካሪዎች በሙሉ አቅም በስራ ላይ እንዲውሉ በመከታተልና የጭነት ተሽከርካሪዎችን ለጭነት በማቅረብ/በማሰማራት ለደንበኞች የተሟላ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት እየተሰጠ ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎች ሲከለሱ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት የዘርፉ/የድርጅቱ/ 60 የጭነት ተሽከርካሪዎች 2,652 ምልልስ በማድረግ 4,018,200 ኪ.ሜ ርቀት በመጓዝ ከጅቡቲ 106,080 ቶን ዕቃ በመጫንና በማጓጓዝ ለደንበኞች የተሟላ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የታቀደ ቢሆንም፣ 1,733 ምልልስ በማድረግ 3,043,565 ኪ.ሜ ርቀት በመጓዝ የምልልስ ዕቅዱን 65% እና የርቀት የዕቅዱን

76% ማከናወን የተቻለ ሲሆን፣ በአጠቃላይ በድርጅቱ 60 የጭነት ተሽከርካሪዎች በተደረገው ምልልስ ከጅቡቲ 67,849 ቶን መጠን ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ በማጓጓዝ የክብደት የዕቅዱን 64% ለመፈፀም የተቻለ መሆኑን፣

- ✓ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚሳተፉ የድርጅቱ የጭነት ተሽከርካሪዎች ምልልስን በተመለከተ ደግሞ፡-

- በ2004 4ኛው ሩብ ዓመት ከድርጅቱ 60 የጭነት ተሽከርካሪዎች ውስጥ 30ዎቹን ወደ ስምሪት በማስገባት ከሞጆ-ጅቡቲ ደርሶ መልስ እያንዳንዳቸው በወር 5.63 ምልልስ እንዲያደርጉ እና በሩብ አመቱ በጠቅላላ 507 ምልልስ እንዲያደርጉ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ አፈፃፀሙን በተመለከተ 283 ምልልስ ወይንም የዕቅዱን 56% የተከናወነ መሆኑን፣

- በ2005 በጀት ዓመት የአንድ ተሽከርካሪ ምልልስ በወር 5.63 እንዲሆንና በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ 3,000 ምልልስ ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ አፈፃፀሙን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 1,312 ምልልስ ያደረጉ ሲሆን፣ ይህም የዕቅዱ 44% እንደሆነ እንዲሁም፣

- በ2006 በጀት ዓመት ደግሞ የአንድን ተሽከርካሪ አማካይ ወርሃዊ የርቀት ሽፋን 4250 ኪ/ሜ ማድረስ እና የተሽከርካሪዎችን ምልልስ በወሩ በአማካይ 5.5 ለማድረስ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ አፈፃፀሙን በተመለከተ በዕቅድ ዘመኑ በኦፕሬሽን ላይ የነበሩትን አማካይ የተሽከርካሪ ቁጥርን/በቀን በአማካይ 53 በመቶ በመያዝ/ ግምት ውስጥ በማስገባት በተደረገ ስሌት ተሽከርካሪዎቹ በወር በአማካይ 116 የጅቡቲ-አ/አ ምልልስ ብቻ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ የአንድ ተሽከርካሪ አማካይ ምልልስ በወር 3.63 በመሆኑ

የዕቅዱ 66 በመቶ ብቻ መሳካቱን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ የድርጅቱን ከባድ ተሽከርካሪዎች ስምሪትን በተመለከተ፡-

- በ2005 በጀት ዓመት የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች ጭነት ዌይቢል እና የተለያዩ ሰነዶችን በመጠበቅ መቆም፤ በጥገና ላይ ከታቀደው የጥገና ጊዜ በላይ በመለዋወጫ ጥበቃ መቆም፤ ከአዲስ አበባ-ጅቡቲ ኮሪደር ውጪ ባሉ ምቹ ባልሆነ መንገድ እንደ ድሬደዋ፣ መቀሌ፣ እና ኮምቦልቻ በመሳሰሉ ቦታዎች መሰማራት፤ በቂ የነዳጅ ጥናት ባልተደረገባቸው መስመሮች ለመሰማራት አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት በመቸገር የስምሪት መዘግየት እንደሚያጋጥም ታውቋል፡፡ እንዲሁም ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ባለ 20 ጫማ ኮንቴነር ቀድሞ ከሚጭነው ከ15-18 ቶን በላይ እስከ 25 /26 ቶን ድረስ በመሙላት በእንዲህ አይነት ሁኔታ ያሉ ኮንቴነሮች ሁለቱ በአንድ መኪና ሲጫኑ በመንገድ ሚዛን በመያዝ ለቀናት መቆማቸውና ይህም ምልልስ ላይ ችግር መፍጠሩን፣

- በ2006 በጀት ዓመት ድርጅቱ ከሚያስተዳድራቸው 61 ተሽከርካሪዎች ስምሪት ላይ እንዲውሉ ከሚጠበቁት 58 ተሽከርካሪዎች መካከል በቀን በአማካይ 32 ተሽከርካሪዎች ብቻ ስራ ላይ የነበሩ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ 29 ተሽከርካሪዎች በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በጥገና፣ በሌላ ስራ መመደብ፣ በአደጋ እና በመሳሰሉት ከስምሪት ውጭ እንደነበሩ፣

- በበጀት ዓመቱ(በ2006) የድርጅቱ 61 ተሽከርካሪዎች የስራ ጊዜ አጠቃቀምና ምልልስ አፈፃፀምን በተመለከተ ተሽከርካሪዎቹ ከጠቅላላ የስምሪት ጊዜያቸው በጥገና 45%፣ በማራገፍ 13%፣ በጭነት ጥበቃ 8%፣ በሰነድ ጥበቃ 0.3%፣ በአበል ጥበቃ 0.4% እና በሌሎች 1.3% ያለ ስራ የሚቆሙ

እንደነበር ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩን ከዚህ ሪፖርት አባሪ ቁጥር 4 ይመልከቱ)

- የስምሪት ክትትሉ በሲስተም የተደገፈና የተጠናከረ አለመሆኑን የሚያሳዩ ችግሮች መኖራቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ ከዚህ በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በጀት ዓመታት የመልቲሞዳል ጭነትን ለማጓጓዝ ከድርጅቱ ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ሌሎች አካላት ተሽከርካሪዎችን አጠቃቀም በተመለከተ፡-

- የመልቲሞዳል ጭነትን ለማጓጓዝ ከድርጅቱ ጋር በቅንጅት የሚሰሩ ሌሎች አካላትን በመደገፍና ክትትል በማድረግ የተሽከርካሪዎች ምልልስ ብዛት በወር 5.63 እንዲሆን በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም፣ አፈፃፀሙን በተመለከተ የሚገልፅ መረጃ አለመኖሩን፣

- ይሁን እንጂ ድርጅቱ የመልቲሞዳል ጭነቶችን የሚያጓጉዘው ከግል የትራንስፖርት ማህበራት ጋር በፈረመው የአገልግሎት ግዢ ኮንትራት በኩል የሚያገኛቸውን ተሽከርካሪዎች በመጠቀም መሆኑንና ከህዳር 2006 ዓ.ም. በፊት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ሲጀመር ከበርካታ ትራንስፖርተሮች ጋር አስገዳጅ ውል ያልታሰረና ተሽከርካሪና ጭነትን የማገናኘት ስራ ጅቡቲ በሚገኘው የጅቡቲ ትራንዚተሮች ማህበር /ATD/ በኩል ይከናወን የነበረና በአሰራር ላይ ከፍተኛ ችግር የነበረ በመሆኑ ከህዳር 2006 ዓ.ም. በኃላ ከ37 ትራንስፖርተሮች ማህበራት ጋር ግልፅና ተጠያቂነትን የሚያስከትል ውል እንዲታሰር የተደረገ ሲሆን፣ ይህን ኮንትራት በመከታተል የስምሪትና የቁጥጥር ስራው ከትራንስፖርት ማህበራት ጋር በጋራ ሲካሄድ የቆየ

እንደሆነና፣ በውሉ መሰረት በቂ ተሽከርካሪ ባላቀረቡት ማህበራት ላይ የቅጣት እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ እንዳለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- በዚህ መሰረትም አዲስ ጨረታ ወጥቶ ውል ከተፈረመበት ጊዜ (ህዳር 2006 ዓ.ም) ጀምሮ በየ10 ቀኑ የእያንዳንዱ ትራንስፖርት ማህበር አፈጻጸም ራሱ ማህበሩ ባለበት ግምገማ የተደረገ መሆኑንና በውጤቱም ደካማ አፈጻጸም ባላቸው ማህበራት ላይ እርምጃ የተወሰደ እንደሆነና ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በጠቅላላው የ37 የትራንስፖርት ማህበራት የ18 ዙር አፈጻጸም ግምገማ እንደተከናወነና በግምገማው ውጤት መሰረትም፡-

- በ1ኛ እና 2ኛ ዙሮች በድምሩ በ37 ማህበራት ላይ 78,193.75 USD ቅጣት የተጣለ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ አብዛኛው ክፍያ ከማህበራቱ ክፍያ ተቀንሶ ለድርጅቱ ገቢ መደረጉን፣

- ይሁንና በዚህ የቅጣት መጠንና በአፈጻጸሙ ላይ በጋራ መድረኩ ላይ ውይይት ከተደረገ በኋላ የመጀመሪያዎቹ 2 ዙር ቅጣቶች በትራንስፖርት መስመሩ ላይ የነበሩትን የምልልስ ማነቆዎች፣ የተሽከርካሪዎቹን ዕድሜና የጥገና አገልግሎቱን ደካማነት፣ የትራንስርት ማህበራቱ አደረጃጀት ተሽከርካሪዎቹን ለመቆጣጠር ያላቸውን የአቅም ውስንነት እና የቅጣቱ መጠን እቃው ባለመነሳቱ ምክንያት በድርጅቱ ላይ ከሚከሰተው ወጭ ጋር ሲተያይ ከፍተኛ መሆኑ በመታወቁና የቅጣት አላማውም ማስተማር እንጂ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያለውን አጓጓዥ አቅም መጉዳት እንዳልሆነ ስምምነት ላይ በመደረሱ የቅጣት አፈጻጸሙ እንዲሻሻል የተደረገ ሲሆን፣ ማህበራቱ ከቅጣቱ በኋላ ያሳዩትን የአፈጻጸም መሻሻል ግምት

ውስጥ በማስገባት የተወሰኑት ዙር ቅጣቶች እንዲቀሩ መደረጉን፣

<u>ከባህር ወደብ የተጫነው ጭነት የታሰበለት መዳረሻ መድረሱን ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ</u>

301. ከወደብ የተጫነ ጭነት መረጃ በየዕለቱ በመያዝና ከየብስ ወደቦችና ትራንስፖርተሮች መረጃ በማገናዘብ የተጫነው ጭነት የታሰበለት መዳረሻ መድረሱን ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ መዘግየት የታየባቸውን ጭነቶች ከአጓጓዦች ጋር በመነጋገር ችግሩን በመረዳት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት በትራንስፖርት ሚኒስቴር አማካኝነት በአገር አቀፍ ደረጃ እየተዘረጋ ያለውን የፍሊት ማኔጅመንት (GPS[4]) ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ዘርፉ የሚሰጠውን የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት በዘመናዊ መልክ በመምራት የትራንስፖርት ወጪን ለመቀነስ፣ ምልልስና ገቢን ለማሳደግ በ2004 በጀት ዓመት GPS ለመዘርጋት የብር 2,000,000 በጀት ተይዞ የነበረ ቢሆንም፣ የሲስተሙን ግዥ ለማከናወን አለም አቀፍ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ በቂ ተወዳዳሪዎች ባለማቅረባቸው ጨረታው እንዲሰረዝ እንደተደረገ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በ2006 በጀት ዓመት ሁሉም ተሽከርካሪዎች የጂ.ፒ.ኤስ. ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በተያዘው ዕቅድ መሰረት በ59 ተሽከርካሪዎች (96 በመቶ) ላይ መሳሪያው ተገዝቶ እንዲገጠም ተደርጎና ሰራተኞች ሰልጥነው ስራ የተጀመረ ቢሆንም፣ ቴክኖሎጂው እንደተገጠመ አካባቢ መሳሪያው ለክትትልና ስምሪት ስራው ጠቃሚ አገልግሎት መስጠት ጀምሮ እንደነበር ተውቋል፡፡

ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኃላ በሶፍትዌርና ሃርድዌር ችግር ምክንያት ከሞላ ጎደል ሁሉም ተሽከርካሪዎች መረጃ መላክ ያቋረጡበት ሁኔታ

[4] GPS- Global Positioning System

በመከሰቱ ችግሩን የትራንስፖርት ሚኒስቴር ጭምር እንዲያውቀው ከተደረገ በኃላ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ/INSA/ በኩል በተወሰደ እርምጃ ተከታታይም ባይሆን 51 ተሽከርካሪዎች መረጃ መላክ የጀመሩ ቢሆንም፣ የሚላከው መረጃ የተሟላና ወቅታዊ እንዳልነበረ ታውቋል፡፡ ቴክኖሎጂው ገና በጅምር ላይ ያለ በመሆኑ እና የሀርድዌርና ሶፍትዌር አቅራቢዎቹ የተሟላ ቅንጅት ስለሌላቸው ክትትልና ቁጥጥሩን በቴክኖሎጂው ላይ ማድረግ የሚያስችል አስተማማኝ ሁኔታ እንዳልተፈጠረ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ከባህር ወደብ የተጫኑ ጭነቶችን 100 በመቶ መዳረሻቸው በትክክል መድረሳቸው የሚረጋገጥ መሆኑን በተመለከተ ደግሞ፡-

- በ2005 በጀት ዓመት ከጂቡቲ ወደብ ተጭነው የመጡ ኮንቴይነሮች ወደ ደረቅ ወደቦች ወይም ወደ ቦንድድ ዌር ሃውስ መድረሳቸውን ለመከታተል፣ የደረሱትን ካልደረሱት በመለየት ያልደረሱትን የት እንዳሉ ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት ፕሮፖዛል ለአይ.ቲ. ቀርቦ ውጤቱ እየተጠበቀ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ስራው ግን በማንዋል እንደተጀመረና ውጤቱ እንደሚያሳየው ወደ ደረቅ ወደቦች የገቡ አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች በገቡበት ቀን ቀርቶ በሳምንትና ከዚያ በላይም ቢሆን መግባታቸው ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን፣

- በ2006 በጀት ዓመት ጭነቶችን ጭነው ከጅቡቲ በተነሱ 31,623 ኮንቴይነሮችን ባጓጓዙ ተሽከርካሪዎች ላይ ቋሚ ክትትል ተደርጎ የበጀት ዓመቱ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት (30/06/2014 እ.አ.አ.) ድረስ 28,542 ያህሉ መድረሻ ጣቢያቸው በትክክል መድረሳቸው የተረጋገጠ መሆኑን እና በዚህ ክትትል ከትክክለኛው ቦታ ውጪ የተጓጓዘ ዕቃ በመገኘቱ ስህተቱን የፈጠረው አካል የማጓጓዣውንና ተያያዥ ወጭዎችን እንዲከፍል መደረጉን፣ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ

የመልቲሞዳል ጭነቶችን ካጓጓዙት 45,473 ጠቅላላ ተሽከርካሪዎች መካከል 31,623 ኮንቴይነሮችን ባጓጓዙ ተሽከርካሪዎች (69 በመቶ) ላይ ብቻ ክትትል የተደረገ በመሆኑ የተጫኑ ጭነቶች 100 በመቶ መዳረሻቸው በትክክል መድረሳቸው የማይረጋገጥ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

<u>በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ወደ ሃገሪቱ ለሚጓጓዘው ኮንቴይነራይዝድ ጭነቶች እና ለተሽከርካሪዎች (RORO) የሚሰጥ የወደብ አገልግሎትን በተመለከተ</u>

302. በመልቲ ሞዳል የትራንስፖርት ሥርዓት ወደ ሃገሪቱ ለሚጓጓዙ ኮንቴይነራይዝድ ጭነቶች እና ተሽከርካሪዎች (RORO) በዕቅድ በተቀመጠው መሰረት የወደብ አገልግሎት፣ የዝግ መጋዘን እና ባዶ ኮንቴይነሮች የወደብ አገልግሎት እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ከ2004 እስከ 2006 ባሉት የበጀት ዓመታት ደረቅ ወደብና ተርሚናሎች በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ወደ ሃገሪቱ ለሚጓጓዘው ኮንቴይነራይዝድ ጭነቶች እና ለተሽከርካሪዎች (RORO) የወደብ አገልግሎት፣ የዝግ መጋዘን እና ባዶ ኮንቴይነሮች የወደብ አገልግሎት የሚሰጣቸውን የሎጀስቲክስ መጠን በየበጀት ዓመታቱ በዕቅድ የተቀመጠ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዚህም መሰረት ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም. ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት የነበረው ዕቅድ እና አፈፃፀም ከታች በተገለፀው መሰረት እንደሆነ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት መረጃዎች ለመረዳት ችለናል፡፡

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት የወደብ አገልግሎት ለመስጠት በዕቅድ ከተያዘው 44,962 የገቢ ሙሉ ኮንቴይነር /በTEU/፣ 6,608 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ እና 30,633 ባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ ውስጥ ማሳካት የተቻለው 19,629 ኮንቴይነር/በTEU/ (43.7%)፣ 2,788 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ (42.2%) እና

12,588 ባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ (41.1%) እንደቅደምተከተላቸው ሲሆን፣

- ✓ በ2005 በጀት ዓመት ደግሞ የወደብ አገልግሎት ለመስጠት በዕቅድ ከተያዘው 82,081 የገቢ ሙሉ ኮንቴይነር /በTEU/፣ 6,707 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ እና 64,560 ባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ ውስጥ ማሳካት የተቻለው 60,799 ኮንቴይነር/በTEU/ (74.1%)፣ 3,870 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ (57.7%) እና 54,028 ባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ (83.7%) እንደቅደምተከተላቸው ሲሆን፣
- ✓ በ2006 በጀት ዓመት ለ70,124 የገቢ ሙሉ ኮንቴይነር /በTEU/፣ ለ4,450 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ እና ለ63,672 ባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ የወደብ አገልግሎት ለመስጠት እና ለ16,128 ቶን ዕቃ የዝግ መጋዘን አገልግሎት እንዲሁም ለ16,129 ኮንቴይነር /በTEU/ የስታፊንግ/አንስታፊንግ/ አገልግሎት ለመስጠት በዕቅድ ከተያዘው ውስጥ ማሳካት የተቻለው 84,869 ኮንቴይነር/በTEU/ (121%)፣ 75,081 ባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ (117.8%) እና ለ35,704 ኮንቴይነር/በTEU/ የስታፊንግ/አንስታፊንግ/ አገልግሎት (221%) ብቻ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ለ4,183 ተሽከርካሪ/በቁጥር/ እና ለ14,866 ቶን ዕቃ የዝግ መጋዘን አገልግሎት በመስጠት የዕቅዱን 94%እና 92% እንደቅደምተከተላቸው የተከናወነ መሆኑን፣
- ✓ በመሆኑም በ2006 በጀት ዓመት ማሳካት ከተቻለው የገቢ ሙሉ ኮንቴይነር/በTEU/ የ121%፣ የባዶ ኮንቴይነር/በTEU/ የ117.8% እና የስታፊንግ እና አንስታፊንግ[5]/በTEU/ የ221% አፈፃፀም በስተቀር በቀሩት የአገልግሎት አይነቶች በሦስቱም የበጀት ዓመታት ከተያዘው ዕቅድ በታች የተፈፀመ

[5] የወጪና የገቢ ዕቃዎችን በኮንቴይነር የማሸግ /Stuffing/ እና ከኮንቴይነር የማውጣት/ Un-stuffing / አገልግሎት

ወይም የየበጀት ዓመታቱን ዕቅድ ማሳካት እንዳልተቻለና ከዕቅድ በላይ የተከናወኑትም ቢሆኑ አፈፃፀማቸው በጣም የተጋነነ መሆኑን፣ እንዲሁም በደረቅ ወደብና ተርሚናሎች የሚሰጡትን ሌሎች አገልግሎቶች ማለትም የዝግ መጋዘን እና የስታፊንግ/አንስታፊንግ ከ2006 በጀት ዓመት በስተቀር በቀደሙት የ2004 እና የ2005 በጀት ዓመታት የተያዘውን ዕቅድ እና ክንውን በተመለከተ የተያዘ ዕቅድም ሆነ አፈፃፀም መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ አፈፃፀሙን መገምገም አልተቻለም፡፡

- ✓ በተጨማሪም ለገቢ ጭነቶች (ኮንቴይነራይዝድ እና ተሽከርካሪ) የሚሰጠው የደረቅ ወደብ አገልግሎት ዕቅድ እና አፈፃፀም የተጠናከረ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚሰጥ አገልግሎት ሽፋንና አድማስን በማሳደግ ከየካቲት 1/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ የኮንቴይነር ጭነቶች በሙሉ እና ከ3 ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ በመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲገቡ በተላለፈው መመሪያ መሰረት እንዳልሆነና፣ በድርጅቱ የጭነት አስተላላፊነት አገልግሎት ዘርፍ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት አማካኝነት ከላይ በተገለፁት የበጀት ዓመታት በየብስ ለተጓጓዙት ጭነቶች መጠን እንኳን ሙሉ ለሙሉ የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጠት እንዳልተቻለ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት በድርጅቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በመለየት፣ ሊደረስበት የሚችል ግብ/ውጤት/ በማስቀመጥና በመተግበር ውጤታማ አፈፃፀም ማስመዝገብ እንዳለበት ይጠበቃል፡፡ የደረቅ ወደብ የአገልግሎት አሠጣጥ ልህቀት መለኪያ የሆነውን ያደገ የገበያ

ድርሻ በመቶኛ/ ማለትም በዕቅድ ዘመኑ በአጠቃላይ በአገሪቷ ከተጓጓዘ የገቢ ጭነት መጠን/በቶን/ በዕቅድ ዘመኑ በድርጅቱ ወደብና ተርሚናል የተስተናገደ የገቢ ጭነት መጠን /በቶን/ ያለውን ድርሻ በተመለከተ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ/ዕትዕ/ የተቀመጠውን 100% ማድረስን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በጀት ዓመታት አፈፃፀም ሲገመገም ወደ ሀገሪቱ ከገባው ዕቃ በደረቅ ወደብ የተስተናገደ ድርሻ በ2004 በጀት ዓመት 5%፣ በ2005 በጀት ዓመት 21% እና በ2006 በጀት ዓመት 22% እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በወደብና ተርሚናሎች የተፈጠረ የማስተናገድ አቅም እና የአገልግሎት ሽፋን በተመለከተ</u>

303. በደረቅ ወደቦችና ተርሚናሎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተሟላ ሁኔታ በሚያስተናግድ ደረጃ መሠረተ ልማት እንዲስፋፋ ሊደረግ የገቢ ዕቃዎች የወደብ አገልግሎት ሽፋን ከ8% ወደ 100%፣ የወጪ ዕቃዎችን ደግሞ ወደ 50% እንዲጨምር ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓቱን በተሟላ መልኩ ለመተግበርና የድርጅቱን የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም እያደገ የመጣውን የአገሪቱን ገቢና ወጪ ዕቃዎች በተሟላ መልኩ ለማስተናገድ እንዲቻል ወደብና ተርሚናሎች ያላቸውን የማስተናገድ አቅም የበለጠ በማጠናከር ለደንበኛው ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ስራዎችን ከ2004 በጀት ዓመት ጀምሮ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ለመረዳት ችለናል፡፡
- ✓ በመሆኑም ቀድሞ ከነበሩት ሞጆ እና ሰመራ ወደብና ተርሚናሎች በተጨማሪ በኮሜት፣ በበከልቻ፣ በድሬደዋ፣

ኮምቦልቻ እና መቀሌ በጊዜያዊነት ከ2005 በጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ ገቢ ዕቃዎችን ማስተናገድ በመጀመራቸው ከዚህ በታች የተገለፀውን የማስተናገድ አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡

- ✓ በዚህም መሰረት ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት የተመዘገበ የአገር ውስጥ ወደቦች ኮንቴይነር የመያዝ አቅምን (ወደ ላይ ከፍታ ድርድር) በተመለከተ፣ በ2004 በጀት ዓመት ከነበረው 4,611 TEU ኮንቴይነር በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመታት 9,216 TEU እና 13,835 TEU ኮንቴይነር እንደየቅደም ተከተላቸው በ85 በመቶ ትክክለኛ የመቀበል አቅም ላይ የተደረሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በ2005 በጀት ዓመት የ4,605 TEU ኮንቴይነር ማለትም የ99.87 በመቶ እና በ2006 በጀት ዓመት ደግሞ በ2005 በጀት ዓመት ከነበረው የ4,619 TEU ኮንቴይነር ማለትም የ50 በመቶ ተጨማሪ ኮንቴይነር የመያዝ አቅም ማስመዝገብ እንደተቻለ ያሳያል፡፡

ከላይ የተገለፀው በየበጀት ዓመታቱ የተፈጠረ የወደብና ተርሚናል ኮንቴይነር የመያዝ አቅም በTEU ማለት ወደብና ተርሚናሎች በአንድ ጊዜ ማስተናገድ የሚችሉትን የኮንቴይነር መጠን ሲሆን፣ ወደብና ተርሚናሎች በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ማስተናገድ የሚችሉትን የኮንቴይነር መጠንን /በTEU/ ለመለካት እንዲቻል በበጀት ዓመቱ የተመዘገበ የአገር ውስጥ ወደቦች ኮንቴይነር የመያዝ አቅምን፣ በበጀት ዓመት ያለውን የስራ ቀናት እና የበጀት ዓመቱ ኮንቴይነሮች በወደቦች ያላቸውን አማካይ የቆይታ ጊዜን/ Dwell time/ በመጠቀም ለመለካት የሚያስችል ቀመር ያለ ሲሆን፣ ይኸውም፡-

- ❖ ወደቦች በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ማስተናገድ የሚችሉት የኮንቴይነር መጠን/በTEU/(Container Throughput)= የተመዘገበ የአገር ውስጥ ወደቦች ኮንቴይነር የመያዝ አቅም ሲባዛ

በጀት ዓመት ያለው የስራ ቀን ብዛት ሲካፈል የኮንቴይነር በወደብ ያለው አማካይ የቆይታ ጊዜ/ Dwell time/ ወይም

- የተርሚናል ዓመታዊ ምርታማነት = <u>የተርሚናሉ በአንድ ጊዜ የመያዝ አቅም X 312</u>

  በወደብ ቆይታ ጊዜ

በዚህም መሰረት በአለም አቀፍ ልምድ አማካይ የኮንቴይነር የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜን/Dwell time/ 10 እንዲሁም በአንድ በጀት ዓመት ያለውን የስራ ቀናትን በተመለከተ ወደቦች በሳምንት ለ6 ቀን አገልግሎት እንደሚሰጡና በዚህም መሰረት በዓመት ውስጥ ያለው 312 የስራ ቀንን በመያዝ/ ግምት ውስጥ በማስገባት በተደረገ ስሌት፡-

- ✓ ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት የተመዘገበውን የወደቦች ኮንቴይነር የመያዝ አቅምን በመውሰድ እና ወደ ወደቦች የገቡ ኮንቴይነሮች ቀጥለው ለሚገቡ ኮንቴይነሮች በችሮታ ጊዜ ውስጥ/እስከ 10 ቀናት/ ከወደብ እንዲነሱ ቢደረግ በየበጀት ዓመታቱ በተመዘገበው የወደቦች የተፈጠረ አቅም ማስተናገድ የሚቻለው የኮንቴይነር መጠን /በTEU/ በ2004 በጀት ዓመት 143,863 ኮንቴይነር/በTEU/፣ በ2005 በጀት ዓመት 287,539 ኮንቴይነር/በTEU/ እና በ2006 በጀት ዓመት 431,652 ኮንቴይነር/በTEU/ ሲሆን፣ ይህም ማለት ከላይ በተጠቀሱት በጀት ዓመታት በድርጅቱ አማካኝነት በባህር ላይ የተጓጓዘውን የኮንቴይነር መጠን/በTEU/ በ2004 በጀት ዓመት 128,476 ኮንቴይነር፣ በ2005 በጀት ዓመት 117,238 ኮንቴይነር እና በ2006 በጀት ዓመት 130,638 ኮንቴይነር መጠንን/በTEU/ ሙሉ በሙሉ ማስተናገድ እንደሚቻል ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት እንደተቻለው ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በጀት ዓመታት በድርጅቱ

ባሉት ወደብና ተርሚናሎች ማስተናገድ የተቻለው የኮንቴይነር መጠን በ2004 በጀት ዓመት 19,630/በTEU/፣ በ2005 በጀት ዓመት 60,799/በTEU/ እና በ2006 በጀት ዓመት 84,869 ኮንቴይነር /በTEU/ ሲሆን፣ ይህም ከወደቦች የአቅም አጠቃቀም በመቶኛ/Capacity Utilization[6]/(ወደቦቹ ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው መስራታቸውን የሚለካ) አንፃር በበጀት ዓመታቱ 13.6%፣ 21.1% እና 19.7% እንደየቅደም ተከተላቸው ብቻ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በድርጅቱ ስር የተቋቋሙት በእያንዳንዱ ወደብና ተርሚናሎች ያለውን የወደብ አቅም አጠቃቀም/Capacity Utilization/ በተመለከተ ደግሞ የሞጆ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት በ2004 በጀት ዓመት ከነበረው የ37.36 በመቶ የወደብ አጠቃቀም በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመታት ወደ 22.27 በመቶ እና 23.24 በመቶ እንደቅደም ተከተላቸው የቀነሰ መሆኑን፣ እንዲሁም የሰመራ ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት በ2004 በጀት ዓመት ከነበረው የ11.93 በመቶ የወደብ አጠቃቀም በከፍተኛ መጠን ቀንሶ በ2006 በጀት ዓመት የወደቡን 1.98 በመቶ አቅም ብቻ መጠቀም የተቻለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በየበጀት ዓመታቱ ወደቦቹ ከነበራቸው አቅም ከአንድ አራተኛ(ከ25 በመቶ) በታች ተጠቅመው መስራታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በወደብና ተርሚናል የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው የጊዜ ተመን (ስታንደርድ) መሰረት የሚከናወኑ መሆኑን በተመለከተ</u>

304. ወደ ወደብና ተርሚናል የደረሱ ገቢ ዕቃዎችን ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ፣ ወደ ወደብ የገቡ ጭነቶች እስኪወጡ ድረስ በሚኖራቸው ቆይታ በአስመጪው (ወኪሉ)፣ በአጓጓዡ፣ በተቆጣጣሪ ተቋማት፣ ጥያቄ መሰረት ለሚቀርቡ ኦፕሬሽን

[6] የወደቦች የአቅም አጠቃቀም በመቶኛ/Capacity Utilization/፡- በበጀት ዓመት በወደቦች የተስተናገደ የኮንቴይነር መጠን/በቲ.ኢ.ዩ/ ሲካፈል በበጀት ዓመት የተመዘገበ የወደቦች ኮንቴይነር የመያዝ አቅም

አገልግሎቶች እንዲሁም በወደብና ተርሚናል የነበሩ ገቢ ዕቃዎችን (Imported Cargo) ለአስመጪው ለማስረከብ የሚፈጀውን ጊዜ በማንዋሉ በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡

በወደብና ተርሚናል የሚከናወኑ ተግባራት አፈፃፀም በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት መሆኑን በተመለከተ የአገልግሎት ቅልጥፍናን ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲቻል እንዲሁም ያለበትን ደረጃ ለመመዘን በየበጀት ዓመታቱ ለተሰጡ ለእያንዳንዱ አገልግሎቶች የክንውን መረጃ ተጠናቅሮ መያዝ፣ በየአገልግሎቶቹ አይነት ተተንትኖ እና ከዕቅድ አንፃር ተገምግሞ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ መያዝ እንዳለበት ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የአገልግሎት አሰጣጡ ያለበትን ደረጃ /አፈፃፀሙን/ ለመገምገም እንዲቻል በወደብና ተርሚናል የሚሰጡ አገልግሎቶችን በሶስት ደረጃ ከፍለን ለማየት የሞከርን ሲሆን፣ እነርሱም፡-

- ወደ ወደብና ተርሚናል የደረሱ ገቢ ዕቃዎችን የመረከብ አገልግሎት
- ወደ ወደብና ተርሚናል የገቡ ጭነቶች እስኪወጡ ድረስ በሚኖራቸው ቆይታ በአስመጪው(ወኪሉ)፣ በአጓጓዡ እንዲሁም በተቆጣጣሪ ተቋማት በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት የሚሰጡ አገልግሎቶች እንዲሁም
- በወደብና ተርሚናል የነበሩ ገቢ ዕቃዎችን(Imported Cargo) ለአስመጪው የማስረከብ አገልግሎት ሲሆኑ፣ በዚህ መሰረትም፡-

በኦዲቱ ወቅት ድርጅቱ በአዲስ መልክ ከተቋቋመበት ከህዳር 11 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ባሉት ሁለት በጀት ዓመታት ወደ ወደብና ተርሚናል የደረሱ ገቢ

ዕቃዎችን ለመረከብ፣ ወደ ወደብ የገቡ ጭነቶች እስኪወጡ ድረስ በሚኖራቸው ቆይታ በአስመጪው (ወኪሉ)፣ በአጓጓዡ፣ በተቆጣጣሪ ተቋማት፣ ጥያቄ መሰረት ለሚቀርቡ የኦፕሬሽን አገልግሎቶች የሚያስፈልገው /የሚፈጀው የጊዜ መጠን /ስታንደርድ/ እንዲሁም በወደብና ተርሚናል የነበሩ ገቢ ዕቃዎችን (Imported Cargo) ለአስመጪው ለማስረከብ የሚፈጀው ጊዜ በግልፅ ያስቀመጠ በወደብና ተርሚናሎች ላይ የሚከናወኑ የኦፕሬሽን እንቅስቃሴዎች ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የደረቅ ወደብ ኦፕሬሽን ማንዋል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ የድርጅቱ ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት ዕቅድ ላይ ደረቅ ወደብ የደረሱ የተጫኑ ገቢ እቃዎች ለመረከብ የሚወስደውን ጊዜ እና ከተለያዩ አካላት አስፈላጊውን የሰነድ ፎርማሊቲ አጠናቆ ለቀረበ ደንበኛ ከደረቅ ወደብ የሚወጡ ገቢ (imported) እቃዎችን ለማስረከብ የሚፈጀውን ጊዜ በተመለከተ ዕቅድ የሚቀመጥና አፈፃፀሙም ከዚሁ አንፃር የሚገመገም ቢሆንም ወደ ወደብ የገቡ ጭነቶች እስኪወጡ ድረስ በሚኖራቸው ቆይታ በአስመጪው (ወኪሉ)፣ በአጓጓዡ፣ በተቆጣጣሪ ተቋማት፣ ጥያቄ መሰረት ለሚቀርቡ የኦፕሬሽን አገልግሎቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች አይነትና የሚያስፈልገው/የሚፈጀው የጊዜ ተመን/ስታንደርድ/ እንዲካተት ያልተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በ2006 በጀት ዓመት አስቀድሞ በተቀመጠ የአሰራር ሂደት የሚሰራ ሥራ ፍትሐዊ ላልሆነ አገልግሎት አሰጣጥ ሊዳርግ እንደሚችል በመታወቁ ይህንን ክፍተት ለመዝጋት ተሽከርካሪ ኮንቴይነር ወይም ሌላ እቃ ጭኖ ወደብና ተርሚናል ገብቶ አራግፎ እስኪወጣና እቃው ለባለንብረት እስኪረከብ ድረስ ያለው የሥራ ፍሰትን መሠረት በማድረግ ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም.

ጀምሮ በሁሉም የአገር ውስጥ የወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ተፈፃሚ የሚሆን የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ዘርፍ የወደብና ተርሚናል ኦፕሬሽን አፈፃፀም ማንዋል የተዘጋጀና ለእያንዳንዱ አገልግሎት የሚፈጀው ጊዜም የተቀመጠ መሆኑን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በዚህ በወደብና ተርሚናል ኦፕሬሽን ማንዋል ውስጥ ስታንደርድ የወጣላቸው 36 ተግባራት እንደሚገኙና ከእነዚህ መካከል 27 ተግባራት በወደቦችና ተርሚናሎች አገልግሎት የሚሰጥባቸው እንደሆኑ የተገለጸ ቢሆንም፣ እነዚህ ተግባራት በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት ስለመፈፀማቸው ለማረጋገጥ በመስክ ጉብኝት በናሙና ከታዩት ከገላን ወደብና ተርሚናል ቅ/ጽ/ቤት በስተቀር በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ለተስተናገዱት ለእያንዳንዱ ኦፕሬሽኖች እያንዳንዱን ተግባራት ለማከናወን የፈጀውን/የወሰደውን ጊዜ በግልፅ በሚያሳይ እና እያንዳንዱ ኦፕሬሽን ስራ ላይ የተሰማራ ፈፃሚ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት መልኩ በሚያሳይ እንዲሁም ለውሳኔ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ መረጃው ተጠናቅሮ የሚያዝ ስለመሆኑ መረጃ ተጠይቆ ሊቀርብልን አልቻለም፡፡

አንዳንድ ቅ/ጽ/ቤቶች በማንዋሉ ላይ ከተቀመጠው የጊዜ ስታንደርድ ውጪ የራሳቸው ስታንደርድ እንዳላቸውና በዚህም መሰረት እያከናወኑ መሆኑን እንዲሁም አንዳንዶቹ ደግሞ በማንዋሉ ላይ የተቀመጠው የጊዜ ተመን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይጣጣምና ለመተግበር አስቸጋሪ እንደሆነ፣ ማለትም ለሚሰጠው የአገልግሎት አይነት ጥቅም ላይ በሚውለው የመሳሪያ አይነት፣ በጭነቱ አይነት ወዘተ. በግልፅ ለይቶ ያስቀመጠ አለመሆኑን ከቅ/ጽ/ቤቶቹ ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት ችለናል፡፡

ዕቃዎች በደረቅ ወደብ ያላቸውን የቆይታ ጊዜ (dwell time) በተመለከተ

305. የገቢ ዕቃዎች በደረቅ ወደብ ያላቸው የቆይታ ጊዜ (dwell time) ከስምንት ቀን በታች እንዲሆን ሊደረግ ይገባል፡፡ ዕቃዎች በተቀመጠው የእፎይታ ጊዜ ውስጥ ከደረቅ ወደቡ እንዲወጡ መደረግ እንዳለበት የሚጠበቅ ቢሆንም በተለያዩ ወደቦች ብዛት ያላቸው ኮንቴይነሮች ለረጅም ጊዜያት ተከማችተው እንደሚገኙ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡ በዚህ መሰረትም ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት የገቢ ዕቃዎች በደረቅ ወደብ ያላቸው አማካይ የቆይታ ጊዜን (dwell time) በተመለከተ ከ2004 እስከ 2006 ባሉት በእያንዳንዱ የበጀት ዓመታት በደረቅ ወደቦች የኮንቴይነሮችና የሌሎች ዕቃዎችን የመቆያ ጊዜ (Dwell time) ከስምንት ቀን በታች በማድረግ በመልቲ ሞዳል ሥርዓት ለሚመጡ ተጨማሪ ዕቃዎች ቦታ ለማስለቀቅ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም፡-

- ✓ በ2004 በጀት ዓመት በአማካይ የኮንቴይነሮች መቆያ ጊዜ በዓመት በአማካይ 17 ቀናት የደረሰ ሲሆን በሁለተኛ ግማሽ ዓመት ግን ደረቅ ወደቡ ዕቃቸውን ለሚያቆዩ ዋና ዋና ደንበኞች ደብዳቤ በመፃፃፍና የእቃዎች መረጃ ዌብ ሳይት ላይ በማውጣት አብዛኛዎቹ ገቢ ዕቃዎች ለደንበኞች እየደረሱ እንደሚገኝ፣
- ✓ በ2005 በጀት ዓመት በአገር ውስጥ ወደቦች የሙሉ ኮንቴይነሮች ሰኔ ወር አማካይ ቆይታ ጊዜ /Dwell time/ የመንግስት (ባለበጀት) ፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች፣ የግል አስመጪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው 46፣ 66፣ 56 ቀናት ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሞጆ ወደብና ተርሚናል 5,457፣ ኮሜት 1,757፣ በበከልቻ 21 ፣ እና በሌሎች ወደብና ተርሚናሎች 269 ባለ 20 ጫማ

ኮንቴይነሮች በጠቅላላ በአገር ውስጥ ወደብና ተርሚናሎች በድምሩ 7,504 ባለ 20 ጫማ (TEU) ተከማችተው እንደሚገኙ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ በ2005 በጀት ዓመት የኮንቴይነሮች በአገር ውስጥ የወደብ ቆይታ ጊዜ በምንመለከትበት ወቅት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ 7,504 ኮንቴይነሮች የነበሩ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 2,017 (27%) ብቻ ከ10 ቀናት በታች ሲሆኑ፤ የተቀሩት 5,487 ኮንቴይነሮች(በTEU) (73%) የሚሆኑት 10 ቀን የነፃ ጊዜያቸውን የጨረሱና ከ11 እስከ 60 ቀናት እና ከዛ በላይ በወደቡ ውስጥ የቆዩ ናቸው፡፡
- ✓ የ2006 በጀት ዓመት ደግሞ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከነበሩት 10,865 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ውስጥ 2,661 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ወይም 24.5 በመቶው እስከ 10 ቀን የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜ ያላቸው ሲሆን፣ 5,397 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ማለትም 46.68 በመቶው ደግሞ ከ11 ቀን እስከ ሁለት ወር የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜ ያላቸው መሆኑንና ከ61 ቀናት በላይ የሚቆዩ 2,805 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ማለትም 25.82% ድርሻ እንደነበራቸው በኦዲቱ ወቅት የተከለሰው መረጃ ያሳያል፡፡

306. በ2005 በጀት ዓመት አስመጪዎች እቃቻቸውን ከወደብና ተርሚናሎች ያላወጡበትን ምክንያት ለማወቅ የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ባንኮችና የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች በተገኙበት ከአስመጪዎች ጋር ሶስት ጊዜ ውይይት የተደረገ መሆኑንና በመጀመሪያው ዙር በተደረገው ውይይት አስመጪዎች የገንዘብ እጥረት የገጠማቸው መሆኑን በውይይት ወቅት ያነሱ

በመሆናቸው የዱቤ አገልግሎት የፍሬት ክሊራንስ እና የኮንቴይነር ዲፖዚት ክሬዲት ለደንበኞች እንዲመቻች በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የዱቤ አገልግሎቱን ለመጠቀም የቻሉት ከ8 የማይበልጡ እንደነበሩ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

307. በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመታት መጨረሻ በወደብና ተርሚናሎች ያሉ ሙሉ ኮንቴይነሮች በአስመጪዎች አይነት /ማለትም በመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በግል ባለሃብት ድርጅቶች/ በሚገኙበት ወደብ በመለየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ✓ በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ በወደብና ተርሚናሎች ከነበሩ 7,504 ሙሉ ኮንቴይነሮች ውስጥ 6,736 ኮንቴይነሮች/ በTEU/ ወይም 89.83% የግል አስመጪዎች ሲሆኑ፣ የባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች 464 ኮንቴይነሮች /በTEU/ ወይም 6.18% እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች 304 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ወይም 3.98% መሆናቸውን፣ እንዲሁም
- ✓ በ2006 በጀት ዓመት ደግሞ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተለያዩ ወደቦች ከነበሩት አጠቃላይ 10,865 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ውስጥ 9,703 ኮንቴይነሮች/ በTEU/ ማለትም 89.3% የግል አስመጪዎች፣ 729 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ማለትም 6.7% የባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች እና 433 ኮንቴይነሮች/በTEU/ ወይም 4% የመንግስት የልማት ድርጅቶች መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የማሻሻያ ሃሳቦች

- በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶች በስትራቴጂያዊ ዕቅድ የተያዙና መንግስት የነደፋቸውን የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች እንደመሠረታዊ ታሣቢ የወሰደ ይዘቱም ከራሱ አልፎ ከሌሎች የልማት ዘርፎች ጋር ያለውን ትስስር በተቀናጀ ዕቅድና አፈፃፀም የሚደግፍ መሆን ይኖርበታል፡፡

- በመልቲሞዳል የትራንስፖርት ስርዓት ለሚጓጓዙ የገቢና ወጪ ጭነቶች የክሊሪንግና ፎርዋርዲንግ አገልግሎት ዕቅድ የተጠናከረ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚሰጥ አገልግሎት ሽፋንና አድማስን በማሳደግ ከየካቲት 1/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ የኮንቴይነር ጭነቶች በሙሉ እና ከ3 ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ በመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲገቡ ከተላለፈው መመሪያ አንፃር መሆን ይኖርበታል፡፡

- በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት በድርጅቱ ተጓጉዘው ባህር ወደብ የደረሱ ጭነቶችን የሚፈለገውን የወደብና የጉምሩክ ፎርማሊቲ በወቅቱ በማሟላት ጭነቱን ለመንገድ ትራንስፖርት ዝግጁ በማድረግንና በተቀመጠው የእፎይታ ጊዜ /8 ቀን/ ውስጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲጓጓዙ መደረግ ይኖርበታል፡፡

- በድርጅቱ (ኢባትሎኢድ) በኩል የሚጠበቀውን ግዴታ በተመለከተ በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት በድርጅቱ/በጭነት አስተላለፈነት ዘርፍ/ በኩል ምን ያህል ኦፕሬሽኖች እንደተከፈቱ፣ በየበጀት ዓመታቱ ከተከፈቱት እያንዳንዱ ኦፕሬሽኖች ምን ያህሉ መርከብ ከመድረሱ ከ48 ሰዓት በፊት ሰነድ ለATD እንዲደርስ እንደተደረገ እና ምን ያህሉ ከስታንደርድ ቀኑ በላይ እንደወሰዱ / የቆዩበትን ቀን፣ ምክንያቱን እና የተወሰደውን እርምጃ ጨምሮ/ እንዲሁም በስምምነቱ ላይ በተቀመጠው ስታንደርድ መሰረት ድርጅቱ ግዴታውን ባለመወጣቱ ያስከተለው ችግር እና ከዚህ ጋር ተያይዞ

በድርጅቱ የወጡ የስቶሬጅ፣ የዲመሬጅ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን መረጃ በየበጀት ዓመታቱ ተተንትኖ እና ተጠናቅሮ መያዝና በየወቅቱ እየተገመገመ ተገቢው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

- ከATD በኩል የሚጠበቀውን ግዴታ በተመለከተ በእያንዳንዱ በጀት ዓመታት ለተከፈቱ ኦፕሬሽኖች በATD ከተከናወኑት የወደብና የጉምሩክ ክሊራንስ ስራዎች ምን ያህሉ በስታንደርድ ጊዜው እንደተከናወኑና ምን ያህሉ እንደዘገዩ፣ ከተከፈቱት አጠቃላይ ኦፕሬሽኖች ውስጥ ምን ያህል ስህተቶች እንደተከሰቱ (ከኮንቴይነር ማሸጊያ/ኮንቴይነር ሲል/ ስህተት፣ የአስተሻሸግ ችግር፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ በማኒፌስት እና በሌሎች በሺፒንግ ሰነዶች)፣ በማን እንደተከሰቱ፣ ያስከተሉትን ተፅዕኖ እና የተወሰደውን እርምጃ በሚያሳይ መልኩ የተተነተነ እና የተጠናቀረ መረጃ በመያዝ በየወቅቱ እየተገመገመ ተገቢው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
- የሀገሪቱን ወጪና ገቢ ንግድ ፍሰቱን የሚደግፍ አስተማማኝ የትራንስፖርት አቅርቦትን ለማረጋገጥ የድርጅቱን ከባድ ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ጭነት ለማጓጓዝ ከድርጅቱ ጋር ውል የገቡ ማህበራትና ድርጅቶች ያስመዘገቧቸውን ተሽከርካሪዎች በሙሉ አቅም በስራ ላይ እንዲውሉ በመከታተል ተሽከርካሪዎቹ ለጭነት እንዲቀርቡ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ከወደብ የተጫነ ጭነት መረጃ በየዕለቱ በመያዝና ከየብስ ወደቦችና ትራንስፖርተሮች መረጃ በማገናዘብ ሁሉም የተጫነው ጭነት የታሰበለት መዳረሻ መድረሱን ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡ መዘግየት የታየባቸውን ጭነቶች ከአጓጓዦች ጋር በመነጋገር ችግሩን በመረዳት ተገቢው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡
- በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ወደ ሃገሪቱ ለሚጓጓዘው ኮንቴይነራይዝድ ጭነቶች እና ለተሽከርካሪዎች (RORO) የወደብ

አገልግሎት፣ የዝግ መጋዘን እና ባዶ ኮንቴይነሮች የወደብ አገልግሎት የሚሰጣቸውን የሎጀስቲክስ መጠን ዕቅድ የተጠናከረ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚሰጥ አገልግሎት ሽፋንና አድማስን በማሳደግ ከየካቲት 1/2004 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ የኮንቴይነር ጭነቶች በሙሉ እና ከ3 ቶን በታች ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሙሉ በመልቲ-ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲገቡ የተላለፈውን መመሪያ መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ድርጅቱ ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓቱን በተሟላ መልኩ ለመተግበርና የድርጅቱን የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም እያደገ የመጣውን የአገሪቱን ገቢና ወጪ ዕቃዎች በተሟላ መልኩ ለማስተናገድ በእያንዳንዱ ወደብና ተርሚናሎች ያለውን የወደብ አቅም አጠቃቀም/Capacity Utilization/ እንዲጨምር መደረግ ይኖርበታል፡፡

- ወደ ደረቅ ወደቦች የሚመጣውን የመልቲ-ሞዳል ዕቃዎች መረጃ በአግባቡ ለመያዝ የሚያስችል የጭነት እንቅስቃሴ መከታተያ ሥርዓት በሁሉም ወደብና ተርሚናሎች ሊዘረጋና ሁሉም ወደ ደረቅ ወደቦች የሚመጡ ዕቃዎች አስቀድመው ሊታወቁ እና ሁሉም ደንበኞች ዕቃው በደረሰበት ቀን እንዲያውቁ መደረግ ይኖርበታል፡፡

- በየበጀት ዓመቱ በቅ/ጽ/ቤቶች ለተስተናገዱት ለእያንዳንዱ ኦፕሬሽኖች እያንዳንዱን ተግባራት ለማከናወን የፈጀውን/የወሰደውን ጊዜ በግልፅ በሚያሳይ እና እያንዳንዱ ኦፕሬሽን ስራ ላይ የተሰማራ ፈፃሚ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት መልኩ በሚያሳይ እንዲሁም ለውሳኔ አሰጣጥ በሚረዳ መልኩ መረጃው ተጠናቅሮ መያዝ እና በየወቅቱ እየተገመገመ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

- በተለያዩ ወደቦች ለረጅም ጊዜያት ተከማችተው የሚገኙት ብዛት ያላቸው ኮንቴይነሮች በአፋጣኝ ከወደቦች እንዲነሱ መደረግ ይኖርበታል፡፡

11.12 የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የባቡር መሰረተ-ልማት ግንባታ አፈፃፀም

308. ፕሮጀክቶቹ ከመጀመራቸው አስቀድመው የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው የበላይ ሃላፊዎች መፅደቅ አለበት፡፡ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነዱም ወቅታዊ ሁኔታዎችን የሚያሳይና በጥናት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

   - ✓ ይሁን እንጂ የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታዎቹ ጥር 2006 እና 2008 እ.ኤ.አ በተዘጋጀው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መመሪያ (Guidelines for the Preparation of Public Sector Projects) መመሪያ አንቀፅ 3.1 ላይ መጀመሪያ የፕሮጀክት ምልመላ ይደረጋል፤ ፕሮፋይል በተዘጋጀላቸው ፕሮጀክት ሃሳቦች ላይ ዝርዝር ጥናት ከመደረጉ አስቀድሞ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ይዘጋጅና ቅድሚያ የሚሠጣቸው የፕሮጀክት ሃሳቦች ወደ ዝግጅት ሂደት እንዲገቡ ይደረጋል ቢልም በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ያሉ የመሠረተ ልማት ግንባታዎቹ በ1999 ዓ.ም በትራንስፖርት ሚኒስቴር መሪነት አጥኚ ግብረ-ኃይል (Technical Advisory Group) ተቋቁሞ አማራጭ የየብስ ትራንስፖርትን አስመልክቶ ያደረገው ጥናት እንጂ እያንዳንዳቸውን ፕሮጀክቶቹን አስመልክቶ የተጠና የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ (Project proposal) ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

309. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መመሪያ መሠረት በፕሮጀክት ምልመላ ሂደት

የሚመረጡና የአዘገጃጀት ቅደም ተከተል የሚወጣላቸው የፕሮጀክት አማራጭ ሃሳቦች በዝርዝር ሊጠኑ አዋጪ መሆን አለመሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- ✓ ሆኖም አ.አበባ ከተማ ቀላል ባቡርን አስመልክቶ ኮርፖሬሽኑ የአዋጭነት ጥናት ያላጠና መሆኑ፣ የአዋጭነት ጥናቱን ያካሄዱት ከኮርፖሬሽኑ ጋር የEPC ውል የገቡት ተቋራጭ ድርጅቶቹ እንደሆኑና፣ የአዋጭነት ጥናቶቹ በተደጋጋሚ ጊዜ እንደሚጠኑና በተጨማሪም አንዳንድ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ከተሰጡ በኋላ የአዋጭነት ጥናት እንደተደረገ ለምሣሌ የአ.አ/ሰበታ- ሜኤሣ-ደወንሌ ፕሮጀክት የባቡር ግንባታው የጀመረው የካቲት 2012 እ.ኤ.አ ሲሆን የአዋጭነት ጥናቱ አማካሪው ድርጅት በመቀየሩ ምክንያት መስከረም 2012 እ.ኤ.አ እንደገና መጠናቱ፣ ኮርፖሬሽኑ የሚያጠናቸው የአዋጭነት ጥናቶች ጥልቅ የሆነ ምርምር የማይደረግባቸው መሆኑና በተደጋጋሚ ጊዜ ከአበዳሪ አገሮች የፋይናንስ አካሄድ መስፈርቶች ጋር ተጣጥመው እንዲጠኑ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

310. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ቅድመ ትግበራ ግምገማ የአዋጪነት ጥናት ውጤቶችን መሠረት በማድረግ በሚዘጋጅ የፕሮጀክት ሰነድ ላይ የክለሣ ሥራ ሊከናወንና ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር፣ እንደገና እንዲዘጋጅ ወይም ውድቅ እንዲሆን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በግንባታ ላይ ላሉት ሁሉም ፕሮጀክቶች ቅድመ ትግበራ ግምገማ እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

311. የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶቹ ክትትል፣ ቁጥጥሩና ድህረ ትግበራው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

የፕሮጀክት አዘገጃጀት ማኑዋል መሰረት መካሄድ አለበት፡፡ እንዲሁም ለክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ሰነዶች መሟላት አለባቸው፡፡

- ✓ ሆኖም ለኢ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ግንባታ የሚያገለግል በኮንትራት ውሉ ውስጥ የተጠቀሱ ለግንባታ ስራ፣ ለቁጥጥርና ክትትል አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችና ማኑዋሎች ለምሳሌ Quality assurance manual, Lab-equipment manual, Original design document, etc (English versions) ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ባለመሟላታቸው ውሉ ውስጥ በተጠቀሰው የጥራት መስፈርት መሠረት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ለመከታተል አስቸጋሪ እንዲሆን ማድረጉ ታውቋል፡፡

312. ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶቹ ግንባታቸው ከመጀመሩ አስቀድሞ ፋይናንሱ መገኘቱን ሊያረጋግጥ እና የፕሮጀክቶቹ ሥራዎች መቼ ተጀምረው መቼ እንደሚጠናቀቁ የጊዜ ሰሌዳ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

- ✓ ለፕሮጀክቶቹ ፋይናንስ ሳይገኝ ወደ ግንባታ የተገባ መሆኑ እና የፕሮጀክቶቹ ሥራዎች መቼ ተጀምረው መቼ እንደሚጠናቀቁ የተቀመጠ የጊዜ ሰሌዳ ያለመኖሩ ታውቋል፡፡
- ✓ በተለያየ ወቅት ከተከለሱት የጊዜ ሰሌዳ (Master Schedule) ላይ ፕሮጀክቶቹ መቼ ተጀምረው መቼ እንደሚጠናቀቁ ቢገለፅም ነገር ግን የመጀመሪያው ተቋራጮቹ ያስገቡት የጊዜ ሰሌዳ (Master Schedule) ላይ ፕሮጀክቶቹ መቼ ተጀምረው መቼ እንደሚጠናቀቁ አልተገለጸም፡፡

313. በመንግስት የሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት ያለፉ ስለመሆናቸው የማረጋገጫ ደብዳቤ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- ✓ ሆኖም በኦዲቱ የታዩት የአዲስ አበባ ከተማ ቀላል ባቡር፣ የአ.አ/ሰበታ ሜኤሃ እና የሜኤሃ ደወንሌ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ጥናት ሰነድና ዲዛይን ያልነበራቸው መሆኑ፣ ቅድመ ትግበራው የሚካሄደው ከብሔራዊ ኮሚቴ በሚገኝ ግብረ መልስ እንጂ በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ያሉ ሁሉም ፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት ያለፉ ስለመሆናቸው የማረጋገጫ ደብዳቤ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዳላገኙ ታውቋል፡፡

314. የባቡር ፕሮጀክቶቹ ሲተገበሩ ከኮንትራት ውሉ ውጪ ለሚጨመሩና ለሚቀነሱ ጉዳዮች ኮርፖሬሽኑ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ እንዲፈቀዱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

- ✓ ሆኖም የሰበታ ሜኤሃ ፕሮጀክት ከ1,639,031,409 የአሜሪካ ዶላር ወደ 1,841,407,000 የአሜሪካ ዶላር ኮንትራት ዋጋው ማለትም ወደ 202,375,591 ዶላር ቢጨምርም ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ቀርቦ ያልተፈቀደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

315. ኮርፖሬሽኑ ለመሠረተ ልማት ግንባታው እስትራቴጂካዊ እቅድ ሊያዘጋጅ እና በፕሮጀክቶቹ ሥር የተቀረፁት ሥራዎች በእቅዳቸው መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ፕሮጀክት ከመጀመሩ በፊት በግንባታው የሚሰሩ ዝርዝር ሥራዎች ተለይተውና ተነድፈው ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ሊዘጋጅላቸውና ዕቅዱም ሊለካ በሚችል መልኩ ተለይቶ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ ከ2003-2007 ዓ.ም የባቡር ሲስተም ኢንጂነሪንግ አቅም ግንባታ ሥራዎች፣ በባቡር መስክ ሃገራዊ የኢንጂነሪንግና የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ክህሎት እንዲፈጠር የማድረግ ሥራዎች፣ የባቡር ትራንስፖርት ንዑስ ዘርፍ ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ሬጉላቶሪ አሰራርና ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግን በተመለከተ የሚሠሩ ሥራዎች፣ የተቋማዊ አቅም ግንባታ ሥራዎችና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት አስመልክቶ በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ የሚደረስባቸውን ግቦች ቢያስቀምጥም የትኛው ሥራ በየትኛው የበጀት ዓመት እንደሚሰራ አላስቀመጠም፡፡

316. ኮርፖሬሽኑ ለመሠረተ ልማት ግንባታው ስትራቴጂክ፣ ዓመታዊና ወርሃዊ የስራ ዕቅድ ሲያዘጋጅ በግንባታ ሂደቱ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ወይም ኃላፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉና አስተያየት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ ለመሠረተ ልማት ግንባታው ስትራቴጂክ፣ ዓመታዊና ወርሃዊ የስራ ዕቅድ ሲያዘጋጅ በግንባታ ሂደቱ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ወይም ኃላፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማለትም አ.አ መንገዶች ባለስልጣን፣ አ.አ ከተማ መስተዳደር የመሬት ልማት ባንክ እና መልሶ ማደስ ኤጀንሲ፣ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣ ኢትዮ ቴሌኮም እና ኢትዮጵያ መብራት ሃይል ባለስልጣን በተዘጋጁ ዕቅዶች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አለማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

317. ኮርፖሬሽኑ የሚያካሂዳቸው የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታዎች የፕሮጀክቶቹን አጠቃላይ አፈፃፀም ሂደት በሚያሳየው ማስተር ፕላን መሰረት ዕቅዱን ተከትለው ሊካሄዱና የፕሮጀክቶቹን

አጠቃላይ ዑደት ምን እንደሚያካትት የሚያሳይ ሰነድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የሚያካሂዳቸው የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታዎች እያንዳንዱን ፕሮጀክት አስመልክቶ የተዘጋጀ ማስተር ፕላን (መሪ ዕቅድ) ያልተዘጋጀላቸውና የግንባታ ስራዎቹም የመጀመሪያ ዲዛይን የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

318. ኮርፖሬሽኑ የባቡር ፕሮጀክቶቹን ከመጀመሩ አስቀድሞ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን በቅድሚያ በማጥናት፣ በመለየትና የስጋት ትንተና (Risk Analysis)፣ የስጋት ቅነሳ (Risk Abatement) እና የስጋት ዝውውር (Risk Transfer) ሂደቶችን ሊለይ፣ የመከላከያና የማስተካከያ ዘዴዎችን ሊያካትትና ቅድመ ዝግጅት ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በኮርፖሬሽኑ ለሚተገበሩ ሁሉም ፕሮጀክቶች (የአ.አ/ሰበታ ሜኤሦ፣ የሜኤሦ ደወንሌ፣ የአ.አ ከተማ ቀላል ባቡር፣ የሃራ ገበያ/ወልዲያ-አሳይታ እና የመቀሌ-ሃራ ገበያ/ወልዲያ ፕሮጀክቶች) የስጋት ትንተና (Risk Analysis)፣ የስጋት ቅነሳ (Risk Abatement) እና የስጋት ዝውውር (Risk Transfer) ሂደቶች አለመካተታቸውና ተግባራዊ አለመደረጋቸው ታውቋል፡፡

319. ማንኛውም ፕሮጀክት ከመተግበሩ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሊደረግና በሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ያሉ አንዳንድ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቱ የተደረገው ግንባታቸው ከተጀመረ በኋላ እንደሆነ ለመጥቀስ ያህል ኮርፖሬሽኑ በሎት ከፋፍሎ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማቸው እንዲጠና ካስደረገው ፕሮጀክት መሐከል የአ.አ/ሰበታ ሜኤሦ

ደወንሌ መሥመር አካል የሆኑት ሁለቱ ሎቶች ማለትም የድሬደዋ አዲጋላ እና የአዳማ ሜኤሦ ሎቶች ግንባታቸው የተጀመረው ፌብሩዋሪ 2012 እ.ኤ.አ ቢሆንም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናታቸው የተጠናው ግን ጁላይ 2013 እና ኖቬምበር 2012 እ.ኤ.አ በቅደም ተከተል የነበረ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለመገንዘብ የተቻለ መሆኑ፤

- ✓ እንዲሁም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎቹ በፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ፈቃድ ቢያገኙም በየክተሞቹና በመስተዳድር ፅ/ቤቶቹ የሚገኙት የሚመለከታቸው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን (ለምሳሌ ፈንታሌ ወረዳ፣ ሚኤሶ ወረዳ፣ አዳማ ከተማ እና ሲቲ ዞን) በጥናቱ ላይ ተሣታፊ አለመሆናቸውና አስተያየት እንዲሰጡበት አለመደረጉ፣ ሰነዱም በሁሉም ማለትም በኦዲቱ በታዩት መስመሮች ላይ የሚገኙት የየክተሞቹ መስተዳደር አካባቢ ባለስልጣናት ሃላፊዎች እጅ የማይገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

320. በፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ የሚጠቀሱ ስራዎች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ባሉ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ የተጠቀሱ ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ እንዳልሆነ ለምሳሌ በአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በርካታ የቱሪስት መተላለፊያ መንገዶችን ሳያስፈቀዱ መዝጋት፣ የፓርኩን ንፅህና አለመጠበቅ፣ ያለ ፈቃድ መንገዶችን በፓርኩ ውስጥ እየቀደዱ ማውጣት፣ በፕሮጀክቶቹ የሚሠሩ ቻይናውያን ባለሙያዎች የዱር እንስሳትን ያለፈቃድ እያደኑ ለምግብነት የሚጠቀሙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በሚኤሶ ወረዳ በአዴሌ፣ ኬንቴሪና ሰባቃ ቀበሌዎች በባቡር መስመር ዝርጋታው ምክንያት ህብረተሰቡ ሲገለገልባቸው የነበሩ የመስኖ ውሃ መስመሮች የተቋረጡ መሆኑ፣ በተጨማሪም በወረዳው የሚገኙት የሚኤሶ፣ አዳሮባ፣ ቶኩማ፣ ጨሮሌ፣ ሮኢ፣ ኬንቴሪ እና ሰባቃ ቀበሌዎች የጎርፍ ስጋት አደጋ እንደተጋረጠባቸው፣
- ✓ የሰበታ-ሚኤሶ የባቡር መስመር አቋርጦት በሚያልፈው አዋሽ ብሄራዊ ፓርክ ውስጥ የሚገኙት ወደ ፍል ውሃ የሚያሳልፍ መንገድ በተቋራጩ የተዘጋ መሆኑና በተጨማሪም ወደ ፈንታሌ አካባቢ ያለ ማሳለፊያ መንገድ (Hyena cave) ለየት ያሉ ክስተቶች የሚታዩበት ስፍራ በመሆኑ ቱሪስቶች በጉጉት ሊያዩት የሚፈልጉት አካባቢ ቢሆንም መንገዱ መዘጋቱና እየተበላሸ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ✓ የሰበታ-ሚኤሶ የባቡር መስመር አቋርጦት በሚያልፈው አዋሽ ብሄራዊ ፓርክ የእንስሳት ዝውውር እንዳይስተጓጎል እና ተሽከርካሪዎች እንዲተላለፉ ኮርፖሬሽኑ ከኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በ12/10/2003 ዓ.ም 11 የእንሰሳትና 2 የተሽከርካሪ መተላለፊዎች እንዲሰሩ ስምምነት ቢያደርግም አለመሰራታቸው ታውቋል፡፡
- ✓ በአዳማ ከተማ መስተዳደር ደቤ ሰሎቄ ቀበሌ ተቋራጩ በተጠቀመው መጠኑ ያልታወቀ ድማሚት አስከ 250 ሜትር ድረስ በመሄድ በአካባቢው ባሉ ከ100 በላይ በሚሆኑ ቤቶችና አባወራዎች ላይ የንብረት ጉዳት ማለትም አጥራቸው የፈረሰ፣ ጣሪያቸው የተበሳሳና የፈረሰ፣ በርና ግድግዳቸው በድማሚት የተሸነቆረና የተሰነጣጠቀ በርካታ ቤቶች ላይ ጉዳት እንደደረሰ የኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ተመልክቷል በተጨማሪም የቀጠና ሁለት ነዋሪ በሆነ አንድ ሰው ላይ ሞትና በአራት ሰዎች ላይ አደጋ እንደደረሰ ለማወቅ

ተችሏል፡፡ እንዲሁም በአዳማ ከተማ መስተዳደር ቀበሌ 14 ኮንደሚንየም ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰ መሆኑ ማለትም ምሶሶዎች እስከ መሠነጣጠቅና መሸንቆር ድረስ ጉዳት እንዳጋጠማቸው ታውቋል፡፡

- ✓ በሶማሌ ክልል ሽንሌ ወረዳ በተቋራጩ ተቆፍሮ ክፍቱን በተተወ ጉድጓድ ውስጥ ውሃ ሞልቶ አንድ ሰው ህይወቱ ማለፉና እስካሁን በአጠቃላይ በክልሉ በዚህ ችግር ምክንያት ሦስት ሰዎች ህይወታቸው እንዳለፈና በሲቲ ዞን በሚገኙ ስድስቱም ወረዳዎች በየ5 ኪ.ሜትሩ ሰፋፊ የሆኑ የተከፈቱና ሳይሞሉ የተተዉ የተቆፈሩ ጉድጓዶች (Borrow pit) መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

321. በሜኢሶ ደዋሌ የባቡር መስመር ግንባታ ያለውን የእሳተ ገሞራ የመከሰት ሁናቴ ሊገመግም የሚችል ጥናት በኮርፖሬሽኑ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የቻይና ተቋራጭ ከሆነው CCECC ጋር በ2011 እ.ኤ.አ በተዋዋለው የውል ሰነድ ተቋራጩ ባቀረበው Technical Proposal ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ያለው የእሳተ ገሞራ 0.5 cm per year rift እንደሚያደርግ ተጠቅሶ ይሄ ትልቁ ሪፍት ቫሊ አሁንም ሪፍት አያደረገ እንደሆነና በዚህም ምክንያት አሁንም በላይኛው የምድር አካባቢ ያለው ክፍል ላይ ከፍተኛ (The great rift valley is still rifiting currently, which results in active crustal movement & frequently occurrence of volcanic eruption & earthquakes) እንቅስቃሴዎች እንዳሉ፣ በተደጋጋሚ ጊዜ ፍንዳታዎችና የመሬት መሰንጠቆች እየተከሰቱ እንደሆነና ኢትዮጵያ ውስጥ በዝርዝር የተጠናና የሚታወቅ Sesmic data እንደሌለ ስለዚህ የእሳተ ገሞራ የመከሰት ሁናቴውን አስተማማኝ

ለማድረግ የእሳተ ገሞራ የመከሰት ሁናቴ ሊገመግም የሚችል ጥናት መደረግ እንዳለበትና ኮርፖሬሽኑ ከአገር ውስጥ ብቃት ባለው ድርጅት አስጠንቶ ጥናቱን እንዲሰጣቸው ቢገልጹም ጥናቱ እንዳልተከናወነ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

322. የአካባቢ ጥናትና በባቡር መስመሮች መዘርጋት ምክንያት የሚከሰቱትን ተፅዕኖዎችን እንዲሁም የካርቦን ክሬዲት የሚያስተናግድ ሲስተም ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ እ.ኤ.አ በNovember 2010 UNFCCC ሁሉንም ፕሮጀክቶች የአካባቢ ጥናትና በባቡር መስመሮች መዘርጋት ምክንያት የሚከሰቱትን ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ እንዲያስችለው ለCarbon Finance እንዲመዘገቡ ማድረጉ፣ ከአፍሪካ ልማት ባንክ ግንኙነት በማድረግ የኢትዮጵያን ምድር ባቡር ብሔራዊ ኔትወርክ NAMA Project ሰርቶ ያቀረበውን በአማካሪ አስጠንቶ Interurban Electric Rail NAMA በሚል ስያሜ በUNFCCC November 2012 ለCarbon Finance ማስመዝገቡ እና ፈንዱን ለማግኘት እንዲረዳው ከኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና ከእንግሊዝ መንግስት የልማት ድርጅት ጋር በቅርብ እየሠራ የሚገኝ ቢሆንም ነገር ግን ሲስተሙን ዘርግቶ ተግባራዊ እንዳላደረገ ታውቋል፡፡

323. ኮርፖሬሽኑ የአምስት ዓመቱ የመንግስት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አካል የሆኑትን ሁሉንም ፕሮጀክቶች ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ካልገጠሙ በቀር በተዘጋጀላቸው የኮንትራት ውል ሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሊጀመሩና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እያንዳንዱ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሥራውን መጀመሩንና በየደረጃው ያሉ ሥራዎችም በተያዘላቸው የጊዜ

ገደብ መጠናቀቃቸውን ለማወቅ አስፈላጊውን የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ ከጀመረ ጀምሮ ግንባታቸው በኦዲቱ ተመርጠው በታዩት ሦስቱ መስመሮች ማለትም አ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት፣ አ.አ/ሰበታ ሜኤሃ እና ሜኤሃ ደወንሌ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ዘግይተው የተጀመሩ መሆኑ ማለትም ቀላል ባቡሩ ውሉ የተፈረመው መስከረም 2009 እ.ኤ.አ ሲሆን ተቋራጩ የካቲት 2012 እ.ኤ.አ እና አማካሪው ድርጅት ሰኔ 2012 እ.ኤ.አ ሥራቸውን የጀመሩ መሆኑ፣ አ.አ/ሰበታ ሜኤሃ ፕሮጀክት ውል የተፈረመው March 2011 እ.ኤ.አ ሲሆን ሥራው የተጀመረው February 2012 እ.ኤ.አ መሆኑ፣ የሜኤሃ ደወንሌ ፕሮጀክት ታህሳስ 2011 እ.ኤ.አ ውሉ ተፈርሞ ግንቦት 2012 እ.ኤ.አ ሥራው መጀመሩ፣ በታቀደላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተካሄዱ አለመሆናቸው በርካታ ያልተጠናቀቁ የወሰን ማስከበር ሥራዎች በመኖራቸውና የአ.አ/ሰበታ-ደወንሌ መሥመር ማስፈፀሚያ የሚሆነው ብድር አለመለቀቁ ፕሮጀክቶቹ በታቀደላቸው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ እንዳይጠናቀቁ ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

324. ኮርፖሬሽኑ በአምስት ዓመቱ የመንግስት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አካል የሆኑትን ሁሉንም ፕሮጀክቶች ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ካልገጠሙ በቀር በተዘጋጀላቸው የኮንትራት ውል ሰነድ ላይ በተያዘላቸው በጀት መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እያንዳንዱ ፕሮጀክት በዕቅድ በተያዘለት በጀት መሰረት ሥራው መካሄዱንና በየደረጃው ያሉ ሥራዎችም በተያዘላቸው በጀት

መጠናቀቃቸውን ለማወቅ አስፈላጊው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ እየተገነቡ ያሉት ሁሉም ፕሮጀክቶች (የኢ.አ/ሰበታ ሜኤሦ፣ የሜኤሦ ደወንሌ እና አ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክቶች) EPC ውሉ ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ ሥራዎች በመኖራቸው በታቀደላቸው ወጪ ሊጠናቀቁ የማይችሉ መሆናቸው ታውቋል፡፡
- ✓ የሰበታ ሜኤሦ ፕሮጀክት መጀመሪያ የነበረው የኮንትራት ዋጋ 1,639,031,409 የአሜሪካ ዶላር የነበረ ቢሆንም የአዋጭነት ጥናቱ በድጋሚ ሲጠና የመጀመሪያው ዲዛይን ውስጥ ያልተካተቱ ሥራዎች በመጨመራቸው ወደ 1,841,407,000 የአሜሪካ ዶላር ማለትም ወደ 202,375,591 ዶላር (12.35%) የኮንትራት ዋጋው ከፍ ማለቱና በተጨማሪም በተቋራጩ በኩል የተነሱ ብዙ (ወደ 7 ቦታዎች) የጭማሪ ሥራ ጥያቄዎች መኖራቸው በተጨማሪም የሜኤሦ ደወንሌ ፕሮጀክት ኮንትራት ዋጋው 1,197,400,000 የአሜሪካ ዶላር የነበረ ቢሆንም የአዋጭነት ጥናቱ በድጋሚ ሲጠና የመጀመሪያው ዲዛይን ውስጥ ያልተካተቱ ሥራዎች በመጨመራቸው ወደ 1,401,800,000 የአሜሪካ ዶላር ማለትም ወደ 204,400,000 ዶላር (17.07%) መጨመሩን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

325. በሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅተው እና በአማካሪ ድርጅቱ ፀድቀው ለኮርፖሬሽኑ የቀረቡ የክፍያ ጥያቄዎች በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ መሠረት ለተከናወኑ ሥራዎች መሆኑ ሊረጋገጥና ክፍያውም በዚሁ መሠረት በወቅቱ ሊከፈል ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ለበሰበታ-ሚኤሶ ተቋራጭ ድርጅት CREC - China Railway Group Limited ኦዲቱ እስከተከናወነበት

ሰኔ 2006 ዓ.ም ድረስ ከአድቫንስ ክፍያ ውጪ (ሁለተኛው አድቫንስ ክፍያ (2nd installement payment 5%) July 30 2012 እ.ኤ.አ መከፈል ሲገባው ዘግይቶ December 20 2013 እ.ኤ.አ መከፈሉ እና የግንባታው አፈፃፀም 30% ቢደርስም ምንም አይነት ክፍያ (Interim payments) ለተቋራጩ እንዳልተከፈለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የሚኤሶ-ደወንሌ ተቋራጭ ድርጅትም CCECC - China Civil Engineering Construction Company 7 ክፍያዎች ያልተከፈለው መሆኑ እና ለአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ተቋራጭም የሚደረጉ ክፍያዎች ዘግይተው እንደሚከፈሉ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

326. ለባቡሩ መሠረተ ልማት ግንባታ በሚዘጋጀው መሬት አካባቢ ሠፍረው ለሚገኙ እና በዚሁ ግንባታ ምክንያት ከኑሮዋቸው ለሚፈናቀሉ የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲከፈል በመንግስት የተፈቀደው ካሳ እቅድ ተዘጋጅቶለት በወቅቱ ሊከፈል ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በግንባታው ምክንያት ለሚፈናቀሉ የአካባቢ ነዋሪዎች እንዲከፈል በመንግስት የተፈቀደው ካሳ እቅድ ቢዘጋጅለትም ኦዲቱን እስካከናወንበት ድረስ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዳልተከፈሉና እስካሁንም በኦዲቱ በታዩት ሦስቱ ፕሮጀክቶች በርካታ የወሰን ማስከበርና ከካሣ ክፍያ ጋር በተያያዘ ችግሮች መኖራቸውን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በአ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ላይ ንዑስ የባቡር መቀበያ ጣቢያዎች (TPLS) (ውቤ በረሃ፣ አውቶቡስ ተራ እና አብነት አካባቢ) ግንባታዎች አለመከናወኑ፣ የድልድይ ፌርማታ (እስጢፋኖስ አካባቢ)፣ ቃሊቲ አካባቢ ባቡሩ ከዴፖ ወደ ዋናው መስመር መግቢያ አለመከናወኑ፣ አያት አካባቢ ባቡሩ ከዋናው መስመር ወደ ዴፖ የሚገባበት ቦታ

አለመከናወኑ፣ የአ.አ መንገዶች ባለስልጣን እስከ ታህሳስ 2006 ዓ.ም ድረስ ማስረከብ የነበረበት የለም ሆቴልና 22 አካባቢ የሚገነቡት ድልድዮች ተጠናቀው አለማለቃቸው፣ የአ.አ መንገዶች ባለስልጣን የመገናኛ አደባባይ አለመጠናቀቅ ይሄ አደባባይ በግንቦት 1 2013 እ.ኤ.አ ተጠናቆ የባቡር ግንባታው ይጀመራል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም እስከ ሐምሌ 1 2006 ዓ.ም ያልተጀመረ መሆኑና የ600 ሚ.ሜ ውሃ መስመር አለመነሳት፣ 61 የኤሌክትሪክ መስመሮች እና 16 የቴሌ መስመሮች አለመነሳት፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ሃይል ለ20 የሃይል መስጫ ጣቢያዎች የተጠየቀ የኤሌክትሪክ ሐይል ዝርግታ አለመከናወኑ፣ የድልድይ ፌርማታዎች (ዘጠኝ) ላይ ያሉ የመብራት ተሻጋሪ መስመሮች አለመነሳት፣ የኮካ ማሳለጫ የድልድይ ዲዛይን የማፅደቅ ስራ አለመከናወኑ፣ ወደ 84 የሚያህሉ Overhead Cabels ኦዲቱ እስከተከናወነበት እስከ ሐምሌ 1 2006 ዓ.ም ድረስ ያልተነሱ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ✓ በተመሣሣይም መከናወን ያለበት የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ አካሄድ (ማለትም- በማን፣ ከየት፣ በምን መልኩ ...ይዘረጋል) ዝርዝር ጉዳይ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ሐምሌ 1/2006 ዓ.ም ድረስ ተለይቶ አልተቀመጠም፡፡
- ✓ እንዲሁም በአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ግንባታ በአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የሚሰሩ 5 መንገዶች ማለትም በልደታ፣ ሜክሲኮ፣ ኡራኤል፣ ሃያ ሁለትና መገናኛ የሚገኙና በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ መነሳት የነበረባቸው ከሜክሲኮ እስከ ማዕድን ሚኒስቴር ያሉ ትላልቅ የውሃ መስመሮች ስራዎች በመዘግየታቸው የባቡር ግንባታውን ለ7 ወራት ማዘግየቱ ታውቋል፡፡

- ✓ በአ.አ/ሰበታ ሜኤሃ ደወንሌ ፕሮጀክት ላይ አሰቦት አካባቢ 152 መቃብሮች፣ ቦርደዴ አካባቢ 150 ሄክታር መሬት፣ ሚኤሶ ላይ 68 ቤቶች ካሣ ያለመከፈሉ እና ቦርደዴ፣ ሜኤሃ እና አሰቦት አካባቢ 155 አዳዲስ መቃብሮች ግምታቸው ያልተሰራና የካሣ ክፍያ ያልተፈፀመላቸው መሆኑ፣ ሃርዲም በምትባል ቀበሌ ወረዳው ያጣራቸው 25 እርሻዎች እስካሁን ካሣ ያልተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡
- ✓ በተመሣሣይም ሽነሌና ኤረር ላይ የስድስት ግለሰቦችና ሁለት የመንግስት ተቋሞች የካሣ ክፍያ ያልተከፈለ መሆኑ፣ ሜኤሃ ላይ ዘጠኝ የእርሻዎች ላይ በካሣ ግመታ ላይ ስምምነት ያለመደረሱና በተጨማሪም ኤረርና ሜኤሶ አካባቢ የሱማሌ ባህላዊ ቤቶች ክፍያቸው ያልተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ✓ በሶማሌ ክልል ሲቲ ዞን ውሉ ውስጥ የሌሉ ባዶ ቦታ (ARID) ተብለው የተዘለሉ በኋላ ተቋራጩ ወደ ሥራ ሲገባ ሊታወቁ የቻሉና ተቋራጩ፣ ኮርፖሬሽኑና ወረዳው በጋራ አጥንተው ስምምነት የተደረሰባቸው ለህብረተሰቡና ለእንስሳት መሰራት የነበረባቸው 19 መተላለፊያዎች አለመሰራታቸው እና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ሦስት ቦታዎች ላይ ስምምነት ያልተደረሰባቸው መሆኑ፤
- ✓ በተጨማሪም በሰበታ-ሚኤሶ-ደወንሌ ፕሮጀክት ግንባታ መስመር ላይ እስካሁን ያልተነሱ ዝቅተኛና ከፍተኛ ሃይል ያላቸው የኤሌክትሪክና የቴሌ ፋይበር ኦፕቲክስ መስመሮች መኖራቸው ታውቋል፡፡

327. ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶችን በመለየትና ሥራዎች ባላቸው የሥጋት ደረጃ በመመደብ አነስተኛ የሥጋት ደረጃ ያላቸውን የፕሮጀክት ሥራዎች ለሃገር ውስጥ ተቋራጮች ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡

በተጨማሪም የኮርፖሬሽኑ ደረጃ አሰጣጥ በአስፈጻሚዎች ዘንድም ሊታወቅ ይገባል፡፡

- ✓ የኮርፖሬሽኑ ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ እንደተገለፀው ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶችን በመለየትና ሥራዎች ባላቸው የሥጋት ደረጃ በመመደብ አነስተኛ የሥጋት ደረጃ ያላቸውን የፕሮጀክት ሥራዎች ለሃገር ውስጥ ተቋራጮች ቅድሚያ መስጠት አለበት ቢልም ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶችን ባላቸው የስጋት ደረጃ ሳይሆን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየትና ከአገር አቀፉ ዕቅድ በመውሰድ ወደ ሥራ እንደገባ ታውቋል፡፡

እንዲሁም ፕሮጀክቶች ባላቸው የስጋት ደረጃ ያልተመደቡ ሲሆን ለአስፈፃሚዎቹም የፕሮጀክቶችን የስጋት ደረጃቸውን ገልፆ ያላሳወቀቸው መሆኑንና የስጋት ደረጃቸውን ያወቁት በፊዚቢሊቲ ጥናትና በዲዛይን ሥራ ወቅት መሆኑ ታውቋል፡፡

328. ኮርፖሬሽኑ ሃገራዊ የባቡር ምህንድስና (Railway engineering) እና የዲዛይን ኮዶች (Design Codes) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ሆኖም ኮርፖሬሽኑ ከተለያዩ የውጪ አገር የባቡር ስታንዳርዶች የተከተሉ የዲዛይንና ግንባታ ስምምነቶች የፈረመ መሆኑ፣ የEPC Turnkey Contract ከተፈራረማቸው የተለያዩ አገር ተቋራጭ ኩባንያዎች የራሳቸውን ስታንዳርድ እንዲጠቀሙ መስማማቱ እና በአሁኑ ወቅት በግንባታ ላይ ያሉት ሁሉም የባቡር ግንባታዎች ማለትም የአ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት፣ የአ.አ/ሰበታ-ሜኤሶ ፕሮጀክትና ሜኤሦ-ደወንሌ ፕሮጀክቶች የባቡር ግንባታዎች በቻይና Railway Engineering Standard Class II እየተሰሩ መሆናቸው፣ ተቋራጮቹ የስታንዳርዱን እንግሊዝኛ ኦሪጂናል

ሰነድ (Chinese Design Standard English Version) እስካሁን ለማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆናቸውና በዚህም በርካታ ችግሮች እየተፈጠሩ እንዳሉ፣ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያማከለ ሃገራዊ የባቡር ምህንድስና (railway engineering) እና የዲዛይን ኮዶች (Design Codes) ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ሊፈጅበት መቻሉና የራሺያ አገር ዩንቨርስቲ ከሆነው ሴይንት ፒተስበርግ የባቡር ዩንቨርስቲ ጋር በመሆን በMay 2014 የሲቪል ሥራውን ማለትም Geometric Design of Railway፣ Track Superstructure፣ Railway Subgrade፣ Bridge and Culverts እና Tunneling ቢጨርስም አሁንም ሙሉ ለሙሉ የስታንዳርዱ አዘገጃጀት አካል የሆነው የኤሌክትሮ ሜካኒል ሥራው እንዳልተጠናቀቀ ታውቋል፡፡

329. ኮርፖሬሽኑ የባቡር ግንባታውን ሥራ በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል በብዛትም ሆነ በጥራት የተጣጣመ የሰለጠነ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የፕሮጀክቱን ሥራ የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠውና በኮንስትራክሽንና ፕሮጀክት አስተዳደር መምሪያ ስር የሚገኘው የመሠረተ ልማት ፕሮጀክት ክትትል ቡድን ለፕሮጀክቱ በተፈቀደው መዋቅር መሠረት በሠው ኃይል መደራጀት አለበት፡፡

- ✓ በኮርፖሬሽኑ ውስጥ የባቡር ግንባታውን ሥራ በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል በመዋቅሩ መሰረት የባቡር ምህንድስና ባለሙያ አለመኖርና አብዛኛዎቹ ባለሙያዎች የባቡር ምህንድስናን በተመለከተ አጫጭር ሥልጠናዎችን ብቻ የወሰዱ መሆናቸው፣
- ✓ እንዲሁም በሰበታ/ሜኤሣ ቅርንጫፍ የፕ/ጽ/ቤት Job description እስከ ሴክሽን ማናጀሮች ላሉ ኢንጂነሮች ብቻ የተሰጣቸው ሲሆን ለሌሎች ኢንጅሮችና ሠራተኞች ያለመሰጠቱ፣ በኢ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕ/ጽ/ቤት ለሁሉም

ሠራተኞች Job description ያልተሰጣቸው መሆኑ፣ በተጨማሪም የጽ/ቤቶቹ ተግባርና ሃላፊነት ተለይተው ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት አለመደረጉን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

330. በኮርፖሬሽኑ የሚፈፀሙ ውሎች አሻሚ ያልሆኑና ተፈፃሚነታቸው ቢጓደል አስፈላጊውን የቅጣት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

- ✓ ኮርፖሬሽኑ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር የዲዛይን ሥራ ለማሰራት ውል ቢገባም ሥራውን በውል በተቀመጠው ቀን ማጠናቀቅ ባልቻሉት ላይ ምንም አይነት የቅጣት እርምጃ አለመወሰዱ፣ ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች ጋር የሚገባቸው ውሎች አሻሚ፣ ግልጽ ያልሆኑና በበቂ ጥናት ላይ ያልተመሠረቱ እንደሆነ፣ ውሉ ላይ የተጠቀሱ አንዳንድ ጉዳዮች የማይፈጸሙ መሆናቸውና ተጨማሪ ወጪ በኮርፖሬሽኑ ላይ ያስከተሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

331. ኮርፖሬሽኑ በፕሮጀክቶች ሥራ ላይ የተሰማሩ አማካሪዎችና ተቋራጮችን ብቃት በየጊዜው ሊገመግምና ለወደፊት የውሳኔ አሰጣጥ እንደ ግብዓት ሊጠቀምበት እንዲሁም በተቋራጮችና አማካሪዎች አካባቢ ያሉ ዋና ዋና ክፍተቶችና ችግሮች ተለይተው የመፍትሄ ሃሳብ ለመስጠት የሚያስችል ሰነድ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

- ✓ የቦርድ ቃለጉባኤ ላይ እንደተገለፀው በግንባታ ላይ በተሰማሩ ተቋራጮችና አማካሪዎች አካባቢ ያሉት ዋና ዋና ክፍተቶችና ችግሮች ተለይተው የመፍትሄ ሃሳብ ለመስጠት የሚያስችል ሰነድ መዘጋጀት አለበት ቢልም ነገር ግን እስካሁን ባለው ሂደት ኮርፖሬሽኑ እየተገበራቸው ባሉና በተገበራቸው የፕሮጀክት ሥራዎች ተሳታፊ በነበሩ ተቋራጮችና

አማካሪዎች የነበሩትን ዋና ዋና ክፍተቶች እና ብቃታቸውን ሊያሳይ የሚችል የተሰራ ደሰሳ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

332. ተቋራጩ ስራውን ከመጀመሩ በፊት የፕሮጀክቱን የጊዜ ሰሌዳ፣ ግንባታው የሚካሄድበትን ዘዴ (Methodology)፣ ስራው እንዴት በቅንጅት እንደሚካሄድና አፈጻጸሙ እንዴት እንደሆነ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊያስቀምጥ፣ የስራውን ፕሮግራም (Programme of works) በዝርዝር ለአማካሪው ድርጅት በጽሁፍ ማሳወቅና ማቅረብ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ከተቋራጮች ጋር ውል ሲገባ በEPC (Engineering Procurement Construction) ውሎቹ ላይ በግንባታው ሥራ ላይ የሚካፈሉትን የተቋራጮቹን ከፍተኛ የባቡር መሃንዲሶች (Initially proposed list of senior personnel) ሊገለፅ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ተቋራጭ የስራውን የጊዜ ሰሌዳ (Master Work Schedule) በ28 ቀናት ውስጥ ማስገባት ቢኖርበትም የግንባታ ሥራው ከጀመረ በኋላ (ግንባታው የጀመረው Jan 31, 2012 ሲሆን) ከአምስት ወር በላይ ከቆየ በኋላ በJuly 2012 እ.ኤ.አ እንዳቀረበ እንዲሁም በዚህ ጊዜም ቢሆን መካተት የነበረባቸው መረጃዎች አለመካተታቸው ለምሣሌ የግንባታው Methodology፣ የሚሠራው ሥራ አጠቃላይ መጠን፣ የገንዘብ ፍሰት ግምት፣ የመሳሪያዎችና የሰው ሃይል አጠቃቀም ያልተካተቱ መሆኑና እነዚህን መረጃዎች አካቶ እንደሚያመጣ ሦስቱም አካላት ባካሄዱት ስብሰባ ማለትም በህዳር 2012 እ.ኤ.አ ቢገልፅም ነገር ግን በዚሁ ወር ባስገባው የጊዜ ሰሌዳ አሁንም BOQ (Bill of Quantities) እና ጠቃሚ መረጃዎቹ ያልተያያዙና ያልተካተቱ መሆናቸው፣ ለሦስተኛ ጊዜ ተቋራጩ በህዳር 23/2012 እ.ኤ.አ ያቀረበው የጊዜ ሰሌዳ አሁንም የሚሠራው ሥራ አጠቃላይ መጠን፣

የገንዘብ ፍሰት ግምት፣ የመሳሪያዎችና የሰው ሃይል አጠቃቀም ያልተካተቱ መሆኑ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ከተቋራጮች ጋር ውል ሲገባ በEPC (Engineering Procurement Construction) ውሎቹ ላይ በግንባታው ሥራ ላይ የሚካፈሉት የተቋራጮቹ ከፍተኛ የባቡር መሃንዲሶች (Initially proposed list of senior personnel) ያልተገለፀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ እንዲሁም የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ተቋራጭ የሆነው CREC - China Railway Group Limited የስራውን ወርሃዊ ፕሮግራም (Monthly Work Program) በውሉ ላይ በተገለፀው መሰረት በወየሩ ማስገባት ቢኖርበትም እስከ የካቲት 2014 እ.ኤ.አ በየወሩ ያላስገባ መሆኑ፣ የGeotechnical Investigation የመጨረሻው ሪፖርት Preliminary Investigation Report ከቀረበ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ቢሆነውም እስከ የካቲት 2014 እ.ኤ.አ ያልቀረበ መሆኑ በአማካሪው ድርጅት የየካቲት 2014 እ.ኤ.አ ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡

333. ኮርፖሬሽኑ የመሠረተ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ (Project management manual) አዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አለበት፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የመሠረተ ልማት ግንባታውን የሚቆጣጠርበት፣ የሚከታተልበት እና የሚገመግምበት የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያ ግንባታዎቹ ከተጀመሩ በኋላ ማለትም EPC Contract Adminstration መመሪያው March 26/2012 እ.ኤ.አ ሲሆን እንዲሁም የConsultant Contract Adminstration መመሪያው March 2012 እ.ኤ.አ እንደተዘጋጁ ታውቋል፡፡

334. ኮርፖሬሽኑ ከሥራ ተቋራጩ ፣ አማካሪ ድርጅቱ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ለሚቀርቡለት መፍትሔ ለሚሹ ጉዳዮች አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ ከተቋራጮች፣ ከአማካሪዎችና ከፕሮጀክት ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶቹ ለሚቀርቡለት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችና አፋጣኝ መፍትሔ የሚሹ ጉዳዮች ተገቢውን ግብረ-መልስ በወቅቱ የማይሰጥ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

335. ኮርፖሬሽኑ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ሊያዘጋጅ፣ ከሃገር ውስጥ ኮሌጆችና የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር በባቡር ኩባንያ አስተዳደር፣ በጥገናና በኦፕሬሽን ክህሎት ያለው የሰው ሃይል ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ እንዲሁም እየተገነቡ ላሉ የባቡር መስመሮች ወደፊት ስራውን የሚረከቡ ባለሙያዎች ተገቢው ስልጠና ተሰጥቷቸው ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ በአቅም ግንባታ ራሱን ለማጠናከር ከኮሌጆችና የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ትስስር ለማድረግና ሥልጠና ለመስጠት በተለይ ግንባታቸው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ማብቂያ ላይ ይጠናቀቃሉ ተብለው በሚታሰቡት በአ.አበባና በቅድሚያ የባቡር መስመሩ በሚዘረጋበት ኮሪደር አቅራቢያ ካሉት የድሬደዋ፣ ሐረር እና ሀሮማያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎችና ኮሌጅ ጋር ሥልጠና ለመጀመር በ2005 በጀት ዓመት ቢያቅድም ግንባታዎቹ ወደ መጠናቀቂያቸው እየሄዱ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ሥልጠና እንዳልተጀመረ፣ በባቡር ነጂነት፣ ጥገናና ሥምሪት ላይ የሚመደቡት ሠራተኞች ሥልጠና የተጓተተ መሆኑ እንዲሁም ክፍሉም ማለትም የአቅም ግንባታ መምሪያ በሰው ሃይል ያልተሟላ መሆኑና አማካሪዎቹ ድርጅቶች የሥራ ላይ ስልጠና (On–the–job training)

ለምሣሌ በDesign review, Construction supervision, Project management መስጠት እንዳለባቸው ውሉ ላይ ቢጠቀስም ከሴፍቲ ስልጠና ውጪ ምንም አይነት ስልጠና አለመስጠታቸውን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

336. ኮርፖሬሽኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልል መንግስታትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ኃዲዱ በሚያልፍበት አካባቢ ሠፍረው ለሚገኙ ህብረተሰቦች መሰረተ ልማቱ ሲጠናቀቅ በሚያስገኘው ጥቅም ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ የግንዛቤ ማዳበሪያ ውይይት ማድረግ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶቹ ከመጀመራቸው አስቀድሞ ግንባታዎቹ የሚያልፍባቸው አካባቢ ነዋሪዎችንና ባለድርሻ አካላትን መሰረተ ልማቱ ሲጠናቀቅ በሚያስገኘው ጥቅም ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ያዘጋጀው የውይይት መድረክ እንዳልነበረ ታውቋል፡፡
- ✓ በተጨማሪም በርካታ የአካባቢ ጥበቃ ሃላፊዎች ለምሳሌ የአዳማ፣ የሜኤሣና የሶማሊ ሲቲ ዞን የአካባቢ ጥበቃ ሃላፊዎችን ስለፕሮጀክቶቹ ከኮርፖሬሽና ጥናቱን ካካሄዱት ድርጅቶች ጋር ምንም ውይይት እንዳላደረጉ ፣ አንዳንድ የመስተዳደር አካላት ሃላፊዎች አዳማ፣ መኤሣ እና ሲቲ ዞን መስተዳደር አካላት ከጥናቱ ጋር በተያያዘ ምንም ነገር እንዳልደረሳቸውና በተጨማሪም በአንዳንድ ወረዳ ሃላፊዎችን ማሳመን ባለመቻሉ ከህበረተሰቡ ጋር ውይይት ማድረግ አለመቻሉና ግንባታው የሚካሄድበት አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ስለ መሠረተ ልማቱ በቂ ግንዛቤ

ስላልተደረገላቸው በርካታ ችግሮች እየደረሱ እንዳሉ በኦዲት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

337. በሃገር ውስጥ ያሉ በሲቪል ኢንጂነሪንግና ኮንስትራክሽን እንዲሁም በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ የተሰማሩ ኩባንያዎች በግንባታው (በዲዛይንና ግንባታ) የሚሳተፉበት የኮንትራትና የህግ አግባብ ተቀርፆ ተግባራዊ ሊደረግና በተጨማሪም ለሃገር ውስጥ ኮንትራክተሮችና ኢንዱስትሪዎች መደበኛ ስልጠና እና የእርስ በርስ ልምድ ልውውጥ ፕሮግራም ተቀርፆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ ለሃገር ውስጥ ተቋራጮችና አማካሪዎች ስልጠናዎች የመስጠትና የርስበርስ ልምድ ልውውጥ የአሰራር ስርዓት አዘጋጅቶ ወደ ተግባር ለመግባት ቢያቅድም ወርክ ሾፖች ከማዘጋጀት ውጪ እስካሁን ድረስ እንዳላሳካ እንዲሁም በሃገር ውስጥ ያሉ በሲቪል ኢንጂነሪንግና ኮንስትራክሽን እንዲሁም በሜካኒካል ኢንጂነሪንግ የተሰማሩ ኩባንያዎች በግንባታው (በዲዛይንና ግንባታ) የሚሳተፉበት የኮንትራትና የህግ አግባብ ተቀርፆ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ለማወቅ ተችሏል፡፡

338. ኮርፖሬሽኑ የመረጃ መረብ ዘርግቶ የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታን በተመለከተ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የመረጃ መረብ ቢኖረውም በየጊዜው ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ ታውቋል፡፡

339. የባቡር ትራንስፖርት ግንባታ፣ አገልግሎት አሰጣጥና ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ የደሰሳ ጥናት ሊካሄድ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ የባቡር ትራንስፖርት ግንባታ፣ አገልግሎት አሰጣጥና ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ ኮርፖሬሽኑ

ኢታልፌር በተባለ የጣሊያን ድርጅት ረቂቅ ጥናት ቢያካሄድም የመጨረሻው ጥናት ተጠናቆ አልቀረበም፡፡

340. በኮርፖሬሽኑ እየተተገበሩ ላሉ ፕሮጀክቶች በዋና መ/ቤትም ሆነ በግንባታ ሳይቶች የኮንትራት ዶክመንቱና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች ተደራጅተው መገኘት አለባቸው፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ በተመለከታቸው ሁለቱ ፕሮጀክቶች ማለትም አ.አ/ሰበታ ሜኤሦ እና ሜኤሦ ደወንሌ ፕሮጀክቶች በማስተባበሪያ ጽ/ቤቶቹ የኮንትራት ዶክመንቱ ውል፣ አካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶቹና፣ የአዋጭነት ጥናቶቹና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች ተደራጅተው አለመገኘታቸው፤
- ✓ እንዲሁም በአ.አ ከተማ ቀላል ባቡር ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤትም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት፣ የአዋጭነት ጥናት ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ተደራጅተው ያልተቀመጡ መሆናቸው ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳቦች

- ❖ ኮርፖሬሽኑ ወደፊት በምዕራፍ ሁለት ለሚሠራቸው ፕሮጀክቶች ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት መነሻ ሃሳብ እንዲሆነውና ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያካትት በመሆኑ በቅድሚያ የፕሮጀክት ረቂቅ ሰነድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
- ❖ ኮርፖሬሽኑ የግንባታ ሥራዎች ከመጀመራቸው አስቀድሞ የሚያስፈልገውን ሃብትና ተጨማሪ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን በመለየት ሥራው ቢሰራ ካለው ወቅታዊ ሁኔታ እና የወደፊቱን ከግምት በማስገባት አዋጭ መሆኑን እንዲጠና ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ኮርፖሬሽኑ ወደፊት በምዕራፍ ሁለት ለሚሠራቸው የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታዎች ፕሮጀክቶቹ ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የሚያስፈልጋቸውን በመለየትና

ፕሮጀክቶቹ በአካባቢዎቹ ላይ የሚስከትሉትን ማህበራዊ፣ አካባቢዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖና ጠቀሜታ ለመለየት እንዲቻል ጥናቱን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ለግንባታ፣ ቁጥጥርና ክትትል አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ፋይናንስ መገኘቱን አስቀድሞ በማረጋገጥ የግንባታ ሂደቱን ሊጀምር ይገባል፡፡
- በሁለተኛው ምዕራፍ የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ቀርበው የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሊከናወንላቸው ይገባል በተጨማሪም በኮርፖሬሽኑ ወደፊት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችም የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት ያለፉ ስለመሆናቸው የማረጋገጫ ደብዳቤ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊያገኙ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች ከኮንትራቱ ውጪ የሚጨመሩ ሥራዎችን በተመለከተ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ቀርበው እንዲፈቀዱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚገነባቸው ፕሮጀክቶች እስትራቴጂክ ዕቅድ ሲያቅድ ሥራዎቹ ተግባራዊ ስለመሆናቸው ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲያስችለው እንዲሁም ከአፈፃፀም ጋር በተያያዘ ችግሮች ሲነሱ በቶሎ መፍትሔ ለመስጠት እንዲያስችለው በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ የሚሰሩትን ዝርዝር ሥራዎች በየትኞቹ የበጀት ዓመታት እንደሚሰሩ ግልፅ በሆነ መልኩ ሊያስቀምጥ፣ ከባቡር ግንባታዎቹ አስቀድሞ ሊጠናቀቁ የሚገባቸውን ሥራዎች ለምሣሌ እንደ ግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የወሰን ማስከበርና ካሣ ክፍያና ሌሎች የዝግጅት ሥራዎች ሊያጠናቅቅ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚከናወኑትን ሥራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ለማከናወን ቅንጅታዊ አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም በበጀት ዓመቶቹ የታቀዱትን ሥራዎች ለተፈፃሚነታቸው አስፈላጊውን

ክትትል ሊያደርግና ችግሮች ካሉ ወቅታዊ የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ለመሠረተ ልማት ግንባታው ስትራቴጂክ ፣ ዓመታዊና ወርሃዊ የስራ ዕቅድ ሲያዘጋጅ በግንባታ ሂደቱ የሚሳተፉ ባለሙያዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በእነሱ የሚሰሩትን ሥራዎች ዕቅዳቸው ውስጥ እንዲያካትቱና ሥራዎቹን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ለማከናወን እንዲችሉና አስፈላጊውን ግብአቶች በቅድሚያ እንዲያዘጋጁ እቅዱን እንዲያውቁትና አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚያካሂዳቸው የባቡር መሰረተ ልማት ግንባታዎች የፕሮጀክቶቹን አጠቃላይ አፈፃፀም ሂደት የሚያሳይ ማስተር ፕላን ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው አስቀድሞ ሊያዘጋጅና ሥራዎቹንም በፕላኑ መሰረት ሊያካሂድ እንዲሁም የፕሮጀክቶቹ አጠቃላይ ዑደት ምን እንደሚያካትት የሚያሳይ ሰነድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት በምዕራፍ ሁለት ለሚተገብራቸው የባቡር ፕሮጀክቶች ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው አስቀድሞ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን በቅድሚያ በማጥናትና በመለየት ሥጋቶቹ እንዳይከሰቱ የሚደረግበት፣ ከተከሰቱም የሚቀነሱበት፣ የሚስተካከሉበትና የሚወገዱበት ወይም ወደ ሌላ የሚተላለፉበትን መንገድ ማጥናትና መለየት ይኖርበታል፡፡

- ወደፊት ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ኮርፖሬሽኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቱ ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው አስቀድሞ ማድረግና በየከተሞቹና በመስተዳድር ፅ/ቤቶቹ ለሚገኙት የሚመለከታቸው የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በጥናቱ ላይ ተሣታፊ እንዲሆኑና አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግና የጥናቱን ውጤት ማሳወቅና መላክ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በሥራው ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ

የሚያደርጉት ተቋራጮቹ፣ አማካሪ ድርጅቶችና ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶቹ የጥናቱ ውጤት እንዲደርሳቸው ማድረግና በሰነዱ ውስጥ በተጠቀሱት ዝርዝር ሥራዎች መሠረት እየተሰሩ መሆናቸውን መከታተል ይኖርበታል በተጨማሪም ተቋራጮቹ ማቅረብ ያለባቸውን Rehabilitation plan በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ማቅረባቸውን ሊከታተልና ለአፈፃጸሙም ተገቢውን ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ በምዕራፍ አንድ ግንባታ ወቅት ያጋጠሙ አካባቢያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዳይከሰቱ ልምድ በመውሰድ ወደፊት ለሚሰራቸው ፕሮጀክቶች በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ ለሚጠቀሱ ጉዳዮች ተግባራዊ ለመሆናቸው ጥብቅ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚያከናቸው ፕሮጀክቶች ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ለሚያጠቃቸው ቦታዎች ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥና የአገሪቱን ውስን ሃብት ከአደጋ ሊጠብቅ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚገነባቸው ፕሮጀክቶች ከሚሰጡት ተጨባጭ ጠቀሜታ በተጨማሪ በአካባቢ ላይ ከፍተኛና ጉልህ ችግሮች ሊያስከትሉ ስለሚችሉ እና ቀጣይነት ያለው የአካባቢ ነባራዊ ሁኔታን የማይጎዳ ሥራ ለመስራት ፕሮጀክቶቹ ከመጠናቀቃቸው አስቀድሞ ስርአቱ ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶቹን በኮንትራት ውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና የገንዘብ መጠን ግንባታቸውን ለማከናውንና ለማጠናቀቅ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ እየሰራ ያላቸውን ፕሮጀክቶችና ወደፊት ለሚሰራቸው ፕሮጀክቶች የባቡር ግንባታዎቹ በተፈለገው ፍጥነትና ቅልጥፍና ለማስኬድ ለተሰሩ ስራዎች ክፍያዎችን በስምምነቱ መሠረት በወቅቱ መክፈል ይኖርበታል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚያከናውናቸው የባቡር ፕሮጀክቶች ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው አስቀድሞ የወሰን ማስከበርና የካሳ ክፍያውን ማጠናቀቅና ቦታዎቹን ነፃ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት በሁለተኛው ምዕራፍ ለሚገነባቸው ፕሮጀክቶች በፕሮጀክት ጥናቱ ውስጥ መካተት ያለባቸውን ጉዳዮች ለመወሰን እንዲያስችለው በሚመደብላቸው የገንዘብ መጠን፣ በውስብስብነታቸው፣ በባህሪያቸውና በመሣሠሉት ደረጃ ለመሥጠት መስፈርት ሊያዘጋጅላቸውና የደረጃ አሠጣጡም ፕሮጀክቶቹን ለሚያካሄዱት ድርጅቶች ማሣወቅ ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ማለትም የማህበረሰቡን አሰፋፈር፣ የቦታዎቹን አቀማመጥ፣ የአየር ንብረቱን ሁኔታ /የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ/ ያማከለ የባቡር ምህንድስና ስታንዳርድ ሙሉ ለሙሉ ሊያዘጋጅና ግንባታዎቹን በዚሁ መሠረት ሊያከናውን እንዲሁም ውሉ ላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች ሙሉ ለሙሉ ካልተፈፀሙ ግንባታውን ሊያስቆምና ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚገነባቸው ፕሮጀክቶች ተቋራጩንና አማካሪ ድርጅቶቹ በጋራ የሚሰሩትን ሥራዎች በሚገባ ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣ መረጃዎችን በተደራጀና በተጠናቀረ ሁኔታ ለመያዝ እንዲችል፣ ፕሮጀክቶቹ ሲያልቁ በሁሉም ዘርፍ ያሉ የባቡር ቴክኖሎጂዎችን ለማስቀረትና በአካባቢተፅዕኖ ግምገማ ውስጥ የተጠቀሱትን ዝርዝር ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ የቅ/ፕ/ጽ/ቤቶቹንና ንዑስ የፕሮጀክት ጽ/ቤቶቹን በበቂ የሰው ሃይልና ቁሳቁሶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ውል ሲገባ ድርጅቶቹ በውል በተቀመጠው ቀን ሥራዎችን የማያጠናቀቁ ከሆነ፣ ውሉ ላይ የተጠቀሱ አንዳንድ ጉዳዮች ለምሣሌ ለክትትልና ቁጥጥር አስፈላጊ

የሆኑ ሰነዶች የማይቀርቡ ከሆኑ እና በኮንትራቱ መሠረት ሥራዎች የማይሰሩ ከሆነ ኮርፖሬሽኑን ካላስፈላጊና ከተጨማሪ ወጪ ለመጠበቅ በውሉ ላይ በተጠቀሰው መሠረት የቅጣት እርምጃ ሊወስድና እንዲሁም ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች ጋር የሚገባው ውሎች አሻሚ ያልሆኑ፣ ግልጽ የሆኑና በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት በምዕራፍ ሁለት ለሚገነባቸው ፕሮጀክቶች እንደግብዓት ለመጠቀም እንዲያስችለውና እየተገነቡ ባሉት ፕሮጀክቶች ላይ የመፍትሔ ሃሳብ ለመስጠት እንዲያስችለው እየተገበራቸው ባሉና በተገበራቸው የፕሮጀክት ሥራዎች በግንባታ ላይ በተሰማሩ ተቋራጮችና አማካሪዎች አካባቢ ያሉትን ዋና ዋና ክፍተቶችና ችግሮች ሊለይና የደሰሳ ጥናት በማድረግ ሰነድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት በምዕራፍ ሁለት ለሚገነባቸው ፕሮጀክቶች ተቋራጮቹ የስራውን የጊዜ ሰሌዳ (Master Work Schedule) በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንዲያቀርቡ ሊያደርግ፣ መካተት የሚኖርባቸው መረጃዎች ማለትም ግንባታው የሚካሄድበት ዘዴ፣ የሚሠራው ሥራ አጠቃላይ መጠን፣ የገንዘብ ፍሰት ግምት፣ የመሳሪያዎችና የሰው ሃይል አጠቃቀም ሊካተቱ፣ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ከተቋራጮች ጋር ውል ሲገባ የባቡር ግንባታው በተቀመጠለት መስፈርት መሰረት እንዲሰራና በተገቢው የጥራት ደረጃ እንዲሠራ ውሎቹ ላይ በግንባታው ሥራ ላይ የሚካፈሉት የተቋራጮቹ ከፍተኛ የባቡር መሃንዲሶች ሊገለፁ፣ በሥራው ላይ የሚካፈሉትና የመጡት የተገለፁት መሀንዲሶች ስለመሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ክትትሉና ቁጥጥሩን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን የሚረዳው የፕሮጀክት ሥራ አመራር መመሪያዎቹ ስለሆኑ በእነዚህ መመሪያዎች መሠረት ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ከስራ ተቋራጩ፣ አማካሪ ድርጅቱ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ለሚቀርቡለት መፍትሔ ለሚሹ ጉዳዮች በወቅቱ መፈታት የሚገባቸው ጉዳዮች ለመፍታት እንዲያስችለው እና በፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳይፈጥር አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ሊያዘጋጅ፣ ከሃገር ውስጥ ኮሌጆችና የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር በመተባበር በባቡር ኩባንያ አስተዳደር፣ በጥገናና በኦፕሬሽን ክህሎት የሚያደረገውን ስልጠና አጠናቅሮ ሊቀጥልና ወደፊት ስራውን የሚረከቡ ባለሙያዎች ተገቢው ስልጠና ተሰጥቷቸው ሊዘጋጁ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ወደፊት ለሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ከመጀመራቸው አስቀድሞ የባቡር መሥመሩ በሚያልፍባቸው አካባቢ ላሉ ነዋሪዎችና ባለድርሻ አካላት መሰረተ ልማቱ ሲጠናቀቅ በሚያስገኘው ጥቅም ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ የመሠረተ ልማቶቹንና በግንባታው ላይ ቀጥተኛ ተሣትፎ የሚያደርጉትን የተቋራጩንና የአማካሪዎቹን ሠራተኞች ከስርቆትና ከአደጋ ለማዳን የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና በሥራው ሂደት ላይ መጓተቶችና አለመግባባቶችን ለማስቀረት ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ማጠናከር ይኖርበታል፡፡
- በኮርፖሬሽኑ የእውቀት ሽግግር እንዲኖርና ወደፊት በሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ላይ በተለያዩ የግንባታ ሥራዎች ላይ እንዲካፈሉ ለማስቻል ለሃገር ውስጥ ተቋራጮችና አማካሪዎች በግንባታው የሚሳተፉበትን የኮንትራትና የህግ አግባብ ሊቀርፅ፣ ተግባራዊ ሊያደርግ፣ ስልጠናዎች ሊሰጥና የርስበርስ ልምድ ልውውጥ መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ አለምአቀፍ ተቋራጮች፣ አማካሪ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና የተለያዩ የውጪ ሃገርና የአገር ውስጥ አካላት

በባቡር ኢንዱስትሪው ላይ ለመካፈል እንዲያስችላቸውና ኮርፖሬሽኑ ስለሚገኝበት ደረጃ ለመረዳት ለሚፈልጉ በቂ የሆነ መረጃ ለማግኘት እንዲችሉ የባቡር ኢንዱስትሪውን በተከተለ መልኩና የኮርፖሬሽኑን እንቅስቃሴ ባገናዘበ ሁኔታ የመረጃ መረብ ሊዘረጋና በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታና አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ በጥናት ላይ ተመስርቶ ሥራውን ለማከናወን እንዲያስችለው ኢታልፌር ከተባለው የጣሊያን ድርጅት ጋር በባቡር ግንባታና አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ የሚያካሄደውን ጥናት ሊቀጥልና ሊያጠናቅቅ ይገባል፡፡
- በማስተባበሪያ ጽ/ቤቶቹ የአካባቢ ግምገማ ጥናቶቹ፣ የአዋጪነት ሰነዶቹና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ሊገኙ እንዲሁም በማስተባበሪያ ፅ/ቤቶቹ ሥር ያሉ ባለሙያዎች በፕሮጀክቶቹ ሰነዶቹ ላይ የተዘረዘሩ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን ሊያውቁና በአካባቢና በማህበረሰቡ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለማስቻል ሥራዎቹ በጥናቶቹ መሠረት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ሊከታተሉ ይገባል፡፡

11.13 በኢትዮጵያ ገቢዎች እና ግሙሩክ ባለስልጣን የተወረሱ ንብረቶች አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ

የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋና የመረጃ ቋት/data base/ የተዘጋጀ ስለመሆኑ፤

341. የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ሊዘረጋ፣ የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችሉ

ፕሮግራሞችና ሶፍትዌሮች በማበልጸግ ሥራ ላይ ሊያውልና የመረጃ ቋት (data base) ሊኖረው ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ የባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በጉምሩክና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ያልዘረጋና የአሰራር ሥርዓቱን መደገፍ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ሥራ ላይ እንዲውሉ ያላደረገ ሲሆን እንዲሁም የንብረቶቹን ሙሉ መረጃ ማለትም መቼ እንደ ተወረሱ፣ መቼ እንደ ተወገዱና ያልተወገዱ ንብረቶችን የሚገልጽ የመረጃ ቋት/ data base/ እንደሌለው ታውቋል፡፡
- ✓ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው አዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ሚሌ፣ አዋሽ መቅረጫ ጣቢያ፣ ድሬደዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች ንብረቶች ተወርሰው ወደ መጋዘን ሲገቡና እና በተለያየ መንገድ ሲወገዱ መረጃቸው በዘመናዊ መልኩ ተደራጅቶ የተያዘ አለመሆኑን ሰነድ በመከለስ ፣ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የተወረሱ ንብረቶች አመዘጋገብና እና የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መድረጉን በተመለከተ

342. ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች ወደ መጋዘን ሲገቡ እና በተለያየ ስልት ሲወገዱ ተገቢውን መረጃ እና ማስረጃ ለመስጠት የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የንብረት አመዘጋገብ እና ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች መጋዘን ሲገቡና በተለያየ መንገድ ሲወገዱ የንብረት አመዘጋገብ ስርዓት ያለ ቢሆንም በአሰራር ስርአቱ መሰረት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ የማይደረግ በመሆኑ

በቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የንብረት አመዘጋገብ እንደሌለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ✓ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መካከል በአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ በሚሌ፣ በድሬደዋ፣ በጅጅጋ ፣ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤቶች እና በአዋሽ ማስተባበሪያ ፣ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶች የተተው፣ ባለቤት የሌላቸው፣ በዱቤ እና በጨረታ የሚሸጡ እንዲሁም ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉና የሚወድሙ ተብለው እንደ ዓይነታቸው እና ባህሪያቸው ተለይተው የማይመዘገቡ ሲሆን የአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች ምን ያህል ንብረቶች እንደገቡና እንደወጡ የሚመዘገቡበት የንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ እንደሌላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ የሂሳብ አያያዝን በተመለከተ በቅ/ጽ/ቤቶችና በዋናው መ/ቤት ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ሂሳባቸው በgeneral ledger እንዲሁም በተላለፈላቸው ድርጅቶች ስም እንደ ጅንአድና አዲስ ፋና እና ሌሎች በየመ/ቤቶቹ ስም ተቀጽላ ሌጀር /subsidary leder/ /የሂሳብ ቋት/ ተከፍቶ አይመዘገብም፡፡
- ✓ እንዲሁም በናሙና ከታዩት በአዲስ አበበባ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ተሽከርካሪ በሚያዝበት ጊዜ በማቆያ ሞዴል 270 ተመዝግቦ በሞዴል 265 ውርስ ሆኖ ገቢ ሳይደረግ በቀጥታ በሞዴል 266 ወጪ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም ተሽከርካሪዎች ሲወረሱ ያላቸው እና የጎደላቸውን ዕቃ መረጃ የሚሞላበት የመረካከቢያ ሰነድ ያለ ቢሆንም በአቃቂ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ሚሌ፣ ድሬደዋና ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤቶች በመረካከቢያ ሰነዱ መሰረት የተሽከርካሪ ርክክብ የማይፈጸም መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ሰነድ በመከለስ ቃለመጠይቅ በማቅረብ እና

የቅ/ጽ/ቤቶችን አሰራር በአካል ተገኝቶ በመገምገም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች መረጃ በአግባቡ መያዙን እና በየበጀት አመቱ ቆጠራ የሚደረግ ስለመሆኑ ፣

343. በባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡ፣ በማውደም የሚወገዱና ሊወገዱ ያልቻሉ ንብረቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይቶ ተገቢው መረጃ በአግባቡ መያዙን ክትትል ሊያደርግና ባለሙያዎች መርጦ በማዋቀር በየበጀት አመቱ የንብረት ቆጠራ ሊያደርግና የቆጠራ ሪፖርት እንዲቀርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ በባለስልጣን መ/ቤቱ በዱቤ የሚሸጡ፣ ለሌሎች መ/ቤቶች የሚተላለፉ፣ በጨረታ የሚሸጡና በማውደም የሚወገዱ የተወረሱ ንብረትቶች በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው መረጃቸው በተሟላ እና በአግባቡ መያዛቸውን በተመለከተ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ ከተከለሱ ሰነዶች፣ ለሥራ ኃላፊዎች ከቀረቡ ቃለመጠይቆችና ከመስክ ግምገማዎች ለማረጋገጥ እንደተቻለው በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በርካታ ንብረቶች ሳይወገዱ ከአምስት እስከ አስር ዓመት ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን የንብረቶች የተጠናቀረ መረጃ የሌለ መሆኑ እንዲሁም መቼ እንደተወረሱ እና የንበረቶቹ ዋጋ በገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ የሚያመላክት መረጃ እንደሌላቸው ታውቋል፡፡ ንብረቶቹ ለምን ሊወገዱ እንዳልቻሉ በተካሄደው ማጣራት ዋና ዋና ምክንያቶች ተብለው የተገለጹት የዕቃዎችን ዓይነት ፣ የተሰራበትን ሀገር አለማወቅ የዕቃዎቹን ዋጋ ለመተመን አስቸጋሪ መሆኑ በአጠቃላይ ንብረቶቹን አስመልክቶ የተሟላ

መረጃ ማግኘት ባለመቻሉ ለዕቃዎቹ የሚዘጋጀው ዋጋ የተጋነነ የሚሆንበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ገዢ እንዳይኖራቸው እንደሚያደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በተመሳሳይ መልኩ ጅንአድ በዋጋ ምክንያት አልወስድ ያላቸው ምንያህል ንበረቶች እንደሆኑ በመጠን እና በብር የተጠናከረ መረጃ ያልተዘጋጀ ሲሆን ለተባባሪ መስሪያቤቶች የሚተላለፉና በጨረታ የሚሸጡ ተብለው ዕቃዎችና ተሽከርካሪዎች ተለይተው እንዳልተያዙ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ✓ እንዲሁም በናሙና ከታዩ በጅጅጋ 38 ፣ በአዲስ አበባ ቃሊቲ 7፣ በአዳማ 3 በሚሌ 18 የተሽከርካሪዎችን ዝርዝር መረጃ የሚገልጽ ማለትም ታርጋ ቁጥር፣ የምርት ዘመን፣ ሞዴል፣ ሻንሲ ፣ ሞተርና ሞዴል ቁጥር እና የተወረሰበት ቀን በአግባቡ ያልተመዘገበ ሲሆን እንዲሁም በናሙና በታዩ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ ቁጥር ያላቸው ተሽከርካሪዎች በወቅቱ አለመወገዳቸው ታውቋል፡፡

ባለስልጣኑ የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

344. በባለስልጣኑ የተዘጋጀው የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ ወቅታዊ ሊሆን እና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው ዋጋ ሊተመን ይገባል፡፡

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ የእቃዎችን ዋጋ ለመተመን የሚጠቅምበት የዋጋ መተመኛ ሲዲ በየጊዜው ወቅታዊ መሆን ያለበት ቢሆንም ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አንድ አይነት መስፈርት ላላቸው ዕቃዎች የተለያየ ዋጋ የሚተመን መሆኑ እና የሲዲ ዋጋ አተማመኑ የንብረተቹን ሁኔታ ያላገናዘበ የተጋነነ ዋጋ

የሚተመንበት አሰራር በመኖሩ ምክንያት እቃዎቹ ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜያት የተቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት የተወረሱ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በሲዲ ዋጋ አተማመን ችግር ምክንያት ከ5 ዓመት በላይ ሊወገዱ አለመቻላቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል ፡፡

የተወረሱ መድሀኒቶች፣ ምግቦችና አደገኛ ዕቃዎች አጠባበቅን በተመለከተ፣

345. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች / ለመድሀኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለለሌሎች ዕቃዎች / እንደ ዓይነታቸውና ባህሪያቸው እንዲሁም ይዞታቸው ሳይለወጥ ተጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ የሚያስችል የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ሊያዘጋጅ እና ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ✓ ባለስልጣኑ በግምሩክ እና በታክስ ዕዳ ለተወረሱ የተለያዩ ንብረቶች አስከ ሚወገዱ ድረስ እንደ እቃዎቹ ዓይነትና ባህሪይ ተለይተው መቆየት የሚችሉበት የተሟላ መሳሪያ ያለው ዝግና ክፍት መጋዘን ያላዘጋጀ፣ ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ በሚቀመጡበት ጊዜ ይዞታቸውንና መሰረታዊ ባህሪያቸውን ሳይለቁ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ እንዲቀመጡ ያላደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ✓ የኦዲት በድኑ በመስክ ምልከታ ወቅት በናሙና ካያቸው በጅጅጋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጉምሩክ የተወረሱ ብዛት ያላቸው ንብረቶች እንደ ዓይነታቸውና ባህሪያቸው ተለይተው የሚቀመጡበት በቂ የሆነ ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን እና የዕቃ ማስቀመጫ መደርደሪያ የሌላቸው በመሆኑ በህግ ጉዳይ ከተያዙት ጋር ተቀላቅለው የሚቀመጡ ሲሆን እንዲሁም

ዕቃዎች ለበርካታ ቀናት በተያዙባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ ተጭነው የሚቀመጡ መሆኑ፡፡

- ✓ እንዲሁም በናሙና በታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች ንብረቶቹ ተይዘው ወደ ውርስ መጋዘን ከገቡ በኋላ ወቅታዊ የሆነ ውሳኔ የማያገኙ በመሆኑ በተለይ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ከፍተኛ የሆነ ክምችት የሚገኝ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በተቀመጠው ጊዜ ገቢ ስለመደረጋቸውና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፣

346. በቅ/ጽ/ቤቶች የሚወረሱ የውጭ አገር ገንዘቦች በባለስልጣኑ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋጋድ መመሪያ ቁጥር 56/2003 መሰረት በ48 ሰዓት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጋቸውን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በህገወጥ መንገድ ከሀገር ሲወጡና ሲገቡ የሚወረሱ የውጭ ሀገር ገንዘቦች በ48 ሰዓትውስጥ ከተያዙበት ቅ/ጽ/ቤት በወቅቱ ገቢ ስለ መደረጋቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ✓ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ቅ/ጽ/ቤቶች በአዋሽ መቅረጫ ጣቢያ የተወረሰ ስድስት ሺህ (6000) የአሜሪካን ዶላር እና 3000 የሳውዲ ሪያል ከአራት ወር በላይ ገቢ ሳይደረግ በመቅረጫ ጣቢያው የሚገኝ ሲሆን ለባለስልጣኑ በወቅቱ ገቢ አልተደረገም፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ፣ ክፍተቶች በመለየት እንዲሻሻሉ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

347. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ፣ ለቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭ እና

ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ እንዲሁም በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጁን መሰረት በማድረግ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣ እና ለቅ/ጽ/ቤቶች ያሰራጨ ቢሆንም በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት መመርያው እንዲሻሻል እንዳላደረገ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር ከተካሄዱ ቃለ መጠይቆይች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ✓ እንዲሁም በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶችን በተመለከተ የሚወገዱበትን አሰራር የሚገልጽ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተዘጋጀው መመሪያ ከሚመለከታቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ውስጥ ያልደረሳቸው ያሉ ሲሆን በተጨማሪም በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በባለስልጣኑ መወገድ የሚገባቸው የተወረሱ ንብረቶች የአወጋገድ ስርዓት ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፣

348. በቅ/ጽ/ቤቶች የተያዙ የከበሩ ማዕድናት በተያዙ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ገቢ ሊደረጉና ወደ ገቢ ሊቀየሩ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ካያቸው ቅ/ጽ/ቤቶች አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምንነታቸው ያልታወቀ 55 ኪ.ግ የተወረሱ የከበሩ ማዕድናት ከአምስት አመት በላይ የተቀመጡ ሲሆን እንዲሁም መጠናቸው ያልታወቀ ማዕድናት በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ ቢሆንም

ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ እና ወደ ገቢ እንዲቀየሩ አልተደረጉም፡፡

- ✓ እንዲሁም በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እና ለማስወጣት ሲሞከር የተያዙ 69,571.5 ግራም ከብር የተሰሩ ጌጣጌጦች እና የተለያዩ ሜታሊክ ሜርኩሪዎች ባለስልጣኑ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከራየቸው አራት የአደራ ማስቀመጫ ሳጥኖች ውስጥ ከተቀመጡ ረጅም ጊዜያትን ስላስቆጠሩ ይዞታቸው እተቀየረ መሆኑን እንዲሁም በዳይሬክቶሬቱ የሚገኝ 146.3 ግራም የብር ጌጣጌጥ ወደ ገቢ እንዲቀየር እና ገንዘቡ በወቅቱ ገቢ እንዲሆን አለመደረጉ ታውቋል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ስለማቋቋሙና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ

349. በባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴ ሊያቋቋም እና አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን የሚያስወግድ ኮሚቴዎች ከተለያዩ የስራ ሂደቶችና ባለድረሻ አካለት በማካተት ያቋቋመ ቢሆንም ኮሚቴው ተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ እንዳልሆነ ፤

- ✓ እንዲሁም በናሙና ተመርጦው በግንቦት 2006 ዓ.ም የመስክ ምልከታ በተደረገባቸው አዲስ አበባ ኤርፖርት፣ አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ሚሌ፣ ድሬደዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና አዋሽ መቅረጫ ጣቢያ ብዛት ያለቸው መድሀኒቶች፣ ኬሚካሎች፣ ቅርሶች እና የህክምና መገልገያ

መሳሪያዎች እንዲወገዱ ሳይደረግከ 2 ዓመትእስከ 7 አመት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑን እንዲሁም ኤሌክትሮኒክሶች ፣ ሞባይሎች፣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በወቅቱ እንዲወገዱ አለመደረጉን በቅ/ጽ/ቤቶቹ ከተከለሱ ሰነዶችና፣ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለመጠይቅ በማቅረብ እና በካል ንብረቶቹን ተዘዋውሮ በመመልከት ንብረቶቹ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲተላለፉ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ የሚተላለፉ ንብረቶች ክፍያ ላይ ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

350. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሽያጭ ለሚተላለፉ ወይም ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በክፍያ ለሚረከቧቸው ዕቃዎች ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ለባለስልጣኑ ገቢ መደረጉን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ከሚያስወግድበት መንገድ አንዱ በዱቤ ሽያጭ ሲሆን በዚሁ መሰረት ከጅንአድ እና አዲሰ ፋና ድረጅቶች ጋር ውል በመግባት ንብረቶችን የሚያስተላልፍ ቢሆንም፣ ነገር ግን ክፍያው በውሉ መሰረት ገቢ ስለመደረጉ ወይም ስለመሰብሰቡ አሰፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

- ✓ በመሆኑም ለጅንአድ በዱቤ ሽያጭ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የተላለፉ ዕቃዎች እስከ ነሀሴ 2006 ዓ.ም በውሉ አንቀጽ ሦስት ንኡስ አንቀጽ 3.4 መሰረት በ120 ቀን ውስጥ መከፈል የነበረበት ብር 343,205,205.36 እና ከአዲስ ፋና ከ2005 ዓ.ም እስከ ነሀሴ 2006 ዓ.ም ብር 311,293.30 ያልተሰበሰበ ሲሆን እንዲሁም በወሉ አንቀጽ ሦስት ንኡስ

አንቀጽ 3.5 መሰረት በወቅቱ ገቢ ካልተደረገ በሀገሪቱ ከፍተኛ የወለድ መጠን መሰረት ይከፈላል የሚል ቢሆንም ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ✓ እንዲሁም የባለስልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ ቤቶች፡በዱቤ ሽያጭ በሚያከናውኑበት ወቅት በሪፖርት የሽያጩን ዋጋ ለዋናው መ/ቤት በደብዳቤ የሚያሳውቁ ቢሆንም ያሰወግዱዋቸውን ንብረቶች ሂሳብ ሌጀር ከፍተው የማይመዘግቡ ሲሆን ዋናው መ/ቤትም ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያሳውቁትን በዱቤ ሽያጭ የወሰዱ ድርጅቶችን ሂሳብ የሂሳብ ቋት / Leadger /በመክፈት ምን ያህል እንደተከፈለና ምን ያህል እንዳልተከፈለ ተገቢውን ምዝገባና ክትትል እንደማያካሂድ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን ወደ ገቢ እንዲቀየሩ መደረጉን በተመለከተ

351. በታክስ እዳ የተያዙ ንብረቶችን በመመሪያው መሰረት በወቅቱ ወደ ገቢ የሚቀየሩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

- ✓ በታክስ ዕዳ የተወረሰ ንብረት ባለንብረቱ ዕዳውን እንዲከፍል ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ክፍያውን ካልፈጸመ ንብረቱ ተሸጦ ዕዳው መከፈል ያለበት ቢሆንም በታክስ እዳ የተወረሱ ንበረቶች መመሪያውን መስረት በማድረግ በወቅቱ ወደ ገቢ እንዲቀየሩ አልተደረጉም፡፡
- ✓ በመሆኑም ከአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ2004 ዓ.ም ግምታቸው 976,684.73 የሆኑ እቃዎች ተወርሰው በ2005 ዓ.ም ለዋናው መ/ቤት የተላለፉ ቢሆንም ወደ ገቢ ያልተቀየሩ መሆኑ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች የተወረሱ እና ለዋናው መስሪያ ቤት ከ2004ዓ.ም ጀምሮ የተላለፉ

ግምታቸው ብር 269,257,415.8 የሆነ ንበረቶች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ተሸጠው ወደ ገቢ እንዲቀየሩ እንዳልተደረገ ታውቋል፡፡

በድርድር ያልተሸጡ ዕቃዎች በጨረታ እንዲሸጡ የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ፣

352. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት መ/ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች በድርድር ለመግዛት ፈቃደኛ ያልሆኑባቸውን ዕቃዎች በጨረታ መሸጥ ሊሸጥ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በባለስልጣን መስሪቤቱ በተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመንግስት መ/ቤቶች በዋናነት ጅንአድ አልወስድ ያለቸው በርካታ ግምት ያለቸው እቃዎች ያሉ ቢሆንም ጨረታ በማውጣት እንዲወገዱ እንዳለደረገ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በባለስልጣን መ/ቤቱ ስር ባሉ አዲስ አበባ ቃሊቲ፣ አዳማ፣ ድሬደዋ ፣ ሚሌ፣ ጅጅጋ፣ ሞያሌ፣ ባህርዳር፣ ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዋናነት ጅንአድ እና ሌሎች መ/ቤቶች አልወስድ ያሉዋቸው ግምታቸው የማይታወቅና የተጠናቀረ መረጃ የሌላቸው ዕቃዎች ያሉ ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የተከማቹ ከፍተኛ ግምት ያላቸው አሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የተለያየ ሞዴል ያላቸው የሞባይል ቀፎዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በጨረታ እንዲወገዱ አልተደረገም ፡፡

ከባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚሰራበት ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና የመግባቢያ ሰነድ ያለው መሆኑን በተመለከተ

353. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከበለድርሻ አካላት ጋር በቅንጀት የሚሰራበት ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉሙሩክ እና በታክስ እዳ የተወረሱ ንብረቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠበቅና ለማስወገድ እንደ ንብረቶቹ አይነትና ባህሪ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት የሌለ እና በዚህ ዙርያ ከሚመለከታቸው ከጅንአድና እና ከአዲስ ፋና በስተቀር ከጤና ጥበቃ፣ ከጤና ስነ ምግብ ክብካቤ ፣ ከቅርስ፣ ከመከላከያ እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትጋር የመግባቢያ ሰነድ እንደሌለው በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከአዲስ አበባ ውጪ እና በአዲስ አበባ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን በተመለከተ

354. የባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዳ የወረሷቸውን ተሽከርካሪዎች ለጨረታ ወይም ለሀራጅ መነሻ ዋጋ የሚሆን የንብረት ዋጋ ግምት ከመንገድ ትራንስፖርት እና አግባብነት ካለቸው የክልል መንግስታት መ/ቤቶች ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዲስ አበባ እና ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ቅ/ጽ/ቤቶች በታክስ እዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በጨረታ ወይም በሀራጅ ተሸጠው ሂሳባቸው በወቅቱ ገቢ እንዲሆን ለማስቻል የመነሻ ዋጋ ለማሰራት ከመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት እና አግባብነት ካላቸው የክልል መንግስታት መ/ቤቶች ጋር ቀልጣፋ እና ውጤታማ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት እንዳልዘረጋ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በመሆኑም በታክስ እዳ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች በዋጋ ግምት ምክንያት ሳይወገዱ ለረጅም ግዜ የተቀመጡ

ቢሆንም ነገር ግን ዋጋ ለማስገመት ከመንገድ ትራንስፖርት ሚንስቴር መ/ቤት ጋር በቅንጅት ስለመስራቱ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

- የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በታክስ ዕዳ እና በጉምሩክ የሚወረሱ ንብረቶችን ለመመዝገብና ለማስወገድ የሚያግዝ ዘመናዊ የሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስርዓት በመዘርጋት ስራ ላይ እንዲውል ሊያደርግ እና ስለ እያንዳንዱ የተወረሰ ንብረት የሚገልጽ ሙሉ መረጃ የያዘ የመረጃ ቋት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የንብረት አመዘጋገብና ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በጉምሩክ ና በታክስ ዕዳ የተወረሱ ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ሂሳባቸውን ለመከታተል የሚያስችል General leadger እና subsdary leadger /ተቀጽላ የሂሳብ ቋት ሊከፍት ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶች በተለያየ መንገድ ሲወገዱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ከፍ ለማድረግ፣ ለቁጥጥርና ለክትትል አመቺ ይሆን ዘንድ ንብረቶችን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት ተለይተው ተገቢው መረጃ በተሟላ መልኩ መያዙን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እና እንዲሁም ንብረቶቹ ለብክነትና ለምዝበራ እንዳይጋለጡ በየበጀት አመቱ ቆጠራ መደረጉን ሊከታተልና የቆጠራ ሪፖርት እንዲቅረብ እና እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተወረሱ ንብረቶችን ለማስወገድ ያዘጋጀውን የዋጋ መተመኛ ዘዴ /ሲዲ/ በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግና በሁሉም

ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለው የዋጋ አተማመን እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚያዙ የውጭ ሀገር ገንዘቦችን ቅ/ጽ/ቤቶች ለባለስልጣን መ/ቤቱ እንዲያሳውቁና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ስለማድረጋቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚያዙ የከበሩ ማዕድናት በቆይታ መሰረታዊ ይዞታቸውን ሳይለቁ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ተላልፈው ለሚፈለገው አገልግሎት እንዲውሉ ሊያደረግና በወቅቱ ወደ ገቢ ሊቀየሩ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ እስከሚወገዱ ድረስ ለመድሀኒቶች፣ለምግቦች፣ ለአደገኛና ለሌሎች ንብረቶች እንደ ዕቃዎቹ ዓይነትና ባህሪያቸው ተለይተው በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተለይተው ሊቀመጡ የሚችሉበትና የተሟላ ግብአት ያለው መጋዘን ሊያዘጋጅ እንዲሁም የተወረሱ እቃዎችን በሕግ ተይዘው ጉዳይ ካለባቸው ዕቃዎች በመለየት ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆናቸውን ድጋፍ ፣ ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተወረሱ ንብረቶች አያያዝ/አጠባበቅ መመሪያ ሊያወጣና እንዲሁም በታክስ ዕዳ የተያዙ ንብረቶች ለማስወገድ የወጣውን መመሪያ ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሊያሰራጭና በወጣው መመሪያ አፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት እንዲሻዳሉ ሊያደርግ እንዲሁም ተግባራዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለስልጣኑ የንብረት አስወጋጅ ኮሚቴው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ ስለመወጣቱ የሚያከናወናቸውን ተግባራት፣ የሚያጋጥሙትን ችግሮች በወቅቱ እንዲፈቱ በማድረግ የተወረሱ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ ስለማድረጉ አፈጻጸሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ እዳ ሚወረሱ ንበረቶችን በመመሪያው መስረት በወቅቱ ወደ ገቢ በመቀየር ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን ማሰደግና የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

11.14 በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በመንገዶች ኮንትራት አስተዳደርና

ካሳ ክፍያ አፈፃፀም

355. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይን ሥራ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ለሥራው የሚያስፈልገው ጊዜና ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ እንዲሁም የሥራ መጠን ስሌቶችና የቅየሳ ሥራዎች በሚፈለገው እስታንዳርድ መሰረት መሰራታቸው በሚመለከታቸው አካላት ግምገማ ተደርጎ ሊፀድቅ ይገባል፡፡

- በናሙና ተመርጠው ከታዩ 12 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት የቀረበላቸው የመቀሌ ስረት መንደርና አርባ ምንጭ በልታ ሲሆኑ የተቀሩት 9ኙ ያልቀረበላቸው መሆኑ/ወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅት-ሆሳዕና፣ ጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን ፣ሁምቦ-አርባ ምንጭ፣አለታ ወንዶ-ዳዬ፣ ሀረር-ጅግጅጋ፣ ሳንጃ ቀራቀር፣ ጊዳሚ-ሙጊ/

- የዲዛይን ጥናቱን የአዋጭነት የግዜ መጠን በቢፒአር ጥናት በተቀመጠ የግዜ መጠን /እስታንዳርድ/ ጋር ለማነፃፀር የቢፒአር ጥናት ያልቀረበ መሆኑ

- ✓ የዲዛይን ጥናቱ ግዜ ተሰጥቶት ባለመጠናቱ ምክንያት በወልቂጤ- አረቅጥ 6 ግዜ የዲዛይን ክለሳ በመደረጉ 6 ተጨማሪ ሥራዎች የታዘዙ ሲሆን ብር 45,056,963.92 ተጨማሪ የተከፈለ መሆኑ፣ በአረቅጥ-ሆሳዕና በመንገድ ግንባታ ሂደት ውስጥ 1 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ 2 ግዜ የዲዛይን ክለሳ

መደረጉ ሲገለፅ 8 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች የታዘዙ በመሆኑ ብር 41,906,619.86ሚሊዮን ተጨማሪ የተመደበ መሆኑበአማካሪ መሀንዲሱ በቀረበ የተጨማሪ ሥራዎች ማስረጃ ላይ የተገለፀ መሆኑ ፣

- ✓ በጅማ- ቦንጋ በዲዛይን ወቅት ለተደጋጋሚ ግዜ የዲዛይን ለውጥ በመደረጉ 12 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመታዘዙ ብር 10,707,118.84 የተመደበ መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ በቀረበ ማስረጃ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣ በቦንጋ-ሚዛን 1 ግዜ ታህሳስ 2009 እ.ኤ.አ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ 9 ግዜ የዲዛይን ለውጥ መደረጉ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ምክንያት 9 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመታዘዛቸው ብር 4,331,654.76 ወጪ መደረጉ፣

- ✓ በጊዳሚ-ሙጊ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 2 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ ለተጨማሪ ሥራ ወጪ ብር 4,334,654.76 የተመደበ መሆኑ፣ በምዕራብ ሪጅን ዳይሬክቶሬት የተገለፀ መሆኑ፣በወሪኢ ሪጅ-አድዋ 6 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በተቋራጭ ሲገለፅ በአማካሪ መሀንዲስ ከኪ.ሜ 158+460 -ኪ.ሜ 159+ 600 የዲዛይን ክለሳ እየተደረገ መሆኑንና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ያላፀደቀው በመሆኑ ዲዛይኑ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ተቋራጭ አልፎት እንዲሄድ በመደረጉ ችግር የገጠመው መሆኑ፡

- ✓ እንዲሁም 10 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመታዘዙ ብር 101,116,054.21 ወጪ መሆኑ፣ በመቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክቱ በሥራ ሂደት ላይ እያለ3 ግዜ የዲዛይን ክለሳ የተደረገ መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ

በሥራ ሂደት ወቅት 6 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ምክንያት 8ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመሰጠቱ ብር 145,395,499.62 ተጨማሪ ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

- ✓ እንዲሁም በቀድሞው ሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክቱ በዲዛይን ወቅት በነበረበት ወቅት 3 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ በዲዛይን ላይ በነበረበት ወቅት 9 ግዜ መከለሱ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ምክንያት ተጨማሪ ሥራዎች 8 ግዜ በመታዘዙ ወጪ የተደረገ ብር 122,361,123.85 የኮንትራት መነሻ ዋጋውን 32.18%፣ አዲሱ ሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክት በግንባታ ላይ እያለ 1 ግዜ ሙሉ በሙሉ የክለሳ ሥራ የተሰራ መሆኑና በቀጣይ ግዜያት 4 ግዜ መጠነኛ ክለሳ መደረጉ የተገለፀ መሆኑ፣ እና ለተጨማሪ ሥራ ብር 4,999,999.25 የተመደበለት መሆኑ፣

- ✓ የአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ደግሞ የዲዛይን ክለሳ ተዘጋጅቶ በታህሳስ 02/2010 ወደ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተላከ ሲሆን፣ በግንባታ ላይ እያለ 15 ግዜ ክለሳ የተደረገለት መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ፣በተቋራጭ ፕሮጀክቱ በግንባታ ላይ እያለ 30 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ መገለፁ፡፡

- ✓ በዚህም ምክንያት 15 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች ቢታዘዙም በመነሻ ኮንትራት ከተገባው የሥራ መጠን መቀነስ ያሳየ በመሆኑ በብር 40,993,684.07 የዋጋ ቅናሽ ያሳየ መሆኑ፣የአለታ ወንዶ-ዳዬ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በዋናነት 2 ግዜ የዲዛይን ክለሳ ሲደረግለት 14 ተጨማሪ አነስተኛ የዲዛይን ለውጥ በመደረጉ ምክንያት ብር

146,537,656.01 የተመደበለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን የሀረር ጅግጅጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 8 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች ታዞለት ብር 109,329,353.80 ወጪ የተደረገለት መሆኑ ከቀረቡ ማስረጃዎች ማወቅ ተችሏል፡፡

356. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራ ከመጀመሩ በፊት በተቋራጮች የሚቀርብ እቅድ የአካባቢ ጥበቃ እና በባለስልጣን መ/ቤት መመሪያ መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (environmental impact assessment) ተዘጋጅቶ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተገምግሞ ሊፀድቅይገባል፡፡ ለመንገድ ግንባታ ግብዓትነት የሚውሉ የተፈጥሮ ሀብትን፣ አካባቢንና የማህበረሰቡን ደህንነት በማይጎዳና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንየአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖን በተመለከተ ተቋራጮች ያቀረቡአቸውን የአካባቢ ጥበቃ እቅዶች በሥራ ከመተግበራቸው በፊት በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ያስገመገማቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት ዘጠኝ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች 9ኙንም፡- በወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ- ሆሳዕና፣በጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን፣በወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣ አዲሱ ሳንጃ ቀራቀር፣የቀድሞውና አዲሱ ሁምቦ- አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች እቅዶችን ያላስገመገመ መሆኑ

357. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በመንገድ ግንባታ ሂደት ላይ እያሉ የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖን ለመከላከል የባለሥልጣን መ/ቤቱን የአካባቢ ጥበቃ መመሪያ እና የኢትዮጵያ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 295/95ን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር

መመሪያውና አዋጁን በሥራ ሂደት እያመሳከሩ የሚጠቀሙ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ በ 8ቱ ፡- በወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ-ሆሳዕና፣ በጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን፣ በወሪኢ ሪጅ አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣ በቀድሞውና በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ በልታ መመሪያውንና አዋጁን በሥራ ሂደት እያመሳከሩ የማይጠቀሙ መሆኑ እና መመሪያውም በአማካሪ መሀንዲሱም ሆነ በተቋራጩ እጅ ያልተገኘ መሆኑ

- ✓ ለመንገድ ግንባታ የሚውል ግብዓት/ማቴሪያል/ የተፈጥሮ ሀብትን፣ አካባቢ ጥበቃንና የማህበረሰቡን ደህንነት በማይጎዳ መልኩ ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ

  - በወልቂጤ- አረቅት እና አረቅጥ-ሆሳዕና በባለስልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ ወርሃዊ የመስክ ክትትል የሚደረግ መሆኑ ለሪጅኑ ዳይሬክተር በ 27/02/2007 ዓ.ም በቀረበ ቃለ መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ ቢሆንም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ

  - በጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛንና ጊዳሚ-ሙጊ አማካሪ መሀንዲስ በቀጠረው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ ባለሙያ/ኢንቫሮሜንታሊስት/ ከሐምሌ 3- 13/2013 እ.ኤ.አ በተደረገ ግምገማ የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም በኦዲት ቡድኑ በመስክ በተካሄደ ጉብኝት ተቋራጮች ግብዓት ያወጡባቸውን ቦታዎች ባለመድፈናቸው ህብረተሰቡ ከብቶቻቸው እየወደቁ የሚሞቱባቸው መሆኑንና እነሱም በወባ በሽታ እየተጠቁ መሆናቸውን የገለፁ መሆኑ

  - በአርባ ምንጭ-በልታ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጭ ግብዓት ያወጣባቸውን ቦታዎች

እንዲያስተካክል በአማካሪ መሀንዲስ ተጠይቆ ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ የሆነ መሆኑ መገለፁ

- በወልቂጤ-አረቅጥ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በእምድብር ከተማ ገዳም ሰፈር ቀበሌ 01 ውስጥ እና በሌሎችም ተቋራጭ ግብዓት ያወጣባቸውን ቦታዎች ባለመድፈኑ ምክንያት ውሃ አቁረው በመያዛቸው የትንኝ መራቢያ በመሆናቸው የአካባቢው ኗሪ በወባ በሽታ እየተሰቃ መሆኑን የተገለፀ መሆኑ

358. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በውል ስምምነት በተያዘላቸው ዋጋና በታቀደላቸው ግዜ መጠናቀቅ እንዲሁም በየበጀት ዓመቱ በተያዘላቸው እቅድ መሰረት መከናወናቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

✓ በናሙና ተመርጠው የታዩ 12ቱም ፕሮጀክቶች በውል በተያዘላቸው ዋጋና በታቀደላቸው ግዜ የተጠናቀቁ አለመሆናቸው፤/ማስታወሻ ሁምቦ አርባ ምንጭ በሁለት ተከፍሎ የተገኘው በዝርዝር ኦዲት ወቅት ነው/

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ስም	ርዝመት በኪ.ሜ	ፕሮጀክቱ የተራዘመት ጊዜ ብዛት	ፕሮጀክቱ ከመነሻ ዋጋ በክለሳ ያሳየው ጭማሪ በብር
1.	ወልቂየጤ-አረቅጥ	63.31	8 ወር	-
2.	አረቅጥ-ሆሳዕና	65.5	8 ወር	-
3.	ጅማ-ቦንጋ	110	3 ዓመት	-
4.	ቦንጋ-ሚዛን	119.17	3 ዓመት	4,331,654.75
5.	ጊዳሚ-ሙጊ	90.66	3 ዓመት	4,334,654.76
6.	ወሪኢ-ሪጅ-አድዋ	67.5	5 ወር	44,168,053.62
7.	መቀሌ ስረት መንደር	64.64	10 ወር	145,395,499.62

8.	የቀድሞ ሳንጃ ቀራቀር	47.95	7 ወር	የተቋረጠ
9.	የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭ	73.5	3 ዓመት ከ 2 ወር	122,361,123.84
10.	አዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ	31.5	-	4,999,999.25
11.	አርባ ምንጭ-በልታ	60	የግዜ መራዘም የተጠየቀለ ት	-
12.	አለታ ወንዶ-ዳዬ	51	2 ዓመት ከ 7 ወር	146,537,656.01
13.	ሀረር-ጅግጅጋ	103.6	2 ዓመት ከ 7 ወር	109,329,353.80
ጠቅላላ ድምር				581,457,995.84

359. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተቋራጭ ለሚያቀርበው የተጨማሪ ሥራዎች ክፍያ በአማካሪ መሀንዲስ ታምኖበት የሚደረገው ጭማሪ የኮንትራቱን ዋጋ ከ 15-25% ያልበለጠ ሊሆን ይገባል፡፡

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ስም	ለተጨማሪ ሥራ የወጣ ወጪ በብር	የመነሻ ኮንትራቱን ዋጋ በፐርሰንት	ምርመራ
1.	መቀሌ ስረት መንደር	145,395,499.62	31.02	ከ 25% በላይ
2.	የቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ	122,361,123.85	32.18	ከ 25% በላይ
3.	አለታ ወንዶ -ዳዬ	118,921,452.80	48.9	ከ 25% በላይ

360. ተቋራጭ በመንገድ ግንባታ ሂደት ውስጥ የሰራቸው የውሃ ማሾለኪያ እና የፍሳሽ መስመሮች በሚያመነጩት ውሃ የአፈር መሸርሸር እና በህብረተሰቡም ላይ ጉዳት እንዳያስከትል መከላከያ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ በአረቅጥ-ሆሳዕና መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በሌራ ከተማ የስትራክቸር ሥራው ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ እየፈራረሰ

መሆኑ፣ የውሃ መውረጃ/ዲች/ስትራክቸር የሚሰራበት ድንጋይ ወደኖራ አፈርነት የተቀየረ መሆኑ፣ መጋጠሚያ /ጃንክሽን/ ላይ የሚጠቀሙበት ቦታ አቃፊ የሌለው መሆኑ ለሀዋክ ተቋራጭ ምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ጽ/ቤት በ 22/07/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑ ፡እንዲሁም በዲች አለመሰራት ምክንያት በመንገዱ ግራና ቀኝ የሚኖሩ ሶስት የግለሰቦች ቤቶች በጎርፍ የተጎዱ መሆኑ፣ በጅማ-ቦንጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ለሸቤ ሰምቦ ወረዳ ጽ/ቤት ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ከመንገድ ጥራት አኳያ ከአስፋልት ወደ ዲች የሚያስገባ የጎርፍ መውረጃ ቀዳዳ ከፍ ብሎ በመሰራቱና ጠባብ በመሆኑ በዝናብ ወቅት ውሃ አስፋልቱ ላይ የሚተኛና ግለሰቦች ቤት በመግባት ንብረት ያበላሽ መሆኑ መገለፁ፡፡

- ✓ በቦንጋ-ሚዛን መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በጨና ከተማ ወደ ምክር ቤት መግቢያ ላይ መንገዱ ሲሰራየአፈር መገደቢያ ግድግዳ ባለመሰራቱ አፈር እየተናደ መሆኑ፣ ወደ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን እና ወደ ጥልቅ ውሃ ጉድጓድ መሂጃ የሚወስደው የመኪና መተላለፊያ ውሃ በሚያልፍበት ቦይ /በዲች/ በመዘጋቱ ማለፊያ የሌለ መሆኑ፤ እንዲሁም በመንገዱ ግራና ቀኝ ዲች የሚፈልጉ ቦታዎች ያልተሰራላቸው በመሆኑ የግለሰቦች ቤት በጎርፍ የተጠቃ መሆኑ በመስክ ኦዲት ማየት የተቻለ መሆኑ፡፡/በፎቶ የተደገፈ/

361. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ለመከታተል የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ተግባራዊ ሊያደርግ፣የግንባታጥራትን ለመከታተል ከአማካሪ መሀንዲስና ከተቋራጭ ጋር በዓመታዊ እቅድ የተካተተ የሶስትዮሽ ግምገማ

ማድረግ፤ እንዲሁም አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ በገቡት ውል መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ✓ በናሙና ተመርጠው በመስክ በታዩ 9 ፕሮጀክቶች ከዋና ዳይሬክተር አስከ ፕሮጀክት መሀንዲስ በዓመታዊ እቅድ ውስጥ በተካተተ መልኩ የመስክ ቁጥጥርና ክትትል እንዲሁም ግምገማ የማይካሄድ ሲሆን፣እንዲሁም አልፎ አልፎ ለሚደረግ የመስክ ጉብኝት የተሰጠ የማሻሻያ ሃሳብ ያልተገኘ መሆኑ፤

362. ባለሥልጣን መ/ቤቱ አማካሪ መሀንዲስም ሆነ ተቋራጭ የገቡት ውል ተፈፃሚ ካልሆነ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ✓ በባለሥልጣንመ/ቤቱአማካሪ መሀንዲስም ሆነ ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ ሥራው በገቡት ውል መሰረት ተፈፃሚ ካላደረጉ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስድ መሆኑ በተግባርናኃላፊነቱ ላይ የተገለፀ ሆኖ በናሙና ተመርጠው በኦዲት ወቅት በታዩት12 ፕሮጀክቶች ወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ-ሆሳዕና፣ጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ- ሚዛን፣ጊዳሜ-ሙጊ፣ ወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣የቀድሞ ሳንጃ ቀራቀር፣ የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ አርባ ምንጭ-በልታ፣ ኦለታ ወንዶ-ዳዬ ና ሀረር- ጅግጅጋ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ የግዜ ማራዘሚያና የኮንትራት ዋጋ ክለሳ ከመፍቀድ ውጪ በውል የገቡትን ግዴታ ሊወጡ ባልቻሉና ተደጋጋሚ ችግር በሚፈጥሩ ተቋራጮችና አማካሪ መሀንዲሶች ላይ ከቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር በስተቀር የወሰደው የማስተካከያ እርምጃ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ የታወቀ መሆኑ፤

363. ባለሥለጣን መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም ካሳ የተከፈለባቸው ንብረቶች

በሚነሱበት ግዜ የሚከሰት የፀጥታ ችግርን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ ባለስልጣን መ/ቤቱ እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በወልቂጤ-አረቅጥ በመንገድ ክልል ውስጥ የገቡ የአገልግሎት መስመሮችን መብራትሃይል በወቅቱ አለማንሳቱ፣ የአካባቢው ኗሪዎች በየግዜው የመንገድ ግንባታው ሥራ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው እና የአስፋልት ሬንጅ ስርቆት መፈፀሙ፣ በጅማ-ቦንጋ በክምችት የተያዙ የግንባታ ግብዓቶች፣ የማሽነሪና ኢኪውፕመንት እስፔር ፓርቶች በአካባቢው በሚኖሩ ግለሰቦች የተሰረቁ መሆኑ በቦንጋ-ሚዛንም በተደጋጋሚ ሥራ እንዲቆም በአካባቢው ኗሪዎች የተደረገ መሆኑ፤ ለአማካሪ መሀንዲስ፣ ለተቋራጭና ለመንገድ መብት ማስከበር ወኪል በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፤

364. ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል የካሳ ግምት የወጣውን ሀገር አቀፍ አዋጅ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

- ✓ ለልማት እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል የካሳ ግምት የወጣውን አዋጅ 455/97 አንቀጽ 4 መሰረት በማድረግ ካሳ ለተነሺ ህብረተሰብ መከፈሉን ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል ማድረጉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 7ቱ ፡-

- በወልቂጤ- አረቅጥ ፕሮጀክት ለወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤት ቅሬታ ካቀረቡ ተነሺ ግለሰቦች 2ቱ ባቀረቡት የቅሬታ አስተያየት 1ኛ በአምቦ ጥርብ የተገነባ ቤት ከተለያዩ ቋሚ ተክሎች ጋር ተመጣጣኝ ካሳ ያልተከፈላቸው መሆኑን ለወረዳ መስተዳድርና ለገማች ኮሚቴ በወቅቱ አመልክተው መልስ ያላገኙ ሲሆን፣ 2ኛ አዲስ መኖሪያ ቤትና የተለያዩ ቋሚ ተክሎች ተነስተው በተመሳሳይ ሁኔታ ተመጣጣኝ ካሳ አለመከፈሉ፣

- በአረቅጥ-ሆሳዕና ፕሮጀክት 2 ግለሰቦች እያንዳንዳቸው በአቀረቡት ቅሬታ 1ኛ ግለሰቡ ከ 200 በላይ ለሚሆን የባህርዛፍ ቋሚ ተክል፣ እንዲሁም 2ኛ ግለሰብ 150 ካሬ ሜትር የከተማ ቦታ/በሌራ ከተማ/ 300 ቋሚ ተክል ጥድ ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ ያልተከፈላቸው መሆኑ፣

- በጅማ-ቦንጋ ለ11 ግለሰቦች ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው 4ቱ ባቀረቡት ቅሬታ 1ኛ በሸክላ የተሰሩ ቡቲክና መጠጥ ቤት ብር 400,000 ወጪ የተደረገባቸው፣ 2ኛ ግለሰብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 ላይ ምትክ መሬት ለማይሰጠው የአንድ ዓመት አማከይ ገቢን በ 10 አባዝቶ እንደሚከፈል የተገለፀ ቢሆንም ለቋሚ ተክል ማንጎ፣ግሽጣ፣ ፓፓያ እና ሽንኮራ አገዳ የተከፈለ የአንድ ዓመት ብቻ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ 3ኛ ግለሰብ የሸቤ ከተማ ኗሪ የሆኑ አዛውንት በቁጥር BU1/203/01 በቀን 30/02/2003 በተፃፈ ደብዳቤ የሸቤ ሰምቦ ወረዳ ማህተም ያረፈበት የባለሥልጣን ፊርማ በሌለው ማስረጃ ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ወጪ ሆኖ ተልኳል በሚል ብር 46,676.16 ተገምቶ ቤታቸው ፈርሶ ያልተከፈላቸው መሆኑ፣ 4ኛ የሸቤ ከተማ ኗሪ ግለሰብ የካሳ መገመቻ ቅፅ ላይ በ 30/02/04 ብር 30,625.76 ተገምቶላቸው ቤታቸው ፈርሶ ግምቱ ያልተከፈላቸው መሆኑ፣

- በቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክት የወዳ ቁልሽ አርሶ አደር ተቋራጭ ምንም ዓይነት ውል ሳይገባ ከመሬታቸው ላይ ለመንገድ ግንባታው አፈር ቆፍሮ መውሰዱንና በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ብር 4000 የምትገመት ላም ወድቃ መሞቷን የገለፁ መሆኑ፤

- በወሪ ሪጅ-አድዋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 12 ግለሰብ ነጋዴዎች በአንድነት ቀርበው ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በአዋጅ 455/97 የ 90 ቀናት የማስለቀቂያ ግዜ በፅሁፍ ተገልፆ የሚሰጥ ቢሆንም በ 6 ቀናት እንዲለቁ በፅፍ መጠየቃቸውን ገልፀው የክልሉ መስተዳድር የከተማና ኢንዱስትሪ ልማት መመሪያ አንቀፅ 42 ተ.ቁ 3 በሚያዘው መሰረት ተለዋጭ ቦታ፣ ቤት፣ቢያንስ የኮንዶሚኒየም ቤት እንዲያገኙ ማድረግ ሲገባ ተፈፃሚ ባለማድረግ እንዲለቁ የተገደዱ መሆኑን መግለፃቸውና በመንገድ መብት አስከባሪ ወኪሉ በኩልም በህግ አግባብ ተፈፃሚ እንዲሆን ትብብር ያልተደረገላቸው መሆኑንየገለፁ መሆኑ፤

- መቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለቋሚ ተክሎች የአንድ ዓመት ክፍያ በመክፈሉ ምክንያት የትግራይ ክልል መመሪያ የ1 ዓመት አማካይ ገቢን በ10 ዓመት አባዝቶ እንዲከፈል ታሳቢ የሚያደርግ በመሆኑ የከተማው መስተዳድር በ 10 ዓመት አስቦ የከፈለ መሆኑ፤ ሆኖም አዋጅ 455/97 እንዲለቀቅ የተደረገ የሰብል ወይም የቋሚ ተክል መሬትን በተመለከተ በአንቀፅ 15 መሰረት እንዲሁም በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 መሰረት ምትክ መሬት መስጠት ካልተቻለ የሚከፈለው የማፈናቀያ ካሳ ሰብሉ ወይም ተክሉ ያስገኘው አማካይ አመታዊ ገቢ በ 10 ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ነው ቢልም

በባለሥልጣን መ/ቤቱ ተግባራዊ ባለማድረጉ የአይደር ክፍለ ከተማ እንዲከፍል የተደረገ መሆኑ የተገለፀ መሆኑ፤

- በሁምቦ አርባ ምንጭመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ምዕራብ ዓባያ ወረዳ ዋጅፎ ከተማ 3 ግለሰቦች በቅደም ተከተል ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ 1ኛ ግለሰብ በመንገድ ግንባታው ምክንያት 3 የዋንዛ ዛፎች፣ 2 እግር ብርቱካን፣30 የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች፣ 2 እግር ባለ 40 እና ባለ 50 ሜትር ስፋት የሚወጣው ሎል እንጨትና 25 ሜትር ርዝመት አጥር፣ 2ኛ/ግለሰብ 79 ግራቪሊያ ቋሚ ተክል፣1 እግር ማንጎ፣2 ዋንዛ፣ 24 ሜትር ርዝመት ያለው አጥር በአጠቃላይ በብር 1,250 3ኛ/ 85 ግራቪሊያ ቋሚ ተክል፣2 ዋንዛና 40 ክዳን ቆርቆሮ ቤት ተመጣጣኝ ባልሆነ ዋጋ መገመታቸው ፍትሃዊ አለመሆኑን በመግለፅ ቅሬታቸውን ለምዕራብ ዓባያ ወረዳና አርባ ምንጭ ዞን ቢያቀርቡም መልስ ያላገኙ መሆኑ፣

✓ ለልማት ሥራ ሲባል ከሚገኝበት መሬት ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ሊተከል እና እንደነበረ አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት ንብረቱን የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪ የሚሸፍን ካሳ ሊከፈል እንደሚገባ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 7 ተ.ቁ 5 በተመለከተው መሰረት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የካሳ ክፍያ መፈፀሙን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ

- በመንገድ ግንባታው ምክንያት ከጅማ-ቦንጋ ፕሮጀክት የተነሱ ግለሰቦች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በፕሮጀክቱ አማከኝነት 50 የአካባቢ ኗሪዎች የሚጠቀሙበት በፊንላንድ ሚሽን የተሰራ የውሃ ፓምፕ ተመልሶ ይሰራል በማለት ተነስቶ ተመልሶ ያልተሰራ በመሆኑ ህብረተሰቡ በውሃ ችግር ላይ ያለ መሆኑን መግለፃቸው፤

- እንዲሁም በአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በቦንኬ ወረዳ ገረሴ ከተማ 4 ግለሰቦች በሚከተለው ቅደም ተከተል ቤቶቻቸው በመንገዱ አጠገብ በመሆናቸው ለማንሳት ካሳ ገማች ኮሚቴ እንዲገምትላቸው ጠይቀው መልስ ያላገኙ መሆኑ፣

1. .የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተቀኝ በኩል 4.4 ሜትር ርቆ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት ባለ 90 ቆርቆሮ ክዳን ለመንገዱ ሲባል የተሞላ ሙሌት በርና መስኮቱን የዘጋውና መንገዱ በሩሎ ሲመታ መሰነጣጠቅ የደረሰበት

2. የቤት ርቀት የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተግራ በኩል6.5ሜትር የሆነ በመንገዱ አጠገብ በመሆኑ የመሰነጣጠቅና የጎርፍ ጉዳት የደረሰበት

3. የቤት ርቀት የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተቀኝ 4.8 ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ በመንገዱ ሥራ ማሽን እንቅስቃሴ ምክንያት መሰነጣጠቅና እንዲሁም የጎርፍ መግባት ጉዳት የደረሰበት

4. የቤት ርቀት የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተግራ በኩል 2.80 ሜትር የሆነ መንገዱ ከመሰራቱ በፊት ሜዳ የነበረ አሁን በግንባታው ምክንያት በ 5 ሜትር ከፍታ በመሰቀሉ ከቤት ተወጥቶ መቆሚያ ደጃፍ የሌለው ሲሆኑ፤ ከአራቱ ሶስቱ ግለሰቦች ችግራቸው በቦንኬ ወረዳ ታምኖበት በ 26/10/06 እና በ27/12/06 ለኔት ኮንሰልታንት አማካሪ መሀንዲስ በተፃፉ ማመልከቻዎች የካሳ ግምት ተሰርቶላቸው ቤታቸውን ወደ ኋላ በማሸሽ እንዲሰሩ ቢጠየቅም መልስ ያልተገኘ መሆኑ፣

365. ለልማት እንዲለቀቅ የሚፈለግ መሬት ባለይዞታ የካሳ ግምት በተከፈለው በ90ኛው ቀን በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 2 መሰረት ንብረቱን ማንሳት፤ እንዲሁም የአገልግሎት መስመር /ቴሌ፣ መብራትና ውሃ/ ባለንብረቶች የካሳ ክፍያ በተፈፀመ በ60 ቀናት ውስጥ ካሳ የተከፈለበትን የአገልግሎት መስመር አጠናቆ በማንሳት በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 6 ተ.ቁ3 መሰረት መሬቱን ማስረከብ ይገባል፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ ግንባታ እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬትባለይዞታው የካሳ ግምት በተከፈለው በ 90ኛው ቀን ንብረቱን አንስቶ ለመንገድ ግንባታ የካሳ አከፋፈል ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 2 መሰረት ርክክብ መፈፀሙን መከታተሉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 2ቱ በወሪኢ ሪጅ-አድዋ ፕሮጀክት ወረኢለህ ወረዳ ማይቀናጣል ከተማ ግለሰቦች ቤት አናፈርስም በማለታቸው ለክልልና ወረዳ መስተዳድር ደብዳቤዎች መስከረም 19/2005 ዓ.ም፣29/9/2005 ዓ.ም እና 8/06/2005 ዓ.ም በመፃፍ የሥራውን ብዙ ወራት አባክነው መፍረሳቸው በመንገድ መብት አስከባሪው የተገለፀ መሆኑ፤

  እንዲሁም በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ ፕሮጀክት ለአርባ ምንጭ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በአማካሪ መሀንዲስ ጥር 26/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በአርባ ምንጭ ከተማ ከኪሜ184+760 አስከ ኪ.ሜ184+800 በቀኝ በኩል የሚገኙት ንብረቶች የካሳ ክፍያ ተፈፅሞላቸው ባለመነሳታቸው በመንገድ ግንባታው ሂደት የግዜ ተፅዕኖ መፍጠራቸው የተገለፀ መሆኑ፣

- በአዲሱ ሁምቦ -አርባ ምንጭ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በምዕራብ ዓባያ ወረዳ አስተዳደር በዋጅፎና በኦሞላንቴ ቀበሌ ግለሰቦች የካሳ ግምት አነሰን በማለት ንብረት ያላነሱ በመሆኑ ሥራው ችግር ያጋጠመው መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ የተገለፀ መሆኑ፣ እና በአርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክት ለተቋራጩ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ በመንገድ ግንባታ ክልል ውስጥ የገቡ ንብረቶች 37+100 እስከ 37+300 እንዲሁም 35 +200 እስከ 35 +300 ያሉ የእርሻ ቦታዎች ባለመነሳታቸው ማሽኖች ለብዙ ቀናት መቆማቸው መገለፁ፣

✓ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንየአገልግሎት መስመር ባለንብረቶች ቴሌ፣ መብራትና ውሃ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 6 ተ.ቁ 3 መሰረት ክፍያው በተፈፀመላቸው በ 60 ቀናት ውስጥ ካሳ የተከፈለባቸውን የአገልግሎት መስመሮች አጠናቆ በማንሳት መሬቱን ለግንባታ ያስረከቡ መሆናቸውን መከታተሉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፡-በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 8ቱ፡-

- በውልቂጤ-አረቅጥ የመብራት ሃይል መ/ቤት ፖሎችን በማንሳት በኩል ችግር በመፍጠር የሥራ ግዜ እንዲጓተት ያደረገ መሆኑ፣ በአረቅጥ-ሆሳዕና በቀቡልና በአረቅጥ ከተማ መብራት ሃይል ለማንሳት ሁለት ዓመት ያስፈልጋል በማለት ያላነሳ መሆኑ፣

- በጅማ-ቦንጋ ፕሮጀክት ውሃ፣ቴሌና መብራት ሃይል ፈጣን ምላሽ የመስጠት ችግር የሚታይባቸው መሆኑ ሲገለፅ በተለይም መብራት ሃይል አጅግ የከፋ መሆኑ፣ በቦንጋ -ሚዛን ፕሮጀክት በሚዛን ከተማና በአካባቢው ያሉ ፖሎችን መብራት ሃይል አለማንሳቱ፣

- በወሪኢ-ሪጅ አድዋ ፕሮጀክት የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን መ/ቤት የማይቀናጣል ከተማ የአገልግሎት መስመሩን ለማንሳት ካሳ በ 2004 ዓ.ም ተከፍሎት በ 2006 ዓ.ም በማንሳት በፕሮጀክቱ ላይ ከፍተኛ የግዜ ጫና ማሳደሩ የተገለፀ መሆኑ፣ በመቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክት በመቀሌና ሀገረ ሰላም ከተማዎች የኤሌክትሪክ ፖሎች በወቅቱ ባለመነሳታቸው ችግር መፍጠራቸው የተገለፀ መሆኑ፣
- በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ ፕሮጀክት የአርባ ምንጭ ቴሌ፣መብራትና ውሃ ልማት ድርጅቶች የአገልግሎት መስመሮቻቸውን ባለማንሳታቸው የፕሮጀክቱ ሥራ እንዲዘገይ ያደረጉ መሆናቸው፤ በተለይ በአርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ በነበረ ሥራ ቴሌ መስመሩን ባለማንሳቱ እንዲዘገይ ማድረጉን ለአርባ ምንጭ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ነሀሴ 01/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑ፣
- በአዲሱ ሁምቦ- አርባ ምንጭ ፕሮጀክት በመንገድ ክልል ውስጥ የገባ ውሃ መስመር የካሳ ግምት ተሰልቶ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ገንዘቡ ፈሰስ ሲደረግ የላንቴ ከተማ የውሃ ኮሚቴ ገንዘቡ ወደግለሰብ አካውንት እንዲገባ በመጠየቁ የክፍያ ሂደቱ በመስተጓጎሉ ጥቅምት 26/2007 ዓ.ም ህብረተሰቡን በማስተባበር ሁከት በመፍጠር ተቋራጭ ሥራ እንዳይሰራ ያደረገ ሲሆን፤ ሂደቱም ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅትምመቀጠሉ የተገለፀ መሆኑ፣ በአርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክት የመብራት ሃይል የመብራት ፖሎችን ባለማንት የሥራ እንቅፋት እየሆነ መገኘቱ በአማካሪ መሀንዲስና በመንገድ መብት አስከበሪ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ወኪሎች የተገለፀ መሆኑ፣

366. መሬት ለመንገድ ግንባታ እንዲለቀቅ ሲወሰን ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በካሳ ክፍያ ሂደት ውስጥ ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 መሰረት የካሳ ክፍያ መፈፀሙን መከታተሉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 8ቱ በወልቂጤ-አረቅጥ በቸሃ አስተዳደር ወረዳ ጽ/ቤት፣በአረቅጥ-ሆሳዕና በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣

- በጅማ-ቦንጋ በሸቤ ሰምቦ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ በቦንጋ-ሚዛን በጨና ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣በወሪኢ ሪጅ-አድዋ በአድዋ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ በመቀሌ ስረት መንደር በዓይደር ክፍለ-ከተማ ጽ/ቤት በሁምቦ-አርባ ምንጭ በምዕራብ ዓባያ ወረዳ ጽ/ቤት እና በአርባ ምንጭ-በልታ በቦንኬ ወረዳ ጽ/ቤት ካሳ የተከፈላቸው ተነሺ ግለሰቦች ህጋዊ ባለይዞታ ስለመሆናቸው የተረጋገጠበት ማስረጃ በመዝገብ ቤታቸው ያልተገኘ ሲሆን፤ እንዲሁም በ ኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በመንገድ መብት አስከባሪ ወኪልነት በሚሰሩ ግለሰቦች እጅም ማስረጃው አለመገኘቱ በኦዲት ቡድኑ ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

367. ለልማት የሚለቀቅ መሬት ስለመሆኑ ውሳኔ የተሰጠው ባለይዞታ ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ ለተሰራ ወይም ለተሻሻለ ቤት፣ለተተከለ

ቋሚ ተክል ወይም በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሳ እንዳይከፈል በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 4ተ.ቁ 1 መሰረት ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

- ✓ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለልመት የሚለቀቅ መሬት ስለመሆኑ ውሳኔ የተሰጠው ባለይዞታ ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ ለተሰራ ወይም ለተሻሻለ ቤት፣ ለተተከለ ቋሚ ተክል ወይም በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሳ እንዳይከፍል ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 የተመለከተውን በካሳ ክፍያ ሂደት ውስጥ ክትትል ማድረጉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በ 2ቱ፡- በጅማ-ቦንጋ የጎላ ችግር መኖሩ በመንገድ መብት ማስከበር የተገለፀ ሲሆን የመንገዶችን ወሰን የሚያስከብር መደበኛ ቋሚ የመንግሥት አካል ማስፈለጉን የገለፁ መሆኑ፣

- ✓ በወሪኢ ሪጅ-አድዋ በመንገድ መብት ማስከበር ወኪል ከተሰጠ መልስና ከውሳኔ አልፎ ካሳ ከተከፈለ በኋላ እርሻ ማረስ፣ተክሎች መትከልና ግንባታዎች መሥራት የመንገዱን ወሰን በማለፍና መሀል መንገዱን በመጠጋት በወሪኢ.ሊህ ወረዳ አድዋ ከተማና አዲአቡን አልመዳ ጨርቃጨርቅ አካባቢ ችግሩ በግልፅ መታየቱን ከቀረበ ቃለ-መጠይቅናበኦዲቱ ወቅት በተ ተደረገ የመስክ ምልከታ ማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳቦች</u>

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ የዲዛይን ሥራዎች በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተው እንዲሰሩ በማድረግ እንዲሁም በቅድመ ዲዛይን ጥናት ወቅት በማህበረሰቡና በመስተዳድር አካላት የሚሰጡ

ሀሳቦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዲዛይን ችግር ምክያት በየፕሮጀክቶች የሚከሰቱ ተጨማሪ ሥራና ወጪ ማስቀረት ይኖርበታል፡፡

- በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ መመሪያ እና የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 295/1995 በአማካሪ መሀንዲሶችና በተቋራጮች እጅ በማኖር መተግበሩን መከታተል ፤እንዲሁም በተቋራጩ የተዘጋጀውን የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ እቅድ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን/በትራንስፖርት ሚኒስቴር አስገምግሞ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ እንዲተገበር ማስደረግ ይገባል፡፡

- በዲዛይን ቅድመ-ጥናት ወቅት መንገዶች የሚያልፍባቸውን የመስተዳደር አካላትና ህብረተሰብ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ከየከተሞቹ አንፃራዊ እድገት ጋር በማገናዘብ እና መንገዱ የሚገነባባቸውን ቦታዎች ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥና የአፈር ዓይነት በባለሙያዎች በማስጠናት የተሻለ የሥራ ልምድ ላላቸው ተቋራጮች ሥራው መሰጠት ይኖርበታል፡፡

- የመንገድ ግንባታ ዲዛይን ሥራ በቂ ግዜ ተሰጥቶት በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሰራ በማድረግ የሚከሰቱ ተጨማሪ ሥራዎችንናአላስፈላጊ ወጪዎችን ማስቀረት ይገባል፡፡

- የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው እስፔስፊኬሽን እና እስታንዳርድ መሰራታቸውን በባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ጥራትና ቁጥጥር ደህንነት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከጄነራል ማናጀር አስከ ፕሮጀክት መሀንዲስ ያሉትን አመራሮች በበጀት ዓመት ውስጥ በእቅድ በተካተተ ፕሮግራም የመስክ ክትትልና ግምገማ የሚያደርግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በዓመታዊ እቅድ በተያዘ

ፕሮግራም የሶስትዮሽ ግምገማ በማድረግ በማስረጃ የተደገፈ የማሻሻያ ሀሳብ ለአማካሪ መሀንዲስና ለተቋራጭ በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ እና ልምድ ያላቸውን የፕሮጀክት መሀንዲሶች በየወሩ ለግመገማ መስክ በመላክ የቅርብ ክትትል እንዲደረግ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደካማ አፈፃፀም በሚፈርጃቸው በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱባቸው ከተሞችና በሚያልፉባቸው አካባቢዎች ካሉ የመስተዳድር አካላት ጋር የጠበቀ ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የመንገድ ግንባታ ሂደትን በተሳካና ውጤታማ መንገድ ሊያካሂድ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣኑ መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደት ለሚከሰቱ ችግሮች በቅድሚያ በደብዳቤ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በካሳ አከፋፈል በታወጀው አዋጅ ቁጥር 455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 የተደነገጉትን አንቀጾች መሰረት በማድረግ ለህጋዊ አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች ከተሰጡት ኃላፊነትና ተግበር የተገለፀ በመሆኑ፤ ካሳ የሚከፈለው አካል የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታና የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ እንዲለቀቅ ውሳኔ በተሰጣቸውና ካሳ በተከፈለባቸው መሬት ላይ ህገወጥ እርሻ፣ ቋሚ ተክል ተከላና ግንባታ ለሚያደርጉ ግለሰቦች በደብዳቤ ካሳወቀ በኋላ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 በሚደነግገው መሰረት በህግ አግባብ እንዲታይ ማድረግ ይኖርበታል

11.15 የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

የመንግስት መ/ቤቶች ንብረት አወጋገድ

368. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በንብረት አወጋገድ ዙሪያ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና እነኝህን መሰረት አድርገው የወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ ሲደረጉ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት አፈጻጸሙን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳብ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና በወቅቱ ተግባራዊ እንዲሆን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የማስወገድ ስራውን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ስለመኖሩ ሲጣራ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የተዘጋጀ የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ፣ በየጊዜው የሚዘጋጁና ወቅታዊ የሚደረጉ የተለያዩ ሰርኩላሮች እና አገልግሎቱ ያዘጋጀው የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2004 መኖሩን፣ እንዲሁም በናሙና በታዩ ሁሉም መ/ቤቶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የተሰራጨ መመሪያ ቁጥር 9/2003 እና ሰርኩላሮቹ መኖራቸው ታውቋል፡፡
- ✓ ሆኖም አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት መመሪያውን ሲያስፈጽም ለአፈጻጸም አዳግተውኛልና ቢሻሻሉልኝ ያላቸውን 12 ነጥቦች ለይቶ በደብዳቤ ቁጥር በቀን የካቲት 18/2005 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 6/1/6/5337 እና በቀን መስከረም 30/2006 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 6/1/03/2448 ለግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ቢያቀርብም ጥያቄው መልስ አለማግኘቱን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

369. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት በሚሰጣቸው መ/ቤቶች እና የትምህርት ተቋማት መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች መረጃ በመረጃ ቋት /data base/ በመያዝ የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በስትራቴጂክ እቅድ አካቶ በየበጀት አመቱ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለማከናወኑ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያዘጋጅ እና ክንውኑ ከእቅዱ ካነሰ ምክንያቱን በመለየት በአፈጻጸም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የማስረጃ ክለሳና ለመ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በየዓመቱ የምን ያህል መ/ቤቶችን ፣ ስንት ተሽከርካሪና ንብረት እንደሚያስወግድ በስትራቴጂክ እቅዱ (2002-2007) ዓ.ም እንዳላስቀመጠ ለማወቅ ተችሏል፡፡

370. በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ዝርዝራቸው የቀረበ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገድ ንብረት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በአመት ሁለት ጊዜ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ የመላክና መልስ መስጠታቸውን ክትትል የማድረግ ስራ በአገልግሎቱ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ ኦዲቱ በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥ (2004-2006 በ.ዓ.) ለመ/ቤቶች የተላከውን ቅጽ በተመለከተ እቅዱ ከአፈጻጸሙ ጋር ስለመጣጣሙ በተደረገው የሰነድ ክለሳ፣ በየካቲት 29/05 ለ133፣ በሐምሌ 22/05 ለ 34፣ በሐምሌ 23/05 ለ 42፣ በህዳር 06/06 ለ 21፣ በህዳር 06/06 ለ19፣ በታህሣሥ 30/06 ለ17 እና በታህሣሥ 30/06 ለ18፣ መ/ቤቶች በደብዳቤ ቁጥር ግንማ13/2/308/5504፣ ግንማ13/2/18/429፣ ግንማ 13/2/7/428፣ ግንማ13/2/247/3453፣ ግንማ13/2/247/3454፣ ግንማ13/2/30/667፣ ግንማ 13/2/302/667፣ እና ግንማ

13/2/070/355 እንደ ቅደም ተከተላቸው የተላከ ሲሆን ይህም በ2004 በጀት ዓመት ለየትኛውም መ/ቤት ቅጹ አለመላኩን በ2005 በጀት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ለ133 መ/ቤቶች መላኩን፣ በ2006 ዓ.ም ያለውም አፈጻጸም ሲታይ አገልግሎት ከሚያገኙ 156 መ/ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ቅጹ እንዳልደረሳቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

371. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ ሊወገዱ ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በቀረቡለት ማስረጃዎች መሰረት በማስወገድ ስራው ላይ ክፍተት የፈጠሩበት የሚከተሉት ምክንያቶች ታይተዋል፡፡

- ➢ በመመሪያ ቁ.9/2003 የማስወገጃ ጊዜ ገደብ አለመኖርና የሚወገዱ ንብረቶች በከፍተኛ ክምችት በአብዛኛው መ/ቤቶች መገኘት፣
- ➢ በተለያዩ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ለብዙ አመት ተከማችተው የሚገኙ ንብረቶች እንዲወገዱ በወቅቱ ውሳኔ አለመስጠትና ለአገልግሎቱ ትክክለኛ መረጃ አለመላክ፣
- ➢ የባለንብረት መ/ቤቱ የሚወገዱ ልዩ ልዩ ንብረቶችን በአንድ ጊዜ አሰባስቦ ከመላክ ይልቅ እየከፋፈሉ በተለያየ ጊዜ መላክ፣
- ➢ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ ሙያተኞች በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ የሌላቸው መሆኑን፣
- ➢ ማንም ሊሰራው ይችላል በሚል አመለካከት ለስራው ተገቢው ባለሙያ የማይመደብበት፣ ስራውም በተለምዷዊ ሁኔታ የሚሰራና ትልቅ ተቋማዊ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን፣

- በአብዛኛዎች የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች በንብረት አስተዳደር ስለሚሰሩ ስራዎች ተገቢውን ትኩረት እንደማይሠጡና መረጃዎች የሌላቸው መሆኑን፣

- ለቦታው ሰራተኞች ምንም የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ የማይጠየቅበት ሁኔታ መኖሩን እንዳንዴም በቅጣት የሚመደቡበት መሆኑን በጥናቱ አስቀምጧል፡፡

- ✓ እንዲሁም የግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ30 መስሪያ ቤቶች ላይ ባደረገው የግዢና ንብረት ኦዲት 19ኙ መ/ቤቶች በወቅቱ መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች አለማስወገዳቸውን፣ በ2006 የ9 ወር ሪፖርቱ ላይ አስፍሯል፡፡

- ✓ በተጨማሪም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በቃለ-መጠይቅና፣ ቦታው ላይ በመገኘት ካገኘው መረጃ በመነሳት የሚከተሉትን ማስረጃዎች አሰባስቧል፤

<u>ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፣</u>

- የኦዲት ቡድኑ በመስክ ምልከታ ወቅት 9 ተሽከርካሪዎች፣ 2 ሞተር ሳይክል፣ 4 ትራክተር፣ በሁለት ሳጥን የተቀመጡ የተሸጡ መኪኖች መለዋወጫዎች በማየቱ ለምን እንዳልተወገዱ ባነሳው ጥያቄ ዩኒቨርስቲው በማዕከል የሚያስተዳድር በመሆኑ ከየካምፓሶቹ ተጨማሪ ንብረቶችን በማሰባሰብ ላይ መሆኑንና አሰባስቦ ሲጨርስ ለአገልግሎቱ እንደሚያሳውቅ፣

<u>ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል፣</u>

- በሆስፒታሉ በርካታና ምንነታቸውን ለማወቅ የሚያስቸግር በሁለት መጋዘን የተከማቹ ንብረቶች ቢኖሩም ንብረቱን ለማስወገድ የንብረት ክፍል ኃላፊዋ ቦታው ላይ ከመጡ ገና አንድ አመት መሆኑንና ስራው እስከዛሬ እንዳልተሰራ ሆኖም

በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁትን አወዳድረው በመቅጠር ንብረቶቹን የመለየት ስራ ለመስራት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣

<u>የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን፣</u>

- በቁጥር 13 የሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች መኖራቸውንና የመገናኛኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር እንዲያስወግዳቸው በደብዳቤ የተጠየቀ መሆኑን፣

<u>ደብረብርሀን ዩኒቨርስቲ፣</u>

- የሚወገዱትንና እንደገና ተጠግነው አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ንብረቶች ለመለየት ጊዜ እንደወሰደባቸው ሆኖም አሁን ቁጥራቸው 1204 የሆኑ የቢሮ መገልገያ እቃዎችንና 275 የተለያዩ ንብረቶችን ዝርዝር ለአገልግሎቱ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣
- ከትምህርት ሚኒስቴር የተላኩና በቁጥር 90 የሆኑ የተለያየ መጠን ያላቸው የኤሌክትሪክና የጋዝ ምድጃዎች፣ የኤሌክትሪክ ወጥ መስሪያዎች(ድስቶች) እና ልዩ ልዩ የወጥ ቤት ቁሳቁሶች በተሻለ መገልገያ እቃ በመተካታቸው ንብረቶቹ ያለአገልግሎት ሰፊ ክፍል ይዘው መቀመጣቸውንና እነዚህን ንብረቶች ለማስወገድ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው /ሞዴል 19/ በመሆኑ በአሰራር ላይ ክፍተት መፍጠሩን፣
- ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት የኦዲት ቡድኑ በትምህርት ሚ/ር ለሚገኙ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ንብረቶቹ 13ቱ ዩኒቨርስቲዎች በተሰሩ ወቅት ለ13ቱም የተገዙና የተሰራጩ መሆናቸውን፣

ደብረብርሀን ዩኒቨርስቲም ንብረቶቹን በትክክለኛው መንገድ ለመረከቡ መረጃ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

- ሆኖም የኦዲት ቡድኑ የቀረበለትን መረጃ ሲከልስ ያገኘው፣ ብሪጅቴክ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ንብረቱን ለዩኒቨርስቲው ማምጣቱንና ዩኒቨርስቲውም እቃውን በቀን 1/7/2000ዓ.ም በአደራ መረከቡን የሚገልጽ ደብዳቤ ለብሪጅቴክ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ማቅረቡን ነው፡፡

<u>ፍትህ ሚኒስቴር፣</u>

- ቁጥራቸው 186 የሆነ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እንዲወገዱላቸው በቀን ህዳር12/05 ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ቢልኩም ምላሽ አለማግኘታቸውን የሚገልጽ ማሥረጃ መቅረቡ፣

<u>አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣</u>

- ብዛታቸው 1200 የሆነ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮች እንዲወገዱ መረጃቸው ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መላኩን፣

<u>የውሃ ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣</u>

- በቁጥር 35 የሆኑ ተሽከርካሪዎች በቀን ጥቅምት 20/2005 የተወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረባቸው፣ ተሽከርካሪዎቹን ለማስረከብ ግን የአንዳንዶቹን መረጃ ለማሟላት እስከ ስምንት ወር ጊዜ የፈጀ መሆኑን፣

<u>የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ፣</u>

- የኦዲት ቡድኑ በምልከታ ባገኘው መረጃ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ አምስት የህትመት መሳሪያዎችንና ሌሎች ንብረቶችን በመጋዘን ተቀምጠው በማየቱ ለምን እንዳልተወገዱ ባነሳው ጥያቄ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ንብረቶቹን

ሊያነሳቸው ሲመጣ ግዙፍ ከመሆናቸው የተነሳ ሊያነሳቸው አለመቻሉንና በኋላም ለአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት እንዲወገድ አለማሳወቃቸውን፣ ለቦታው አዲስ መሆናቸውም ክፍተቱን እንደፈጠረ፣

<u>ብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ፣</u>

- ሊወገዱ የሚገባቸው ነገር ግን ያልተወገዱና ከ20 አመት በላይ እድሜ ያስቆጠሩ ልዩ ልዩ ንብረቶች፣ ጐማና ባትሪ፣ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ ብረታብረት፣ የኮሚኒኬሽን ሬዱዩኖች፣ ማቀዝቀዣ የመሳሰሉት ባሏቸው 11 ቅርንጫፍ መ/ቤቶች መኖራቸውን፣

<u>ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣</u>

- ቁጥራቸው 215 የሆነ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እንዲወገዱላቸው በቀን 06/05/06 ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር መረጃ ቢልኩም መልስ አለማግኘታቸውን የሚገልጽ ማሥረጃ መቅረቡ፣
- በስቶር የተከማቹ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መገልገያ እቃዎች (ሴክሽን ማሽን፣ አንስቴዢያ ማሽን፣ ኢንኩቤተር፣ አልትራሳውንድ፣ ዋርመር፣ የህጻናት ኦክስጂን እና የተለያዩ የላቦራቶሪ እቃዎች) መኖራቸውና ለማስወገድ የባለሙያ እገዛ እየጠበቁ መሆናቸውን፣

<u>አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣</u>

- ዩኒቨርስቲው ወርክሾፕ ያለው በመሆኑ የተሰባበሩ እንጨቶችንና ብረታብረቶችን እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶችን ከማስወገድ ይልቅ በግብዓትነት የሚጠቀምበት በመሆኑ የሚወገዱ ንብረቶች እንደሌሉት፣

የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ፣

- በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ቁጥራቸው 832 የሆነ ንብረት እንደተወገዱለትና ካለው የንብረት ብዛት ጋር ሲነጻጸር የተወገደው አንድ መቶኛ ያህል መሆኑን፣
- ንብረት የማሰባሰብ ሥራው አድካሚና ሥጋት ያለው በመሆኑ ኮሚቴዎችን በስራው ለማሳተፍ ምንም አይነት ማበረታቻ ስለሌለው አሮጌ እቃዎችን ማስተካከል ጊዜ መውሰዱን፣
- ✓ በተጨማሪም ከየመስሪያ ቤቶች ኮምፒውተሮችንና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን እንዲወስድ ስልጣን የተሰጠው የመገናኛኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ንብረቶቹን ለምን እንደማያነሳ የአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ በተገኘበት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው የቃል ጥያቄ እስከአሁን የሰበሰባቸው ብዙ እንደሆኑና ተጨማሪ ለመሰብሰብ ያለው ቦታ ውስን በመሆኑ እንደማያስችለው ሆኖም ለዚሁ ስራ በመገንባት ላይ ያለው ህንጻ ሲጠናቀቅ ማሰባሰብ እንደሚጀምር ገልጸዋል፡፡
- ✓ የኦዲት ቡድኑ ባሰባሰበው ማስረጃ መሰረት በየመ/ቤቶቹ የሚገኙ የስራ ኃላፊዎች ስለሚወገዱት ንብረቶች ተፈላጊውን መረጃ በወቅቱ በማሰባሰብ አፋጣኝ እርምጃ አለመውሰዳቸውን፣ ይህ ደግሞ ንብረቶቹን ለከፋ ብልሽት፣ ለአካባቢ ብክለት፣ ለስርቆት እንዲጋለጡ ያደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

372. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ አገልግሎቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲችል የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኘና በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡

- ✓ በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ወቅታዊ ተደርጎ በቀረበው መረጃ መሰረት ሁለቱ የስራ ሂደት (የንብረት ዋጋ ግምትና

ማስወገድ እና የሚወገዱ ንብረቶች መረጃና ጥናት) ለ34 ሰው የስራ መደብ ሲኖረው አሁን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 18 ብቻ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

373. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለሚወገዱ ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ እንዲኖር ቀመር ሊዘጋጅላቸው የሚችሉ የንብረት አይነቶችን በጥናት በመለየት ቀመር ሊዘጋጅላቸው፣ ቀመር ሊዘጋጅላቸው የማይችሉ ንብረቶችንም ወጥ በሆነ አሰራር እንዲወገዱ ለማድረግ በግልጽ የተቀመጠ የአሰራር መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ በተከለሰው ማስረጃ መሰረት ለተሽከርካሪ የተቀመጠ ቀመር በመኖሩ ለሚወጣው ጨረታ የመነሻ ዋጋ ተዘጋጅቶለት ተጫራቹ ያንን መሰረት በማድረግ የሚጫረት መሆኑን፣ ከተሽከርካሪ ውጪ ላሉ ንብረቶች ግን ቀመር አለመኖሩንና አገልግሎቱ ወቅታዊ የገበያ ጥናት አድርጎ ያዘጋጀውን ዋጋ በማየት ተጫራቹን እንደሚያወዳድር ታውቋል፡፡
- ✓ በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ከከለሰው ማስረጃ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ስለጉዳዩ የሚከተሉትን እንደችግር አስቀምጧል፡፡
- ✓ ለሚወገዱ ልዩ ልዩ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ መነሻ ዋጋ ለማዘጋጀት ቀመር አለመኖር፣
- ✓ አንዳንድ አምራቾችም ሆነ አስመጪ ድርጅቶች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ሲጠየቁ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን፣ ቢሰጡም ደግሞ የተጋነነ ዋጋ ወይም የወረደ ዋጋ መስጠታቸውን፣
- ✓ እንዲሁም የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ንብረቶችን ለማስወገድ ቀመር ለምን እንዳልተሰራ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ ለአሁኑ ቀመሩ አለመኖሩን ቢሰራ ግን

ለአሰራር የሚያመች በመሆኑ ሀሳቡን እንደግብዓት እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

- ✓ በተጨማሪም የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ በየመ/ቤቶች ተከማችተው የሚገኙ ንብረቶችን የኋላ ታሪክ የያዘ መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ የንብረቶቹ አይነት እጅግ ብዙ ስለሆኑ ቀመር ማዘጋጀት ሰፊ ጥናቶችና ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን፣ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ ቀመር ለማዘጋጀት በመመሪያ መደገፍ እንዳለበትና የተሽከርካሪ ማስወገጃ ቀመሩም በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- ✓ ሆኖም አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በየጊዜው ለሚያስወግዳቸው ንብረቶች ቀመር ባለመኖሩ፣ የመተኪያ ዋጋ ለማግኘት የገበያ ጥናት ማድረግ የማስወገዱን ስራ ረጅም ጊዜ እንዲወሰድ፣ ወጪው እንዲጨምር እና ወጥ አሰራር እንዳይኖር አድርጎታል ፡፡

374. አገልግሎቱ ለሚወገዱ ንብረቶች የሚወጡ ጨረታዎችን ጥሪ የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ተሳታፊዎችን ለመድረስ የሚችል ሰፊ ሽፋን ያለው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ✓ ይሁን እንጂ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የመ/ቤቶችን ንብረትና ተሽከርካሪ ለማስወገድ የሚጠቀምበት የጨረታ ማስታወቂያ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ በተጨማሪም የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ጨረታ መውጣት እንዳለበት የሚደነግግ በመሆኑና በዚሁ መሰረት አዲስ ዘመን

ጋዜጣ በአገር ደረጃ ሰፊ ሽፋን ያለው መሆኑ የታመነበት በመሆኑ ጨረታው እንዲወጣ እየተደረገ መሆኑን፣ አንዳንድ ጊዜም የተፈቀደውን በጀት መሰረት በማድረግ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቭዥን እንዲተላለፍ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም አራት ጊዜ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቭዥን እንዲተላለፍ የተደረገ ማስታወቂያ ማስረጃ ቀርቧል፡፡

- ✓ ይሁንና በቋሚነት የሚጠቀምበት የጨረታ ማስታወቂያ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ መሆኑ የተሻለ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች እንዳይገኙ፣ በዚህም ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ እንዲያንስ ፣ የተሻለ ዋጋ የሚያቀርቡ እንዳይሳተፉና ከመረጃ እጥረት የተነሳ ጨረታውን ለመሳተፍ የሚችሉ እድል እንዳያገኙ ስለሚያደርግ፣ አማራጭ የጨረታ ማስታወቂያ ዘዴዎችን አለመጠቀሙ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

375. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎችን ወቅታዊነትና ትክክለኛነት ሰነዱ ለጨረታ ከመቅረቡ በፊት ሊያረጋግጥና ለአሸናፊውም ተጫራች በሰነዱ መሰረት ርክክብ ሊደረግለት ይገባል፡፡

- ✓ በመሆኑም የኦዲት ቡድኑ በጉዳዩ ላይ ባደረገው የሰነድ ክለሳ የሚከተሉት ተስተውለዋል፤

- ➢ ባለንብረት መ/ቤቱ የሚልከው የተሽከርካሪ መረጃና በአካል የሚገኘው መረጃ መለያየት፣ /የ2005 ዓ.ም. ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት/
- ➢ በሥራ ሂደቱ ባለሙያዎች የታዩ ድክመቶች ከፌዴራል መ/ቤቶች የሚመጡትን የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ዕቃዎች ዝርዝር በየጊዜው መረጃውን አኘዴት

አለማድረግና የመረጃውን ፎቶ ኮፒ አለመያዝ፣ /የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ስለማካሄድ ገጽ 2/

- በተሽከርካሪ መረጃ አሰባሰብ ላይ የሞተርና የሻንሲ ቁጥር ከመኪና ከፍቶ አለማየት ከሊብሬ ብቻ መረጃ ሰብስቦ መምጣት፣ /የ2004 እና የ2005 የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት/

- ✓ ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በተከናወነው ጨረታ የኦዲት ቡድኑ ተገኝቶ በመጠይቅ ባሰባሰበው ማስረጃ መሰረት ተሽከርካሪ በጨረታ አሸንፌ አውቃለሁ ካሉ 23 መልስ ሰጭዎች ውስጥ 5ቱ የተሽከርካሪ ርክክብ ሲደረግ የንብረት መጉደል እንዳጋጠማቸው የጎደለውን ንብረት ዘርዝረው አስቀምጠዋል፡፡

376. የሚወገዱ ንብረቶችን ተጫርቶ ያሸነፈ ተጫራች ያሸነፈውን ንብረት በወቅቱ እንዲረከብ አገልግሎቱ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ የኦዲት ቡድኑ ንብረቶችን በጨረታ የገዙ ባለሀብቶች ክፍያቸውን ከፈጸሙ በኋላ ንብረታቸውን በወቅቱ ስለመረከባቸው ባደረገው የሰነድ ክለሳ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- የገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን እና የአዲስ አበባ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በጨረታ ለሚወገዱ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች በጨረታው አሸናፊ ለሆኑት ተጫራቾች ዜሮ ዲክላራስዮን በወቅቱ አለመስጠትና የስም ዝውውር ላይ አስፈላጊውን የሥራ ትብብር አለማድረግ፣
- ከቤተ-መንግሥት የተወገዱ ተሽከርካሪዎች ለተፈጠረው የሞተር እና ሻንሲ ቁጥር ስህተት ለማስተካከል ለ8 ደንበኞች ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያገኙ በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ጽ/ቤት በኩል ለተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደብዳቤ እንዲፃፍላቸው መገለጹ፣

- ✓ በተጨማሪም ንብረትነታቸው የውሀ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚ/ር የሆኑና በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የተወገዱ 35 መኪኖች ጨረታውን ላሸነፉ ባለንብረቶች በወቅቱ ርክክብ ስለመፈጸሙ የኦዲት ቡድኑ ለሚ/ር መ/ቤቱ የግዢ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ መሟላት የሚገባቸው መረጃዎች ስላልተሟሉ አንዳንዶቹን ተሽከርካሪዎች ለተጫራቾች ለማስረከብ እስከ 8 ወር ጊዜ ፈጅቶ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

377. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችንና ተሽከርካሪዎችን የሚያስወግድበት ሂደት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የሚወገዱ ንብረቶችን የተሟላ መረጃ ለማጠናቀር ፣ ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ ለማዘጋጀት ፣ ለመ/ቤቶች በመረጃ አያያዝና በንብረት አወጋገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት፣ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት/ጋር የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ፣ በስራ አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ጠንካራና ደካማ ተሞክሮዎችን ሰብስቦ በመረጃነት ለመጠበቅና ለማስተላለፍ፣ በአጠቃላይ የአወጋገድ ስርዓቱ ጥራቱን የጠበቀ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ አሰራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አይደለም፡፡

- ✓ በተጨማሪም የሥራ ሂደቱ ንብረት የማስወገድ ስራውን ዘመናዊ ለማድረግ ቴክኖሎጂ መጠቀም አስፈላጊ ነው የሚል እምነት ቢኖረውም ለዚሁ የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂ በወቅቱ አለመገንባቱን እንደ ስጋት መውሰዱን በስትራቴጂክ እቅዱ ያስቀመጠ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

378. አገልግሎቱ ንብረት ከሚወገድላቸው የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ አያያዝ እና አወጋገድ ዙሪያ ውይይት የሚደረግበት መደበኛ እና ተከታታይ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ሊያዘጋጅ እና በውይይቱ ለሚነሱ ጉዳዮች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ✓ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በጉዳዩ ላይ ባደረገው የሰነድ ክለሳ፡-
  - ➢ በፌዴራል መስሪያ ቤቶች ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ ልዩ ልዩ ንብረቶችና ተሽከርካሪዎች በብዛት ቢገኙም የባለንብረት መስሪያ ቤቶች ስለንብረት ማስወገድ ያላቸው ግንዛቤ በእጅጉ አናሳ በመሆኑ ንብረቶችን አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ይዘው እንደሚገኙና ይህ ደግሞ ለሥራ ሂደቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ የሚያሳድር ስለሆነ ለሚመለከተው ሁሉ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ቢደረግ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል፣
  - ➢ የሚወገዱ ንብረቶች መረጃና ጥናት የሥራ ሂደት በ13 የፌዴራል መ/ቤቶች ላይ በንብረት አያያዝ ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ላይ የተስተዋሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ዝርዝር ለማኔጀመንቱ ሲያቀርብ አንዱ ግኝት የግንዛቤ ችግር መሆኑ፣
  - ➢ የፌዴራል መ/ቤቶች ፣ አገልግሎቱ እና ባለድርሻ አካላት ተቀራርበው አለመስራታቸው የማስወገድ ሂደቱን ቀልጣፋ እንዳይሆን ማድረጉ፣
- ✓ አገልግሎቱ ከመ/ቤቶች በቀረበ ጥያቄ መሰረት በአካል በመገኘት፣ በደብዳቤ ፣ በስልክ እና በስልጠና ለመ/ቤቶች በመረጃ አያያዝና በንብረት አወጋገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ እንደሚሰጥ በእቅዱ ማስቀመጡንና በተያዘው እቅድ መሰረት ኦዲቱ በሸፈነው ጊዜ ውስጥ (2004-2006በ.ዓ) የ160

መ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በአካል አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በመምጣት፣ ለ42 መ/ቤቶች በስልክ ፣ ለ4 መ/ቤቶች በደብዳቤ ለ5 መ/ቤቶች በስልጠና ሙያዊ ድጋፍ መሰጠቱን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቧል፡፡

- ✓ ሆኖም በናሙና በተመረጡ መ/ቤቶች በንብረት አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ምን ያህሉ ግንዛቤውን እንዳገኙ ለማወቅ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ፣ በናሙና በታዩ ሁሉም መ/ቤቶች በስራው ላይ የሚገኙ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ሰራተኞች አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ባዘጋጀው ስልጠና ተሳትፈው እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

- ❖ የሰነድ ክለሳን በተመለከተ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003ን በሚመለከት ከአገልግሎት ሰጪውና ከሌሎች የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ያሰባሰበውን ግብዓት በመጠቀም መመሪያውን ለማሻሻል የጀመረው የክለሳ ስራ ቢፋጠን በአፈጻጸም የሚፈጠረውን ክፍተት ስለሚሸፍን አፈጻጸሙ ላይ ትኩረት ሊሰጠውና አገልግሎቱም ለአፈጻጸሙ ክትትል በማድረግ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

- ❖ የመረጃ አሰባሰብን በተመለተ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት ከሚሰጣቸው መ/ቤቶች መረጃዎችን በመሰብሰብ በስትራቴጂክ እቅዱ ሊያካትታቸውና በየበጀት አመቱ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለማከናወኑ አፈጻጸሙን ሊለካ ይገባል፡፡

- ❖ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ፣

- ንብረቶችን በአግባቡ የመረከብ፣ የመያዝ፣ ለተገቢው ስራ የመጠቀምና የአገልግሎት ጊዚያቸው ሲያበቃ የማስወገድ ተግባር ትልቅ ተቋማዊ ትኩረት የሚያስፈልገው በመሆኑ የተቋማት ኃላፊዎች ቦታው ላይ የሚመደቡ ሰራተኞችን የስራ ብቃት ሊለኩና በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ባለው የሰው ኃይል ሊያደራጁትና ቦታው ላይ ስለሚሰራው ስራ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን አጽንኦት ሰጥተው ሊከታተሉ፣
- በስጦታም ሆነ በግዢ የተገኙ ንብረቶችን በአግባቡ የመረከብ፣ የመያዝ፣ ለተገቢው ስራ የመጠቀምና የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ማስወገድ እንዲቻል ቋሚ ንብረቶች ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ገቢና ወጪ ደረሰኝ ሊኖራቸው፣
- ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ርም መ/ቤቶች የሚወገድ ንብረት መኖሩን ሲያረጋግጡ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ የሚያስችል አስገዳጅ የጊዜ ገደብ ሊያበጅ፣
- ኮምፒውተሮችንና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን እንዲወስድ ስልጣን የተሰጠው የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር አቅሙን የማሳደግ ስራውን በማፋጠን የተሰጠውን ኃላፊነት ሊወጣ፣
- አገልግሎት ሰጪውም ቀመር ሊዘጋጅላቸው የሚችሉ ንብረቶችን ለይቶ ቀመር በመስራት በየጊዜው የመተኪያ ዋጋ ጥናት ለማድረግ የሚወስደውን ጊዜና ወጪ ለቀንስና ወጥ አሰራርን ሊያሰፍን፣
- በማስወገዱ ስራ ላይ የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ሊሰጥ ሊሰጥ፣ ይገባል፡፡ ይህም ሁኔታ ተፈጻሚ ሲሆን የሚወገዱ ንብረቶች ለባሰ ብልሽትና ሥርቆት ሳይጋለጡና ለአካባቢ ብክለትን ሳይፈጥሩ በአፋጣኝ እንዲወገዱ ፣ በዚህም አገሪቱ የጀመረችውን የልማት ስራ ለማፋጠን የሚያስችል ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ያስችላል፡፡

- የጨረታ ማስታወቂያ ጥሪን በተመለከተ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የራሱን ድረ-ገጽ ጨምሮ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ጥሪ ቢያደርግ በጨረታው የተሻለ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች እንዲገኙ ያግዛል፡፡ ይህም ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ እንዲያድግ ፣ በተሻለ ዋጋ የሚያቀርቡ ተሳታፊዎች እንዲገኙና ከመረጃ እጥረት የተነሳ እድል ላላገኙ ተጫራቾች እድል ለመስጠት በር የሚከፍት በመሆኑ የአዋጪነት ጥናት በመስራት አማራጮችን ሊጠቀም ይገባል፡፡

- አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ንብረቶችንም ሆነ ተሽከርካሪዎችን በጨረታ ለመሸጥ ሲፈልግ ጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን አስቀድሞ ሊያጣራ፣ መረጃቸው ያልተሟላ ንብረቶች ለጨረታ እንዳይቀርቡ ሊያደርግ፣ ሲሸጡም የጨረታው አሸናፊዎች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው ማስረጃ መሰረት ከባለንብረት መ/ቤቱ በወቅቱ መረከባቸውን ሊያረጋግጥ፣ የአሰራር ክፍተት ካለ ጣልቃ በመግባት ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- በየመንግስት መ/ቤቱ የተከማቹና ለከፋ ብልሽት እየተጋለጡ ያሉ ለመ/ቤቶቹም ቦታዎችን በመያዝ ለአያያዝና አጠባበቅ ችግር የፈጠሩና በአፋጣኝ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች በመኖራቸው፣ ሲወገዱም የሚያመጡትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባትና አገልግሎት ሰጪው መ/ቤትም ይህንኑ ስራ ለማፋጠን የሚያደርገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ የሰው ኃይሉን አሟልቶ ቢንቀሳቀስ አፈጻጸሙ የተሻለ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

- አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የሚሰራው የማስወገድ ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ቢታገዝ አገልግሎቱ አገር አቀፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አፈጻጸሙን ለማሻሻልና ተደራሽ ለማድረግ የጎላ ሚና ስለሚኖረው፣

በምርጥ ተሞክሮዎች ላይ የተመሰረተ ሶፍትዌር ዴቭሎፕ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በናሙና የታየው አዳማ ዩኒቨርስቲ እንደማሳያ ሆኖ በተለይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወርክ ሾፖች ቢኖሯቸውና ንብረቶች ለሽያጭ ከሚቀርቡ ይልቅ ቢጠገኑ ወይም በግብዓትነት ቢጠቀሙባቸው የስራ እድል ከመፍጠራቸውም በተጨማሪ የሀገር ሀብትን በአግባቡ መጠቀም ያስችላሉ፡፡

11.16 በማዕድን ሚኒስቴር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ፈቃድ አስተዳደር፣ግብይትና ቁጥጥር

379. የሚኒስቴር መ/ቤቱን ስልጣንና ተግባር አስመልክቶ ለወጡት አዋጆች የማስፈፀሚያ ደንብ እንዲወጣላቸው ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና የቀድሞውም ስራ ላይ እንዲውል አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይትን ለማስፋፋት፣ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን መሰረት አደርጎ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

380. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአዋጅ ቁጥር 651/2001 እና 678/2002 የማስፈፀሚያ ደንብ አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲፀድቅ አላደረገም፡፡ በአሁን ወቅት በስራ ላይ ያለው የማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 182/1986 ከአዋጅ ቁጥር 678/2002 በፊት የወጣና በተጠቀሰው አዋጅ የተደነገገው ዋና ዋና ጉዳዮች የሚያካትት በግልፅና በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማብራሪያዎች ባለመኖራቸው በአፈፃፀም ላይ ችግር እየተፈጠረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማዕድን ሚኒስቴር ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት

እና ግብይት አስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን መሰረት አደርጎ ዝርዝር የአፈጻጸም መመርያ አለማዘጋጀቱ ታውቋል፡፡

381. ሚ/ር መ/ቤቱ በየበጀት ዓመቱ በሚያዘጋጀው ዕቅድና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች ወቅታዊ የስራ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ በማድረግ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ እንዲሁም መደበኛና ተከታታይ የስራ አመራር /የማኔጅመንት/ የውይይት መድረክ እንዲኖር በማድረግ በውይይቱ ላይ የሚነሱ ነጥቦችን በቃለ ጉባኤ በአግባቡ በመያዝ ጠንካራ የስራ አፈፃፀም ማሻሻያ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ሚ/ር በመ/ቤቱ በየበጀት አመቱ በሚያዘጋጀው ዕቅድና የዕቅድ ክንውን ሪፖርት የሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶችን መሰረታዊ ምክንያታቸውን ለመለየት የሚያስችል ጠንካራ የስራ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ስርዓት የሌለው መሆኑ፣

- ✓ እንዲሁም በ2004 እና በ2005 የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለብሄራዊ ባንክ የቀረበው የወርቅ መጠን ዕቅድ አፈፃፀማቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤ ከዚህም በተጨማሪ በሚ/ር መ/ቤቱ በ2004 ዓ.ም ለታቀደው ዕቅድ ሁለት ዓይነት የአፈፃፀም ሪፖርቶች ያዘጋጀ በመሆኑ ምክንያት የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በኦዲት ወቅት ለመገምገም አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም የ2004 ዓ.ም ዕቅድና አፈፃፀም ከ2005 ዓ.ም ዕቅድና አፈፃፀም ጋር ሲገመገም በይዘትም ሆነ በቁጥር አንድ አይነት መሆናቸው ታውቋል፡፡
- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/07/2006 ዓ.ም የሚ/ር መ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ሁኔታን አስመልክቶ ለሚካሄደው የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎች እንደማይያዙ ታውቋል፡፡

382. ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ሊቋቋም እና የማዕድን ማምረት ፈቃድ ሲሰጥ በቅድሚያ

የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሁንታ በመጠየቅ ሊሆን እንዲሁም የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች የሚያካሂዷቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ ለአካባቢ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

383. በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ሚ/ር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት መቋቋም እንዳለበት ቢደነገግም እስካሁን ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት አለመቋቋሙ ታውቋል፡፡ እንደዚሁም ከሚ/ር መ/ቤቱ ፈቃድ ካገኙ ከአምስት የከበሩ ማዕድናት አምራች ባለፈቃዶች ውስጥ ሚ/ር መ/ቤቱ ለ3ቱ (60%) ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ይሁንታ ማግኘታቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

384. ከዚህም በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች የሚያካሂዷቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ አካባቢ ለልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን በተሟላ መልኩ አያረጋግጥም፡፡በኦዲቱ ወቅት በታዩት በኦሮሚያ፣በደቡብ እና በትግራይ ክልሎች በባህላዊ መንገድ ለረጅም ዓመታት ወርቅ ሲመረቱባቸው የነበሩ የተጐሣቆሉና መልሶ የማቅናቱ ሂደት ያልተከናወነባቸው ሰፋፊ ቦታዎች መኖራቸው (ለምሳሌ፡- በደቡብ ክልል ወደ 81 ጉድጓዶች)፣ የከበሩ ማዕድናት የሚያመርቱ አምራቾች ባለፈቃድ እና ህገወጥ ግለሰቦች ወርቅ ለማግኘት ብለው በአብዛኛው ጉድጓዶችን ቆፍረው እንደ ማይደፍኑ እና አከባቢውን እንደማያለሙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

385. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች /ድርጅቶች/ ወደ ውጭ የሚልኳቸውንና የሚያዘዋውሯቸውን

ጥሬ የከበሩ ማዕድናት የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲያሳውቁ የሚያደርግበት እና የማዕድን ማምረትና የምርመራ ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጽ ነፃ ያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በትክክል ለማዕድን ሥራው ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

386. ሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው ግለሰቦች /ሰዎች/ ወደ ውጭ የሚልኳቸውንና የሚያዘዋውሯቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት ጥራትና መጠን የሚያመለክት የላብራቶሪ ውጤት የተገኘበትን ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውንና የከበረውን ማዕድናት ኘሮሰስ ያደረገውን ስምና የፈቃድ ቁጥሩን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንዲያሳውቁ ስርዓት በመዘርጋት እንደማይከታተል ታውቋል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት የታዩት ኦሮሚያ፣ ደቡብና ትግራይ እንዲሁም ማስረጃቸው ከሚ/ር መ/ቤቱ የተገኘው በኦሮሚያና በጋምቤላ ክልሎች የሚገኙ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪነት ባለፈቃዶች የሚያዘዋውራቸውንና ለባንክ ወርቅ ሲያስገቡ በማዕድን አዋጁ መሰረት የከበሩ ማዕድናትን ሕጋዊ ምንጭና አከባቢያቸውን ለፈቃድ ሰጪ አካላት እንደማያሳውቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ እንዲሁም በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት የማዕድን ማምረትና የምርመራ ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በትክክል ለማዕድን ሥራው ማዋላቸውን የሚያረጋግጥበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ ቢገለፅም ሚ/ር መ/ቤቱ በተሟላ መልኩ እንደማይከታተል ለማወቅ ተችሏል፡፡

387. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ 20 ዓመት፣ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት የፈቃድ ጊዜ 10 ዓመት እና የባህላዊ ማዕድን የማምረት የፈቃድ ጊዜ 3 ዓመት ሊሆን እንዲሁም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራውን ሊጀምርና የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ሊያከብር ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ ክልሎች ከፈቃድ ዘመናቸው በላይ ፈቃዱን ይዞ የመቆየት እና ወደሌላ የፈቃድ ደረጃ ያለመሸጋገር ችግርም መኖሩን ከነዚህም ውስጥ በደቡብ ፈቃድ ከወሰዱት 16 ባለፈቃዶች ውስጥ 15ቱ፣ በኦሮሚያ ከ65 ባለፈቃዶች ውስጥ 56ቱና በትግራይ ክልል 78 ባለፈቃዶች በአዋጁ መሠረት በባህላዊ የማምረት የፈቃድ ዘመናቸውን ጨርሰው ፈቃድ ያልመለሱ እንዲሁም የፈቃድ ዘመናቸው ከተጠናቀቀ በኃላ ወደሌላ የፈቃድ ደረጃ ሳይሸጋገሩ ከ9ወራት እስከ 11ዓመታት በማስቆጠር በፈቃዱ እንደተጠቀሙ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ✓ በተጨማሪም በኦሮሚያ፣ በደቡብ እና በትግራይ ክልል ማዕድን ቢሮዎች በአነስተኛ የማዕድን ማምረት ወይም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ተሰጥቷቸው የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች በማክበር ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራ ያልጀመሩ መኖራቸው ታውቋል፡፡

388. የማዕድን ሚ/ርም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ ሊከታተሉና ሊቆጣጠሩ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ የማዕድን ስራዎችን መካሄዳቸውን በማዕድን ደንቦች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች እና አግባብ ባላቸው ስምምነቶች (በማዕድን ውል) መሠረት ሊያስተዳድርና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

389. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ የማዕድን ስራዎች መካሄዳቸውን በማዕድን ደንቦች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች እንዲሁም አግባብ ባላቸው ስምምነቶች (በማዕድን ውል) መሰረት ፈቃዱን አለማስተዳደሩ፣ አለመቆጣጠሩና አለማረጋገጡ ታውቋል፡፡

በኦዲቱ ወቅት እንደታየው ፍቃዳቸውን ሳያሳድሱ በዘርፉ ላይ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች/ድርጅቶች ያሉ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይታደሱ የቆዩ ፍቃዶችን በመለየት ፍቃዶቹን የመሰረዝ እርምጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዳልወሰደ ታውቋል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ በክልሎች የከበሩ ማዕድናትን ሳያስረክቡ የሚያከማቹ፣ በባህላዊ ደረጃ ከተፈቀደላቸው መሳሪያ ውጪ የሚያመርቱ፣ ፈቃድ ሳይኖራቸው ከ1 ኪ.ግራም በላይ የከበሩና በከፊል ከበሩ ማዕድናትን የሚያመርቱና የሚሸጡ እና የሚያዘዋውሩ መኖራቸው፣

- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ/ሂደት/ ወጥ በሆነና በተሟላ መልኩ በሁሉም ክልሎች ላይ የማይከታተሉና የማይቆጣጠሩ መሆኑ እንዲሁም ለክትትል በተኬደባቸው አከባቢዎችም ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ ከክልል እስከ ወረዳ ያሉት የማዕድን ቢሮዎች/ፅ/ቤቶች መፍትሄም ሆነ የግብረ-መልስ ሪፖርት ለባለፈቃዶቹ እንደማይልኩላቸው ታውቋል፡፡

390. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ፈቃድ ሰጪ አካላት መቆጣጠራቸውን ሊከታተል እንዲሁም ወርቅ አቅራቢዎች፣ በክልሎች ለሚገኙ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለወርቅ ግዥ ጣቢያዎች ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ እንደሚስተናገዱ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወሰነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲያቀርቡ ሁሉም ፈቃድ ሰጪ አካላት ስለመቆጣጠራቸው ወጥ በሆነ መልኩ ከ2004-2006 ዓ.ም በመደበኛነት ክትትል እንደማያደርግ እና ክትትል በተደረገባቸው ክልሎችም ወርቁ ሊቀንስ የቻለበትን ምክንያቶች በመለየት ለችግሮቹ አፋጣኝ መፍትሔ ሊያስወስድ የሚችል የግብረ መልስ ሪፖርት አለመላኩ ታውቋል፡፡

391. የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 651/2/ መሠረት የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ

ባለፈቃድ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወስነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለባንኩ ማቅረብ አለበት ቢልም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ በደቡብ፣ በኦሮሚያ እና በትግራይ ክልሎች ከ2004-2006ዓ.ም ለብሄራዊ ባንክ የሚቀርበው ወርቅ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተጨማሪም የማዕድን ሚኒስቴር ወርቅ አቅራቢዎች በክልሎች ለሚገኙ ለአራት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች /አዋሣ፣ ጅማ፣ መቀሌና አሶሳ /ወርቅ ሲያቀርቡ በወቅቱና ሥርዓትን በተላበሰ መንገድ የሚስተናገዱ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

392. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተል ይገባል፡፡

393. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በተሸጠበት ዋጋ ላይ መከፈል የሚገባውን የሮያሊቲ እና የመሬት ኪራይና ሌሎች ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ሊሰበስብና ሊመረምር ይገባል፡፡

በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ፈቃድ ሰጪ አካላት ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በተሸጠበት ዋጋ ላይ ለከበሩ ማዕድናት 8%፣ በከፊል ለከበሩ ማዕድናት 6% ሮያሊቲ፣ ተመን ላልወጣለት ማዕድን ጊዜያዊ የሮያሊቲ ክፍያ ተመን በማውጣትና ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በወጣው ህግ መሰረት እንዲሁም የመሬት ኪራይና ሌሎች (የመንግስት ነፃ ድርሻና ግብር) ክፍያዎች ሂሳብ በወቅቱ ተከታትለው የማይሰበስቡና የማይመረምሩ መሆኑ፣

ይህም በመሆኑ

- ✓ የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓት ቢዘረጋም አለመከታተሉ ታውቋል፡፡
- ✓ የማዕድን ሚኒስቴር የከበሩ ማዕድናት ዕደ-ጥበብ ፈቃድ እና የከበሩ ማዕድናት የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት በክልሎች መሰጠት እንዲጀምርና ፈቃዱን ማስተዳደር እንዳለባቸው ውክልና መስጠቱን እና የተሰጡ ፈቃዶችና የብቃት ማረጋገጫዎች በግልባጭ እንደሚያሳውቃቸው ከመጋቢት 08 እስከ ሚያዚያ/2006 ዓ.ም. በደብዳቤ ለኦሮሚያ፣ ለትግራይ፣ ለአማራና ለደቡብ ክልል ማዕድን ቢሮዎች ያሳወቀ ቢሆንም ውክልና ሰጥቶ ፋይላቸውን ለክልሎች በወቅቱ ባለመላኩ እስከ 04/02/2007 ዓ.ም የክትትል ስራው በክልሎች ያልተጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡በ2005 ዓ.ም ኦሮሚያ ክልል ከብር 426,982,815.56 በላይ ከሮያሊቲ ገቢ ያጣ መሆኑ፤
- ✓ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከጉጂ ዞን እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ80 - 85% የሚሆነው የወርቅና የታንታለም ማዕድን ከሕገወጥ አምራቾችና ሮያሊቲ ካልከፈሉ ማህበራት ተገዝተው የሚቀርቡ መሆኑን፣

- ✓ እንዲሁም ከከበሩና በከፊል ከከበሩ የሮያልቲ አከፋፈልን በተመለከተ የቀድሞ አዋጅ ላይ ለከበሩ 5% እና በከፊል ለከበሩ ያልተገለፀ ሲሆን፣ በአዋጅ ቁጥር 678/2002 ደግሞ 8%ና 6% ቢልም ከሜድሮክ ጎልድ ከከበሩና በከፊል ከከበሩ ማዕድናት ላይ ሮያሊቲ በ5% ብቻ በመሰብሰቡ ከ2004-2006 በጀት ዓመት ከወርቅ በ3% ማለትም ብር 252,961,236.45 እንዲሁም ከብር በ1% ማለትም ብር 413,394.46 በድምሩ 253,374,630.91 የሮያሊቲ ገቢ አገሪቷ ያጣች መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

394. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም ባለፈቃድ ሮያሊቲ በወቅቱ ካልከፈለ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ከገዛ፣ በማዕድን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ መሰረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርቦ ከተገኘ እንዲቀጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ሮያሊቲ በወቅቱ ለማይከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ለሚገዙ በማዕድን አዋጅ ደንብ መመሪያ መሠረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርበው ለተገኙ የማዕድን ባለፈቃዶች በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በክልል ማዕድን ቢሮዎች በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ እየሆነ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

- ✓ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን በኦዳ ሻክሶ ወረዳ በመሬት ኪራይ ክፍያ ዙሪያ በፊት ህገ ወጥ ግለሰቦቹ ሲከፍሉበት እንደነበረ በማስመሰል ህገ-ወጥ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ (ተመሳሳይ የደረሰኝ ቁጥር ያላቸው ለምሳሌ ደ.ቁ 42608፣ 42638ና 42645) በአንድ ጊዜ በተለያዩ ባለስልጣናት የተፈረመ እና ከመንግስት ግብርም አንፃር ከፍተኛ ስህተት የሚያስከትል ማስረጃ/ደረሰኝ/ መገኘቱ፤

- ✓ ማንኛውም ሰው የከበሩ ማዕድናት(ወርቅ) ግብይትን ለማካሄድ የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው በ651/2001 አዋጅ መሰረት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ አካል ቀርቦ በንግድ መዝገብ በመመዝገብ የተሰጠ የጸና ፈቃድ ወይም የታደሰ የከበሩ ማዕድናት (ወርቅ) ንግድ ሥራ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡
- ✓ በናሙና ተመርጠው በታዩ ክልሎች እና ፋይላቸው ከሚ/ር መ/ቤቱ ቀርቦ በተከለሱ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በትግራይ፣ በአማራ እና በጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ቀርበው በንግድ መዝገብ ሳይመዘገቡና የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው በአዋጅ 651/2001 መሰረት የተሰጠ የጸና ፈቃድ ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናትን ግብይት እያካሄዱ የሚገኙ ህገ ወጥ ግለሰቦች መኖራቸው ታውቋል፡፡

395. ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋት በወጣው አዋጅ እና በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ሊያድስ፣ ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ፈቃዱን ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም በፈቃድ ወይም በፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከተመለከተው ውጭ ከተሰማሩ፣ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ሪፖርት ካላደረጉ እና ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይኖራቸው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ ከተሰማሩ በተቀመጠው ህግ መሰረት እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ በሚ/ር መ/ቤቱ እና በናሙና በታዩት በደቡብ፣በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ውስጥ በሶስቱም ክልሎች ፈቃድ ወይም የፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጣቸው የማዕድን ባለፈቃዶች በየአንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ፈቃዳቸውን እንደማያሳድሱ

ታውቋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ከ2004-2006 በጀት ዓመት በትግራይ 119 ባለፈቃዶች፣ በኦሮሚያ 53 ባለፈቃዶች እንዲሁም በደቡብ ክልል 8 የአዘዋዋሪ ባለፈቃዶች ፈቃዳቸውን በእያንዳንዱ ፈቃድ ዘመን መጨረሻ ሳያሳድሱ ግብይት በማከናወንና ለባንኮችም ወርቅ በማቅረብ ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

396. እንዲሁም በማዕድን ስራዎች አዋጅ እና በደንብ መሰረት በሚ/ር መ/ቤቱ በከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ መሠረት ከ2002 ዓ.ም ጀምረው በባሕላዊ ምርትና ግብይት ማስተባበሪያ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች ቢኖሩም ፈቃድ የማደስ ሥራ በዕቅድ መሠረት አለመሠራቱና በባህላዊ መንገድ ፈቃድ ሰጥቶ ከሚያስተዳድራቸው ዘጠኝ ዓይነት የማዕድን ፈቃዶች ውስጥ በስድስት የፈቃድ ዓይነቶች ላይ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ በመስራት ላይ ያሉ ባለፈቃዶች መኖራቸው፣ ፈቃዳቸውን ያሳደሱትም ከዕድሳት ጊዜው ከ4-7 ወራት በመዘግየት መሆኑን፣ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በከፍተኛ ደረጃ በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ምርትና ምርመራ ላይ ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም ፈቃድ ካገኙት ውስጥ 90ዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠጣቸውን የቆይታ ጊዜ ጨርሰው በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ ከ1 እስከ 15 ዓመታት ፈቃዱን ይዞ በመቆየት በመሥራት ላይ መሆናቸው እንዲሁም 14ቱ ደግሞ በአዋጅ 678/2002 አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀስ 1 ላይ በተጠቀሰው መሠረት የመጀመሪያ የፈቃድ እድሳት ከ1 እስከ 5 ዓመት በመዘግየት ያሣደሱ መሆኑ እንዲሁም ሌሎች ሶስት ባለፈቃዶች ደግሞ የፈቃድ ዘመናቸው ከተቃጠለ ከ3-6 ዓመታት ያስቆጠሩ ቢሆንም ፈቃዱ ያልተሰረዘ ወይም ያልታገደ መሆኑ፤

- ✓ ከዚህም ሌላ በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን በአዶ ሻክሶ ወረዳ ከተገኘው የ65 ባለፈቃዶች ዝርዝር ውስጥ የማዕድን ፈቃዳቸውን አሳድሰው የማያውቁ 39 (60%) ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ፈቃድ የወሰዱ ባለፈቃዶች እንዳሉ ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣በደቡብ ክልል ፈቃድ ከተሰጣቸው 97 የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ባለፈቃዶች ውስጥ 81ዱ (84%ቱ) ባለፈቃዶች ፈቃዳቸው ስለመሰረዙ እና ስላለመሰረዙ ምንም ዓይነት ማስረጃ በክልሉ አለመገኘቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ✓ በአዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት ሚ/ር መ/ቤቱ እና የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት በማዕድን ስራዎች አዋጅ፣ በደንብ እና በመመሪያ መሰረት የማዕድን ፈቃድ ባላሳደሱ እንዲሁም ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ፈቃዳቸውን አለመሰረዛቸው ወይም አለማገዳቸው ታውቋል፡፡

397. ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ የሚያደርግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ የሚያደርግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት አልዘረጋም፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች ውስጥ የማዕድን ህገ ወጥ ዝውውርና ግብይት አለመወገዱ፣ ህገ ወጥ የወርቅ አዘዋዋሪዎች እየተስፋፉ መምጣታቸው፣ ለህጋዊ ግብይቶች ህጋዊ ከለላ ከመስጠትና ኮንትሮባንድን ከመከላከል አኳያ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ፣ ክትትል አለመደረጉና በህገ ወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ወርቆችን ለመቆጣጠር የፍተሻ ኬላና ዘመናዊ የፍተሻ መሳሪያ አለመኖሩ፣ ከዚህም በተጨማሪ በኬላዎች ላይ የተጠናከረ ድንገተኛና መደበኛ ፍተሻ አለመደረጉ እንዲሁም ሕገወጦች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ የማዕድናት ምርትና ግብይት እንቅስቃሴ ከምርቱ ጀምሮ እስከ ግብይቱ ድረስ ስርዓትን ያልተከተለ እንዲሆን ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

398. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት አምራቾችና ነጋዴዎች (አዘዋዋሪዎች) ያለባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረክ ሊኖረው ይገባል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በደቡብ፣ በኦሮሚያ በትግራይና በአማራ ክልል ለሚገኙት የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት አምራቾችና ነጋዴዎች (አዘዋዋሪዎች) ያለባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መደበኛ በሆነ መልኩ የመወያያ መድረኮችን ያላዘጋጀ እና ለሌሎች ክልሎች ደግሞ ለመወያየትም ጥሪ አድርጎላቸው እንደማያውቅ ታውቋል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ሶስት አምራቾችና 10 አዘዋዋሪዎች በድምሩ ከ14ቱ ባለፈቃዶች ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2004-2006ዓ.ም ለ5ቱ (36%) አምራችና አዘዋዋሪዎች የመወያያ መድረኮችን ፈጥሮላቸው የማያውቅ ሲሆን ለ 9ኙ (64%) የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት አምራቾች፣ አዘዋዋሪዎች እና ለጌጣጌጥ ላኪዎች ደግሞ የመወያያ መድረኮችን ቢፈጥርላቸውም ያለባቸውን ችግሮች በተዘጋጁት መድረኮች አማካኝነት ሊፈታላቸው እንዳልቻለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

399. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የማዕድን ምርቱን ፈቃድ ለማስተዳደር እና የግብይት አሠራርን ለማጠናከር እንዲያስችል በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ በኦዲቱ ከታዩት 10 ባለድርሻ አካላት ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ8ቱ (80%) ጋር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ የማዕድን ምርቱን ፈቃድ ለማስተዳደር እና የግብይት አሠራርን ለማጠናከር እንዲያስችል በመቀናጀት እንደማይሰራ እንዲሁም ከደቡብ ክልል ማዕድን ኤጀንሲ ጋር ደግሞ የተጠናከረ የቅንጅት አሰራር እንደሌለው የታወቀ ሲሆን፡ከዚህም በተጨማሪ በየደረጃው የሚገኙ የክልል ማዕድን ቢሮዎች ፣ የዞንና የወረዳ ማዕድን ፅ/ቤቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት የላላ በመሆኑ በመናበብና በመቀናጀት እንደማይሰሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

400. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር የከበረና በከፊል የከበረ ማዕድናት ምርትና ሽያጭ ዙሪያ የሪፖርት አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ ሊኖረው እና የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታ /ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ፣ የፈቃድ

ዕድሳት ጊዜ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜ ወዘተ/ ለመከታተል የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ ሊኖረው ይገባል፡፡

- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት ምርትና ሽያጭ ዙሪያ የሪፖርት አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ የመግባቢያ ሰነድ እንደሌለው ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሚ/ር መ/ቤቱ የባለፈቃዶችን ወቅታዊ ሁኔታ /ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ፣ የፈቃድ ዕድሳት ጊዜ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜ ወዘተ/ ለመከታተል የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ አያያዝ ዘዴ ካዳስተር ሲስተም እንዳለው ቢገልጽም ከክልሎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ባለመኖሩ የተደራረቡ የፈቃድ ቦታዎች እንዳሉ ታውቋል፡፡

401. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ ተመን በማውጣት ለግብይቱ ህጋዊ ድጋፍ እንዲሁም በክልሎች ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች (የወርቅ፣) የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) ሊሰጥ ይገባል፡፡

402. ከሀገሪቱ እሴት ሳይጨመርባቸው ወደ ውጭ ሀገር የሚወጡ (ለምሳሌ ኦፓል፣ አማዞናይት፣ ኮረንደም ሳፋየርና ሩቢ ኤመራልድ እና ግራን ቶርማን እንዲሁም የመሳሰሉ ማዕድናት) እንዳሉ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ የጌጣጌጥ ማዕድናት የላኪነት ፈቃድ ያላቸው ባለፈቃዶች በአዋጅ 651/2001 ከተመለከተው ውጭ በክምችት ከ74 እስከ 21,001 ኪሎ ግራም በከፊል የከበሩ ማዕድናት ይዘው እንደሚቆዩ ታውቋል፡፡

- ✓ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በደቡብ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልል በናሙና ከታዩ 3 የማዕድን ቢሮዎችና 13 ባለፈቃዶች ውስጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ1 የማዕድን ቢሮና ለ11ዱ (85%) ባለፈቃዶች ከ2004-2006ዓ.ም በክልሎቹ ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች የቴክኒክ ድጋፎችን (የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች) ያልሰጠ መሆኑ እንዲሁም ለሁለት ክልሎችና ለ2 (15%) ባለፈቃዶች ደግሞ በተሟላ መልኩ የተሻሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና ድጋፎች እንዳልሰጣቸው ታውቋል፡፡

403. ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊነቱን ሊከታተል፣የምርት ባለፈቃድ ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የምርት ዓይነትና መጠን እንዲሁም የእደ-ጥበብ ባለፈቃድ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን በወቅቱ ለፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

404. የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ቢዘረጋም በኦዲቱ ወቅት ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት ተግባራዊነቱን እንደማይከታተሉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለማዕድን ስራዎች እና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆች በስራ ላይ የአፈፃፀም ችግር እንዳያስከትሉ እንዲሁም የሚፈጠሩትን

ክፍተቶችን ለመቀነስና የበለጠ አሰሪ ለማድረግ እንዲረዳ የማስፈፀሚያ ደንብ በማውጣት እንዲፀድቅለት ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና ሊከታተል እንዲሁም ለከበሩና በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ምርት እና ግብይት አስተዳደር የወጡ አዋጆች እና ደንቦችን የበለጠ ግልፅ የሚያደርግ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይገባል፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ በየበጀት አመቱ በሚያዘጋጀው የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶች እርምጃ ሊወስድ እንዲሁም በመደበኛና በተከታታይ ለሚደረገው ለስራ አመራር /የማኔጅመንት/ ውይይት በውይይቱ ወቅት ለሚነሱት ሃሳቦች የማሻሻያ እርምጃዎችን ለመውሰድ እንዲያስችለው በማኔጅመንት የሚደረጉ ስብሰባዎችን በቃለ-ጉባኤ በመያዝ ተከታታይ ቁጥር ሰጥቶ በተገቢው ቦታ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚያማክር የማዕድን ስራዎች ምክር ቤት ሊቋቋም እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገርን ጥቅም ከማስከበር እና በአከባቢና በማህበረሰቡ ላይ የሚደርሱትን ጉዳት ከመከላከል አንፃር ለማዕድን ምርት ባለፍቃድ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሁንታ ሊጠይቅ እና የአከባቢን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ለማልማትና የማዕድን ማምረት ሥራ ተከናውኖባቸው የተጐሳቆሉ አካባቢዎችን መልሶ የማቅናት ሥራ እንዲሰራባቸው ባለፈቃዶች የሚያካሂዷቸው የማዕድን ስራዎች የአከባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ የአከባቢ ለልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናትን የአዘዋዋሪነት እና የላኪነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተሰጠው ሰው ወደ ውጭ የሚልካቸውንና የሚያዘዋውራቸውን ጥሬ የከበሩ ማዕድናት ጥራትና መጠን የሚያመለክት የላብራቶሪ ውጤት፣ ማዕድኑ የተገኘበትን

ሕጋዊ ምንጭና አካባቢያቸውን እና የከበረውን ማዕድናት ኘሮሰስ ያደረገውን ስምና የፈቃድ ቁጥሩን እንዲያሳውቁ እንዲሁም የማዕድን ባለፈቃዶች ለማዕድን ሥራ ከውጭ ሀገር ከቀረጽ ነፃ ያስገቧቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች በትክክል ለማዕድን ሥራው ማዋላቸውን የሚቆጣጠርበትና የሚከታተልበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የከፍተኛ ደረጃ ፣ የአነስተኛ ደረጃና የባህላዊ ማዕድን የማዕድን ማምረትየፈቃድ ዘመን በማዕድን ስራዎች አዋጅ መሠረት ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ መብለጥ የለበትም፡፡ እንዲሁም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ የምርት ስራውን ለመጀመር እና የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች እንዲያከብሩ ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለፈቃዶችን በማዕድን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እና ውሎች ሊያስተዳድርና ሊቆጣጠር እና ፈቃድ ሰጪ አካላት በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ መሠረት የሚፈለገው የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ በማሟላት ወደ ማናቸውም ክልል በመግባት በፈቃድ ክልላቸው ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የማዕድን ስራ እንቅስቃሴ በአግባቡ መሠራታቸውን ሊቆጣጠሩና ሊከታተሉ እንዲሁም የከበሩ ማዕድናት እደጥበብ ባለፈቃድ ለስራ የሚያስፈልገውን ጥሬ ወርቅና ብር ከብሄራዊ ባንክ ብቻ እንዲገዙ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓት በመዘርጋት ሊከታተል ይገባል ፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ ወርቅ አቅራቢዎቹ የሚስተናገዱበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ሊዘረጋ እንዲሁም የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣ አዋጅ ቁጥር 651/2/001ና በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩ ማዕድናት አዘዋዋሪ ባለፈቃድ

በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት በስምምነት የሚወስነውን ወርቅና ብር ማዕድናት መጠን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአራቱም ክልል የወርቅ ግዥ ጣቢያዎች የሚያቀርቡ መሆኑን ፈቃድ ሰጪ አካላት ስለመቆጣጠራቸው ሊከታተል ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ፈቃድ ሰጭው ባለስልጣን ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የሚገኘውን የሮያሊቲ፣ የመሬትና ሌሎችክፍያን እንዲሁም ለባህላዊ ማዕድናት በክልሎች በሚወጣው ህግ መሰረት ወጥ በሆነ መልኩ ሊሰበስብና ሂሳባቸውን ሊመረምሩ እንዲሁም የማዕድን ባለፈቃዶች ሮያሊቲ በወቅቱ ካልከፈሉ፣ ሮያሊቲ ያልተከፈለበት ማዕድን ከገዙ፣ በማዕድን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ መሰረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርበው ከተገኙ በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር 678/2002ና 651/2002 መሰረት ማንኛውም ሰው ወርቅ ወደ ሚመረትበት አከባቢ ሄዶ ወርቅ ለማምረት እና የከበሩ ማዕድናት ግብይትን ለማካሄድ አግባብ ባለው መሥሪያ ቤት ቀርቦ በንግድ መዝገብ በመመዝገብ የጸና ፈቃድ ሊያገኝ ወይም የታደሰ የከበሩ ማዕድናት ወርቅ ንግድ ሥራ ሊኖረው፣ በየፈቃድ ዘመኑ መጨረሻ ወቅቱ ሣያበቃ የምርትና የግብይት ሥራ ፈቃዱን በየዓመቱ ሊያሣድስ ይገባል፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ በባህላዊ አምራቾች የሚመረቱ የወጪ ንግድ ማዕድናት ወይም ጥሬ እና እሴት የተጨመረባቸው የጌጣጌጥ ማዕድናት በኮንትሮ ባንድ ንግድ ከሀገር ውጭ እንዳይወጡ ለማድረግ እንዲያስችልና ሀገሪቷም ከማዕድኑ የሚታገኘውን ገቢ እንዳታጣ እስከ ክልል የሚወርድ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማዕድን ፈቃድ ሊያድስ እንዲሁም ባለፈቃዶቹ በአዋጁ መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ ፈቃዱን ሊያግድና ሊሰርዝ እንዲሁም በፈቃዱ ወይም በፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከተመለከተው ውጭ ከተሰማራ፣ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን ሪፖርት ካላደረገ በህጉ መሰረት ሊቀጣ ይገባል ፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸውን በማሰልጠንና ግንዛቤ በመፍጠር እንዲሁም ከወረዳ እስከ ዋና ከተሞች የፍተሻ ኬላዎችን በማቋቋም የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ዙሪያ ክትትል በማድረግ ተገቢው ፈቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሳይኖረው የከበሩ ማዕድናት ግብይት ሥራ ላይ በተሰማሩት ግለሰቦች/ድርጅቶች ላይ በአዋጅ ቁ 651 መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ባለፈቃዶች የሚገጥማቸውን ችግሮች በማየትና በየጊዜው መደበኛ የሆነ መድረክ በመፍጠር የመፍትሔ አቅጣጫ በማስቀመጥ የሚፈጠሩትን ክፍተቶች ሊቀርፍ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሰራ ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከባንኮች ጋር የከበረና በከፊል የከበረ ማዕድናት ምርትና ሽያጭን በተመለከተ ወጥነት ያለው የሪፖርት አቀራረብ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ እና የማዕድን ባለፈቃዶች ሪፖርት የሚያቀርቡበት፣ የፈቃድ እድሳትና የክፍያ መፈፀሚያ ጊዜን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ አያያዝና ልውውጥ ዘዴ ተግባራዊ ሊያደርግ ሊኖረውይገባል፡፡

- የማዕድን ሚኒስቴር የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ በጥናት ላይ የተመሰረተ ተመን በማውጣት እና ወቅታዊ የገቢያ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ በየጊዜው በማሻሻል ለባለፈቃዶቹ

በመስጠት በግብይቱ ዙሪያ ህጋዊ ድጋፍ ሊያደርግላቸው እንዲሁም የባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ምርት ለማሳደግ እንዲረዳ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን(የቴክኒክ ድጋፎችን) በማስተዋወቅ የማዕድናት አምራቾችን የማምረት ክህሎት በማሳደግ ባለፈቃዶቹ እንዲበረታቱ በማድረግ የተሸሻሉ የማምረቻ መሳሪያዎችንና የሰርቶ ማሳያ ስልጠና በመስጠት በክልሎች ለሚገኙ ለባህላዊ ማዕድናት አምራቾች ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ሚ/ር መ/ቤቱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት ምርትና ግብይት ባለፈቃዶች ያመረቱትን ወይም የሸጡትን የማዕድን ዓይነትና መጠን ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚያሳውቁበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊነቱን ሊከታተል እና የምርት ባለፈቃድ ያመረተውን ወይም የሸጠውን የምርት ዓይነትና መጠን እንዲሁም የእደ-ጥበብ ባለፈቃድ ከግለሰብ የሚሰበስባቸውን የወርቅና ብር መጠን በህጉ በተቀመጠው ጊዜና በወቅቱ ለፈቃድ ሰጭው አካል ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡

11.17 የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት እና የወጪ ንግድ አፈፃፀም

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት በተመለከተ የኢንቨስትመንት ድጋፍ አሰጣጥ፣ የማበረታቻ ስርዓትና በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የተዘረጋው አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ፤

405. የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ከሚመለከታቸው ከክልልና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ለማቆየትና ለማበረታታት የሚያስችል

የኢንቨስትመንት የማትጊያ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እና ስለሚሰጠው ድጋፍ ለባለሃብቶች ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡

- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ኢትዮጲያ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ያላትን አቅምና ተወዳዳሪነት(Comparative advantage) ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እና በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በክፍለ አህጉር ደረጃ በተለይም በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ ውጤታማ የሆኑ አገሮችን ተሞክሮ በመቀመር በዘርፉ ሊሰማሩ የሚችሉ ባለሀብቶችን በተሻለ ለመሳብ የሚያስችል የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ያገናዘበ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ዘላቂነት ያለው እና አስተማማኝ የድጋፍ ማዕቀፍ(Comprehansive incentive package) ያልተዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ ባለሀብቶችም እንዲያውቁት ያልተደረገ መሆኑ፣

- በኤጀንሲው ሊዘጋጅ የሚገባው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተለይ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛትን ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍን፣ በብድር አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍን ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተመለከተ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍን እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር

በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፉ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ በኤጀንሲው ያልተዘጋጀና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲውቁት ያልተደረገ መሆኑ፣

- ✓ እንዲሁም መንግስት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ያስቀመጠው የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ በጉምሩክ አሰራር ቀልጣፋ ባለመሆን በጉምሩክ ወደብ ላይ ረጅም ጊዜ የሚቆዩ በመሆኑ ባለሀብቶችን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጋቸው መሆኑ፣

- ✓ በተጨማሪም በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከ2003-2007ዓ.ም በስትራቴጂክ ዕቅድ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ 23,040.4 ሄክታር መሬት በባለሀብቶች ይለማል ተብሎ ዕቅድ ቢያዝም እስከ 2006 ዓ.ም መጨረሻ በባለሀብቶች የተያዘው መሬት 13,084.2 ሄክታር 57 በመቶ ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆኑ መሬቶችን በማጥናት ለባለሀብቶች ማስተዋወቅን በተመለከተ፤

406. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኢንቨስትመንት አመቺ የሆኑ መሬቶችን በዝርዝር ሊያጠና እና ባለሃብቶችን ለመሳብ የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ በሁሉም ክልሎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሆን መሬቶች የተለዩ ቢሆንም ከኦሮሚያ ክልል ውጭ ያሉት የተለዩ መሬቶች በትክክል ለዘርፉ የሚውሉ ስለመሆናቸው

በሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ጥናት ያልተከናወነባቸው እና መሰረታዊ መረጃዎች ተለይተው ያልተያዙ መሆኑ ታውቋል፣

ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬት እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ለባለሀብቶች በወቅቱ እንዲሟላላቸው የተዘረጋ ስርዓትን በተመለከተ፤

407. ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን (ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲሟላላቸው ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሰርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ኤጀንሲው ከኦሮሚያ ክልል ጋር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ የሚመቻችበት እና አፈፃፀሙን በቅርበት ክትትል የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በመተግበር ላይ የሚገኝ ቢሆንም በተለይም በመሬት አቅርቦት በኩል በክልል፣ በዞንና በወረዳ የሚገኙ ኃላፊዎች እርስ በእርስ ተናበውና ተግባብተው የማይሰሩ መሆኑ፣ መመሪያ ሲወጣ ወይም ውሳኔ ሲሰጥ አፈፃፀሙ ደካማ መሆኑ፣ ኤጀንሲው (ከኦሮሚያ ክልል ውጪ) ከሌሎቹ ክልሎች ጋር የጋራ ስምምነት ባለመኖሩ የመሬት አሰጣጥ ሂደቱንና አፈፃፀሙን ክትትልና ድጋፍ የማያደርግ መሆኑን፣ በአጠቃላይ የመሬት አሰጣጥ ስርዓቱ ቀልጣፋ ያለመሆኑ፣

- ✓ ኤጀንሲው በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች በወቅቱ የመሰረተ ልማት አገልግሎት (ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲያገኙና ለግንባታ ከውጪ ሀገር የሚገዙ ግብአቶች እንዲገቡ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ የሚገዙ ግብአቶች በወቅቱ

እንዲቀርቡ የድጋፍ ደብዳቤ የሚፅፍ ቢሆንም አፈፃፀሙ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት በኤጀንሲው ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን መፈታት የሚችለውን እንዲፈታ መፈታት ያልቻሉትን ችግሮች በማጥናት ለሚመለከተው የበላይ አካል በማቅረብ እንዲፈታ ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም ተከታትሎ አፈፃፀሙን ክትትል ማድረግ ላይ ችግሮች መኖራቸው ታውቋል፣

አትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ...ወዘተ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

408. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የተፋጠነ የጉምሩክ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ አገልግሎቶችን እና የባለሀብቶችን የካፒታል አቅም ለማጎልበትና ወደ ልማት በአፋጣኝ እንዲገቡ ለማድረግ ባለሀብቶች ከፋይናንስ ተቋማት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን የሚሰጠው አገልግሎት ቀልጣፋ ያለመሆኑ፣ የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሬ እድገት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ትላልቅ ባለሀብቶች(ሞዴል የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎች) ተለይተው የሚስተናገዱበት አሰራር ያለመኖሩ፣ የልማት ባንክ ከሌሎች ባንኮች ጋር ተቀናጅቶ የማይሰራና የብደር ጥያቄ ሲቀርብ ለመወሰን ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑ እንዲሁም በባንክና ጉምሩክ መካከል የሚካሄደው የኤክስፖርት መረጃ ፍሰት ወቅታዊ፣ ተመሳሳይ፣ ትክክለኛና ያልተሟላ መሆኑ፣ ኤጀንሲው ከባለሀብቶች በየጊዜው የሚነሱ ችግሮች ለመፍታት ለሚመለከታቸው አካላት የድጋፍ ደብዳቤ

ከመፃፍ በዘለለ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ እንዲያገኙ ጥረቶች ቢኖሩም የተጠናከሩ አለመሆናቸው፣

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ መዋላቸውን በተመለከተ፤

409. ኤጀንሲው ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተከለሉና ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች እና የተሰጡ ድጋፎች በአግባቡና በወቅቱ ለታቀደላቸው አላማ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ክትትል የሚያደረግበት ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም መሬት ወስደው ወደ ልማት ያልገቡ ባለሀብቶች በአግባቡ ተለይተው በአፋጣኝ ወደ ልማት እንዲገቡ ካልሆነም እርምጃ የሚወሰድበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ ከ2003-2006 ዓ.ም በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉ ከተሰማሩ 38 ባለሀብቶች ውስጥ 11 ባለሀብቶች ወደ ልማት ያልገቡ መሆናቸው፣ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆናቸው፣ አጠቃላይ በአትክልትና ፍራፍሬ ለባለሀብቶች ከተላለፈ መሬት (16,756 ሄክታር) የለማው እስከ 2006 ዓ.ም 11,517 ሄክታር (69%) ብቻ መሆኑ፣ እንዲሁም ወደ ልማት ከገቡት 27 ባለሀብቶች ውስጥ ደግሞ 17 ባለሀብቶች የሚያመርቱትን ምርት ለውጪ ገበያ የማያቀርቡ መሆኑ፣ የኤክሰፓርት አትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ለማምረት እና ኤክስፖርት ለማድረግ ውል ቢገቡም ለሀገር ውሰጥ ገበያ የሚያቀርቡ፣ የኤክስፓርት ስራቸውን ያቋረጡ እና ከውል ውጪ የሚያመርቱ ባለሀብቶች መኖራቸው፣ በአጠቃላይ ኤጀንሲው ለባለሀብቶች የተመደቡ መሬቶች እና የተሰጡ ድጋፎች በአግባቡና በወቅቱ

ለታቀደላቸው አላማ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የክትትል ሂደቱ የተጠናከረ አለመሆኑ፣

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ስርዓት ዘርግቶ በአገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ገበያ ጥራቱን የጠበቀ ተወዳዳሪ ምርት ለማምረት እንዲቻል የሚሰጠው ድጋፍና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

በአትክልትና ፍራፍሬ በኮንትራት ልማት የሚሳተፉ አርሶ አደሮችን (አውቶግሮዎሮችን) በመመልመል የስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤

410. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው ከክልሎች ጋር በመተባበር በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚሳተፉ የኮንትራት አርሶ አደሮች (አውቶግሮዎሮች) በመመልመልና በማደራጀት የስልጠናና የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የኤክስፖርት ምርት ማምረት የሚችሉ የኮንትራት አርሶ አደሮችን (አውትግሮዎሮችን) ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ምቹ በሆኑ ክልሎች እንዲደራጁና ወደ ምርት እንዲገቡ እና ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠናዎችና የቴክኒክ ድጋፎችን በመቂ አካባቢ ላሉ አውትግሮዎሮች የሚያደርግ ቢሆንም በሌሎቹ አካባቢዎች ያልተስፋፋ መሆኑ፣ እንዲሆም የኮንትራት አርሶ አደሮች (አውትግሮዎሮች) ማበረታታት የሚችሉ የግብይት፣ የብድርና የሎጀስቲክስ መሰረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲሟላላቸው የድጋፍና ክትትል ስርዓቱ ያልተጠናከረ መሆኑ፣

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የምርት አመራረትና አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በመሰብሰብና ማንዋሎች በማዘጋጀት በስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱን በተመለከተ፤

411. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን ውጤታማ የሚያደረጉ ቴክኖሎጂዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በመሰብሰብ ለባለሀብቶችና አውትግሮዎሮች (የኮንትራት አርሶ አደሮች) የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረትና ምርት አያያዝ፣ የመሰኖ አጠቃቀም፣ የአግሮኖሚ እንክብካቤ፣ ዝሪያ አመራረጥ፣ ምርት አጠባበቅና፣ ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ያካተተ ማንዋሎችን በማዘጋጀት ስልጠና ሊሰጥና ወደ አውትግሮወሮች መውረዱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አመራረትና ምርት አያያዝ የስልጠና ማንዋሎች የተዘጋጁ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲሆኑ የስልጠናና የግንዛቤ ስራዎች በስፋት ባለመከናወናቸው በአርባ ምንጭና በድሬዳዋ የልማት ኮሪዶር የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አሰባሰብና አያያዝ በአውትግሮዎሩም ሆነ በባለሀብቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ሳይንሳዊ ሂደትን የተከተለ አለመሆኑ፣ ስለ አመራረት ሂደት፣ ድህረ-ምርት አሰባሰብና አያያዝ፣ የምርት ማጠራቀሚያ፣ የምርት አስተሸሸግ፣ የምርት ማጓጓዝ ዘዴ፣ የኬሚካል አጠቃቀምና አያያዝ ባህላዊና ኃላቀር በመሆኑ እና የግንዛቤ እጥረት መኖሩ፣ በመድኃኒት ርጭት ወቅት የሚደረግ የግል ደህንነት (personal safetey) የማያደርጉ መሆኑ እንዲሁም ኤጀንሲው በበሽታና ተባይ መካላከል በወረርሽኝ መልክ ካልተከሰተ በስተቀር ለቅድመ ጥንቃቄ የሚረዳ ሙያዊ እገዛ የማይደረግ መሆኑ፣ በአጠቃላይ ኤጀንሲው የአትክልትና

ፍራፍሬ ምርት በስፋት የሚከናወንባቸው አካባቢዎችን በመለየት አርሶ አደሮችን በማደራጀት በአውትግሮዎር ደረጃ አቅም በመፍጠር ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ በማድረግ ኤክስፖርት እንዲያደርጉ የድጋፍና ክትትል ስርዓቱ ያልተጠናከረ መሆኑ፣

ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መሰፈርቶችንና ስታንዳርዶችን ያሟሉ መሆናቸውን በተመለከተ፤

412. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጓቸው ምርቶች አለም አቀፍ የምግብ ደህንነት መስፈርቶችን እና ስታንዳርዶችን (የዩሮ ጋፕ፣ ግሎባል ጋፕ፣ አውሮፓ ጋፕ) መሰረት የሚመረቱ መሆኑን ክትትል ሊያደርግ እና በዚህ ረገድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት የሚያደርጉዋቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች የምግብ ደህንነት መስፈርቶችና አለማአቀፋዊ ስታንዳርዶች (ኤምፒኤስ፣ቴስኮ፣ የአውሮፓ ጋፕና ግሎባል ጋፕ) የመሳሰሉትን ቤንች ማርኮች በኤጀንሲው በኩል ለባለሀብቶችም ሆነ ለአውትግሮዎሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ ያለመሰራታቸው፣ በተጨማሪም ለገበያው የሚቀርቡ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከደንበኛው ፍላጎት አንፃር እንዲሁም ከየሀገሩ መመሪያ በተጣጣመ መልኩ የገበያውን መስፍርት/ ስታንዳርዶች የማያሟሉ መሆኑ፣

የምርት ግብዓት በወቅቱና በሚፈለገው መጠን እንዲቀርብ ድጋፍና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

413. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በወቅቱ በሚፈለገው ጥራት፣ መጠንና አይነት እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ ለአትክልትና ፍራፍሬ ግብዓት አቅራቢ የሆነው የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅት(AISE) በዘርፉ የሚፈለገውን የምርት ግብዓት በሚፈለገው መጠን፣ አይነትና ወቅት የማቅረብ ችግር ያለበት መሆኑ፣ በተጨማሪም ኬሚካሎችን እና ግሪንሀውስ ፕላስቲክ የምርት ግብዓቶች የማያስመጣ መሆኑ እንዲሁም የግብዓት አቅራቢ አስመጪዎች በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው እጥረት በተከሰተ ቁጥር እርስ በእርስ በመነጋገር ዋጋ የሚሰቅሉ መሆኑ እና ኤጀንሲው የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ የአገር ውስጥ አቅራቢዎችንና የሚመለከታቸውን በማስተባበር የድጋፍ አሰጣጡ ያልተጠናከረ መሆኑ፣

የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች ዕቅድ እና አፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ፤

414. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች የዕቅድና የአፈፃፀም ክትትል የሚያደርግ መሆኑ እና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን የሚገጥማቸውን ችግሮች በመዳሰስ አፋጣኝ ምላሽ በወቅቱ እንዲያገኙ የሚደረግ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በዘርፉ የሚነሱ ችግሮችን በወቅቱ ከሚመለከተታቸው አካላት ጋር በመሆን አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ የሚደረግበት አሰራር ያልተጠናከረ እና ለዘርፉ ልማት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ለመለየት በየጊዜው የደሰሳ ጥናቶች በማካሄድ መፍትሄ የሚወሰድበት አሰራር ያልተዘረጋ መሆኑ፣

ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥራቱን የጠበቀ እና ተወዳዳሪ ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ማድረጋቸውን እንዲሁም ከአልሚ ባለሀብቶች፣ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶችና ዩኒየኖች የውጪ ንግድ አፈፃፀም መከታተሉን በተመለከተ፤

415. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ላኪ ድርጅቶች የውጪ ንግድ የምርት ሽያጭ የመንግስት ፖሊሲ፣ መመሪያና ደንብን ተከትለው መፈፀማቸውን እንዲሁም ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች በተያዘው እቅድና በተፈጽመው ውል መሰረት መከናወናቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ✓ ባለሀብቶች በየአመቱ ኤክስፖርት የሚያደርጉትን የምርት መጠን ዕቅድ ለኤጀንሲው ቢያሳውቁም እቅዳቸው መሰረት አድርገው ለውጭ ገበያ ማቅረብ ያልቻሉ መሆናቸው፣
- ✓ እንዲሁም በ2003 እና በ2004 ዓ.ም የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ለማድረግ በምርት መጠንና በገቢ ያቀደ ሲሆን አፈፃፀሙ በምርት መጠን ከዕቅድ በላይ ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም በገቢ ክንውኑ ከዕቅዱ ከ50% በታች መሆኑ፣

- በ2003 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 74.3 ሺ ቶን ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 93.01 ሺ ቶን(125 በመቶ) የተከናወነ ቢሆንም የሽያጭ ገቢ ዕቅድ 153 ሚሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዶ 40 ሚሊዮን ዶላር (26.1 በመቶ) ብቻ መከናወኑ፣

- በ2004 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 149.9 ሺ ቶን ኤክስፖርት ለማድረግ ታቅዶ 224.77 ሺ ቶን(149.9 በመቶ) የተከናወነ ቢሆንም የሽያጭ ገቢ ዕቅድ 126.04 ሚሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዶ 53.15 ሚሊዮን ዶላር(42.05 በመቶ) ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣

✓ በ2005 እና በ2006 ዓ.ም የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ለማድረግ በምርት መጠንና በገቢ ያቀደ ሲሆን አፈፃፀሙ በምርት መጠንም በገቢ ክንውኑ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣

- በ2005 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 148.96 ሺ ቶን ክንውን 137.66 ሺ ቶን(92.40 በመቶ) እና በገቢ ዕቅድ 153.11 ሚሊዮን ዶላር ክንውን 49.63 ሚሊዮን ዶላር(32.41 በመቶ)

- በ2006 ዓ.ም በመጠን ዕቅድ 249.54 ሺ ቶን ክንውን 145.11 ሺ ቶን(58.15 በመቶ) እና በገቢ ዕቅድ 158.73 ሚሊዮን ዶላር ክንውን 45.72 ሚሊዮን ዶላር(28.80 በመቶ) መሆኑ፣

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

416. የሆርቲካልቸር ምርት ልማት ኤጀንሲ የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች በተፈፀመው ውል መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁና በወቅቱ የተዘጋጁ መሆናቸውን የሚከታተልበት የሚቆጣጠርበት

እና ድጋፍ የሚያደርግበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ኤክስፖርት አገልግሎት የሚውሉ አገራዊ የፓኬጂንግ ስታንዳርድ (specification and standard) የሌለ መሆኑ እና ኤክስፖርቱ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ማምረት የሚችሉ ሀገራዊ ፋብረካዎች ያልተጠናከሩ መሆናቸው እንዲሁም ወደ ጅቡቲ የሚላከው የአትክልትና ፍራፍሬ አላላክና አስተሻሸግ ጥራት የጎደለው መሆኑ፣

የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣያ፣ የትራንስፖርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶችን እንዲሟሉላቸው ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ፤

417. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣያ፣ የትራንስፖርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶች ከሌሎችም ሀገሮችን ልምድ በማጥናት ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡

- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በኢትዮጲያ አየር መንገድን ከፍተኛ የበረራ ፕሮግራም መዛባት(መዘግየት) የተነሳ ባለሀብቶች የሚልኳቸውን ምርቶች በወቅቱ ለደንበኞቻቸው ስለማይደረስ ተጨማሪ ወጪዎች እና የጥራት ጉድለቶች የሚከሰቱ መሆኑና በተለይም ወደ አፍሪካ አገሮች ምርቶችን ለመላክ የአውሮፕላን በቂ ቦታ ባለመኖሩ ምርቶችን በተፈለገው መጠን ለመላክ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ✓ እንዲሁም በአርባ ምንጭ የምርት ማደራጃና ማቀዝቀዣያ መጋዘን በኢትዮጲያ ባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት ግንባታው እንዲከናወን በ2005 ዓ.ም

ስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም እስካሁን ግንባታው ያልተጀመረ መሆኑ እና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በብዛት የሚመረትባቸው አካባቢዎች (አርቦ ምንጭ፣ ራያቆቦ፣ ምሰራቅ ሀረርጌና ድሬደዋ) የተሟላ የምርት ማደራጃያና ማከማቻ መጋዘን ያለመኖሩ፣

የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ተጠቃሚ መሆናቸውን በተመለከተ፤

418. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ሊያሰራጭ እና በአምራቾች መካከል የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለተጠቃሚዎች ከማድረስ አንፃር የተሰራ ስራ ያለመኖሩ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ያልዘረጋና የገበያ ትስስር ያልተፈጠረ በመሆኑ አምራቾች የገበያ መረጃ የማጣት ችግር ያጋጠማቸው መሆኑ በኦዲቱ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

- ✓ በሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ፍራፍሬን በተለይ የሙዝ ምርትን በተመለከተ የሳውዲ አረቢያ የገበያ ዋጋ፣ የጥራት መረጃ እና የማሸጊያ ፍላጎት የመሳሰሉት መረጃዎች ተሰብስበው እና ከሙዝ አምራቾች ዩኒየንና ኮሜርሺያል የሙዝ አምራቾች ጋር በጋራ በመሆን የሙዝ አቅርቦት ዝርዝር መረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም በሌሎቹ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ የገጠዎችን ሀገራት የጥራት ፍላጎት ደረጃዎችን ለይቶ መረጃዎችን በማጠናቀር ለአምራች ላኪዎች እንዲሰራጭ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ✓ በተጨማሪም ወደ ጅቡቲ ኤክስፖርት የሚደረግበት የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ከአለፉት 32 ዓመታት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በአንድ አይነት የመሸጫ ዋጋ እየተሸጠ የሚገኝ መሆኑ፣ ከጅቡቲ ሌላ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት አማራጭ ገበያ የሌለ መሆኑ በተጨማሪም በድሬደዋ እና በአርባ ምንጭ ያለው የአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ዋጋ ሁኔታ በአካባቢው ያሉ ደላሎች የገበያ ዋጋን እንደፈለጉ የሚጨምሩና የሚቀንሱ በመሆናቸው አምራቹን፣ አርሶ አደሩን ወይም ባለሀብቱን ተጠቃሚ የማያደርግ መሆኑ፣ በአጠቃላይ የተጠኑ የገበያ መዳረሻዎች እና የተዘረጋ የግብይት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡

የሀገሪቱን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚመለከቱ መረጃዎች በዘመናዊ መልክ የሚደራጁበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

419. በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዱ የመረጃ መረብ በመፍጠር የዚህ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊደረግ ይገባል፡፡ በኢንቨስትመንት ረገድ የሚወጡ አዳዲስ ወቅታዊ መመሪያዎችን ባለሀብቶች በወቅቱ እንዲያውቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዳ የመረጃ መረብ (Web Site) ያልተዘረጋ መሆኑ፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው የሚቀያየሩ ቢሆንም ኤጀንሲው በወቅቱ የማስተዋወቅ ስራ የማይሰራ በመሆኑ እና ለባለሀብቶች በወቅቱ ሳይገለፅ በመቅረቱ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤቱ(በተለይ ጉምሩክ ላይ) ሲሄዱ ተቀይሯል በማለት የሚጉላሉ መሆኑ፣

ዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤

420. በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲና ዘርፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ኤጀንሲው የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለሙያዎች የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ በማመቻቸት በጋራ ለልማቱ የሚያግዙ እርምጃዎች የሚወስድበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በመሬት አሰጣጥ፣ በመሰረተ ልማት ማሟላት፣ በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ በአጠቃላይ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ ያለመሆኑ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት በእቅድ የማይመራ መሆኑና ከኦሮሚያ ክልል ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ከሌሎች ክልሎች የተሻለ ቢሆንም መደበኛ የሆነ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ፣ እንዲሁም የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ፣ የሆርቲካልቸር ማህበርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ቋሚ እና መደበኛ መድረክ ያለ ቢሆንም በታቀደው ጊዜ እየተካሄደ ያለመሆኑ፣

የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤትን በተመለከተ፤

421. የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች ሊሰበሰቡ፣ ሊደራጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በምርምር ማእከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ✓ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማእከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች

እንዲጠናከሩ ከማድረግ አንፃር የተሰሩ ስራዎች ስለመኖራቸው መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

የስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ፤

422. የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የስራቴጂክ እቅዱን መሰረተ በማድረግ አመታዊ እቅድ ሊያቅድና አፈፃፀሙ ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች መንስኤዎቻቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በእቅድ ዝግጅት ወቅት ነባራዊ ሁኔታን በትክክል ባገናዘበ መልኩ ሊያቅድ፣ የእቅድ ዝግጅቱን ዋና ፈፃሚውንና ባለሀብቱን አሳታፊ ሊያደርግ እና መድረክ በመፍጠር ሁሉንም ሰራተኞችና ባለሀብቶች እቅድ ላይ በቂ ግንዛቤ(ኦረንቴሽን) ሊሰጥ ይገባል፡፡

- ✓ የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከ2003-2007 ዓ.ም የስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም ከ2003 እስከ 2006 ዓ.ም የተዘጋጀው ዕቅድ የስራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ አለመሆኑ(ሰንጠረዥ 3)፣ የ2003-2006 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም በተለይ በውጪ ንግድ በምርት መጠንም ሆነ በገቢ ከዕቅድ በታች መሆኑ፣ በአፈፃፀም ሪፖርት ላይ በየዓመቱ ተደጋጋሚ ችግሮች የሚገለፁ እና እነዚህን ችግሮች በየበጀት ዓመቱ መንስኤዎቻቸውን በመለየት የመፍትሄ እርምጃ የማይወሰድባቸው መሆኑ፣

የማሻሻይያ ሃሳቦች

- ❖ በኤጀንሲው ሁሉን አቀፍ የድጋፍ ማዕቀፍ የአትክልትና ፍራፍሬን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የድጋፍ አይነቶችን ማለትም በግብዓት አቅርቦት ድጋፍ፣ ከምርምርና መሰል ተቋማት በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተለይ በዘር ፍተሻ ማለማመድና ማባዛትን በተመለከተ፣ በመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ድጋፍን በተመለከተ፣ በብድር አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ

አቅርቦትና ዝውውር ድጋፍን በተመለከተ፣ በትራንስፖርት ዘርፍ ሊኖር ስለሚችል ድጋፍ በተመለከተ፣ የአለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያግዝ የቴክኒክና የስልጠና ድጋፍን እንዲሁም ለዘርፉ የሚያስፈልጉ መረጃዎች አቅርቦት እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በመጓጓዝ ሂደት ለሚያጋጥማቸው አደጋና ብልሽት ሊኖር ስለሚችል የዋስትና አቅርቦት ድጋፍ የመሳሰሉ የድጋፍ ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት ድጋፍ የሚሰጠውን አካል ኃላፊነት፣ ድጋፉ ሊገኝ የሚችልበትን ጊዜ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ ለማግኘት ሊያሟሉ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር በመለየት ከአንድ መስኮት አገልግሎት(One window shopping) መሰረተ ሀሳብን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ የማበረታቻ የድጋፍ ማዕቀፍ በኤጀንሲው ሊዘጋጅና በዘርፉ ሊሰማሩ ለሚችሉ የሀገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች እንዲውቁት ሊደረግ ይገባል፡፡

- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በሁሉም ክልሎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሊሆኑ የሚችሉ መሬቶችን በጥናት በመለየት መሰረታዊ መረጃዎች ለይተው በመያዝ ወደ ልማቱ መግባት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መሬትና የግንባታ ፋቃድ እንዲያገኙ እና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን (ውኃ፣ መብራት፣ ስልክ፣ መንገድ ወዘተ) እንዲሟላላቸው ድጋፍና ክትትል በተጠናከረ መልኩ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ከባለሀብቶች በየጊዜው የሚነሱ ችግሮች ለመፍታት ለሚመለከታቸው አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ከመፃፍ በዘለለ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ እንዲያገኙ ጥረቶች

ተጠናክረው ሊቀጥሉና ኤጀንሲው በቅርበት ሞዴል የሆኑት ባለሀብቶች ከአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል ፡፡

- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መሬት ወስደው ወደ ልማት ያልገቡ፣ በከፊል ያለሙ፣ ምርታቸውን ኤክስፖርት ማድረግ ያልቻሉ፣ ምርታቸውን ከዕቅድ በታች ኤክስፖርት የሚያደርጉ እና ምርታቸውን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርቡ ባለሀብቶችን በየደረጃው ድጋፍና ክትትል በማድረግ ሊሻሻሉ ያልቻሉትን ምክንያት በመለየት እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የኮንትራት አርሶ አደሮችን በማደራጀት እና በስልጠናና በቴክኒክ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በጥራትና በብዛት እንዲያቀርቡ እና ኤክስፖርት ከሚያደርጉ ባለሀብቶች ጋር በማስተሳሰር ወይንም በአውትግሮዎር ዩኒየን ደረጃ ምርታቸውን ኤክስፖርት እንዲያደርጉ የሚደረግበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ኤጀንሲው ዘርፉን የሚደግፍ ቴክኖሎጂዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር በመሰብሰብ፣ ልማቱ ላይ የመሰኖ አጠቃቀም፣ የአግሮኖሚ እንክብካቤ፣ ዝሪያ አመራረጥ፣ ምርት አጠባበቅና፣ ሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂ ፓኬጅ ያካተተ የሙያ ማሻሻያ አውደጥናትና ስልጠና እንዲሁም የአቅም ግንባታ ድጋፎች በተጠናከረ መልኩ መስጠት የሚቻልበት አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸል ልማት ኤጀንሲው በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች አለም አቀፍ መስፈርቶችን እና ስታንዳርዶችን መሰረት አድርገው በማምረት ኤክስፖርት እንዲያደርጉ የድጋፍና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በግብዓት አቅራቢነት የተሰማሩ ኩባንያዎች ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ልማት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በወቅቱ በሚፈለገው ጥራት፣ መጠንና አይነት እንዲቀርቡ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም እጥረት በሚፈጠርበት ወቅት በማስተባበር ችግሩን የሚፈታበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው የአትክልትና ፍራፍሬ አልሚዎች አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በዘርፉ የሚነሱ ችግሮችን በወቅቱ ከሚመለከተታቸው አካላት ጋር በመሆን አፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ የሚደረግበት አሰራር ሊጠናከር እና ለዘርፉ ልማት እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ለመለየት በየጊዜው የደሰሳ ጥናቶች በማካሄድ መፍትሄ የሚወሰድበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ ኤክስፖርት ለማድረግ ወደዘርፉ የገቡ ኩባንያዎች በዕቅዳቸው መሰረት ምርታቸውን በብዛትና በጥራት ኤክስፖርት ማድረግ እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የሚያገለግሉ የምርት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ደረጃ በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ምርት ልማት ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከመጓጓዛቸው በፊት የሚቆዩበት የማቀዝቀዣያ፣ የትራንስፖርትና ሌሎችም የሎጂስቲክስ ፍላጎቶች የሚሟሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እንዲሟላ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ የገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብና ለባለሀብቶች ሊያሰራጭ እና ዋና ዋና ገበያዎችን በማየት

ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያስችል የገበያ መረጃ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲው በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚረዳ የመረጃ መረብ (Web Site) ሊያዘጋጅ፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በየጊዜው እና በወቅቱ ለባለሀብቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሆን እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በመሬት አሰጣጥ፣ በመሰረተ ልማት ማሟላት፣ በግብዓት አቅርቦት ዙሪያ በአጠቃላይ ዘርፉ የሚጠይቀውን አገልግሎት ከማቀላጠፍና ከማሳደግ ረገድ ከሁሉም ክልሎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የተጠናከረ ሊሆን ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ የአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶች፣ በምርምር ማእከላትና በየክልሉ የሚገኙ የቲሹካልቸር ላብራቶሪዎች እንዲጠናከሩ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሆርቲካልቸር ኤጀንሲው ዓመታዊ ዕቅድ ሲያዘጋጅ የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሰረት ሊያደርግና በቅቅድ ዝግጅት ወቅትም በዕቅድ አፈፃፀም ላይ የታዩ ችግሮችን መንስኤዎቻቸውን በመለየት በወቅቱ መፍትሄ የሚያገኙበትን አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

11.18 የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አሰባሰብ፣ አስተዳደርና አከፋፈል

በኤጀንሲው መውጣት ሲገባቸው ያልወጡ መመሪያዎችን በተመለከተ፤

423. ኤጀንሲው በጡረታ ፈንድ አመዘጋገብ፣ አሰባሰብ እና አከፋፈል ተግባር የወጣውን አዋጅና ደንብ ለማስፈፀም መመሪያዎች ሊያወጣና መተግበሩን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ✓ በኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያደርግ አስገዳጅ ህግና የጡረታ መዋጮ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶች ላይ ህጉን ለማስፈጸም የጨረታ ኮሚቴ የሚቋቋምበት የህግ ማዕቀፍ፣ የፈንድ አስተዳደር ማንዋል የሌለ መሆኑ እንዲሁም በኤጀንሲው የሂሣብ አያያዝ ማንዋል በረቂቅ ደረጃ ቢኖርም በሚመለከተው አካል ታይቶና ጸድቆ ከዋናው መ/ቤት በስተቀር በሁሉም ሪጅንና ቅ/ጫ/ፍ/ጽ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን አለመደረጉና ኤጀንሲውን አስተማማኝ የማህበራዊ ዋስትና ተቋም እንዲሆን ለማድረግና የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር ከትሬዠሪ ቦንድ በተጨማሪ አዋጭና አስተማማኝ በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ አለመውጣቱን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና

ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ ያጠናው ጥናት መኖሩን በተመለከተ፣

424. በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛት ትክክለኛነት ለማወቅ በኤጀንሲው ጥናት ተጠንቶ ሊያዝና መረጃው ካላቸው አካላት /ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ./በመውሰድ በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ የሚያስችል በኤጀንሲው የተጠና ጥናት አለመኖሩ ታውቋል፣

ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ መሸፈን ያለባቸው የግል ድርጅቶችና ሠራተኞች እንዲሸፈኑ ማድረጉን በተመለከተ

425. ኤጀንሲው ማንኛውም የግል ድርጅት ከሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም. በኋላ እና ከዛ በፊት የተቋቋመ እና የኘሮቪደንት ፈንድ ያላቋቋመ ወይም አቋቁሞ ተግባራዊ ያላደረገ ድርጅት በጡረታ ዐቅዱ እንዲሸፈን ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ የግል ድርጅቶችን በጡረታ ዐቅዱ ለመሸፈን ከ2003-2007 ዓ.ም. 119,700 የግል-ድርጅቶች ለመመዝገብ በስትራቴጂክ ዕቅድ ቢታቀድም በ2004፣ በ2005 እና በ2006 ዓ.ም. የግል ድርጅቶች የምዝገባ ዕቅድ አፈጻጸም ዝቅተኛ ሲሆን 81,033/68%/ የተመዘገቡ ሲሆን 38,667/32%/ ያልተመዘገቡ መሆናቸው፣

ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች በአዋጁ መሰረት በየወሩ እንዲከፍሉ ማድረጉንና
ለመክፈላቸውም የሚከታተልበትና የሚቆጠርበት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

426. ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅዱ የሚሸፈን የግል ድርጅት አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት ለሰራተኛው በሚከፍለው መደበኛ የወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሰራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደሞዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ እንዲከፍል ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ በኤጀንሲው የግል ድርጅቶች በአዋጁ መሠረት በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያስችል የተዘረጋ ጠንካራ ሥርዓት የሌለ በመሆኑ በናሙና በታዩት በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ሪጅን፣ በደብረማርቆስ፣ በጎንደር፣ በሆሳዕና፣ በአዲስ አበባ በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ ቅ/ጫጽ/ቤቶች እንዲሁም በዋናው መ/ቤት ከ3 ወር እስከ ሁለት አመትና ከሁለት አመት በላይ

የማይከፍሉ ድርጅቶች መኖራቸው፣ በዋናው መ/ቤት ብቻ ከሐምሌ 2003 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 2006 ዓ.ም. ከተለዩት 557 ድርጅቶች ውስጥ 500 የሚሆኑት ከ5 ወር በላይ ያልከፈሉና ከነዚህ ውስጥ 342ቱ ከአመት በላይ ያልከፈሉ ድርጅቶች መኖራቸው፣

- ✓ በጎንደር ወደ 1000 የሚጠጉ የእርሻ ባለሀብቶች የራሳቸውን ድርሻና የሠራተኞቻቸውን ጡረታ መዋጮ ሰብስበው ገቢ የማያደርጉ መሆኑ፣
- ✓ እንዲሁም በሀገሪቱ ባሉ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሥር ያሉ የትራንስፖርት ባለሙያዎች የሥራ ግብር በቁርጥ በአመት አንዴ በመክፈላቸው የጡረታ መዋጮ ማስከፈል አለመቻሉ፣
- ✓ በሁሉም ጽ/ቤቶች ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ክፍያ ያልጀመሩና ጀምረው ያቋረጡ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን፤ 2006 ዓ.ም. በደብረማርቆስ፣ በደብረታቦርና በጎንደር በተከታታይ የጡረታ መዋጮ መክፈል ያልጀመሩ 173፣ 314ና 1053 ድርጅቶች እንዲሁም ጀምረው ያቋረጡ 80፣ 183ና 8 ድርጅቶች፣ በባህር-ዳር ያልከፈሉ 721ና ጀምረው ያቋረጡ 73 ድርጅቶች፣ በሀዋሳ በናሙና ከታዩት 100 ድርጅቶች ውስጥ 24ቱ መክፈል ያልጀመሩ መሆናቸው፣
- ✓ በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ ግብርንም ሆነ የጡረታ መዋጮ የማይከፍሉ የግል ድርጅቶች መኖራቸውና በተጨማሪም በደብረታቦር ከተመዘገቡት ድርጅቶች 90 በመቶና በጐንደር ከ300 በላይ ድርጅቶች የሥራ ግብር ስለማይከፍሉ ማስከፈል አለመቻሉ፣ በሰሜን ምዕራብ ሪጅን /በባህርዳር/ በፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር፣

በጃቢ ጠህናን ዙሪያ ወረዳዎች ቡሬ ከተማ አስተዳደር፣ ቡሬ ዙሪያ ወረዳ፣ ደንበጫ ከተማ አስተደደር፣ ደንበጫ ዙሪያ ወረዳዎች፣ በአዴት ከተማ አስተዳደር፣ በአሆኑም ከተማ አስተዳደር፣ ይልማና ዴንሳ ካሉት 577 ድርጅቶች ውስጥ 320 የሥራ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን ሥራ ግብር ከሚከፍሉት ውስጥ 185 የጡረታ መዋጮ የማይከፍሉ መሆናቸው፣

- ✓ በአዲስ አበባ በየወረዳው ባሉ 116 የገቢ ጽ/ቤቶችና በሪጅንና ቅ/ጫ/ቤቶቹ ያሉ ውክልና የተሰጣቸው የገቢ ጽ/ቤቶች የሥራ ግብር ቢሰበስቡም የጡረታ መዋጮ የማይሰበስቡ መኖራቸው፣ በደብረ ማርቆስ /ሽበል፣ ደብረ ኤሊያስ እና አንዳድ ወረዳዎች/ የገቢ ጽ/ቤቶቹ የሥራ ግብር የሚሰበስቡ ሲሆን የጡረታ መዋጮ የማይሰበስቡ መሆናቸው፣

- ✓ የግል ድርጅቶች አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያስችል ጠንካራ የክትትል ሥርዓት ባለመኖሩ፤ ከሰራተኛው ደመወዝ እየቆረጡ ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉ የግል ድርጅቶች መኖራቸው/በሀዋሳ ብሉ ናይልና በባህርዳር ሳትኮን ኮንስትራክሽ/፣ እንዲሁም መክፈል የሚገባቸውን የጡረታ መዋጮ ሳይከፍሉ ሥራቸውን ኮንትራታቸውን ጨርሰው የሚወጡ የግል ድርጅቶች መኖራቸው /በጎንደር ገምሹ በየነና አዘዞ ጎርጎራ መንገድ ኮንስትራክሽን ድርጅት ሰኔ/2003-ሰኔ/2006 ዓ.ም. ለሦስት አመት ሰርቶ ኮንትራቱን የጨረሰ፣ በባህርዳር ኤምቢ ኮንስትራክሽን የተባሉ ድርጅቶች ይገኙበታል/፣ታውቋል፡

፡

የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ሂሳብ በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ

አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን በተመለከተ፣

427. የጡረታ መዋጮ ገቢን ለመሰብሰብ በኤጀንሲው የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የጡረታ መዋጮ ገቢ ከተደረገበት ልዩ ባንክ ሂሳብ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያ ሦስት የሥራ ቀን ለጡረታ ፈንድ ሂሳብ በትክክል ገቢ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

- ✓ አዲስ አበባ ባሉ ውክልና የተሰጣቸው የገቢ ጽ/ቤቶች የተሰበሰበው የጡረታ መዋጮ ውስጥ በየወሩ ገቢ የማይሆኑ ሂሳቦች እንዳሉና በአመቱም መጨረሻ ብዙ ሂሳቦች ወደ ቀጣይ አመት እንዲዞሩ የሚደረጉ ሲሆን እንዲሁም በኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላት በአዋጁ መሰረት በትክክል ገቢ ስለማድረጋቸው የተዘረጋ የክትትል ሥርዓት ቢኖርም ክትትሉ ክፍተት ያለው በመሆኑ የጡረታ መዋጮ ሂሳቦች ወደ ሌላ አካውንት የሚገቡ መሆኑ፡-

- ➢ በ2004 በጀት ዓመት በአዲስ አበባ ውክልና የተሰጣቸው የገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤቶች የተሰበሰበ የጡረታ መዋጮ ሂሳብ ከነሐሴ 2003 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 2004 ዓ.ም. ከከፍተኛ ግብር ከፋዮች ብር 2,036,110.72፣ ከምዕራብ ቅርንጫፍ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 3,260.38ና ከምሥራቅ ቅርንጫፍ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 663,141.19 በጠቅላላ ብር 3,714,478.71፣

- ➢ በ2004 ዓ.ም. የመስከረም፣ ጥቅምትና ታህሳስ ወር በአማራ ገቢዎች ባለሥልጣን በኩል የተሰበሰበ የሐይላንድ ኮሌጅ የጡረታ መዋጮ ሂሳብ ብር 3,441.60፣ ከሣሊኒ ኮንስትራክሽን ሠራተኞች የተሰበሰበ የጡረታ መዋጮ ሂሳብ ብር 336,361.23፣ በትግራይ ክልል የተሰበሰበ ብር 3,954.67ና በግንቦት 2004 ዓ.ም ከጋምቤላ ቅርንጫፍ

የተሰበሰበብር ብር 29,449.31፣ ከ3/5/04 እስከ 22/3/05 ዓ.ም የተሰበሰበ ብር 150 ሚሊዮን ብር እና፣

- በ2006 በጀት ዓመት በሚያዚያ ወር የተሰበሰበ ብር 703,849.99፣ በግንቦት ወር ከሰሜን ምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት የተሰበሰበ ብር 1,019,787.77ና በሰኔ ወር ከተለያዩ የግል ድርጅቶች የተሰበሰበ ብር 1,707,088.08፣ በ7/6/2006 ከተለያዩ ሪጅኖችና ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰበሰ ብር 377,982.04፣ በጥር 2006 ዓ.ምና ከሲጂሲ ኦቨርኤስ ኮንስትራክሽን የተሰበሰበ ብር 17,265.28 እና ብር 4,917.84 በስህተት ወደ መንግሥት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የገባ መሆኑ፣
- በ25/07/2004 ዓ.ም የኤጀንሲው ብር 30,394.35 ገንዘብ ወደ ትግራይ ብ/ክ/መ/ገቢዎች ልማት ኤጀንሲ መግባቱ፣
- በ2005 በጀት ዓመት የኤጀንሲው ብር 15,669,113.23 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ አካውንት የገባ ሲሆን፣ ከኤጀንሲው አካውንት ወደ ሌላ አካውንት የገባ ሂሳብ ተመልሶ ወደ ኤጀንሲው አካውንት ለመግባት ከአራት ወር እስከ አንድ አመትና ከዛም በላይ መውሰዱና እንዲሁም ወደ መንግሥት ማህበራዊ ዋስትና ከገባውና በ7/6/2006 ዓ.ም. ከተለያዩ ሪጅኖችና ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰበሰ ብር 377,982.04ና ከነቀምቴና ከበደሌ የመንገድ ሥራ ኮንስትራክሽን ድርጅት በ21/01/2014 የገባ ብር 7,265.29 እና 4,917.84 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጥር 2007 ዓ.ም. አለመመለሱ፣
- ከኤጀንሲው አካውንት ወደ ሌላ አካውንት የገቡ ብሮች ተመልሰው ወደ ኤጀንሲው ለመግባት የአንድ አመት ጊዜ መውሰዱና ችግሩ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መፈታት አለመቻሉ ለማወቅ ተችሏል፣

- ✓ ወደ ኤጀንሲው የገቡ ገንዘቦች ካለ ኤጀንሲው ዕውቅና ከዝግ አካውንት ማውጣት የማይቻል ቢሆንም አስገቢው መ/ቤት ስለጠየቀ ብቻ መውጣቱ፣

- ➢ ከጅማ መብራት ኃይል በመስከረም 2006 ዓ.ም ብር 194,455.43 ሳንቲም ገንዘቡን የሊሙ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢ ያደረገው ነው ቢልም ባንኩ ከኤጀንሲው ዕውቅና ውጭ አውጥቶ ተመላሽ ማድረጉ፣
- ➢ ከምዕራብ አነስተኛ ግብር ከፋዮች በተለያየ ጊዜያት ከ2004 ዓ.ም. እስከ 2005 ዓ.ም. ገቢ የተደረገ ብር 1,323,746.61 በሚያዚያ 3/2006 ዓ.ም. ከቅ/ጽ/ቤቱ ያለ ኤጀንሲው ዕውቅና ወጪ ተደርጎ ለገቢ ሰብሳቢው መመለሱ፣

- ➢ ከማይጨው ቅ/ን/ባንክ 53,529.78 ብር ወደ አዲስ አበባ ንግድ ባንክ ከተላለፈ በኋላ እንደገና ተመላሽ መደረጉ፣ በጎንደርም እንደዚሁ በተደጋጋሚ በተለያየ ወር ከኤጀንሲው እውቅና ውጭ እየወጣ መሆኑና በነሐሴ ወር በአንድ ጊዜ እስከ 70 ሺህ ብር፣ እንዲሁም በመስከረም ወር ብቻ ከ11 ጊዜ በላይ የወጣ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፣

- ✓ በተጨማሪም በትክክል የማን እንደሆኑ የማይታወቁና የማን እንደሆኑ እስኪጣሩ ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ሂሳቦች ያሉና ከተሰበሰበው በብልጫ ባንክ የሚገቡ ሂሳቦች ቢኖሩም የሂሳቦች ምንነት በዝርዝር አለመታዋቅና እስኪታወቅ ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆኑ፡-

- ➢ በምሥራቅ ሪጅን ጽ/ቤት ከሐምሌ እስከ መጋቢት 2006 ዓ.ም. የተሰበሰበ ብር 1,642,780.75 እስከ 28/01/07 /6 ወር/ የማን እንደሆኑ አለመታወቃቸው፣

- ➢ በአዲስ አበባ ባሉ የክፍለ ከተማ ገቢ ጽ/ቤቶች ከሐምሌ/2005-ህዳር/2006 የተሰበሰበና ገቢዎች ሪፖርት

ያደረገው ብር 96,908,029.93 ሲሆን የአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ 100,329,016.93 ሪፖርት ማድረጋቸውና በብልጫ 3,420,986.99 ቢኖርም እስከ ጥር ወር /2 ወር/ የማን እንደሆነ አለመታወቁ፣

- የ2005 ዓ.ም. ከገቢ ጽ/ቤቶች የተሰበሰበ የጡረታ መዋጮ በብልጫ የአዲስ ከተማ ብር 1,389,297.17፣ የቦሌ ብር 2,564,966.12፣ የአቃቂ ቃሊቲ ብር 400,658.84፣ ኮልፌ ቀራንዮ ብር 533,978.22፣ መርካቶ ቁ.1 ብር 338,944.36 በጠቅላላ ብር 5,227,844.78 ገቢ የተደረገ ቢሆንም እስከ 16/05/06 /7 ወር/የማን እንደሆነ አለመታወቁ፣

- ✓ እንዲሁም ከኤጀንሲው በተገኘ መረጃ ከሌላ መ/ቤት ወደ ኤጀንሲው ገቢ የሆኑ ሂሳቦችና ባንኮች ከኤጀንሲው አካውንት ገንዘብ ሲያወጡ በኤጀንሲው ሳይታወቅ እስከ ስድስት ወር የሚቆዩ ሂሳቦች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኤጀንሲውም በውሉ መሰረት እየሰሩና በትክክል ገቢ ማድረጋቸውን መከታተሉን በተመለከተ፣

428. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ሰብሳቢና የጡረታ አበል ከፋይ ተቋማት ጋር በተደረገው የውል ስምምነት መሠረት ውሉን እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ሊከታተል እና ችግሮች ሲኖሩ በአፋጣኝ ማስተካከያዎች ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ ኤጀንሲው ከገቢ ሰብሳቢ አካላት ጋር በተዋዋለው ውል አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ላይ ውክልና የተሰጠው ገቢ ሰብሳቢ አካል የጡረታውን መዋጮ ሂሳብ ይሰበስባል ቢልም በሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤቶች ባሉ የገቢ ሰብሳቢ ጽ/ቤቶች እንዲሁም አዲስ አበባ ባሉ የወረዳ ገቢ ጽ/ቤቶች ገቢ መሰብሰብ

ሲገባቸው የማይሰበስቡና የግል-ድርጅቶቹ ራሳቸው የጡረታ መዋጮ ሂሳባቸውን በቀጥታ ወደ ባንክ የሚያስገቡ መሆኑ፣

- ✓ በውሉ አንቀጽ 8 ቁጥር 5 ላይ ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ጽ/ቤቶች ወደ ጡረታ ፈንድ ገቢ የተደረገውን የጡረታ መዋጮ ዝርዝር መግለጫ በማዘጋጀት ከባንክ ስቴትመንትና ዴቢት አድቫይስ ጋር የገቢ መረጃዎችን ሰብስቦና አደራጅቶ ይልካል ቢልም የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓቱ ወጥ ያልሆነና /በደቡብ ሪጅንና በሰሜን ምዕራብ ሪጅን ጽ/ቤቶች በራሳቸውና በገቢ ጽ/ቤቶቹም በሁለቱም ሲሰበሰብ በአዲስ አበባ ደግሞ በገቢ ጽ/ቤቶቹ ብቻ መሰብሰቡ/ እንዲሁም ውክልና በተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበው መረጃ የገቢ ጽ/ቤቶቹ ለስራው ትኩረት ስለማይሰጡ መረጃዎችን በአግባቡ ሰብስበውና አደራጅተው የማይዙና ለኤጀንሲው የማያስተላልፉ መሆኑ፣

- ✓ በውሉ አንቀጽ 8 ቁጥር 6 ላይ የገቢ ግብር በትክክል ስለመሰብሰቡ የሒሳብ ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ ለግል ድርጅቱ ሠራተኞች ወይም ለግለሰቡ በተከፈለው ደመወዝ መጠን ተገቢው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ስለመደረጉ ይመረምራል ያጣራል ቢልም በአዲስ አበባም ሆነ በክልል ባሉ ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶቹ ውክልና የተሰጣቸው የገቢ ጽ/ቤቶች ለግል ድርጅቱ ሠራተኞች ወይም ለግለሰቡ በተከፈለው ደመወዝ መጠን ተገቢው የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ስለመደረጉ የሒሳብ ምርመራ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኤጀንሲው ለገንዘብ ትልፈልፍ የአሠራር ሥርዓት መዘረጋቱን በተመለከተ፤

429. ኤጀንሲው ከገቢ ሰብሳቢዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ትልፍልፍን በተመለከተ የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ✓ በ29/08/05 የተላለፈ መመሪያ በወሩ መጀመሪያ እስከ 15ኛው ቀን የተሰበሰበውን በ16ኛው ቀን እና ከ16-30ኛው ቀን የተሰበሰበው በሚቀጥለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንድ መቶ ብር ብቻ በባንኩ ቀሪ ሆኖ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወዳለው የኤጀንሲው የባንክ ሂሣብ ቁጥር እንዲተላለፍ ለባንኮች መመሪያ ቢወርድም እየተተገበረ አለመሆና ወደ ብሔራዊ ባንክ ተላልፈው ነገር ግን ብሔራዊ ባንክ ሳይገቡ እስከ 8 ወር የሚቆይ ገንዘብ መኖሩ እንዲሁም ከገቢዎችም ሆነ ከንግድ ባንክ እስከ 1 አመት ሳይተላለፉ የቆዩ ገንዘቦች መኖራቸው ፤

- ✓ ለአብነት ያህል በወልቂጤ ወልቂጤ ንግድ ባንክ/ቅ በ3/13/04 ብር 889,802.14 ወደ ብሔራዊ ባንክ ተላልፎ እስከ 24/12/05 ድረስ አንድ አመት፣ ወላይታ ንግድ ባንክ በ30/06/05 ብር 261,861.25 ወደ ብሔራዊ ባንክ ተላልፎ እስከ 30/03/06 9 ወር ብሔራዊ ባንክ አለመግባቱ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ ሪጅን በተከታትይ በሐምሌ 2005፣ በነሐሴ 2005፣ በመስከረም 2006ና በጥቅምት 2006 ዓ.ም. ብር1,907,512.43፣ 2,837,096.45፣ 4,153,194.87ና 3,702,891.44 ገንዘቡ መሰብሰቡ ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም ንግድ ባንኩ እስከ 25/03/06 ከ5 ወር እስከ 1 አመት አለማስተላለፉና በ10 ክልሎች ከሐምሌ 2003 እስከ ሰኔ/2004 ዓ.ም. አመቱን ሙሉ የተሰበሰበ ብር

146,793,837.41 ውስጥ ብር 18,594,612.215 እስከ 19/03/06 ድረስ ያልተላለፈ መሆኑ ታውቋል፡፡

ኤጀንሲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ማውጣቱን በተመለከተ፤

430. ኤጀንሲው ለጡረታ ዕቅድ ምዝገባ፣ የጡረታ መዋጮ አሰባሰብ እና አበል መወሰንና የክፍያ አፈፃፀም አገልግሎቶች አሰጣጥ ስታንዳርድ አውጥቶ ሊተገብር ይገባል፡፡

- ✓ በዋናው መ/ቤትም ሆነ በኤጀንሲው የአበል ውሳኔን አስመልክቶ የዜጐች ቻርተር ላይ ስለአበል ውሳኔው የተቀመጠ ነገር የሌለ ሲሆን በባላንስ ስኮር ኮርድ ላይ ጡረታ የሚወጣ አንድ የግል ድርጅት ሰራተኛ በአንድ ወር ውስጥ የአበል ውሳኔ ማግኘት አለበት ቢልም የአበል ውሳኔዎች እስከ 3 ወር የሚዘገዩበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኤጀንሲው ግዴታቸውን በማይወጡ የግል ድርጅቶች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና ህጋዊ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ

431. ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ፣ መረጃ በማይሰጡ እና በወቅቱ በማይከፍሉ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ስርአት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ በናሙና በታዩት በሰሜን ምዕራብና በደቡብ ሪጅን፣ በአዲስ አበባ በሰሜን፣ በምዕራብና በደቡብ ሪጅን ያልከፈሉ ድርጅቶች መረጃዎች ተለይተው አለመያዛቸው፣ በዋናው መ/ቤት መረጃው ቢኖርም ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል ምልኩ ምን ያህል እንዳለባቸውና ከመቼ እስከመቼ መሆኑን ጥርት ባለ መልኩ የማያሳይ መሆኑና

በዚህም የተነሳ የግል ድርጅቶች ውዝፍ መዋጮ እንዲከፍሉ የተደረገ መሆኑ፣ /በዋናው መ/ቤት የአስመላሽና ልጆቹ ኃ.ላ.የተ.የግ ማህበር ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ብር 3,000,000.00፣ በደብረማርቆስ ሲጂሲ ብር ከሐምሌ/03-ጥቅምት/05 ብር1,412,347.00 እንዲከፍሉ መሆኑ/፣

- ✓ በዋናው መ/ቤት ትክክለኛ መረጃዎች ተለይተው በጥራት ለህግ ክፍል ባለመድረሳቸውን በርታ ኮንስትራክሽን ከሐምሌ 2003-ነሐሴ 2004 ዓ.ም. ብር 493,756.14 የከፈለ ቢሆንም መረጃው ለህግ ክፍሉ ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ እንዳለበት ተደርጐ መተላለፉ፣ በቀለ ሞላ ሆቴል ያለበትን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ መስከረም ላይ የከፈለና ለሚመለከተው አካል ያሳወቀ ቢሆንም በታህሳስ 2007 ዓ.ም ወር ላይ በህግ ክፍሉ አካውንቱ እንዲዘጋ መድረጉ፣

- ✓ በዋናው መ/ቤት ከሐምሌ/2003 እስከ ሚያዝያ 2006 ከአመት በላይ ያልከፈሉ ከ300 በላይ የሚሆኑ የግል ድርጅች እንዳሉ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም እርምጃ የተወሰደባቸው በ2006 ዓ.ም 10 ድርጅቶች ብቻ ላይ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ እስከ 3 አመት ቆይተው የተወሰደባቸው መኖራቸው፣ /ኤ.ቢ.ሲ ሴክሪውቲና የሰው ኃይል አገልግሎት ኃ.የተ.የግ.ማህበር ከሐምሌ/03 እስከ ሐምሌ 30/05 ብር 1,401,718.63 1 ያልከፈለ ቢሆንም 8/12/06 3 አመትና ዱበደብረማርቆስ የሲጂሲ ኦሲ ሐምሌ/2003 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/05 ውዝፍ ብር 1,377,197.11 መስከረም01/2006 ሁለት አመት ቆይቶ እርምጃ መወሰዱ/

- ✓ በሆሳዕና አስቴር መንግሥቴ ጠ/ስ/ተቋራጭ ሐምሌ/2003 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/05 ብር 417,444.34 ውዝፍ ያለበት ቢሆንም እስከ 18/02/06 ድረስ 2 አመት ቆይቶ

ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ክፍያውን አለመፈጸሙ፣

- ✓ በሰሜን አዲስ አበባ ቅ/ጫ/ጽ/ቤት የጡረታ መዋጮ ያልከፈሉት ላይ መረጃው ተለይቶ ስላልደረሳቸው እርምጃ አለመውሰዳቸው፣ በምዕራብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እርምጃ የወሰዱበት ድርጅት እስካሁን አለመኖሩ፣

- ✓ በጎንደር እና በሆሳዕና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የህግ ክፍል ባለሙያ ባለመኖሩ ወደ ህግ የሚሄዱ ጉዳዮች ቢኖሩም መውሰድ አለመቻላቸው፣

- ✓ በሀዋሳ ፣ ደብረማርቆስ እና በአዲስ አበባ ፍትህ አካላት ግዴታቸውን ባልተወጡ የግል-ድርጅቶችን አፋጣኝ ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የግንዛቤው እጥረት መኖሩ፣

- ✓ መዋጮ ያለባቸው ድርጅቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በአሁን ሰዓት ባንክ አካውንት ቁጥር መመዝገብ ቢጀመርም ከዚህ በፊት ድርጅቶች ሲመዘገቡ ባንክ አካውንት ባለመያዙ /ቅጹ ላይ ባለመኖሩ/ የአካውንት ቁጥራቸውን ሲጠየቁ መልስ የማይሰጡ ወይም የውሸት አካውንት በመስጠታቸው አካውንት ቁጥራቸውን ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑና የባንክ አካውንት ቢገኝም ካለባቸው ውዝፍ እዳ በጣም ያነሰ ብር በአካውንታቸው የሚገኝባቸው የግል-ድርጅቶች በመኖራቸው እርምጃ ለመውሰድ አለመቻሉ፣

- ✓ ያለባቸውን ዕዳ በማይከፍሉት ላይ ወደ ቀጣይ እርምጃ ለመሄድ ማለትም ንብረት ይዞ ለመሸጥ የተዘረጋ አሰራር ወይም ምቹ ሁኔታ የሌለ ሲሆን እንዲሁም የጨረታ ኮሚቴ የሚቋቋምበት የህግ ማዕቀፍ እና ንብረት ለመያዝ ንብረት

ማቆያ ቦታ ባለመኖሩና /መኪና ማስቀመጫ አለመኖሩ/ በአፈፃፀም ላይ ችግር የፈጠረ መሆኑ ታውቋል፣

ኤጀንሲው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የጡረታ መዋጮ ገቢ ማቀዱንና አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤

432. ኤጀንሲው የግል ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና የሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በቀጣይ አመት መሰብሰብ ያለበትን የጡረታ መዋጮ ገቢ አቅዶ በዕቅዱ መሠረት ሊተገብርና የተሰብሳቢና የተከፋይ ሰነዶችን፣ ከኢንቨስትመንት የተገኘ ገቢ (ትርፍ) እና የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴን በመከታተል የኤጀንሲውን አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያሳይ የሂሳብ ትንታኔ መዘጋጀት እና መግለጫ ሊቀርብ ይገባል፡፡

- ✓ ኤጀንሲው በአገር አቀፍ ደረጃ ከግል ድርጅቶች እና ሰራተኞች መሰብሰብ የሚገባውን የማህበራዊ ዋስትና የጡረታ መዋጮን በተመለከተ በእስትራቴጂክ እቅዱ ያካተተ እና ለፈጻሚ አካላት ያወረደ ቢሆንም በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገነዘበ ሳይሆን በግምት/ይህን ያህል የግል ድርጅቶች ብንመዘግብ ይህን ያህል እንሰበስባለን በሚል እና የግል ድርጅቶችም ሆነ የሠራተኛው የጡረታ መዋጮው ድርሻ በየዓመቱ ስለሚጨምር ይጨምራል በሚል /መነሻ ብቻ መሆኑና የኤጀንሲውን አጠቃላይ የጡረታ ፈንድ አቋም የሚያ ሳይ የሂሳብ ትንታኔ በኤጀንሲው አለመዘጋጀቱ፣

ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ኢንቨስትመንቶች ላይ በመሰማራት ፈንዱን ማዳበሩን በተመለከተ፤

433. ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጦ ሊሰበስብና የጡረታ መዋጮ ገቢ ፈንድን ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ዘላቂና አስተማማኝ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ በመሰማራት ፈንዱን ሊያዳብር ይገባል፣

- ✓ ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢ ፈንድን በትሬዥሪ ቦንድ ሽያጭ ላይ ብቻ የሚያውልና ተጨማሪ ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ዘላቂና አስተማማኝ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ አለመሰማራቱ፤ ኤጀንሲው የጡረታ አዋጁ አንቀጽ 13 ቁጥር 1/ለ/ ላይ ለትሬዥሪ ቦንድ መግዣና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰኑ ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች ያውላል ቢልም እየዋለ ያለው በትሬዥሪ ቦንድ ሽያጭ ላይ ብቻ መሆኑ፣ በተጨማሪም ለትሬዥሪ ቦንድ ግዢ እያዋለው ያለው ገንዘብ በወቅቱ ተሰብስቦ ወደ ብሔራዊ ባንክ ባለመግባቱ ማግኘት የሚገባውን ትርፍ ማግኘት አለመቻሉ፣

ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ፈፃሚ አካላትንና ባለድርሻ አካላትን ማሳተፉን በተመለከተ፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት ስልጠና መስጠቱን እንዲሁም በኤጀንሲው የሚሰጡ አገልግሎቶችን በመገምገም ግብረ መልስና ሙያዊ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፤

434. ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ የሪጅን፣ የቅ/ጽ/ቤቶችንና ባለድርሻ አካላትን ሊያሳትፍ፣ የተቋማቱን አቅም ለማጐልበት የፍላጎት ጥናት በማድረግ ስልጠና ሊሰጥ እንዲሁም በሪጅንና በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑና የሚሰጡ አገልግሎቶችን አፈፃፀም

ሊገመግምና በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስና ሙያዊ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፣

- ✓ ኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ እና አመታዊ ዕቅድ ሲያቅድ ሪጅን ቅ/ጽ/ቤቶችን ያላሳተፈ ሲሆን እንዲሁም ሪጅንና ቅርጫፍ ጽ/ቤቶች ሲከፈቱ ክለሳ ያላደረገ መሆኑ፣ ሪጅኖች፣ ክልልሎችና የአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ለኤጀንሲው በሚልኩት ሪፖርት መነሻነት ከሚደረገው ግምገማ በስተቀር ወጥ በሆነ መልኩ በዕቅድ ይዞ ክትትል በማድረግና ክፍተቶችን በመለየት ግብረ መልስም ሆነ ድጋፍ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ✓ ኤጀንሲው ውክልና ለሰጣቸው የገቢ ጽ/ቤቶችም ሆነ ለፈፃሚ አካላት የፍላጎት ጥናት በማድረግ አስፈላጊውን ስልጠና የማይሰጥና አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞችም ምንም አይነት ስልጠና ሳይሰጥ ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚደረግ መሆኑ በአዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኤጀንሲው አገልግሎቶቹን በተጠናከረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

435. ኤጀንሲው አገልግሎቶቹን በቅልጥፍናና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርአት መኖሩንና በሁሉም ሪጅኖችና ቅ/ፅ/ቤቶች ተሟልተው ጥቅም ላይ መዋሉን እንዲሁም ከጽ/ቤቶቹና ከተገልጋዮች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት (ድረ-ገጽ፣ ኢ-ሜል) ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ✓ በኤጀንሲው ጅምር ሥራ ቢኖርም በኤጀንሲ ጠንካራ የሆነ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ባለመኖሩ በጡረታ መዋጮ ምዝገባና አሰባስብ ሥራ እንዲሁም የመረጃ ልውውጡ ቀልጣፋ እንዳይሆን ማድረጉን ታውቋል፡

ኤጀንሲው ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱንና በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ መደበኛ የውይይት መድረክ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

436. ኤጀንሲው ለግል ድርጅቶችና ሠራተኞች እንዲሁም በኤጀንሲው ውክልና ለተሰጣቸው የጡረታ መዋጮ ገቢ ሰብሳቢና ከፋይ ተቋማት በጡረታ ዕቅዱ እንዲሸፈኑ በጠቀሜታው ላይ እና የጡረታ መዋጮን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦች፣ አዋጆችና መመሪያዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ፣ ስለተግባራዊነታቸውም ሊከታተልና በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ችግሮች ለይቶ የሚፈታበት ወጥ የሆነ የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

- ✓ ኤጀንሲው ለተገልጋዮችና ለባድርሻ አካላትና እንዲሁም ለግል ድርጅቶች የሰው ኃይል መልቀቅ እንደመኖሩና አዲስ ድርጅቶች እንደመከፈታቸው በተከታታይና ወጥ በሆነ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ያልሰጠ መሆኑ ፣
- ✓ እንዲሁም በኤጀንሲው በ2006 ዓ.ም. የግንዛቤ ማስበጫ ለመስጠት የሚያስችል የተመደበ በጀት አለመኖሩ፣
- ✓ በዋናው መ/ቤት ውክልና ከተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላት ፣ በሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶች ውክልና ከተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ አካላትና የፍትህ አካላት ጋር በየጊዜው በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ ለመወያየትና መፍትሔ ለማስቀመጥ ወጥ በሆነ መልኩ በመደበኛነት የሚዘጋጅ የውይይት መድረክ አለመኖሩ ታውቋል፣

የማሻሻያ ሃሳቦች

- የግል ድርጅቶች እና ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ መዋጮ ምዝገባን፣ ገቢ አሰባሰብ እና የአከፋፈል ሥርዓት ብቃትያለውና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤
- በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ በማህበራዊ ዋስትና የጡረታ ባለመብት የግል ድርጅቶችና ሰራተኞች ብዛት ለማወቅ በአዲስ አበባም ሆነ በክልሎች በክልላቸው ባለው ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት እንዲያጠኑ ወይም አንድ ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ክልል ድረስ ወርዶ እንዲያጠና በማድረግ መረጃ ሊኖረውና ዕቅድ ሲያቅድ መረጃውን መነሻ በማድረግ ሊያቅድ እንዲሁም በየጊዜው መረጃው ካላቸው አካላት /ከኢንቨስትመንት፣ ከንግድ ኢንዱስትሪ/ ኤጀንሲው መረጃ በማምጣት ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በጡረታ ዐቅድ መሸፈን ያለባቸውን ሠራተኞችና የግል ድርጅቶች የተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶችን በማዘጋጀት የጡረታ መዋጮ ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤው ሊሰጥና የሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤቶችን አቅም በማሳደግ የግል-ድርጅቶቹ በራሳቸው ተነሳሽነት በዐቅዱ እንዲሸፈኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የግል ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ በየወሩ እንዲከፍሉ የሚያስችል አስገዳጅ ህግ ሊያወጣና በትክክል በአዋጁ መሠረት ስለመክፈላቸው እስከ ወረዳ ድረስ የሚወርድ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በውል መሠረት ገቢውን እንዲሰበስቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር /የጡረታ መዋጮው መሰብሰቢያ ሶፍትዌር እንዲኖራቸው በማድረግ እንዲሰበስቡ ሊያደርግና በትክክል በየወሩ ገቢ ስለመሆናቸው ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት

ሊዘረጋና ከመንግሥትና ማህበራዊ ዋስትና ጋር ያለውን የአካውንት መደበላለቅ ችግር በመነጋገር በጋራ ሊፈታ ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ገንዘብ ትልልፉን አስመልክቶ ከባንኮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር በየጊዜው በመነጋገርና በመከታተል ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- አበል ውሳኔ በተመለከተ ከመንግሥት ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መምጣት ያለባቸው የጡረታ ጊዜያቸው የደረሱ ሰራተኞችን መረጃ አስቀድሞ በመለየትና በማምጣት እንዲሁም ከወዲሁ ለጡረታ አስፈላጊ የሆኑና በግል ድርጅቶች/አሰሪዎች ያልተሟሉ መረጃዎችን በማሟላትና ሪጅንና ቅ/ጫ/ጽ/ቤቶች ጋር ኔትወርክድ የሆነ አሠራር በመዘርጋትና አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በቀላሉ እንዲለዋወጡ በማድረግ በወቅቱ ሊወስን ይገባል፡፡
- የጡረታ መዋጮ በወቅቱ በማይከፍሉ፣ የሂሳብ መዝገብ በማይዙ እና መረጃ በማይሰጡ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ መረጃዎችን በመለየት በወቅቱ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

❖ ጡረታ መዋጮ ፈንዱን ለማዳበር የጡረታ መዋጮውን አሟጦ በመሰብሰብ ትርፋማ እና ውጤታማ በሆኑ ኢቨንስትመንት ላይ ለማዋል በጥናት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ መታቀዱንና በታቀደው መሠረት መተግበሩን በተመለከተ፤

- ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢን ሲያቅድ በተጨባጭ በከተሞችንና በሪጅን ደረጃ ያሉ የግል-ድርጅቶችን የደመወዝ መረጃዎችን በመሰብሰብና ጥናት በመጥናትና ጥናቱን መሠረት በማድረግ ሊያቅድ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የጡረታ ፈንዱን ለማዳበር መሰብሰብ የሚገባውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ አሟጦ ሊሰበስብና የጡረታ መዋጮ ገቢ ፈንድን ትርፋማነታቸው በተረጋገጠ ዘላቂና አስተማማኝ በሆኑ

የሥራ መስኮች ላይ ለመሰማራት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴ መመሪያ ሊወጣና ሊተገበር ይገባል፡፡

- ❖ ኤጀንሲው ከሪጅንና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፣ ከተገልጋዮች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሠራር መኖሩን፣ የተደራጀ እና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ እንዲሁም ጠንካራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፤
- ➢ ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶችን ሊያሳትፍ እንዲሁም ወጥ በሆነ መልኩ በእቅድ ይዞ ክትትል በማድረግና ክፍተቶችን በመለየት ግብረ መልስም ሆነ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ➢ ኤጀንሲው ዕቅድ ሲያቅድ ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶችን ባይኖሩም ሪጅንና ቅ/ጽ/ቤቶቹ ከተቋቋሙ በኋላ በማሳታፍ ክለሳ ሊያደርግ፣ ለወደፊቱም እነሱን በማሳተፍ አቅማቸውን በማገናዘብና እንደ ክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ የሚሰጡ አስተያየቶችን መሰረት ማስተካከያ በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡
- ➢ ኤጀሲው ዕቅድ በመያዝ ወጥ በሆነ መልኩ የፈፃሚ አካላትን ሥራ ሊከታተልና በተገኙ ክፍተቶች ላይ ግብረ መልስ በመስጠት ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ➢ ኤጀንሲው በሪጅንና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላሉ ሠራተኞች እንዲሁም ውክልና የተሰጣቸው ገቢ ሰብሳቢ ተቋማትን ያለባቸውን ክፍተት በመለየትና የፍላጎት ጥናት በማድረግ በተደራጀ መልኩ ሞጁልና ማንዋልን መሠረት ያደረገ ስልጠና ሊሰጥና አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞችም የጡረታ ምዝገባ አሰባሰብ አዲስ እንደመሆኑ እንዲያው ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ➢ ኤጀንሲው ተገልጋዩች፣ ባለድርሻ አካላትና ፈጻሚ አካላት የጡረታ አዋጆች መመያዎችና ደንቦችን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ፣

የጡረታ አመዘጋገቡና አሰባሰቡ ቀልጣፋ እንዲሆን የኢንፎሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው ተገልጋዩች፣ ባለድርሻ አካላትና ፈጻሚ አካላት ስለ ጡረታ አዋጁ ጠቀሜታና በወጡ ጡረታ አዋጆች መመሪያዎችና ደንቦችን እንዲያውቁትና እንዲተገብሩት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም /በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት፣ የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም.../ በየአመቱ ግንዛቤ ሊሰጥ ይገባል፡፡

12. ልዩ ኦዲት

በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍ/ቤቶች ትህዛዝ ፣ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ እንደዚሁም በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 6 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውኖ ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡ በዚህም ምክንያት በመደበኛው የኦዲት ሥራ ላይ ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮብን አልፏል፡፡. የተከናወኑትም ኦዲቶች፣

1. የትግራይ ክልል የዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2005 በጀት ዓመት
2. የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት የግዥ ሂሳብ
3. በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የዳያስፖራ ፕሮጀክት ሂሳብ
4. የአዋሽ ተፋሰስ ባለስልጣን ልዩ ኦዲት
5. በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የግዥ ሰራተኛ ሂሳብ
6. ወደ ግል ባለሃብት የዞረ በፕራይታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዲስ መለዋወጫ እቃዎች አሰመጪና ላኪ ድርጅት ሂሳቦች ኦዲት ተደረጎ የኦዲት ሪፖርታቸው ተልኳል፡፡

የ2006 በጀት ዓመት የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶች

1. መግቢያ

የፌዴራልዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት በመንግሠት በጀት እና በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ የመንግሠት ልማት ድርጅቶችን፣ በመንግሥትና በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ የሚከናወኑትን ፕሮጀክቶችን፣ እንዲሁም የብድርና እርዳታ ሂሣቦችን ኦዲት እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በመ/ቤቱ የአቅም ውስንነት የተነሳ ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሣቦች በሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት ያስደርጋል፡፡ በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መሰረት መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊው ማሻሻያዎችና እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊው ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ የበላይ መ/ቤቶች እንዳስፈላጊነቱ ማሳሰቢያ በመስጠት፣ ውጤቱን ከሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጋር ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡

በዚሁ መሠረት የ2006 በጀት ዓመት በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የሥራ እንቅስቃሴ እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በተከናወነው ኦዲት የተገኙ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

2. የሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ2006 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ

2.1 የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን በአዋጅ ቁጥር 126/1969 ሲቋቋም፣ መንግሥታዊ የሆኑ ወይም አብዛኛው ድርሻቸው በመንግሥት ለተያዙ የማምረቻና

የማከፋፈያ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ማድረግና የኦዲት ሙያን ማዳበር ሲሆን፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው በአዋጅ ቁጥር 25/1984 እንዲተዳደሩ ከተወሰነ ወዲህ ግን፣ የኦዲት ሥራውን በጨረታ ካሸነፈ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችንም ሆነ የግል ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

2.2 <u>የኦዲት ሪፖርት ዝግጅትና ስርጭት</u>

የሂሣብ ምርመራ አልግሎት ኮርፖሬሽን የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ኦዲት ሪፖርቶችን ለድርጅቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ወይም ለሥራ አመራር ቦርድ ሲልክ በግልባጭ ለተመርማሪው ድርጅት ያሳውቃል፡፡

በተጨማሪም ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርቱን ተመልክተው ክትልል እንዲያደርጉና አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ በግልባጭ እንዲያውቁት ያይደረጋል፡፡

2.3 <u>የስራ ዕቅድና ክንውን</u>

ኮርፖሬሽኑ በ2006 በጀት ዓመት በዕቅድ የያዘቸውና ያከናወናቸው የሂሳብ ምርመራ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ተ ቁ	መግለጫ	የ2006 በጀት ዓመት			የ2005 በጀት ዓመት ክንውን
		ዕቅድ	ክንውን	ልዩነት	
1	የአምራች ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	146	140	(6)	149
2	የአገልግሎት ሰጪና የማከፋፈያ ድርጅቶች ኦዲት መምሪያ	94	96	2	80
	ድምር	**240**	**236**	**(4)**	**229**

ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት ወጪ የሆኑት 236 ሪፖርቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነተኑ፤አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቃፊታ የሌለበት አስተያየት የተሰጠባቸው/Clean opinion/ 122፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆኑም ነቀፊታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው/Except for./ 82፤አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው /Disclaimer/ 21፣አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቀውሞ አስተያየት የተሰጠበቸው/Adverse/ 1 እና የልዩ ኦዲት ሪፖርቶች 10 ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የ2006 ክንውን ሪፖርት ብዛት ከዕቅዱ ጋር ሲነጻፀር በ4 ሪፖርቶች የሚያንስ ሲሆን፣ ከ2005 በጀት ዓመት ክንውን ጋርም ሲነጻፀር በ7 ሪፖርቶች ወይም በ3.00% በመብለጥ አሳይቷል።

ከዚህም በተጨማሪ ኮርፖሬሽኑ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንደስትሪ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል አ.ማ ሂሳብን በማጣራት ላይ ሲሆን፤ ከዚህም በበጀት ዓመቱ ብር 551,812.00 ገቢ አግኝቷል፡፡

2.4 <u>የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል ሁኔታ</u>

በ2005 በጀት ዓመት መጨረሻ የነበረው የኮርፖሬሽኑ የሰው ኃይል 112 ሲሆን፣ በ2006 በጀት ዓመት አዲስ የተቀጠሩ 38 በድምሩ 150 ሰራተኞች ውስጥ በጡረታ የተገለሉ 1፣ በሞት የተለዩ 1 እና በፈቃዳቸው የለቀቁ 11 በመሆኑ፣ በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 137 ሰራተኞች በስራ ላይ እንደነበሩ ተውቋል።

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበረው የሰው ኃይል ሙያ ደረጃ ሲተነተን ፕሮፌሽናል /ኦዲተሮች/ 88 ፣አስተዳደርና ፋይናንስ 49 እና 1 የትምህርትና ስልጠና ሲሆኑ፣ በፆታም ሲታይ ወንድ 88 እና ሴት 49 በድምሩ 137 ናቸው ።

2.5 <u>የሰው ኃይል ስልጠናን በተመለከተ</u>

ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ ከሆነው የኦዲት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር የኦዲት ሙያ ይበልጥ የሚዳብርበትንና ሀገርቱም በዚህ ሙያ ረገድ

በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን እንድትችል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ በመሆኑ፣በእንግሊዝ ሀገር ከሚገኘው አሶሴሽን ኦፍ ሰርቲፋይድ አከውንታንትስ (ACCA) የሚሰጠውን የተልዕኮ የሙያ ትምህርት የኮርፖሬሽኑ ኦዲተሮች እንዲከታተሉ የፈተና ዝግጅት ጊዜ፣ በገንዘብና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እና በደመወዝ ጭማሪና በመሳሰሉት ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚሁ መሰረት 17 ኦዲተሮች/14 የመጀመሪያ፣3 ደግሞ በፕሮፌሽናል ደረጃ / ትምህርቱን በተለያየ ደረጃ በመከታተል ላይ ናቸው።

የኮርፖሬሽኑን ሰራተኞች የሙያ ብቃት ከፍ ለማድረግና የስልጠናውንም ጥራት ለማገዝ ባለው ዓላማ መሰረት የኮርፖሬሽኑ ቤተ መጽሐፍት ለተጠቃሚዎች ዘወትር በስራ ቀናት ክፍት በማድረግ እና እንዳስፈላጊነቱ ከ11፡30 በኋላ ፣ቅዳሜና እሁድ እና በበኃላት ቀናት ክፍት በማድረግና የሚያስፈልጉ መጻሕፍት በማቅረብ በአገልግሎቱ ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

የኦዲት ሙያ ያለቀጣይና ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሊከናወን እንደማይችል በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነበት በመሆኑ፣ ኮርፖሬሽኒ በዚህ ረገድ ለሠራተኛ የሚሰጠው ስልጠና ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

2.6 <u>የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ</u>

በኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘው ገቢ ሲሆን፣ በተጨማሪም ከሂሣብ ማጣራትና ከሕንጻ ቢሮዎች በሚገኝ ኪራይ ነው፡፡

በ2006 በጀት ዓመት በእቅድ የያዘውና አገልግሎቱን አከናውኖ ያገኘው ገቢ፣ እንዲሁም ሥራውን ለማከናወን ያቀደው ወጪና በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሂሣብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የ2006 የፋይናንስ እቅድና ክንውን

መግለጫ	ገቢ ብር	ወጪ ብር	ያልተጣራ ትርፍ /ከታክስ በፊት/ ብር
ዕቅድ	18,400,062.00	11,063,550.00	7,336,512.00
ክንውን	16,405,543.00	10,370,895.00	6,034,648.00
ክንውን በመብለጥ(በማነስ)	1,994,519.00	(692,655.00)	1,301,964.00

የ2006 የእቅድ ክንውን ከ2005 ጋር ሲነጻፀር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

የበጀት ዓመት	ገቢ ብር	ወጪ ብር	የተጣራ ብር ትርፍ
2006	16,405,543.00	10,370,895.00	5,135,559.00
2005	15,517,846.00	10,409,030.00	5,108,816.00
ልዩነት በመብለጥ (በማነስ)	1,519,245.00	(38,145.00)	26,543.00

የ2006 የገቢና ወጪ ከ2005 ጋር ሲነጻፀር ገቢው ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል፣ ወጪው ግን በማነስ ይታያል፡፡

3. የ2006 በጀት ዓመት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ኦዲቶች

በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑና በ2006 በጀት ዓመት ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 78 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 174 በድምሩ 252 (ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ መ/ቤት

ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር ተወስዷል) ናቸው፡፡

በነዚህ ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) 161፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) 71 ፣አቀም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 18፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቀውሞ አስተያየት የቀረበባቸው(Adverse) 1 እና የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት 1 በድምሩ 252 ናቸው፡፡

4. የኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

በ2006 በጀት ዓመት በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች ሂሣባቸው ኦዲት ተደረጎ ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ጉልህ የሆኑ የየድርጅቶቹ የሂሣብ አያያዝ ጉድለቶች የተነሳ የኦዲት ሪፖርቱ ውጤት አቋም ለመውሰድ የማይቻል ነው ተብለው በኦዲተሮች አስተያየት የተሠጠባቸው ድርጅቶች ሁኔታ እና ከሁለት ዓመት በላይ ሂሳባቸውን ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

4.1. አቋም ሊወሰድበት የማይቻል የኦዲት አስተያየት የቀረበባቸው

አቋም ሊወሰድበት የማይቻል (Disclaimer opinion) የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የመንግሥት ልማት ድርጅቶችና አስተያየቱን ሊያሰጡ የቻሉ ዋና ዋና ድክመቶችና የሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

4.1.1 የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ

ሰኔ 30/2000፣ 2001 እና 2002 ዓ.ም የተጠናቀቀው የኤጀንሲው የሂሣብ መግለጫዎች በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው ውስጥ የተመለከተው ብር 315,842,257.00 የኪራይ ተሰብሣቢ ሂሣብ ለረዥም ጊዜ ሳይሰበሰብ

የቆየ ከመሆኑ አንጻር፣ ይህ ሂሣብ በሕግ አስገዳጅነት ሊሰበሰብ ስለመቻሉ አሣማኝ ማስረጃ ያልቀረበባቸው በመሆኑ፣

- በተሰብሣቢ ሂሣብ ውስጥ የተመለከተው ሌላው ለኮንትራክተሮች ቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 57,166,549.00 ለረዥም ጊዜ የቆየ በመሆኑና በግንባታ ያለ ወይም በግንባታ ሂሣብ ላይ በካፒታል መመዝገብ ሲገባው ይህም ከሆነ ተገቢው የእርጅና ተቀናሽ ሂሣብ ተሰልቶበት በወጪ መታሰብ የሚገባው ሂሣብ ስላልተያዘ በዓመቱ የተጣራ ሀብት ላይ ተፅእኖ ያለውና ይህም ምን ያህል እንደሆነ መወሰን የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ፣
- በሀብት እና ዕዳ መግለጫው ከተመለከተው ተሰብሣቢ በድምሩ ብር 5,000,000.00 ከተለያዩ መንግሥታዊ መ/ቤቶች እንደሚሰበሰብ የሚያሣይ ቢሆንም በህግ አስገዳጅነት መሰብሰብ ስለመቻሉ አሣማኝ ማስረጃ ሲቀርብልን ባለመቻሉ፣
- የቀድሞ የቤት ባለንብረቶችን በመወከል ለረዥም ጊዜ የቤቶች ዕዳ ለባንክ የተከፈሉ ብር 20,658,254.00 ከቤት ባለንብረቶች የሚሰበስብ ተብሎ ቢያዝም ከጊዜ ብዛት አንጻር ይህ ሂሳብ ሊሰበሰብ ስለመቻሉ ከፍተኛ ጥርጣሬ በመኖሩ ሙሉ በሙሉ የመጠባበቂያ ሂሣብ ሊያዝበት የሚገባ በመሆኑ፣
- በሀብትና እዳ መግለጫ ሂሣብ ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ ላይ ለመድረስ ብር 5,744,504.00 ኔገቲቪ የሂሣብ ሚዛን ለምን እንደተቀናነሰ እና ይህም ሚዛን እንዴት ሊከሰት እንደቻለ በቂ ማብራሪያ ሊሰጥ ባለመቻሉ፣
- በባንክ ሂሣብ ማስታወቂያ በወጪ የተያዘ በድምሩ ብር 5,644,417.00 እና የገቢ ሂሣብ በድምሩ ብር 2,740,584.00 በሂሣብ መግለጫው ላይ ያልተካተተና ለምን እንዳልተካተተም ማብራሪያ ሊሰጥበት ባለመቻሉ፣

- በሰኔ 30/2002 ዓ.ም የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት ምንም ጥሬ ገንዘብ አለመኖሩ ቢገለጽም፣ ለሂሣብ መግለጫው ዝግጅት በሂሣብ ሌጀር የተመለከተው ብር 3,955,902.00 የተወሰደ በመሆኑና ይህም የጥሬ ገንዘብ እና የባንክ ሂሣቡ በብር 3,955,902.00 በብልጫ የሚያሣይ በመሆኑ፣
- በሀብት ዕዳ መግለጫው ከተመለከተው ተከፋይ ሂሣብ በድምሩ ብር 25,000,000.00 ለረዥም ዓመታት ሣይከፈል የቆየና ኤጀንሲው በሕግ ሊከፍል የሚገደደበት ዕዳ ስለመሆኑ በቂ ማብራሪያ ሊሰጥበት ባለመቻሉ፣
- ከኪራይ የሚሰበሰበው ገቢ ላይ በቂ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋና ለኦዲቱ አሣማኝ ባለመሆኑ የተመዘገበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አማራጭ የኦዲት ስልት ተግባራዊ ማድረግ ያልተቻለ በመሆኑ፣
- በኤጀንሲው መቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 555/2007 መሠረት የሂሣብ መግለጫዎቹ በተሻሻለው የመንግስት የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ባለመዘጋጀታቸው፣ ይህም የዓመቱን ወጪ በመቀነስ ኤጀንሲው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊከፍል የሚገባውን ከገቢ ላይ ትርፍ ሊጨምር የሚችል ቢሆንም ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ለመወስን የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ፣
- የቋሚ ንብረቶች ፣ ለወደፊት በወጪ ሊመዘገቡ የቆዩ ወጪዎች እና የክምችት ዕቃዎች በኤጀንሲው ሀብትና እዳ መግለጫ የተመለከቱ ቢሆንም በተሻሻለው የመንግስት የጥሬ ገንዘብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት እነዚህ ሂሣቦች በሀብትና ዕዳ መግለጫው መያዝ ስለማይገባቸው በኤጀንሲው መቋቋሚያ አዋጅ መሠረት ሊስተካከሉ ወይም አዋጁ ከዚህ አንጻር ሊስተካከል ይገባ ነበር፣

ከላይ የተመለከቱት ጉልህ የሆኑ ጉዳዮች በተመለከተ በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃዎች መገኘትና ሊቀርብ ባለመቻሉ በሂሣብ መግለጫዎች

ላይ አስተያየት መስጠት አልተቻለም በማለት ኦዲተሮች ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ የኤጀንሲው ሂሣብ ኦዲትም በሶስት ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ ሲሆን በተከታታይ የሂሣብ መግለጫዎች ቀርበው ኦዲት እየተደረጉ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

4.1.2 <u>የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት</u>

30 June 2011 እ.ኤ.አ የተጠናቀቀው የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት የሂሣብ መግለጫዎች በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ድርጅት ኦዲት ተደርጎ የተሰጠው አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በሂሣብ እንቅስቃሴዎች ምዝገባው ላይ ለኦዲት ሊተመንበት የሚቻል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በአግባቡ ባለመዘርጋቱና ለኦዲቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ተሟልተው ባለመቅረባቸው በድርጅቱ በተዘጋጁት የሂሣብ መግለጫዎች ላይ ተጨማሪ ማስተካከያዎች ሊያስፈልጉ ስለመቻላቸው መወሰን ባለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተው የቋሚ ንብረት ሂሣብ በድምሩ ብር 28,483,055.00 በሂደት ላይ ያለ የሕንጻ ግንባታ በሚል የሚታይ ቢሆንም የግንባታ ሂደቱ በተለያዩ ምክንያቶች የተቋረጠ በመሆኑና ድርጅቱ የግንባታ ሂደቱን ለማስቀጠልና ለማጠናቀቅ የተያዘ በጀትና ዕቅድ ስለመኖሩ ባልታወቀበት ሁኔታ ይህን ሂሣብ ሚዛን ማስተካከያ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው የቋሚ ንብረት ሂሳብ የተጣራ የተሸከርካሪ ሂሳብ ብር 2,348,520. የተመለከተ ሲሆን፣ በርካታ ተሽከርካሪዎች የድርጅቱ ንብረት ያልሆኑ ወይም በከፍተኛ ብልሽት የተጎዱ በመሆኑ በንብረትነት መያዝ ስለመቻላቸው ለመወሰን የሚያስችል ተጨባጭ ማስረጃ ባለመኖሩ የቋሚ ንብረት ሂሳቡ አለአግባብ በዚህ መጠን የተጋነነ/ከፍ ያለ በመሆኑ፣

- የክምችት ዕቃዎች ሂሳብ ብር 450,201,267.00 በሀብትና ዕዳ መግለጫው የተመለከተ ቢሆንም፣
- ሀ. የክምችት ዕቃዎቹ በአካል ስለመኖራቸው በቆጠራ የሚረጋገጥበት የተጠናከረ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ባለመኖሩ ለኦዲቱ አስተማማኝ ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ፣
- ለ. የሥራ አመራሩ የክምችት ዕቃዎች በዝቅተኛ ዋጋው ወይም በገበያ ዋጋ ባለመታመኑና ከዋጋው ላይ ለተበላሹ የክምችት ዕቃዎች የመጠባበቂያ ሂሳብ በመቀነስ በመያዙ ይህም ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ያፈነገጠ እና በምን ያህል መጠን ልዩነት ሊኖር እንደሚችል መወሰን ባለመቻሉ፣
- በክምችት ዕቃዎች ሂሳብ የተመለከተው የሽያጭ ዋጋውና ባልተጣራ ትርፍ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚኖረው በመሆኑ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው በክምችት ዕቃዎች ከተመለከተው ሂሳብ በጉዞ ሂደት ላይ ያሉ ዕቃዎች በድምሩ ብር 31,916,021.00 ኔጋቲቪ ሚዛን የሚያሳይ እና እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ምንም ማብራሪያ ሊሰጥበት ባለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው በክምችት ዕቃዎች ከተመለከተው ሂሳብ በጉዞ ሂደት ላይ ያሉ ዕቃዎች በድምሩ ብር 41,938,616.00 ለረዥም ዓመታት ሳይጣራ የቆየና ለምን እንዳልተጣራ ማብራሪያ ሊሰጥበት ባለመቻሉ ስለትክክለኛነቱ ምንም አሳማኝ ማስረጃ ባለመኖሩ፣
- በሀብትና ዕዳ መግለጫው ከተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 147,216,917.00 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ተብሎ የተመለከተ ቢሆንም ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሪፖርት የተደረገው ብር 2,219,356.00 ብቻ በመሆኑ፣ ስለልዩነቱ ምንም ማብራሪያ ባለመሰጡትና ስለትክክለኛነቱ በቂ ማስረጃ ሊቀርብልን ባለመቻሉ፣

- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው ከተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 22,637,758.00 ምንም ማስረጃ ስለሌለው የድርጅቱ ሀብት ነው ተብሎ ስለመያዙና ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ሊቀርብ ባለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን ላይ ለመድረስ ብር 27,339,049.00 የመጠባበቂያ ሂሳብ የተቀነሰ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ ትንተና በአግባቡ ተሰርቶ ባልቀረበበት ሁኔታ ስለትክክለኛነቱ አስተማማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው የተመለከተው የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሚዛን ብር 764,371,167.00 የሚታይ ቢሆንም በድርጅቱ የሂሳብ መዝገብ እና የባንክ ምዝገባ መካከል ስለሚታየው ልዩነት ምንም ማብራሪያ ባለመሰጠቱ ሪፖርት የተደረገው ሂሳብ ትክክለኛነት ማስረጃ ማግኘት ባለመቻሉ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው ከተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የረዥም ጊዜ ብድር ብር 10,708,605.00 ለበርካታ ዓመታት የቆየ እና ከአበዳሪውም የቀረበ ጥያቄ ባለመኖሩና የይርጋ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ይህ ሂሳብ የድርጅቱ ዕዳ ነው ብሎ መያዝ አግባብነት የሌለው በመሆኑ፣
- በሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫው ከተመለከተው ተከፋይ ሂሳቦች ውስጥ በድምሩ ብር 276,474,058.00 ለበርካታ ዓመታት የቆየና እስካሁን ላለመከፈሉ ምክንያት የሆነ ጉዳይ ባለመስጠቱ ስለዕዳው ትክክለኛነት አስተማማኝ ማስረጃ ባለመኖሩ፣

በድርጅቱ በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አስተያየት ለመስጠት አለመቻላቸውን ኦዲተሮቹ ገልፀው ሪፖርት አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት ለድርጅቱ የታዩትን ጉድለቶች የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለቀረበው ጥያቄ የመርሃ ግብር አዘጋጅቶ እንዲላክ በተጠየቀው መሠረት መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ሆኖም ቀደም ባሉት ዓመታት የድርጅቱ ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ተመሳሳይ ግኝቶችና አስተያየት የተሰጠ በመሆኑ መርሃ-ግብር አዘጋጅቶ ቢያቀርብም ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ ከኦዲት ሪፖርቱ መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ ተቆጣጣሪው አካል የማስተካከያ እርምጃዎቹ ተግባራዊነት ላይ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

4.1.3 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን

ሰኔ 30/2003 ዓ.ም የተጠናቀቀው የብረታ ብረትና ኢንጅሪንግ ኮርፖሬሽን ዋና መ/ቤት እና በሥሩ ከሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የ13 ሂሳብ መግለጫዎች እና የተጠቃለለ (conciliated accounts) በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት ተደርጎ የተገኘው ውጤት ቀርቧል፡፡

የኮርፖሬሽኑን ዋና መ/ቤት ጨምሮ ኦዲት ከተደረጉት ኢንዱስትሪዎች የሂሳብ መግለጫ በአስራ አንዱ /11ኢንዱስትሪዎች/ ላይ የኦዲት አስተያየት መስጠት እንዳልተቻለ እና የተጠቃለለውም ሂሳብ መግለጫ ላይ አስተያየት መስጠት አለመቻሉ ተገልጿል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም የየኢንዱስትሪዎቹ የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ በየኦዲት ሪፖርታቸው የተገለፁ ሲሆን ፣የአሁኑ ሂሳብ ኦዲትም በ2 ዓመታት ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የተጠቃለለ ሂሳብ ሪፖርት በተመለከተም፦

- በቋሚ ንብረት፣ ክምችት ዕቃዎች፣ በተሰብሳቢ ሂሳብ፣ በየኢንዱስትሪዎቹ መካከል የተደረገ የሂሳብ እንቅስቃሴዎች (Intra industry balances) የሂሳብ ሚዛን ላይ ለኦዲት ሥራው የሚረዳ በቂ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ባለመዘርጋቱ የእነዚህን ሂሳቦች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሌላ አማራጭ የኦዲት ዘዴ ሊገኝ ባለመቻሉ፣
- በምሥረታ ወቅት የኮርፖሬሽኑ የተከፈለ ካፒታል ብር 3,178,914,605. ቢሆንም፣ ከዚህ በተቃራኒ የዋና መ/ቤት ሂሳብ የተከፈለ ካፒታል ተብሎ የተያዘ ብር 836,847,506.00 በሰኔ 30/2003 የተጠቃለለው ሂሳብ መግለጫው የተመለከተው ካፒታል

ብር 2,690,695,012.00 ብቻ በመሆኑ በልዩነት ለሚታየው ብር 488,219,593.00 በቂ የሆነ ማብራሪያ ሊሰጥ ባለመቻሉ፣

ከላይ በተመለከቱት ጉዳዮች የማስረጃ ውስንነት በመገደባቸውና ከጉዳዮች ከፍተኛነትና ጉልዕነት የተነሳ በተጠቃለለው የኮርፖሬሽኑ ሂሳብ ሪፖርት ላይ አስተያየት መስጠት እንዳልቻሉ ኦዲተሮቹ ገልፀዋል፡፡

በዚሁ መነሻ ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ኮርፖሬሽኑና ኢንዱስትሪዎቹ በተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት እርምጃ እንዲወስዱና መርሃ-ግብር በመዘጋጀት ተግባራዊ እንዲያስደርጉ ለፃፍነው ማሳሰቢያ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ኮርፖሬሽኑ ራሱን የቻለ ተቋም መሆኑንና ለሚኒስቴሩ ተጠሪ አለመሆኑን ጠቅሶ ምላሽ የሰጠን ሲሆን፣ ግልባጭ የተደረገለት ኮርፖሬሽን ግን ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ የሰጠን ምላሽ የለም፡፡

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑና ኢንዱስትሪዎቹ ሂሳባቸውን በየወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ፣ በኦዲት የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲያደርጉና የንብረትና የሂሳብ አያያዙም የሂሳብ አያያዝ መረጃዎችን፣ የመንግስት ደንብና መመሪያ የተከተለ እንዲሆን ከተቆጣጣሪው አካል በቂ ክትትል በየወቅቱ ሊያደርግ ይገባል።

5. <u>በከፍተኛ ኪሣራ ስለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች</u>

5.1 <u>የኮስቲክ ሶዳ አ.ማ</u>

የአክስዮን ማህበሩ የተጠራቀመ ኪሳራ የመዘገበውን ካፒታል እስከ 137% የደረሰ ሆኖ እያለ የአ.ማህበሩ ቦርድ የኢትዮጵያ ንግድ ኮድ 1960 አንቀጽ 543 መሠረት ስለማህበሩ መንግሥት ያልመከረ ወይም እንዲፈርስ ውሣኔ ያልቀረበ በመሆኑ የአ.ማህበሩ በሥራ የመጠቀል ሕልውና ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ እንዳለ በተከታታይ ኦዲቶች በመገለጹ ለፕራይቬታይዘሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እና ለሥራ አመራር በቦርዱ የተወሰደ እርምጃ እንዲገለጽልን፣ እንዲሁም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በ16/10/2006 በአ.ማህበሩ ቀጣይነት በተመለከተ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ማሣሰቢያ ቢሰጥም በቂ እርምጃ

ስለመወሰዱ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ለመ/ቤታችን የደረሰ መረጃ የለም፡፡

ለፕራይቬታይዘሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በ30/10/2006 በተፃፈ ደብዳቤ ኤጀንሲው በተለያዩ ጊዜያት የፋብሪካውን መሠረታዊ ችግሮችና መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች በመለየት ከድርጅቱ፣ ከኤጀንሲውና ከሌሎች ልማት ድርጅቶች በተውጣጡ አባላት ጥናቶች በማካሄድ በተገኘው ውጤት መሠረት ክትትል እያደረገ ስለመሆኑ ወደ ግል ለማዛወር በተደጋጋሚ ጨረታ በማውጣት ሙከራ ያደረገ ቢሆንም ድርጅቱ ባለበት የተወሳሰበ ችግር በተለይ የግብር እዳ ምክንያት አስመልክቶ ገልጾ ፋብሪካው ይዘት የተነሰበት ቴክኖሎጂ እጅግ ኋላ ቀር እና አዋጪ እንዳልሆነ በመታመኑ አንድም አዲስ ኢንቨስትመንት ተደርጎ ድርጅቱ እንዲቀጥል አለበለዚያ አክስዮን ማህበሩ የግል በመሆኑ መጠቀል ስለማይል በሕግ እንዲፈርስ የውሣኔ ሃሣብ በኢንድስትሪ ሚኒስቴር ቀርቧል በማለት ገልጿል፡፡

ይህም ቢሆን ወደ ተግባራዊ እርምጃ ስለመሸጋገሩ የተገኘ መረጃ ባለመኖሩ ከጉዳዩ አሳሳቢነት አንፃር በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት የድርጅቱ በንግድ ሥራ በመጠቀል ሕልውና አስጊ ስለሆነው ድርጅት አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

5.2 <u>የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት</u>

የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት የተለያዩ በጀት ዓመታት ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ የድርጅቱ የተጠራቀመ ኪሣራ ከድርጅቱ መመስረቻ ካፒታል ¾ በላይ መሆኑና የተያዘውን መጠባበቂያ (Reserve) በመሆኑ በኢትዮያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 166/1952 አንቀጽ 495(1)ሸ እና (2) መሠረት ለድርጅቱ መፍረስ በቂ ምክንያት እንደሆነ ኦዲተሮች ገልጸው ሪፖርት ባቀረቡት መሠረት ለከተማ ልማት፣ ቤቶችና በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በተደጋጋሚ፣ እንዲሁእ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲገለጽልን ማሣሰቢያ የተሠጠ ቢሆንም ይህ ሪፖርት

እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የተወሰደ ተጨባጭ እርምጃ ስለመኖሩ የደረሰ ደረጃ የለም፡፡

በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና በድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ መካከል የደብዳቤ ልውውጥ ስለመኖሩ በግልባጭ የደረሰን ቢሆንም፣ ከጉዳዩ አሳሳቢነት አንፃር በቂ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በተጨማሪም በቁጥር 914/መ250/14 በ20/06/2007 በተፃፈ ደብዳቤ ስለድርጅቱ ቀጣይነት ምንም ሳያወሳ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ እርምጃ ሲወስድ የድርጊት መርሐ ግብር ብቻ ልኳል፡፡

በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት በጉዳዩ በቂ ትኩረት በመስጠት አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

6. ስለልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሳብ አያያዝና ንብረት አጠባበቅ በተመለከተ

የልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የሂሳብ አያያዝ ፣ንብረት አጠባበቅና አስተዳደርን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችና መፍትሔያቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

6.1. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

- በርካታ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ የሌላቸው፤ ያላቸውም ቢኖሩ ምዝገባቸው ያልተሟላ አንዳንዶች ደግሞ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶችን አንድ ላይ መዝግበው መገኘታቸው፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የቋሚ ንብረት መዝገብ ቢይዙም የግዥ፤ ሽያጭንና ዝውውርን በተመለከተ የተሟላ መረጃ ካለመመዝገባቸው የተነሳ መዝገብ ውስጥ ያለው የዋጋና የአገልግሎት ቅናሽ ሂሳብ በዋናው መዝገብ ጋር በየወቅቱ ባለመመሳከሩ በሁለቱ መዝገቦች መካከል ልዩነቶች እንደሚያጋጥሙ፣
- በመዝገብ የተዘረዘሩት ንብረቶች በእውን መኖራቸውንና ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቋሚ ንብረት ቆጠራ

እንደማይደረግና የተደረገም ከሆነ ከመዝገቡ ጋር የማይገናዘብና ልዩነት ከተገኘም እንዲታረቅ የማይደረግ መሆኑ፣

- በውርስና በተለያዩ መንገድ ቋሚ ንብረቶች ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ሲዛወሩ በተገቢው መንገድ ርክክብ የማይካሄድና በሰነድ ያልተደገፈ በመሆኑ ምክንያት ቋሚ ንብረቶች በተረካቢውም ሆነ በአስረካቢው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ውስጥ በትክክል የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ለቋሚ ንብረቶቻቸው የገዙት የመድን ዋስትና በቂ ያልሆነና በአደጋ ጊዜ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የማይችል ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ ለንብረቶቻቸው የመድን ዋስትና ያልገቡ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት መጥፋት የተከሰተ መሆኑ ለመረዳት ቢቻልም ንብረቱ የጠፋበት ምክንያት ተጣርቶ እንዲተካ እንደማይደረግ በኦዲት ወቅት ታይቷል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በንብረት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርጉና የንብረት ሂሳባቸው ትክክለኛውን ሂሳብ ለማንጸባረቅ እንዲቻል አስፈላጊውን ሁሉ እንዲደረግ በየኦዲት ሪፖርቱ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

6.2. <u>በመጋዘን ያሉ እቃዎች</u>

- በመጋዘን ያሉ ክምችት እቃዎች (stock) በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ ላይ ቆጠራ የማያደርጉ ወይም ከፊል ቆጠራ ብቻ ማድረጋቸውና ሌሎች ደግሞ ቆጠራ ቢያካሂዱም የቆጠራውን ውጤት ከሂሳብ መዝገቡ ጋር ተገናዝቦ ልዩነት ካለ አስፈላጊውን ማስተካከያ የማያደርጉ መሆኑ፤
- አንዳንድ ድርጅቶች በመጋዘን ያሉ እቃዎች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት መቆጣጠሪያ መዛግብት (stock card) እንደማይዙ፤ ሌሎች ደግሞ አሟልተው የማይመዘግቡና የምዝባ ስህተቶች /ልዩነት ሲያጋጥሟቸው ጉዳዩን ሳያጣሩ በተሰብሳቢ ወይም ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሚይዙ መሆኑ፣
- በብዙ ድርጅቶች ውስጥ በብልሽትና በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ለረዥም ጊዜ ተከማችተው የቆዩ እቃዎች መኖራቸውና በአንዳንድ ድርጅቶችም እነዚህ እቃዎች በዝርዝር ተመዝግበው ባለመያዛቸው ለእቃዎች መጠባበቂያ ተብሎ በመዝገብ የሚታየው ሂሳብ ትክክለኛነት ለመገመት የማይቻል መሆኑ፣

- ከሀገር ውጭ በሚገዙ እቃዎች እስከሚደርሱ ድረስ በጉዞ ላይ ያሉ እቃዎች በሚል ሂሳብ ውስጥ እስከ 6 ወር ያህል ጊዜ ብቻ መዝግቦ መቆየት የሚቻል ቢሆንም በበርኮታ ድርጅቶች በጉዞ ላይ የሚገኙ እቃዎች ተብሎ ከሁለትና ከዚያ በላይ ዓመት የሚቆዩና አንዳንዶቹም በሰነድ ያልተደገፉ ሂሳቦች፤ የጠፉ ወይም የተበላሹ እቃዎች ከሆኑም በወቅቱ የመድን ካሳ ያልተጠየቀባቸው መሆኑ፣
- በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከረዥም ጊዜ በፊት አንዳንዱም ከውርስ ጊዜያቸው ጀምሮ በምርት ዕደት የነበሩ ወይም ለሌላ አገልግሎት ያልዋሉና በየጊዜው ምንም እንቅስቃሴ የማያሳዩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሳ ጥቅም ላይ ወይም ለምርት ግብዓት ስለማይውሉ እነዚህ ዓይነት ንብረቶች የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያዝላቸው ወይም ከሂሳብ መዝገብ ውስጥ እንዲቀነሱ የማይዳረግ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት በተደጋጋሚ የተገኙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጅቶቹ በክምችት እቃዎች ላይ የሚያደርጉት ቁጥጥር እንዲጠናከርና የታዩት ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ በየኦዲቱ ሪፖርት ማስገንዘቢያ ተሰጥቷል፡፡

6.3. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- አብዛኞቹ ድርጅቶች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሳይሰበስቡ ከዓመት ዓመት ስለሚያሸጋገሩ ተሰብሳቢው እየበዛና ጊዜው እየረዘመ በሄደ ቁጥር ባለዕዳዎችን በውዴታ ወይም በሕጋዊ መንገድ ለማስከፈል ችግር መፍጠሩና ድርጅታቸው በውዝፍ ያሉትን ሂሳቦች ገቢ እንዲደረጉለት ተገቢውን ጥረት የማያደርጉ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተሰብሳቢ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ከማን መሰብሰብ እንዳለባቸው የማይታወቁ መኖራቸው፤እንዲሁም ድርጅቶቹ የሂሳብ ግንኙነት ካላቸው መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የተሟላ አድራሻ ባለመያዛቸዉ በኦዲት ወቅት የተመረጡ ድርጅቶችን በዓመቱ መጨረሻ የነበረው ሂሳብ በቀጥታ ከድርጅቶች ለማጣራት/ማረጋገጫ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት አልተሳካም፣

- በብዙ ድርጅቶች ለሠራተኞች ብድርና የቅድሚያ ደመወዝ ብድር መስጠት የተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች ስለአወሳሰዱ፣ አፈቃቀዱና አሰባሰቡ መመሪያ የሌላቸው፣ መመሪያ ያላቸውም ቢሆኑ በትክክል ስለማይተገብሩ ከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ በሠራተኞች ስም በተሰብሳቢ ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ብድር ያለባቸው ሠራተኞች ከመ/ቤቱ ሲሰናበቱ ወይም ወደሌላ ድርጅት ሲዛወሩ ያለባቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ ወይም እንዲጣራ ስለማይደረግ ለረዥም ጊዜ የቆዩ የብድር ሂሳቦች ሲንከባለሉ የሚታዩ መሆኑ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለአንድ ባለዕዳ ሁለትና ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ ቋት ስለሚከፈት የሂሳቦች መመሰቃቀልና አለመስማማትን የሚያስከትል ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ቁጥጥር እንዲጠናከር፣ ሊሰበሰቡ የሚችሉ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ይህም ካልተቻለ ከሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካል ጋር በመመካከር ሂሳቡ እንዲሰረዝ በማድረግ ሂሳቦቹ ትክክለኛ የድርጅቱን የተሰብሳቢ ሂሳብ ገጽታ የሚያሳዩ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚገባ በኦዲቱ ሪፖርት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

6.4. <u>በባንክና በካዝና ያለ ገንዘብ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች የሚሰበስቡትን ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማያደርጉና ከዚህም ገንዘብ ላይ ክፍያዎች እንደሚፈጽሙ፤ በርካታ ድርጅቶች በባንክ ያላቸውን ሂሳብ በየወሩ ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ ጋር በወቅቱ በማገናዘብ እንደማያስታርቁ፤ የባንክ መዝገባቸውና የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ መካከል ልዩነት ቢያጋጥም እንኳ የልዩነቱን መንስኤ እንደማያጣሩና አንዳንዶችም ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው የባንክ ሂሳቦች ውስጥ የተቀመጠ ገንዘብ መኖሩ፣
- በርካታ ድርጅቶች በሂሳብ ዘመኑ መጨረሻ በካዝና የነበረውን ጥሬ ገንዘብ እንደማይቆጥሩ፣ ቢቆጥሩም በዓመቱ መጨረሻ የሚደረገው የጥሬ ገንዝብ ቆጠራ ከመዛግብቱ ጋር በማመሳከር ልዩነቱ ካለ እንደማያጣሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች በባንክ ያለውን ሂሳብ በትክክል ለመቆጣጠር ከባንክ የሚላከውን ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያና ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ

ከሂሳብ መዝገብ ጋር ማስታረቅና ልዩነቶችና ስሕተቶችን እንዲሁም አላግባብ ወጪ የሆኑ ሂሳቦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ተከታትሎ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ተገልጾላቸዋል፡፡

6.5. <u>ተከፋይ ሂሳቦች</u>

- በርካታ ድርጅቶች ለመንግሥት መከፈል የሚገባቸውን ግዴታዎች ማለትም ከሰራተኞች ደመወዝ የተቀነሰ የሥራ ግብር፣ የጡረታ ማዋጮ እንዲሁም የሽያጭና የንግድ ትርፍ የታክስ ሕጉ በሚያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው እንደማይከፍሉ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች ተካፋይ ብለው ከያዙት ሂሳብ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩና ለማን መክፈል እንዳለባቸው የማይታወቁና ለረዥም ጊዜ ሳይከፍሉ የቆዩ የረዥም ጊዜ ብድሮች እንዳለባቸውና ከአበዳሪዎች ጋርም በየጊዜው የሂሳብ መግለጫዎች ስለማይለዋወጡ በኦዲት ወቅት ከአበዳሪዎች /ተከፋይ ድርጅቶች/ ማረጋገጫ በሚጠየቅበት ጊዜ መልስ የማይሰጡ ቢሰጡም ድርጅቶቹ አለን ከሚሉት ሂሳብ ጋር ከፍተኛ ልዩነት የሚታይ መሆኑ የሂሳቦቹን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ድርጅቶች የተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ በየወቅቱ እንዲከፍሉ ትክክለኛነቱንም እንዲያጣሩ በተላከላቸው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

6.6. <u>ስለሂሳብና የሰነድ አያያዝ</u>

- አንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ቫውቸሮች በሂሣብ ሠራተኞች ከተዘጋጁ በኋላ ተገቢው የሥራ ኃላፊ ተመልክቶት ትክክለኛነታቸውን መርምሮ ሳያፀድቅ በሂሣብ መዝገብ እንደሚመዘገቡ፣
- በአንዳንድ ድርጅቶች ለሂሣብ ሠነዶች የሚያደርጉት ቁጥጥር እናሳ መሆኑና በማተሚያ ቤት ቁጥር ተሰጥቶአቸው የሚወጡ ሰነዶች እንቅስቃሴ እየተመዘገበ ቁጥጥር እንደማይደረግ፤ ከክፍያ ሠነዶች ጋር የተያያዙ የወጪ ደጋፊ ደረሰኞች የተወራረዱ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ምልክት

እንደማይደረግባቸውና በአንዳንድ ሂሣቦችም የአርዕሰት አመዘጋገብ ስህተት እንደሚታይ ታውቋል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር የድርጅቶችን ገንዘብ ለብክነት የሚዳርግ፤ የሂሣብ ሠነዶችን በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት ስለማይቻል ፤ሠነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች ሪፖርት ተልኳል፡፡

7. <u>በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ</u>

በመንግሥትና የልማት አጋሮች ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የሂሳብ አያያዛቸው በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሲሆን፣ በአብዛኛው የተሰጠው የኦዲት አስተያየትም ነቀፌታ የሌለበት (clean opinion) እንደሆነ ተመልክቷል፡፡
ሆኖም በአብዛኛዎቹ ፕሮጀክት ፈፃሚዎች ትኩረት ያልተሰጣቸውና በተደጋጋሚ በሥራ አመራር ሪፖርት ላይ የሚጠቀሱ በኦዲት ሪፖርቱም መሠራት የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተለየ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ለሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ለብቻ የባንክ ሂሳብ አለመክፈትና በየወቅቱ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀት፣
- በባንክ ሂሳብ ማሳወቂያ እና በባንክ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶች መንስኤ አለማጣራት፣
- ከፍተኛ መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ በሳጥን እንዲቀመጥ የሚደረግ መሆኑ፣
- በዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማድረግ እና ወይም የቆጠራውን ውጤት ከመዝገብ ጋር አለማመሳከር፣
- በበርካታ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖር እና በዕድሜ ተተንትኖ አለመገለጽ፣
- አልፎ አልፎ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሚታዩ መሆኑ፣
- ቅድሚያ ክፍያና ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ

- የአንዱን በጀት ዓመት ፕሮጀክት ወጪ ለሌላው በጀት ዓመት የመመዝገብ ሁኔታ አልፎ አልፎ የሚታይ መሆኑ፣
- አንዳንድ ድርጅቶች የፕሮጀክት ሂሳብ መዝገብ ያለመቋቋመቸው፣አልፎ አልፎም ደጋፊ የሂሳብ ማስረጃዎቹን ለኦዲት አለማቅረብ፣
- ከዋናው መ/ቤት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠንና በፈፃሚ መ/ቤት/ቅ/ጽ/ቤት ገቢ የሆነው/የተመዘገበው ሂሳብ መካከል ልዩነት መኖሩ፣
- በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው በርካታ መጠን ያለው ገንዘብ ሥራ ላይ ሳይውል ወደ ቀጣይ ዓመት የሚዞር መሆኑ፣
- በፕሮጀክት ሂሳብ የሚገዙ ቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ የማይካሄድና መለያ ቁጥር በአግባቡ የማይሰጥ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም በየፕሮጀክቶቹ ሂሳብ አያያዝ የተመለከቱት ችግሮች እንዲስተካከሉ በየኦዲት ሪፖርቶቹ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ፣የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ስለተግባራዊነቱ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።

8. የችግሮቹ ምክንያቶችና መፍትሄያቸው

8.1. የችግሮቹ ምክንያቶች

በሂሣብ አያያዝና ቁጥጥር ረገድ በሚታዩት ችግሮች ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በብዙዎቹ ድርጅቶች ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋትና ካለም ተግባራዊ አለማድረግ፤
- የድርጅቶች የበላይ ኃላፊዎችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በውጭ ኦዲተሮች የሚሰጡ የእርምትና የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰድ ናቸው፡፡

8.2. ችግሮቹን ለማቃለል ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃች

- የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በማንኛውም ድርጅት መዋቅርና የአሠራር ፕላን ውስጥ መዘርጋት ያለበት ሲሆን፣ የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም የምዝበራና ብኩንነት ሁኔታ ከምንጩ በመከልከል፣
- የድርጅቶች የሂሣብ መዛግብትና ሠነዶችና መረጃዎች አስተማማኝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ቅልጥፍናና የውጤት ጥራት እንዲኖር ለማድረግ፣
- ማኔጅመንቱ የሚያውቃቸውና ከበላይ አካል የሚወጡ መመሪያዎች ሁሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ተገቢ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ከውስጥና፤ ከውጪ ኦዲተሮች የሚሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦችን ተግባራዊ ማድረግና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም በኦዲት ሪፖርቶች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

9. ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ ድርጅቶች

መ/ቤታችን ባለው መረጃ /እስከ ሚያዝያ 30/2007 ዓ.ም የተሰበሰበ /መሰረት ከ2 ዓመት በላይ የቆዩ ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት ያላስደረጉ 17 የመንግስት ልማት ድርጅቶች/ ዝርዝር በአባሪ-37 ተመልክቷል/ እንዳሉ ታውቋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ መ/ቤቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ኦዲት እንዲያስደርጉ፣ የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ክትትል ሊያደርጉ ይገባል።